
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፪ መጋቢት/ሚያዝያ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

## ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቁ እርስ በርሳቸውም ይታረቃሉ።



## ምሕረት ይቅር ባይነት ዕርቅ

## የፈሰሰ ደም እንዲደርቅ ነባር ቂም በቀል እንዲርቅ

© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ማጽናኛችሁ አይለየን

እኔ ወታደር ነኝ፡፡ አሁን የምገኘው በትግራይ ክልል ሽራሮ አካባቢ ነው፡፡ በአካባቢው በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ተተክለዋል፡፡ ይሁንና በየሰበካው ታቦት ክብረ በዓል ቀን ቅዳሴ ተቀድሶ ሲያበቃ ለበዓሉ የሚያስፈልገው ዝግጅት ተሟልቶ እያለ ጽላተ ኪዳኑ ወጥቶ አይከበርም፡፡ እኛም ታቦቱ ከአሁን አሁን ይወጣል ብለን የካህናቱን ዐይን ዐይናቸውን ብናይ «አይነግሥም» ይሉናል፡፡ በሌላ በኩል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሰንበት ት/ቤት መርሐ ግብር ጀምረናል፡፡ ወታደሮች ስለሆንን ቀድሞ የተማርነውን ነገር ዘንግተነዋል፡፡ ልምድ ያላቸው የተወሰኑ ሲቪል ሠራተኞች አባላት አሉን፡፡ ይሁንና በረድኤተ እግዚአብሔርና በእናንተ ድጋፍ በርትተን የሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን መርሐ ግብር እናጠናክራለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ማጽናኛችሁ አይለየን፡፡

*ወታደር ብርሃኑ አምሳሉ*
*317ኛ ሬጅመንት*
*ሽራሮ*

## መፍትሔ እፈላልጉን

በመንፈሳዊ ሕይወት ያደግ ሁበት ሰንበት ትምህርት ቤት ከተቋቋመ ኻያ ዓመት ኾኖታል፡፡ ይሁንና ምንም ዐይነት ለውጥ አይታይበትም፡፡ አባላቱ ለሰንበት ትምህርት ቤታቸው አገልግሎት ቅንዐት የላቸውም፤ የማርፈድ አባዜ ተጠናውቷቸዋል፡፡ ይህን የሚያዩ አዳዲስ አባላትም ለመጽናት አልቻሉም፡፡ በሥራ ምክንያት በአጥቢያው የሚኖሩ ታላላቅ ወንድሞችም ትዕግሥታቸው አልቆ በዝምታ ያዩናል፡፡ እባካችሁ ለሰንበት ትምህርት ቤታችን ችግር መፍትሔ በማፈላለግ እርዱን፡፡ በተጨማሪም ከገጠር አብያተ ክርስቲያናት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ያልተቋቋሙባቸው ይበዛሉ፡፡ ምክንያታቸውም «ማን ያስተምረናል?» የሚል ነው፡፡ በወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች አስፈላጊው ትብብር ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

መላኩ አደሬ
ባሌ-ጋሠራ
ታምራት ደምሴ
ወልድያ- ሳዋ ሜዳ

## በ«ጥምቀት» የገባው በ«ተክሊል» እንዳይወጣ!

በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን የሚፈጽሙ ወጣቶች በርካታ ናቸው፡፡ ይሁንና ጋብቻቸውን ከፈጸሙ በኋላ ትዳርና አገልግሎት የማይጣጣሙ እስኪመስሉ ድረስ የቀደመ ትጋታቸው ሲሸሻቸው ይታያል፡፡ «እገሌ ምን ኾኖ ነው ትጋቱን የቀነሰው?» ሲባል «አግብቶ ነው» ከሚለው በተጨማሪ «ቤቃ፥ እገሌም በሚቀጥለው ያገባና...» ማለት የተለመደ ሆኗል፡፡ ስለዚህ የደከሙትን ለማበርታትና የበረቱትን ለማጽናት፡ - የአገልግሎትን ምንነት ማስረዳት፣ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣ ተከታታይና ተገቢ የምክክር አገልግሎት መስጠት ያሻል፡፡ አልያ በምሥጢረ ጥምቀት የገባው በምሥጢረ ተክሊል እንዳይወጣ ያሰጋል፡፡

*በላይነህ ይርዳው*
*ሸኖ*

## መምህራኑ በስደት ካህናቱ በቀበሌ ተመራጭነት

በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን በሥራ ምክንያት በቆየሁበት ወቅት የታዘብኩት ነው፡፡ በአንዳንድ የገጠር አካባቢ ያየኋቸው መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን አጥተው ለመዘጋት የደረሱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም አርሶ አደር ልጆቹን ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት መላክ ስላለበትና የአብነት ትምህርት እንደ ኋላቀርና ጥቅም የሌለው ተደርጎ በመቆጠሩ ነው፡፡ መምህራኑም ተማሪዎችን ሲያጡ ወደ ከተማ እየፈለሱ ይሄዳሉ፡፡ በአንዳንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ካህናቱ ለመንግሥት ሥራ የቀበሌ ተመራጭ እየኾኑ በአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ሥራዎች ስለሚጠመዱ በክብረ በዓላት ሳይቀር ቅዳሴ ይታጎላል፡፡ በትምህርቱም ይሁን በአገልግሎቱ ተተኪ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ያስፈልጋልና ጉዳዩ በጥሞና ታይቶ መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል፡፡

*አዲሱ መልኬ*
*እስቴ-መካነ ኢየሱስ*


በዋናስ አሳታሚ ድርጅት
በመለከት መጽሔት ዝግጅት ክፍል
ተዘጋጅቶ በምእመናን፣ በሰንበት ት/ቤቶች፣
በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ከፍተኛ
ተፈላጊነትን ያገኘው
መዝሙረ ተዋሕዶ ቁጥር አንድ መጽሐፍ
በምእመናን ጥያቄ ለአራተኛ ጊዜ ታትሞ
በገበያ ላይ ውሏል፡፡
ቁጥሩ አነስተኛ በመሆኑ
ከማለቁ በፊት ገዝተው ይጠቀሙበት፡፡
የአንዱ ዋጋ ብር 12 ሲሆን በብዛት ወስደው
ለሚያከፋፍሉ የዋጋ ቅናሽ የምናደርግ
መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡
አድራሻ፡- ፒያሳ አያሌው ሙዚቃ ቤት
ፎቅ ላይ

ዋናስ አሳታሚ ድርጅት


ኢትዮጵያዊው የዜማ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ

ዋናስ የኅትመትና ማስታወቂያ ድርጅት

ማሳሰቢያ፡-
በተመሳሳይ ስም አሳትመው
የሚሸጡ ስላሉ
ዋናስ የሚለው መለያችን
መኖሩን ያረጋግጡ፡፡

0111 - 11 - 08 - 73
0111 - 56 - 58 - 97

14130


**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ**

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com



«... የዕርቅ ቃሉንም በእኛ ላይ አደረገ፤ የይቅርታውን መልእክትም ሰጠን። እኛስ በክርስቶስ ስምላይ እንለምናለን፤ እግዚአብሔርም በእኛ ስማላጅነት ደስታን ይሰጣችኋል፤ እግዚአብሔርን በክርስቶስ ደስ ታሰኙት ዘንድ እንለምናችኋለን።» /2ቆሮ.5.18-20/

~ ~ ~

ትላንት ብንቀያየምም ነገ ግን በምሕረትና ዕርቅ አንድ ኾነን፤ በዕዮነታችን ተስማምተን በአንድነት መጓዝ እንችላለን። ይህም ተስፋ ቢፈጸም የሚችለው አንድን ነገር ዛሬ ነገ ሳንል ለመፈጸም ከበቃን ነው - ሳንዘገይ በመተማመን ተቀራርበን በሥርዐት፣ በጨዋነትና በግልጽ ተወያይተን፣ ችግሮቻችንን ለይተን ይቅር በመባባል። አስፈላጊ በኾኑ የጋራ ጉዳዮቻችን ሁሉ በራሳችን ጊዜ ተማምነን፣ ተቀራርበን፣ በሥርዐትና በጨዋነት ለማወያየት ይቻል ዘንድ ደግሞ ሕዝባችን በኑሮ ሒደቱ ያዳበራቸው ባህላዊ ልምዶች እንደ ተጠበቀ ኾነው ቤተ ክርስቲያናችንም በማንም እና በምንም የማይተካ፣ ምድራዊና ሰማያዊ፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ መዐኮች ያሉት፣ ውጤቱ ከፍተኛ የኾነ ሚና እንዳላት አሙን ነው፤ ይኸውም በሕዝቡ ላይና በሕዝቡ መካከል ለማስተማር፣ ለመናዘዝ፣ ለኃጢአት ይቅርታን ለመስጠት፣ ለማማለድ፣ ለማስታረቅ የሚያስችላት መንፈሳዊ ሥልጣንዋና የላቀ ባለሟልነትዋ ነው።

/የማኅበሩ መልእክት/


ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ዳንኤል ክብረት
ም/ ዋና አዘጋጅ - አሉላ ጥላሁን
ሪፖርተር - ዲያቆን ደረጀ ጅማ
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ጸዳለ ሁንዴሳ
- ገነት ግርማ



E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org
ስልክ 011-1-242753
011-1-225729
መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ


«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፬ኛ ዓመት ቁጥር ፪
መጋቢት/ሚያዝያ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.


# ይዘት


የማኅበሩ መልእክት
- አንድ ነገር እንቻል-ይቅር መባባል..................፪

ደብዳቤዎች ......................................፫

ወቅታዊ ጉዳዮች

- ምሕረት፣ይቅር ባይነት፣ ዕርቅ..........................፬
  - ወቅታዊው የቤተ ክርስቲያን አገራዊ ሚና..........፯
  - «እግዚአብሔር ሲቆጣ አያነሣም በትር......»..........፲
  - ምሕረትና ይቅር ባይነት..........................፲፬

ትምህርተ ሃይማኖት
- ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ፣ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት..........................፳፬
- ሰባኪ ሲዳናት..........................፳፮
- ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ..........................፳፰

ኪነ ጥበብ
- አዳኙ..........................፴፩
- ደባ ተውኔት መንፈሳዊ ይዘትም ኾነ ፋይዳ የለውም..........................፴፫

እናስተዋውቃችሁ
- አባ ገብረ እንድርያስ የጦር መኰንን እና መነኩስ..........................፴፬
- እልፍኝ እና ሥዕል ቤት ቤተ መንግሥት እና ታቦት..........................፴፮

ሐመረ ሕይወት
- መንፈሳዊ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ የምክክር አገልግሎት ..........................፴፰


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

# የማኅበሩ መልእክት

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::*

# አንድ ነገር እንቻል፡ ይቅር መባባል

አሁን በመጾም ላይ ያለነው ዐቢይ ጾም፣ ከፊት ለፊታችን የሚመጡት ሰሙነ ሕማማት፣ የስቅለት እና የትንሣኤ በዓላት በመሠረታዊ ደረጃ አንድ ታላቅ ነገርን ያስተምሩናል- *ይቅር ባይነትን::* መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ የጾመው፣ በቀራንዮ አደባባይ መከራን የተቀበለው፣ የተሠዋውና ሞትን የቀመሰው ለሌላ ለምንም ነገር ሳይሆን በሰው እና በእግዚአብሔር፣ በነፍስ እና በሥጋ፣ በሰው እና በመላእክት፣ በሕዝብ እና በአሕዛብ መካከል ኃጢአት የወለደውን ልዩነት አስወግዶ ሰውን ይቅር ለማለት ነው::

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ የፈጸመው ጥፋት በይቅር ባይነት ባይሻር ኖሮ መፍትሔ ባልተገኘለት ነበር:: አዳምና የልጅ ልጆቹ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተው የኖሩበት አሰቃቂ የፍዳና የጨለማ ዘመን እልባት የተሰጠው *በመለኮታዊ ይቅር ባይነት* ነው:: በመልዕልተ መስቀል ከተነገሩት ነገሮች አንዱ «*ይቅር በላቸው*» (ሉቃ.23፥34) የሚለው ቃለ ኃይል ነው::

***በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ይቅር ባይነት የህልውናው መሠረት ሆኖ የኖረ እና የሚኖር ነው:: ለምን?***

*1. <u>የዲያብሎስ ሤራ የሚከሽፍበት በመሆኑ፡-</u>* ጠብ ጫሪነትን፣ ቂምን እና በቀልን የሚጠነስሰው፣ ሰዎችን ደም የሚያቃባው እና እርስ በእርሳቸው ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪያቸው ጋርም የሚያጣላቸው ዲያብሎስ ነው:: /ዘፍ.3፥1-21/:: ይህ በዲያብሎስ ጠንሳሽነት የሚወጠነው ጠብ፣ ግጭት እና ጠላትነት ሊፈታ የሚችለው ይቅር በመባባል እና የከረመ ያለመግባባት ፋይልን በመዝጋት ነው::

***2 እልቂትን የማቆሚያ መንገድ በመሆኑ፡-*** በትውልዶች፣ በሕዝቦች እና በቡድኖች መካከል በታሪክ አጋጣሚ የሚፈጠሩ ግጭቶች ደም እያቃቡ እና ከዘር ዘር እየተዋረሱ የእልቂት መንገድን ይቀጥላሉ:: ለእነዚህ ነገሮች ካሣ ለመካሥም ሆነ ወደ ኋላ ተመልሶ ታሪካዊ መፍትሔ ለመስጠት አስቸጋሪ ነው:: ይህን ወደ ትውልድ የሚዘምት እልቂት ማቆም የሚቻለው ይቅር ተባብሎ በምሕረትና የይቅርታ አቅዋም ያለፈ በደልን በመደምሰስ ብቻ ነው:: በያዕቆብ እና በዔሳው መካከል የተፈጠረው ጠብ ወደ ልጅ ልጅ ተዛምቶ የትውልድ ነቀርሳ እንዳይኾን የተገታው በሁለቱ መካከል በሰፈነው ምሕረትና ይቅር ባይነት፣ ዕርቅና ሰላም ነው:: ዘፍጥ.27፥41-46፣32፥1-21፣33፥1-17::

***3 የእግዚአብሔርን ይቅርታ የማገኛ መንገድ በመሆኑ፡-*** እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው:: ልጆቹም በፍቅር እንዲኖሩ ይፈልጋል:: ስለዚህም የፍቅር ጠላት የሆኑት አለመቻቻል፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቂምና በቀል በይቅርታ እንዲደመሰሱ አዝዟል :: «ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋል:: ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም::» /ማቴ.6፥14-15/:: ***የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስናገኝ እርስ በርሳችንም እንታረቃለን::*** /ኤፌ.2፥14-16/:: ***ስለዚህም ይቅር ባይነት የሌለበት ክርስትና የተቃጠለ እምፑል ማለት ነው::***

ዛሬ ከሚያስፈልጉን ነገሮች አንዱ የይቅር ባይነት መንፈስ ነው:: ሰዎች ከራሳቸው ጋር፣ ከሌላው ሰው ጋር፣ አንዱ ወገን ከሌላኛው ጋር፣ አንዱ ቡድን ከዚያኛው ጋር በታሪካዊ አጋጣሚዎች፣በጥቅም ግጭት፣ በአመለካከት ልዩነት፣ በሥልጣን ሽሚያ፣ በአሉባልታ ... ወዘተ በተፈጸሙ ጥፋቶች ምክንያት የመካሰስ ስሜቶች እየነገሡ፣ ከዚያም አልፎ አንዱ ሌላውን የማግለል፣ በታሪካዊ ጠላትነት የመተያየት አዝማሚያ፣ የጽንፈኝነትና የመጠፋፋት ፍንጮች እየተስተዋሉ ናቸው::

በዚህ ጊዜ ከራስ ጋር መታረቅ፣ ሌላውን ይቅር ማለት፣ ይቅርታን ለመቀበልም መዘጋጀት፣ የትላንት ቁርሾን በይቅርታ መዝጋት፣ ጥላቻን በፍቅር፣ ቂምን በዕርቅ ማሸነፍ፣ ለዚህም መንፈስን ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል:: ሐዋርያው፡- «ወንድሙን የሚጠላ በጨለማ ይኖራል» /1ዮሐ.2፥11/ እንዳለ የጥላቻ መንገድ፡- የድንቁርና እና የኋላ ቀርነት ብሎም የጦርነት ጨለማ የወረሰው መንገድ ነው:: በጦርነት፣ በጠብ እና በእርስ በርስ መወነጃጀል እና መጠፋፋት ያደገ፣ የሠለጠነ እና የበለጸገ ማንም የለም::

ሐዋርያው «እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱ እርስ በርሳችሁ ትጠፋፋላችሁ» እንዳለ ያለ ፍቅር፣ ያለ ዕርቅ እና ያለ ይቅር ባይነት ሀገርን በሰላምና ልማት ጎዳና ማቅናት ከባድ ነው:: ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፣ ወገኖች፣ እምነቶች፣ ቡድኖች፣ አመለካከቶች ...ወዘተ ባሉባት ሀገር፣ ትላንት በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩትን የተለያዩ ጥፋቶች፣ ስሕተቶች፣ ግጭቶች እና ጠቦች በቂም በቀል ማውረስ እንደ አንድ ባህል በሚወሰድባት ሀገር የሚታየውን አስከፊ ሁኔታ በይቅር ባይነት ካልዘጋነው ማለቂያ ወደሌለው የጥፋት አዘቅት መግባታችን የማያጠራጥር ነው::

ስለሆነም አንድ ቦታ ላይ አቁመን የትላንቱን የውዝግብ አጀንዳ እንዝጋው:: *መቃቃርና መገፋፋት* በተጠናወተው መንፈስ ስለ ትላንት ብቻ መነጋገር አቁመን ስለ ነገም እንምከር:: ትላንት ብንለያይም ነገ አንድ ሆነን መቀጠል እንችላለን:: ትላንት ብንጋጭም ነገ ግን መፋቀር እንችላለን:: ትላንት ብንቀያየምም ነገ ግን በምሕረትና ዕርቅ አንድ ኾነን፥ በልዩነታችን ተስማምተን በአንድነት መጓዝ እንችላለን:: ይህም ተስፋ ሊፈጸም የሚችለው እንድን ነገር ዛሬ ነገ ሳንል ለመፈጸም ከበቃን ነው- ***ሳንዘገይ በመተማመን ተቀራርበን በሥርዐት፣ በጨዋነትና በግልጽ ተወያይተን፣ ችግሮቻችንን ለይተን ይቅር በመባባል::*** አስፈላጊ በኾኑ የጋራ ጉዳዮቻችን ሁሉ በራሳችን ጊዜ ተማምነን፣ ተቀራርበን፣ በሥርዐትና በጨዋነት ለማወያየት ይቻል ዘንድ ደግሞ ሕዝባችን በኑሮ ሒደቱ ያዳበራቸው ባህላዊ ልምዶቹ እንደ ተጠበቁ ኾነው ቤተ ክርስቲያናችንም በማንም እና በምንም የማይተካ፣ ምድራዊና ሰማያዊ፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ መልኮች ያሉት፣ ውጤቱ ከፍተኛ የኾነ ሚና እንዳላት እሙን ነው፤ ይኸውም በሕዝቡ ላይና በሕዝቡ መካከል ለማስተማር፣ ለመናዘዝ፣ ለኃጢአት ይቅርታን ለመስጠት፣ ለማግለድ፣ ለማስታረቅ የሚያስችላት መንፈሳዊ ሥልጣንዋና የላቀ ባለሟልነትዋ ነው:: ምእመናን ክርስቶስና ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይም እንደ ሕዝብ ለዘመናት ባዳበሩት የ<ሲቪላዊነት> ትውፊታዊ ውርሳቸው፣ ምሁራኑ ባካበቱት የዕውቀት አዝመራቸው፣ አበው እና እመው ደግሞ በአረጋዊነት ክብራቸው ቤተ ክርስቲያናችን ቀድሞም ስታከናውነው የኖረችውንና ዛሬም ልታደርግ የሚገባትን ጥረት ሊያግዙና ሊያስተባብሩ ያሻል እንላለን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## መንፈሳዊ ሕይወትና ሳይኮሎጂ

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም «ሐመረ ሕይወት» ዓምድ *«መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ለጠባይ ለውጥ»* የሚለውን ተከታታይ ጽሑፍ ተመልክቼዋለሁ:: እንደ ሳይኮሎጂ መምህርነቴና ከጽሑፉ የሐሳብ አቀራረጽና አቀራረብ እንደ ተገነዘብኹት የሳይኮሎጂ ሞያ የችግር አፈታት ዘዴ ለመንፈሳዊው የምክክር አገልግሎት እንደ ሚጠቅም ነው:: ሳይኮሎጂ የሚያጠናው አስተሳሰብን፣ ስሜትንና ጠባይን /ተግባርን/ /thought, emotion and action/ ነው:: ይህ ደግሞ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው:: የሰው ልጅ ከምናየውና ከምናውቀው ሥጋዊ በሽታው ይልቅ በሥነ ልቡናዊ /Psychological/ ሕመም እንደ ሚሠቃይ የማያጠራጥር ነው:: የችግሩ ምንጭ ውስጣዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ሊኾን ይችላል:: በውጤቱም በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ጫና ይፈጠራል:: በመኾኑም በቤተ ክር ስቲያናችን አባቶችና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የአገልግሎት አካላት በሚሰጠው መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት የሳይኮሎጂ ሞያንና ሞያተኞችን አቀናጅተን ብንጠቀም መልካም ነው:: በምሕንድስና ሞያ ሕንጻን እንገነባለን፤ በምክክር አገልግሎት ሞያ ደግሞ ሰውን እናንጻለንና::

*መ/ር አምሳሉ ለሜሳ*
*መቐለ ዩኒቨርስቲ*

## ፖለቲከኛ ባለመባል....

ቤተ ክርስቲያናችንም ሀገራችንም «የሰው ያለህ» በሚሉበት ዘመን እውነተኛ ሰው ኾኖ መገኘት ከባድም ፈታኝም ነው:: ነገር ግን እውነቱን እውነት፥ ሐሰቱን ሐሰት ብሎ መናገር የሚገባ ነው:: በ13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም እንደ ቀረበልን ክቡር ሚኒስትሩ በአደባባይ የተናገሩትን እንዳልተናገሩት አስመስሎ የማለባበስ አስተያየት መስጠት፣ በዚህ ረገድ የተደረገውንም የዝግጅት ክፍሉን ጥረት ማቃለል አግባብ አይመስለኝም:: በእውነቱ የዝግጅት ክፍሉ አባላት ከእውነተኛ ሰው የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ተግባር አከናውነዋል:: አንባብያንም መመልከት ያለብን የጉዳዩ ባለቤቶች «ፖለ ቲከኞች ናቸው፥ አይደሉም» የሚለውን ሳይሆን የጉዳዩን እውነተኝነት መኾን አለበት:: ፖለቲከኛ ላለመባል በእውነትና በሐሰት መካከል መቆም የጽድቅን ባለቤት ያሳዝነዋል:: በመ ሠረቱ ጉዳዩን አንሥቶ ለመጠየቅም ፖለቲከኛ መኾን አያስፈልግም:: ማኅበረ ቅዱሳንም ኾነ መጽሔቱ እንደ አጠቃላይ በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ ገብተው አቅዋም አይዙም፤ ሊይዙም አይችሉም:: ነገር ግን በእናት ቤተ ክርስቲያን ክብርና ህልውና ላይ የሚነሡትን ለመቋቋም ወደ ኋላ ማለት የለባቸውም:: ምናልባትም እውነትን በመ ግለጻችን የሚደርስብን እንግልትና መሥዋዕትነት ሊኖር ይችላል:: ያንንም እንደ ክርስቲያንነታችን በአኰቴት ከመቀበል ውጭ ምርጫ የለንም:: ነገር ግን ከ«መሞት መሰንበት» ብሎ ማድበስበስ መንፈሳዊነት አይመስለኝም:: ከዚህ አንጻር የሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም ያተኮረበት ርእስ ጉዳይ ዘግይቷል ሊባል ይችል ይሆናል:: ያም ኾኖ ግን እትሙ በተለየ ሁኔታ መመስገን ያለበት ብቻ ሳይሆን ለወደ ፊቱም ይበል የሚያሰኝ አርቶዶክሳዊ ተግባር ነው::

*ዮሴፍ ታምራት - አ.አ*
*በላይ ዘገዬ - ከሚሴ*
*ቸርነት ዘውዴ - ባሌ -ጊንር*
*መ/ር አራጋው አንተነህ -ሞጣ*
*ዘደቡብ -ጂንካ*
*ረድኤተ አባተ-አዳማ ዩኒቨርስቲ*

## የታሪክ ምሁሩ ታሪክ ሠርተዋል

በ14ኛ ዓመት ቁጥር አንድ እትም ወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ *«በታሪክ ጥናት ትልቁ ወንጀል»* በሚል ርእስ አቶ አበባው አያሌው ከአ.አ.ዩ ያቀረቡልን ወቅታዊ ጽሑፍ ከዚህ ቀደም በተለምዶ ከምናውቀው የተለየ፣ እውነቱን ከሐሰት ለመለየት የሚያስችል ሞያዊ ገለጻ የቀረበበትና ለእኛም መንፈሳዊ ኩራትን ያጎናጸፈ በሳል ዝግጅት ነው:: የታሪክ ምሁሩ ታሪክ ሠርተዋል:: ጊዜው ደርሶ ሐቁን ለማወቅ አብቅተውናል:: «ቃለ ሕይወት ያሰማልን፤ ረጅም ዕድሜን ከተሟላ ጤንነት ጋር ይስጥልን» ብለናል:: ለምሁሩ ገለጻ መንሥኤ የነበሩት ነጥቦች በተነሡባቸው የውይይት መድረኮች ከተገኙት አንዱ ነኝ:: በበኩሌ በወቅቱ ቤተ ክርስቲያናችንን አስመልክቶ በተሰነዘሩት ትችቶች ላይ ከመጠየቅ ያልሰነፍኩ ቢሆንም ያስደሰተኝ ግን ሙስሊሞች ሳይቀሩ ተቃውሟቸውን በማሰማታቸው ነበር:: «ጉዳዩ አልፏል፤ ጊዜው አይደለም፤ አሁን መወያየት ያለብን ስለ ሀገራችን ጉዳይ መኾን አለበት» ሲሉ ነበር:: ሕዝብን እንዲፋቀር እንዲተሳሰብ እንጂ ማቃቃር ለማንም አይበጅም:: የኾነውን ሁሉ ሳስበው አልቅስ አልቅስ ይለኛል:: ለማንኛውም እንደ አቶ አበባው አያሌው ያሉ፣ ለቤተ ክርስቲያናችንም ለሀገራችንም እውነታውን የሚገልጡ «አፖሎጂስቶች» ያስፈልጉናል:: ዝምታ አላዋጣም:: ስለሆነም አቶ አበባው አያሌው የጀመሩትን ጽሑፍ አስፋፍተው በመጽሐፍ መልክ ቢያሳትሙት በበኩሌ ያስደስተኛል:: ሌሎች ምሁራንም የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል:: እናንተም እነርሱን እያፈላለጋችሁ ማበረታታት ይገባችኋል::

*ኃይለ ማርያም እሸቱ -አ.አ*
*ዲ/ን ዳዊት ሰሎሞን- ጅማ ዩኒቨርስቲ*
*ዲ/ን ተመስገን ዘገየ - ወረታ ግቢ ጉባኤ*
*መሥፍን መንገሻ- አቃቂ*
*አዜብ አብዱላሂ -ሐረር*

## በጉጉት የሚጠብቋት ሆናለች

የኅዳር /ታኅሣሥ 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትምን አንድ ወዳጄ ልኮልኝ ለማንበብ ዕድሉን አግኝቼአለሁ:: አሁን ያለሁበት አገር ሳልመጣ የመጽሔቷ ቋሚ ደንበኛ ነበርኩ:: በይዘቷ የተሟላችና የምታኮራ ለመሆኗ ምስክር ነኝ:: አሁን በምኖርበት ግዛት ግን የመናፍቃኑ ቁጥር ከመብዛቱ የተነሣ «ቪዛ ያገኙት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከደው ነው እንዴ?» ያሰኛል:: ያም ኾኖ ካህናት አባቶችና መምህራን ጥረት ያደርጋሉ:: ይህን ጥረታቸውን ለማገዝ የሐመር መጽሔት ሥርጭት አድማስ ሊሰፋፋ ይገባል:: እዚህ ያለውም ምእመን ከመጽሔቷ ማዕድ መቋደስ አለበት:: ለመኾኑ ችግራችሁ ምንድን ነው? የሥርጭቱን ሓላፊነት በወኪልነት ለመሥራት በስቴታችን ያሉት ካህናትና መምህራን ወደ ኋላ የሚሉ አይመስለኝም:: እባካችሁ በሰው አገር በሰው ባህልና ቋንቋ ለምንኖር ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችሁም አስቡ:: በርከት ያሉ ኮፒዎች በወቅቱ ላኩልን:: እኔ ዘንድ ያለችዋን የቅርብ እትማችሁን ያልተዋሰኝ ሰው የለም:: ሐመር ሁሉም የሚወዷትና በጉጉት የሚጠብቋት መጽሔት ሆናለች:: ልዑል እግዚአብሔር አገራችንን ይጠብቅልን:: አገልግሎታችንን ይባርክልን::

*አበጀ ሲሳይ*
*ሚኒያፖሊስ -አሜሪካ*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ኦ ዘአጸሩብ መብቀለ በእንቲአነ ስምዖን እምሳክነ ወመድኃኒነ /ጌታችንን መስቀል እንዳሸከሙት/



ኦ ዘቀነዉከ በመልዕልተ መስቀል በእንቲአነ ስምዖን አምላክነ ወመድኃኒነ /ጌታችንን በመስቀል ላይ እንደ ቸነከሩት/

በ«መንግሥተ እግዚአብሔር» /theocracy/ ይመራ በነበረው በቀደመው ማኅበረሰብ ውስጥ ሃይማኖት የሰውን ሁለንተናዊ አነዋወር ይመራና ይቆጣጠር እንደ ነበር እሙን ነው:: የትምህርት፣ የሕክምና፣ የረድኤት /የሕዝብ በጎ አድራጎት/ ተቋማት እንዲሁም የሞያ /ጥበበ እድ/ ማኅበራት ሳይቀሩ መገኛቸው በእምነት ተቋማት ዘንድና በአሠራራቸውም በእነርሱ ተጽዕኖ ሥር ነበሩ:: ኋላ ላይ ግን ከዓለማዊ መንግሥታተ ሕዝብ /Secular States/ መስፋፋት፣ የኅብረተሰብ የሥራ ክፍፍልና መንግሥታዊ ቢሮክራሲ መዳበር ጋር ተያይዞ ከላይ ለአብነት የተጠቀሱት የእምነት ተቋማቱ የምርትና የአገልግሎት መስጫ ይዞታዎች በብዛት በዓለማዊ ማኅበሮች ቁጥጥር ሥር በመዋላቸው ሃይማኖት የነበረውን ***ማኅበራዊ ተጽዕኖ*** እያጣ ሔዷል:: The Phenomenon of Religion የተሰኘ መጽሐፍ ደራሲ ሞጃን ሞመን እንደ ሚያስረዱት ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ሃይማኖት በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ያለውን በጎ ተጽዕኖ እያጣ መሔዱ ከፍ ያለ ጉዳት ነው:: እንደ ሞጃን ሞመን ገለጻ ከቅርብ መቶ ዓመታት ወዲህ ሃይማኖትንና ሃይማኖተኛነትን እያናጋ ያለው ሁለተኛው ጉዳት ደግሞ በሠለጠነው ዓለም ***ለግላዊነት*** */Individualism/* እየተሰጠ ያለው ከፍተኛ ዋጋ ነው::

በግላዊነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ፍልስፍናና ሥልጣኔ ደግሞ የመንፈሳዊነትን አስተምህሮና ሥርዐት ከመቃረኑም በላይ የእምነትን አንድነትና ማእከላዊነት ያሳጣል:: ለኅብረተሰባዊ ድቀት /social decay/ ይዳርጋል:: ሌላው ደራሲ ዴቪድ ኸል SAVIOR OR SERVANT? PUTTING GOVERNMENT IN ITS PLACE /1996/ በሚል ርእስ የመንግሥትን ምንነትና የክርስቲያኖችን ሱታፌ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ባስረዱበት መጽሐፋቸው:- «የግላዊነት አስተሳሰብ በመጨረሻ የሚያደርሰው እስራኤላውያን በኅብረተሰብ ድቀት ወደ ተዘፈቁበት የዘመነ መሳፍንት አዘቅት ነው::» ይላሉ:: መስፍነ እስራኤል ኢያሱ ከሞተ በኋላ በእስራኤል ዘንድ ግብረ ገባዊነት ጠፍቶ «ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር::» /መጽ.መሳ.21፥25/:: መጽሐፈ መሳፍንት ከምዕራፍ 17 እስከ 21 ባለው ክፍሉ በግልጽ እንደ ሚያሳየን በዘመኑ:- ጣዖት አምልኮ፣ ግብረ ሰዶማዊነት /በብንያም ነገድ - ምዕ.19፥22/፣ ማኅበራዊ ጭቆና፣ የእርስ በርስ እልቂትና ተደጋጋሚ የውጭ ወረራ በእስራኤል ላይ ሰፍኖ ነበር::

በዘመናችንም የካፒታሊዝም ዕድገታቸው በግላዊነት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ፍልስፍናና ሥልጣኔ ላይ በተመሠረተና በልማት በገፉ አገሮች ኅብረተሰባዊ ድቀት ጎልቶ ይታያል:: እንደ ዴቪድ ኸል ገለጻ ለኅብረተሰባዊ ድቀት መድኀኑ:- *«የሕግና የፖለቲካ ሥርዐቱ መሻሻል በጠንካራና በተሻሻሉ የግብረ ገብ ትምህርቶች መታገዙ ነው::»* ለዚህም ስኬታማነት የአሜሪካ ሕገ መንግሥትን መሠረተ ሐሳቦች ከቀረጹት አንዱ የነበረውና የፕሬዝቢቴሪያን ፕሮቴስታንት እምነት መሥራች የኾነውን የጆን ካልቪንን /1509-1564 እ.አ.አ/ አስተምህሮ በማጽናት:- *«ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ተጽዕኖ ነጻ ኾና፣ አንዱ በሌላው ጉዳይ ጣልቃ ሳይገባ ተባብረው መሥራት ይኖርባቸዋል::»* ብለዋል::

ዴቪድ ኸል እንደ ሚያስታውሱት በአሜሪካ እ.አ.አ ከ1960 -1970ዎቹ አጋማሽ ድረስ መንፈሳዊው ጉዳይ በሥርዐተ ትምህርቱና በመንግሥት የፖሊሲ ቀረጻዎች ሂደት ቸል በመባሉ የዕንስ ማስወረድን ሕጋዊ ማድረግ /1973/፣ በትምህርት ቤቶች የግብረ ገብነት ትምህርትና የመጸለይ መብት መከልከል /1963/ የመሳሰሉ ርምጃዎች ተወስደዋል:: እ.አ.አ ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ መንግሥት ተጠብቀው ለቆዩ የክርስትና እሴቶች ግድ እንደሌለው ያስተዋሉ የእምነት ተቋማት በበኩላቸው ***«ለመንፈሳዊ ሕይወት ሚጠት»*** */Christian Reconstructionism/* ከመነሣሣታቸውም በላይ በፖለቲካ ሥርዐቱ ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ ለጀመሩት ተከታዮቻቸው ከፍተኛ ድጋፍ ሰጥተዋል:: /SAVIOR OF SERVANT, pp. 2-3,372-375/:: በአውሮፓና በላቲን አሜሪካ አንዳንድ ሀገሮችም በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በሊበራል ፓርቲዎች አንጻር ግራ ዘመም የሆኑ ፓርቲዎች /የክርስቲያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የሶሻሊስት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ.../ መቋቋም የጀመሩት ለማኅበረሰብ ደኅንነትና ፍትሕ ለመታገል፣ በተለይ ደግሞ የክርስቲያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎቹ ነባራዊ የክርስትና እሴቶችን /ለድሆችና ሥራ አጦች ርዳታ መስጠት የመንግሥት ሐላፊነት መሆኑን እንደ ማስገንዘብ የመሳሰሉ/ ማኅበራዊ ችግሮች በፖሊሲ ቀረጻዎች ሒደት ዋነኛ አካል ሆነው ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ በሚል ነው:: የማኅበራዊ ኑሮ እና ክብካቤ አማካሪዋ ወይዘሮ ፊሊቀች መታፈሪያ ከካናዳ ዳርትማውዝ ባደረሱን ስፊ መጣጥፋቸው እንዳብራሩት ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን አዳብረናል በሚሉት ያደጉ ሀገሮች ያሉ አንዳንድ ሐሳቦችና ፍልስፍናዎች ነገረ እግዚአብሔርን ችላ ብለው ከቆዩ በኋላ ዛሬ ያስከተሉት የኑሮ ዘይቤ መረን ወጥቶ ማጣፊያው የቸገረ ከመሆኑ የተነሣ:- *«Post Modernism'* ብለው ወደ ቀደመው በጎ አነዋወር የመመለስ ሁኔታ ይታያል::»


በአጠቃላይ ከጊዜ በኋላ ዛሬ በመላው አውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በአንዳንድ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች /ለምሳሌ:- ጋብቻ/ ወደ ቀደመ መልኩ እንዲመለስ ጥረት እየተደረገ ነው:: ለውጤታማነቱም በሰብአዊነት ላይ ያተኮሩ /Religion of Humanism/ እና በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የእምነት ተቋማትን /state funded religion/ እስከ መመሥረት የደረሱ ሀገሮች አሉ:: ነባሮቹ የእምነት ተቋማትም በማኅበራዊ ሥነ ልቡናው የረጋ ኅብረተሰብ እንዲኖር ያደርጉ ዘንድ የመንግሥት እገዛ እየተደረገላቸው ይገኛል:: በተለይም ***«ሽብር ሃይማኖት የለውም»*** እንዲሉ ከመስከረም አንድ ቀን 1994 ዓ.ም የኒውዮርኩ የሽብር ጥቃት፣ ከመጋቢት 2 ቀን 1996 ዓ.ም የስፔን - ማድሪድና ከሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም የለንደኑ የምድር ውስጥ ባቡር ቦንብ ፍንዳታዎች ወዲህ የክርስትናውም ኾነ የእስልምናው እምነት ክፍሎች እርስ በርሳቸው፣

# ምሕረት ፣ ይቅር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org





*«ሁለቱን [ምእመናን እስራኤልንና አሕዛብን] አንድ ያደረገ ሰላማችን እርሱ ነውና በሥጋውም በመካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰ። ጥልን ሻረ፤ ዕርቅንም አደረገ፤ በመስቀሉም በአንድ በሥጋው ሁለቱንም ወደ እግዚአብሔር አቀረባቸው፤ በእሱም ጥልን አጠፋ። መጣ፤ ቀርበን ለነበርነው ሰላምን፥ ርቀን ለነበርነውም ሰላምን ሰጠን።»*

ከመንግሥት የአስተዳደር ተቋማትና ከብዙኀን መገናኛ ጋር በመተባበር ሁኔታው የፈጠረውን የእርስ በርስ መጠራጠር፣ ስጋት፣ ቁጣና ብስጭት ለማርገብ፣ የጥላቻና የጽንፈኝነት ስሜቶችን ለማራቅ የሲቪል ማኅበራትንና ፈርጀ ብዙ ማእከላትን አቋቁመዋል። በእኒህም አማካይነት የስፖርት፣ የመዝናኛና የሌሎች ***በእምነት፣ በዘር እና በቀለም ልዩነት ውስጥ አብሮነትንና መቻቻልን*** /Multiculturalism/ የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ ዐውደ ትርኢቶችን እያዘጋጁ በማቅረብ ላይ ናቸው።

የእምነት ተቋማቱ /ለምሳሌ፡- «የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን»/ የባሪያ ንግድን በመሳሰሉ አሳፋሪ ታሪኮች የነበራቸውን ተሳትፎ ገምግመው ይፋዊ ይቅርታ ለመጠየቅ ከመዘጋጀት ጀምሮ መንግሥታቸው በኢራቅ ላይ ያካሔደውን ዘመቻ /አሁን ሀገሪቱ ባለችበት ሁኔታ ለቆ አለመውጣቱን ቢደግፉትም/ እና በሽብርተኝነት ላይ የሚያራምደውን አቋም ክፉኛ እስከ መተቸት ደርሰዋል። በሌላ በኩል ከአህጉራችን አፍሪካ፥ በደቡብ አፍሪካ ያለውን የመንግሥትና የእምነት ተቋማት ግንኙነት ስንቃኝ በዘር መድልዎ ሳቢያ የተፈጠረውንና በቀጣይነት ሊፈጠር ይችል የነበረውን ሀገራዊ ቀውስ ለማስወገድ ከአፓርታይድ አገዛዝ ውድቀት በኋላ እ.አ.አ በ1994 የተቋቋመውን ***«የእውነት አፈላላጊና የዕርቅ ኮሚሽን»*** */Truth and Reconcillation Commission/* በመምራት የላቀ ሚና የተጫወቱትን የሰላም ኖቤል ተሸላሚና የአንግሊካን እምነት መሪ ዴዝሞንድ ቱቱን እናገኛለን። አቶ ፍቅረ ሥላሴ አርአያ ለዚህ እትማችን ባቀረቡልን ጽሑፍ እንደ ሚገልጹት፡- ኮሚሽኑ የአፓርታይድ አገዛዝ ተዋንያን በድርጊታቸው እንዲጸጸቱና ምሕረት እንዲያገኙ፣ ብሎም በዕርቅና ይቅር ባይነት መንፈስ የበቀል ፍትሕ እንዲወገድ በዘረጋው ሥርዐት አርአያነት ያለው ተግባር አከናውኗል። ልዩነቶቻቸውን በፖለቲካዊ ቀውስ ለመፍታት ለሚታመሱት ሀገሮችም ምሳሌ /global model/ ሆኗል።

ከዚህም ባሻገር ዴዝሞንድ ቱቱ የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ድህነትን ለመቀነስና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት ያደረገውን ጥረት የሚደግፉና የሚያደንቁ ቢሆንም በፀረ ድህነት ትግሉ የታየውን ዘገምተኛነትና ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ 4.5 ሚልዮን ያህል ዜጎች መድኃኒት ማቅረብን በተመለከተ መንግሥት የሚከተለውን ዘይቤ ነቅፈዋል። አማራጮችንም አቅርበዋል። ለእርሳቸው ነቀፌታ ፕሬዝዳንቱ ታቦ ምቤኪ ስለ ሰጡት ጠንካራ ምላሽ በኒውስዊክ መጽሔት /ዲሴምበር 24፣ 2004/ የተጠየቁት ዴዝሞንድ ቱቱ፡- *«የምናገረው ከጥላቻ አይደለም። ከነበርንበት ሁኔታ አንጻር የደረስንበት ደረጃ አስደናቂ ነው። የበለጠ አንጸባራቂ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችለን ዕምቅ አቅም ግን አለን። ይህች የምወዳት አገሬ ነች። መንግሥታችንም ተሳክቶለት ለማየት እወዳለሁ። ሲከናወንለት ጎሽ ብዬ አመሰግነዋለሁ፤ የሚቀረውንና ሊያተኩርበት የሚገባውን ጉዳይ ለመጠቆም ደግሞ ወደ ኋላ አልልም።»* ብለዋል። ቱቱ ከሀገራቸው አልፈው አሜሪካ መራሹን የኢራቅ ዘመቻ ያካሔዱትና የደገፉት ወገኖች ሁሉ፡- «በተሳሳተ መረጃ ላይ ስለ መመሥረታቸው ገልጦ የመናገር ጨዋነት ይጠበቅባቸዋል።» ሲሉ መክረዋል። አያይዘውም፡- «በጓንታናሞ ቤይ- ኩባ ሰዎች ያለ ፍርድ መታሰራቸው ብዙዎቻችን የሰብአዊ መብትና ነጻነት ተሚጋች አድርገን ከምንመለከታት አሜሪካ የሚጠበቅ አይደለም።» ብለዋል። ከዚህ ሁሉ እንክን ጋር ፕሬዝዳንት ቡሽ ዳግመኛ በመመረጣቸው መገረማቸውን ያልሸሸጉት ዴዝሞንድ ቱቱ፡- በአሜሪካ ለፖለቲካ ሥልጣን በሚደረገው የምርጫ ፉክክር ውስጥ ሃይማኖት አለው ስለሚባለው ሚና ተጠይቀው ምላሻቸውን የሰጡት እንዲህ በማለት ነበር፤ ***«ሃይማኖት በራሱ ከሞራል አኳያ ገለልተኛ መኾኑን ለሰዎች ከመናገር ተቆጥቤ አላውቅም። እንደ አያያዝህ ልትጎዳበት አልያም ልትጠቀምበት ትችላለህ።»***

በአሁኑ ጊዜ እንደ ተጠቃሚው ወገን ፍላጎት የዴሞክራሲ መልኩ እየተቀያየረ ባለበት ሁኔታ ስለ ዴሞክራሲ በምዕራባውያን የሚለፈፈውን ሁሉ አምኖ ለመቀበል እያዳገተ መሆኑን የማኅበራዊ ኑሮና ክብካቤ ባለሞያዋ ወይዘሮ ፈለቀች ይናገራሉ። አያይዘውም፡- «እንደ ኢትዮጵያ የልዩ ልዩ እምነትና ባህል ሚዚየም በሆኑ ሀገሮች የፖለቲካ ፍልስፍናን፣ የልማት አስተሳሰብንና የሀገር አስተዳደርን ከሕዝቡ ሃይማኖትና መንፈሳዊ እሴቶች ጋር አዛምዶና አዋዶ በመቅረጽ /ነዋሪ ባህላችንንና ዘመናዊ ሥልጣኔን በማስታረቅ/ ረገድ ከተሳካልን ነባራዊ ሁኔታው ለዕድገት የሚበጅ ማኅበራዊ አቅም /Socal Capital/ ይፈጥርልናል። ከዚህ ውጭ ኃያላኑ በዴሞክራሲ ካባ ተሸፍነው የሀገር ፖለቲካን በኀይልም ይሁን በእጅ አዙር ቅኝ በሚያደርጉበት፤ በነጻ ገበያ፣ በልማት ብድርና ርዳታ ሰበብ ኢኮኖሚውን ለጥገኝነት በሚዳርጉበት፣ በባህል ወረራ የሕዝቡን ሥነ ልቡናዊ ጥንካሬ በሚሰልቡበት ሁኔታ ***'ዴሞክራታይዜሽን'*** ሳይሆን ***'ዲሞራላይዜሽን'*** ይንሰራፋል። ስለሆነም የዴሞክራሲን መልክና በስሙ የሚፈጸመውን ድርጊት በሐቀኛ ይዘቱ ሬጋ ብለን ልናጤነው ይገባል።» በማለት ያሳስባሉ።

በውጭው ዓለም የመንግሥትንና የእምነት ተቋማትን ገንቢ መተባበር ከሞላ ጎደል በዚህ መልኩ ከቃኘን የሀገራችንስ ነባራዊ ሁኔታ ቀደም ሲል እንደ ምሳሌ ባወሳናቸው የግንኙነት መልኮች ጠገግ ምን ይመስል ነበር? ምላሹን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ምንጮች፣ ከነገሥታቱ ዜና መዋዕሎች፣ ሲሻን ደግሞ የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያን መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት በግልጽ ከሚያሳዩን የዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ታላቅ ቅርሳችን፥ ፍቅር እስከ መቃብር ልቦለድ ታሪክ፥ መገንዘብ እንችላለን።

ብዙዎች እንደ ሚናገሩት በአጠቃላይ ሲታይ የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው። ጦርነቶቹ በአብዛኛው ለሀገር አንድነት /ለግዛት ማስፋፋት/፣ ለከፍተኛ ሥልጣንና የውጭ ወራሪዎችን ለመከላከል በነገሥታቱ፣ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ መሪነት የተካሔዱ ናቸው። የውጭ ወራሪዎችን ለመከላከል ከተደረጉት ጦርነቶች ውጭ በሹማምንቶቹ መካከል ለሥልጣን የበላይነት /ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ እንደ ሚሉት፡- ከግዛታዊ መሪነት ወደ ዐፄአዊ ዙፋን ለመውጣት/ የተካሔዱት የእርስ

# ባይነት፣ ዕርቅ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በርስ ግጭቶች፡- «የባለሥልጣናቱን የአእምሮ፣ የመንፈስና የአስተዳደር ውድቀት ያመለክታሉ» ቢባሉም በሕዝብ ደረጃ አንድነትን ማጠንከራቸውና የግዛት አንድነትን ማስጠበቃቸው ደግሞ የተሻለ ገጽታቸው እንደ ኾነ ይገለጻል፡፡ ይኸውም ሕዝቡ በመወለድ ብቻ ባገኘው ዘር፣ ቋንቋና እምነት ተለያይቶ ከመዋጋት ይልቅ በአንዱ ክፍል ግፍ ቢበዛበት ወደ ሌላው ሔዶ፣ እፎይ ብሎ ለመኖር፣ ለመተዋወቅና በጋብቻ ለመዛመድ በመቻሉ ነው፡፡ ለዙፋን ተፋላሚዎቹም ቢሆን በፍልሚያ ፍጅታቸው መሐል «ተከታይ እኔ ነኝ፥ አንተ አይደለህም» በሚል ሊቆናጠጡት የሚሹት ዐፄአዊ ዙፋን ከመገንጣጠል ይልቅ የአንድነት ምልክት ኾኖ ቆይቷል፡፡

የብዙ ቋንቋዎች፣ እምነቶችና ባህሎች ቅድስት መካን /Multiculturalist/ በኾነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ የመንግሥታት በጠመንጃ ኃይል መለዋወጥና ከዚህም ጋር ተያይዞ ግጭትና መተባበር ተደጋግሞ የታየ ቢሆንም ሕዝቡ እንደ ሕዝብ እርስ በርሱ ባለመናቆርና ባለመለያየት አንድነቱን አጽንቶ /Coherency/ ሊኖር የቻለው በሃይማኖቱ መንፈሳዊ መሠረትነት በተገነባ፣ በይሉኝታ በታፈረ፣ ከገኾዎቹ በላቀ ከፍተኛ *የ«ሲቪ ላዊነት» ትውፊታዊ ውርሱ* ነው፡፡ *«ሲቪላዊነት»፡-* ከክፋትና ጭካኔ ይልቅ ምሕረትንና ሰብአዊ ርኅራኄን፣ ከጦረኛነትና ጠበኛነት ይልቅ ዕርቅንና ሰላምን፣ ከመገንጣጠል ይልቅ ቤተሰባዊነትንና መልካም ጉርብትናን፣ ከቂም በቀለኛነት ይልቅ ይቅር ባይነትን የመውደድ በጎ ኀብረተሰባዊ ጠባይዕ ነው፡፡ ይህም ዓለም የመሰከረውና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያኮራ ነው፡፡ /ዶክተር ጠንክር ቦንገር፥ *የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ዕድገትና ልማት ከየት ወዴት? እንዴት?*፥ 1997 ዓ.ም፥ ገጽ 1-2፣ 69፤ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ፥የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966 ፥1989 ዓ.ም.፥ ገጽ 241፤ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፥ *ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?* 1986 ዓ.ም፥ ገጽ 3-4፣ 50/፡፡

እኒህን መልካም ኀብረተሰባዊ ጠባዕያት በመከባከብ፣ በሕግና ሥርዐት በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ ሕዝቡ በባህሉ ያዳበራቸው በርካታ መተዳደሪያዎችና የግጭት መፍቻ ስልቶች /Norms of Moral and Customary Conflict Resolution Mechanisms/ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም ጋር ደግሞ ሕዝቡ በየጊዜው የተሻሻለ ደረጃን ሲይዝ በአገራችን የመንግሥት ታሪክ ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀሱና ሁሉንም ማኅበራዊ ግንኙነቶች እንደ ጠባዕያቸው ለማስተናገድ የሚያስችሉ የሥጋዊና መንፈሳዊ ሕጎች መድበል /ፈውስ መንፈሳዊ፣ ፍትሐ ነገሥት/ ምንጭ ከመኾን ባሻገር ንጉሡ በሚያዝዘውና ጳጳሱ በጸሎትና ቡራኬ በሚያደላድለው *ሥርዐተ ደብር* ለተበደለ፣ ለገደለ መማጠኛ፣ የምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም መገኛ ማእከል በመኾን ቤተሰብን፣ ሕዝብን፣ ሕዝብንና መንግሥትን፣ መሳፍንቱን፣ መኳንንቱንና ነገሥታቱን እርስ በርሳቸው በማቀራረብ፣ በማስታረቅና በማዋሐድ ለጋራ ዓላማ መንፈሳቸውን፣ አእምሯቸውንና ክንዳቸውን እንዲ ያስተባብሩ ተቋማዊ የዳኝነትና ኀላፊነቷን ስትወጣ የኖረችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ /*መጽሐፈ ሕግጋት ዐበይት*፥1962 ዓ.ም፤ ዶ/ር ዘውዱ ውብ እንግዳ፥ *የፌደራላዊ መንግሥት አመጣጥ ችግሮች*፥1997 ዓ.ም፥ ገጽ 160፤ *ፍትሐ ነገሥት ፍትሐ መንፈሳዊ* ፥ አንቀጽ 47፥ 1681፣1700፣ 1701፤ አንቀጽ 50፥ 1794/፡፡

ቤተ ክርስቲያን በሕዝቡ መካከል የመንፈስ ሥልጣንና የላቀ ባለሟልነት አላት፡፡ የባለሟልነትዋ መሠረቱ በህብተ ክህነትዋ የምታድለው ጸጋ እና ሰላም ነው፡፡ የማስታረቅ አገልግሎትዋ ሥጋዊና መንፈሳዊ፣ ምድራዊና ሰማያዊ መልክ ያለው ሲኾን ውጤቱም ከፍተኛ ነው፡፡ ጌታችን በአንቀጸ ብፁዓን ትምህርቱ፡- «ዕርቅ የሚያደርጉ /የሚያስታርቁ/ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና፡፡» /ማቴ.5፥9/ ሲል አስተምሯል፡፡ ይህም በትርጓሜ ወንጌል እንደ ሚከተለው ተብራርቷል፤ «አቀበቱን ወጥተው ቍልቍለቱን ወርደው ሰውን ከሰው ጋር የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፡፡ … አንድም፡- ሰውን በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቁ ቀሳውስት ንዑዳን ክቡራን ናቸው፡፡ ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ፣ ወደ መቃብር ወርዶ ሰውን ከእግዚአብሔር እንዳስታረቀ እነርሱም አቀበቱን ወጥተው፣ ቁልቁለቱን ወርደው በማስታረቃቸው ወልደ እግዚአብሔርን መስለውታልና የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ፡፡» «ወንድማማቾች በማይገባ ነገር ተጣልተው፣ በሐሳብ ተለያይተው፣ የማይግባቡና የማይስማሙ ከዚያም አልፎ ነገራቸው ከዳኛ የሚያደርሳቸው፣ አንዱ በአንዱ ላይ ክፉ ለመሥራት የሚገፋፋቸው ኾኖ ሲገኝ ከጠቡ አግባብ የሌላቸው ወዳጆች፣ ባልንጀሮች፣ ሽማግሌዎች በመሐከል ገብተው፣ ማልደው፣ በፍቅር ተቆጥተው ወይም አባብለው ለዕርቅ ቢያደ ርሷቸው ሊፈርስ የነበረ ቤት ይታነጻል፤ የፈሰሰ ደም ይደርቃል፤ ነባር ቂም በቀል ይርቃል፡፡ በዚህም ምክንያት ጥንት ጠበኞች የነበሩ ሰዎች ሙሉ ሰላም አግኝተው አዲስ ኑሯቸውን ሲያሻሽሉ፣ አስታራቂዎቹም በሁለቱ ዕርቅ ተቀባይ ወገኖችና ጉዳዩን በሚያውቁት ሁሉ ዘንድ ሞገስ ያገኛሉ፡፡ ጥቅሙም ለሥጋና ለነፍስ ስለሆነ በነፍሳቸውም ብፅዕናን ያገኛሉ፡፡»/ አለቃ አያሌው ታምሩ፥ ***ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም***፥ 1992 ዓ.ም ፥ገጽ 10/፡፡

ሰው በድሎ ከክብሩ ከተዋረደ ከተድላ ገነት ከተሰደደ በኋላ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ኃጢአት የወለደውን ልዩነት ጊዜው ሲደርስ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ኾኖ፣ በሥጋ ተገልጦ በመስቀሉ ጠርቆ አስወግዶታል፡፡ ኤፌ.2፥14-18፡፡ ከአሮን ክህነት በላቀና በረቀቀ የክህነት ሥርዐት፣ ካህን፣ አስታራቂ፣ መታረቂያ፣ መሥዋዕት ኾኖ በፈጸመው ቤዛነቱ የሰውና የእግዚአብሔር ዕርቅ ከፍጻሜ ደረሰ፡፡ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል በሥራ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ካስታረቀ በኋላ የማስታረቅን መብት ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል፡፡ በቃልና በሥራ የፈጸመውን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አውርሷል፡፡

በትንሣኤው ቀን ማታ በመካከላቸው ተገኝቶ፡- «ሰላም ለሁላ ችሁ ይሁን» ብሎ ሰላሙን ከሰጣቸው በኋላ፡- «አባቴ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን ወደ ዓለም እልካችኋለሁ» አላቸው፡፡ በላያቸውም እፍ ብሎ መንፈስ ቅዱስን አሳደረባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ፡- «ኃጢአቱን ይቅር ያላችሁት ይሰረይለታል፤ ኃጢአቱን ይቅር ያላላችሁት አይሰረይለትም፤» /ዮሐ.19፥20-23/ ብሎ ሥልጣነ ክህነትን ሰጣቸው፡፡ በዚህም ቃል የማስተማር፣ የመናዘዝ፣ ለኃጢአት ይቅርታን የመስጠት፣ የማማለድ፣ የማስታረቅ፤ በጠቅላላው ከዓለም ልዩ የኾነ ሥራ ለመሥራት፣ ልዩ ኃይል የማድረግ፤ በምድር በሰማይ ባለሟል ለመኾን የሚችሉበትን ሥልጣን መሠረተላቸው፡፡ ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ሁለተኛ መልእክቱ፡- «… *የዕርቅ ቃሉንም በእኛ ላይ አደረገ፤ የይቅርታውን መልእክትም ሰጠን፡፡ እኛስ በክርስቶስ አምሳል እንለምናለን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማላጅነት ደስታን ይሰጣችኋል፤ እግዚአብሔርን በክርስቶስ ደስ ታሰኙት ዘንድ እንለምናችኋለን፡፡»* /2ቆሮ.5፥18-20/ ሲል ተማፅኗል፡፡ እንዲህም ስለሆነ ዛሬ አማላጅነት /አስታራቂነት/ የቤተ ክርስቲያን ሀብት ነውና ቀሳውስት፣ ጳጳሳት ጸጋ ሀብትን በረከትን ይሰጣሉ፤ ይልቁንም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አማላጅና አስታራቂ ኾነው ይቆማሉ፣ ግዳጃቸውንም ይፈጽማሉ፡፡ የእምነት ተቋማት ባሉበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋፅኦ የሚያመላክቱ ሌሎች መወሰኛዎች መኖራቸውን የሚዘረዝሩት አቶ ፍቅረ ሥላሴ አርአያ፡- *«ረጅም ታሪክ፣ በርካታ ምእመንና ጉልህ ማኅበራዊ ሚና ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በራስዋም ኾነ ከሌሎች የእምነት ተቋማት ጋር በመተባበር በአገራችን ልዩ ልዩ ቦታዎችና ምክንያቶች የሚነሡ ግጭቶችንና አለመረጋጋቶችን በውይይት፣ በዕርቅና ሁሉም ወገኖች በሚጠቀሙበት ሁኔታ የሚፈቱበትን መንገድ ማፈላለግ፥ ምእመናንዋና መላው የአገሪቱ ዜጎች አጥብቀው የሚሹት ወቅታዊ አገራ ዊ ሚናዋ ይመስለኛል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ግንባር ቀደም የይቅርታና ዕርቅ መልእክተኛ የመኾን ማኅበራዊ ሚናዋ በማንምና በምንም የማይተካ ነው፡፡»* ይላሉ፡፡

ለብዙ ሰዎች ሰላም ማለት ጦርነት የሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ <ሰላም>ን ዓለም የሚያውቀው በደረቅ ቃሉ ብቻ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ የታፈነ ጥላቻ በነገሠበት አፍዓዊ ጸጥታ ብቻ የተሟላ ሰላምን ሊያመጣ አይችልም፡፡ ጥላቻ ክፉ ጦርነት ነው፡፡ ወዲህም ደግሞ ኃጢአትና የኃጢ አት ጎምዛዛ ፍሬ÷ <ሞት> በአለበት ዓለም ሰላም የለም፡፡ ከስሕተት በኋላ ሰው ከኃጢአት ያገኘው ፍሬ ሞት ስለሆነ በዓለም እስካለ ድረስ ስንቁ ጭንቀት፣ ስጋት፣ ፍርሃትና ድንጋጤ ኾኗል፡፡ ይህ ሁሉ ሁኔታ አባታችን አዳም በበደለበት ቅጽበት በዔደን ገነት በዛፎች መካከል ተሰውሮ ሳለ በራ ሱ ላይ ታይቷል፡፡ ለልጆቹም ተላልፏል፡፡ ዘፍጥ.3÷1-21፡፡ እያንዳንዱ ሰውም በኃጢአቱ የራሱ ገዳይ ነው፤ የራሱ ደም ከራሱ ይፈለግበታል፡፡ ስለዚህም በነፍሱም በሥጋውም በሚጠብቀው ቅጣት ሲጨነቅ፣ ሲጠበብ፣ ሲደነግጥ፣ ሲፈራ ኖሯል፡፡ ኋላ ግን ሥግው ቃል ፍጹም አስታራቂ /Perfect Reconciler/ ኾኖ ሲጨነቁ ለነበሩት ሁሉ ለሥጋም ለነፍስም ከሦ ለሞት ለኃጢአት ከመገዛት ነጻ አወጣቸው፡፡ ዕብ.2÷15-19፡፡ ያን ጊዜ ፍ ጹም ዕርቅ፣ ዕረፍትና ጸጥታ ተገኘ፤ ልብ ከጭንቀት ዐረፈ፡፡ ሰላም ይህ ነው፡፡

> *በጥላቻ ላይ ኅብረት አይመሠረትም፡፡ ዕርቅን ረግጦ ሰላምን መሻት አያዋጣም፡፡ ምልጃን ንቆ መታመንን ማግኘት ያዳግታል፡፡ በጥላቻና ፕርጣሬ ደግሞ አገርን መገንባት አይቻልም፡፡*

ሰላም የመንፈስ ደስታና እርካታ ነው፡፡ ሰላም በራስና በሌሎችም ሰዎች መካከል መተማመን ሲኖር ነው፡፡ ጌታ «ሰላሜን እተውላችኋለሁ፤ የአባቴን ሰላም እሰጣችኋለሁ፤» ያለውን ተስፋ ለመፈጸም «ሰላም ለእናንተ ለሁላችሁ ይሁን» ብሎ ለጊዜው በሥርዐተ ትስብእት በአጠገቡ ለነበሩ ደቀ መዛሙርቱ የማያልቅ ሀብቱን ሰላምን ሰጠ፡፡ እነርሱም በቃላቸው ለሚያምኑት ሁሉ ሰላምን እንዲያድሉ፣ በገቡበት ቤት፣ በዋሉበት ባደሩበት ስፍራ ሰላም የሚገባው፣ ለምሕረት የሚበቃ ምሕረት ጠያቂ ካለ ሰላማቸውንና ምሕረታቸውን እንዲሰጡ ሥልጣን ሰጣቸው፡፡

***ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቁ እርስ በርሳቸውም ይታረቃሉ፡፡*** አይሁድና አሕዛብ በክርስቶስ አንድ ኾነዋል፡፡ ኤፌ.2፥14-16፡፡ በአንጻሩ መንገደኛው ኃይለ ገብርኤል ዘሐና «እግዚአብሔር ሲጣላ አያናግም በትር፥ ምክር አሳጥቶ ያደርጋል ድንግርግር» የሚለውን የአበው ብሂል ያስታውሰናል፤ የዕርቅ፣ የአስታራቂ፤ የምክክር የአመካከሬ መጥፋት የእግዚአብሔር ቁጣ መሆኑን ለመግለጽ፡፡ ክርስቲያኖች ማንኛውንም መለያየት በዕርቅ መወሰን ሲገባቸው በአሳበ ግትርነት እስከ ዳኛ የሚደርሱ ከኾነ ይህ አፈጻጸም ለእነርሱ እንደ ማይገባ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ቀዳማይ መልእክቱ አስረድቷል፡፡ 1ቆሮ.6፥7፡፡ ቁጣን እያበረዱ፣ ፍቅርን እያጸኑ በመኖር ፈንታ ቂም እየያዙ ጥልን እያጠነከሩ መሔድ ለክርስቲያኖች የማይገባ መኾኑ ተገልጿል፡፡ «ፀሐይ ሳትጠልቅ ቁጣችሁን አብርዱ፡፡» እንዲል፡፡ ኤፌ.4፥26፡፡ በየሰዓቱ፣ በየቀኑ የሚበድልና ከአምላኩ ምሕረት የሚጠይቅ ሰው እርሱም በበኩሉ የመድኃኔ ዓለም ክርስቶስን ፈለግ ተከትሎ ምሕ ረት እንዲያደርግ ታዝዟል፡፡ ጌታችን በዕለተ ስቅለት በመስቀል ላይ ሳለ ስለ ጠቅላላ ምእመናን ባቀረበው ጸሎት፡- «አባት ሆይ፥ የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ወቅታዊው የቤተ ክርስቲያን አገራዊ ሚና

## «ዕርቅን የማያውቅ ኅብረተሰብ ተስፋ የለውም::»

/ፍቅረ ሥላሴ ሥላሴ አርአያ/

*መግቢያ:-*

*አገራችን ከግንቦት 1997 ዓ.ም ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ወዲህ ስላለፈችበትና አሁንም ስላለችበት ሁኔታ ብዙዎቻችን የቅርብ ክትትል እንዳለን አምናለሁ:: ታድያ በሆነውና እየሆነ ባለው ነገር ሁሉ የአገራችን የእምነት ተቋማት ምን ሚና ተጫወቱ የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ትኩረት ያገኘ አይመስለኝም:: በዚህ ላይ በመመሥረት ነው በጉዳዩ ላይ አስተያየቴን ለመስጠት የተነሣሁት:: ይህን ለማድረግ ስነሣ ግን የግል አቋሜን እና የሐመር መጽሔትን አካሔድ ለማስታረቅ መጣር ነበረብኝ:: የቻልኩትን ሞክሬያለሁ:: በመሆኑም አንባብያን በዚህ ጽሑፍ የሚንጸባረቁት አስተያየቶች የጸሐፊውን እንጂ የአዘጋጆቹን አቋም እንደ ማያንጸባርቁ ለማሳሰብ እወዳለሁ::*

*የእምነት ተቋማት ባሉብት ማኅበረሰብ ውስጥ በርካታ ሚና ሊኖራቸው ይችላል:: የተቋማቱን ሚና ስፋትና ጥልቀት በአብዛኛው የሚወስኑት የእምነታቸው ተከታዮች ብዛት፣ የአመራር፣ ከመንግሥትና ከሌሎች የኅብረተሰቡ አካሎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንዲሁም የተቋማቱ ዕድሜና ታሪክ ነው:: እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ረጅም ታሪክ፣ በርካታ ምእመናን፣ ጉልህ አገራዊና ማኅበራዊ ሚና ያላቸው የእምነት ተቋማት የኅብረተሰባቸውን ችግሮች ለማቃለልና ሕዝብን ለማስተባበር፣ እንዲሁም የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች ለማቀራረብ ከሌሎች የተሻለ ብቃትና ተቀባይነት የሚያገኙበት ዕድል ጥቂት አይደለም:: የእምነቱ ተቋማት እና መሪዎቻቸው በኅብረተሰባቸው ውስጥ በርካታ ሚና ሊኖራቸው እንደ ሚችል ቀደም ሲል ጠቅሰናል:: እነዚህን ሚናዎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ብለን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ልንከፍላቸው እንችላለን::*

### ከመንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮ የሚመነጭ ውሱን ፖለቲካዊ ተሳትፎ

ከአገሪቱ ፖለቲካዊ ሥርዐትና ፖለቲካዊ ሒደት አንጻር ዐበይት የእምነት ተቋማት ታሪካዊ ሚና ሊኖራቸው ይችላል:: ቤተ ክርስቲያናችን ለረጅም ዘመናት በአገሪቱ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታዎች ውስጥ የነበራትን ሚና በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል:: የሮም ካቶሊክ በአውሮፓና በደቡብ አሜሪካ አገሮች፣ የፕሮቴስታንት እምነት ተቋማት በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ፣ የእስልምና እምነት ተቋማት መሪዎች በመካከለኛው ምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ አገሮች የነበራቸውንና ያላቸውን ፖለቲካዊ ሚና በተጨማሪ ማስታወስ ይቻላል:: በአጭሩ ፖለቲካዊ ሚና የምንለው የእምነት ተቋማቱ በመንግሥት ምሥረታና በመሪ አመራረጥ፣ እንዲሁም መንግሥት የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች በመደገፍ ወይም በመቃወም ወዘተ. የሚኖራቸውን ተሳትፎ ነው:: በዚህ መሰሉ ፖለቲካዊ ተሳትፎ የእምነት ተቋማቱ እና መሪዎቻቸው በቀጥታ ሊጠቀሙም ላይጠቀሙም ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የተወሰኑ የእምነት መሪዎች የሚጠቀሙበት፣ ነገር ግን በአጠቃላይ እምነቱ /የእምነት ተቋሙ/ እና ተከታዮቹ የማይጠቀሙበት አልፎም የሚጎዱበት የፖለቲካ ተሳትፎ ሊኖር ይችላል:: ይህን መሰሉ አጋጣሚ በተቋሙ ተቀባይነትና የመንፈስ ልዕልና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ስብራቱን ለመጠገን ብዙ ጥረት ሊጠይቅና ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል:: የእምነት ተቋማት የፖለቲካ ተሳትፎ ሁልጊዜም አንዱን ደግፎ ሌላውን ከመቃወም ጋር ብቻ የተያያዘ ነው ብሎ መነሣት ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል:: ለምሳሌ: - የእምነት ተቋም/መሪ/ የአማኞቹን ሕይወት /አኗኗር ወይም በአጠቃላይ አገሪቱን ይጎዳል የሚለውን የመንግሥት ፖሊሲ ሊቃወምና ማሻሻያ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል:: በተቃራኒው ደግሞ ፖሊሲው ለሕዝብ የሚጠቅም ኾኖ ሲያገኘው ሊደግፈው ይችላል:: ይህም ማለት ፖሊሲው ላይ ካለው አቅዋም ባለፈ ተቋሙ የአንዱ ፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊ የሌላው ፖለቲካ ፓርቲ ተቃዋሚ ሆኗል ማለት አይደለም:: በኅብረተሰባቸው ውስጥ ረጅም ታሪክ ያላቸው የእምነት ተቋማት ከሚኖርባቸው ታሪካዊና ማኅበራዊ ሐላፊነት የተነሣ አንዳንድ የመንግሥት ፖሊሲዎችን በቅርበት የመከታተልና አስተያየታቸውን የመስጠት መንፈሳዊ ግዴታ ሊኖርባቸው ይችላል፣ የሕዝበ ክርስቲያኑ እረኞች ማለትም ጠባቂና ተከባካቢዎች ኾነው ተሾመዋልና:: ዮሐ.21፥15-17፤ የሐዋ.20፥28::

የእምነት ተቋማት በኅብረተሰቡ ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን የመንፈስ ልዕልና እና ተቀባይነት

---

በላቸው::» ሲል ጸልዮአል:: ሉቃ.23፥34፤ ማቴ.18፥21-22፤ ያዕ.2፥1-13፤ ሉቃ.6፥36፤ ሮሜ.12፥19:: ማንን፣ ምንን ይቅር እንበል? ስንት ጊዜ፣ መቼ ይቅር እንባባል? የይቅርታ ጠላቶች እነማን ናቸው? ይቅር አለማለትና ችግሮቹ ምንድን ናቸው? ትርፎቹስ? ለእነዚህ ጥያቄዎች ኃይለ ሚካኤል ዘማርያም ምላሽ ይሰጠናል::

እንደ ዕርቅ ሁሉ ምሕረትም ሥጋዊና መንፈሳዊ ገጽታ አለው:: ***ምሕረት ሥጋዊ:-*** ለደካሞች፣ ለሕሙማን፣ ለድኾች ቸርነትና ርዳታ ማድረግ፣ ቀዶ ማልበስ ቆርሶ ማጉረስ ነው:: በተጨማሪም ምሕረት ሥጋዊ ቢበድሉ ማፍኘታ መጠየቅና ቢበደሉ ይቅርታ ማድረግ ነው:: ***ምሕረት መንፈሳዊ:-*** ክፉውን ምግባር በምክርና በትምህርት አስትቶ በጎውን ምግባር ማሠራት ነው:: ምሕረት ሥጋዊም ምሕረት መንፈሳዊም የብፅዕና ተግባራት ናቸው:: «የሚራሩ ብፁዓን ናቸው፣ ለእነርሱም ይራሩላቸዋልና» ተብሎ ተጽፎአል:: ማቴ.5፥7::

ሰው በኃጢአቱ ከራሱና ከእግዚአብሔር ጋር ቢጣላ በንስሐ ይታረቃል፣ ጸሎቱ ተሰሚ መሥዋዕቱ ግዳጅ ፈጻሚ ይሆናል:: በማንኛውም ምክንያት ሰው ከባልንጀራው ጋራ ቢጣላ በዕርቅና ይቅር ባይነት ስሜት ከቂምና በቀል ልቡናውን በማጽዳት የግሉንና የኅብረተሰቡን ሰላም ይመልሳል:: ይህን ሁሉ ማተታችን በሰዎች መካከል ልዩነት ከቶ አይኖርም ማለታችን አይደለም:: ፈረንሳዮች «*ልዩነትን ያኑርልን!*» ይላሉ:: እንደ ሚነገረው ልዩነት የሕያውነት ምልክት እንጂ በራሱ መጥፎ ነገር ላይኾን ይችላል:: ይህ ይሆን ዘንድ ግን ልዩነታችን በመንፈሳዊ ብስለት፣ መቻቻልና መተማመን አጥር ውስጥ መጠበቅ ይኖርበታል:: ያን ጊዜ በልዩነታችን ላይ የምንፈጥረው መስማማት ኅብረታችንን ያጠናክራል፤ ዕድገታችንን ያፋጥናል፤ እርስ በርሳችን ለመተራረም፣ የጎደለንን ለመሙላት፣ የተጣመመውን ለማቃናትና የተሻለውን ለመከተል ዕድል ይሰጠናል:: በጥላቻ ላይ ኅብረት አይመሠረትም:: ዕርቅን ረግጦ ሰላምን መሻት አያዋጣም:: ምልጃን ንቆ መታመንን ማግኘት ያዳግታል:: በጥላቻና ጥርጣሬ ደግሞ አገርን መገንባት አይቻልም:: ሀገራችን ከምትገኝበት መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እውነታና በተለይም ከያዝነው ዐቢይ ጾም አንጻር ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ በጥሞና ልናጤነው ያስፈልጋል::

ይህ የያዝነው ዐቢይ ጾም ***«ጾመ አስተምህሮ»*** ይባላል:: ሁሉን ነገር በቅጽበት ያለ ድካም ማድረግ የሚችለው አምላካችን እንደ መልካም መምህር ራሱን ዝቅ አድርጎ ፈተናን በትሕትና እና በትዕግሥት ማሸነፍ እንደ ሚቻል በጾሙ አስተምሮናል:: አዳምንና ሔዋንን በገነት በመብል የረታቸውን ዲያብሎስን በገዳም በጾሙ ድል አድርጎ ለእኛም ፈቃደ ሥጋችንን /ጥልን፣ ምቀኝነትን፣ ቁጣን፣ መግደልን.../ የምናሸንፍበትን ፍቅርን፣ ሰላምን፣ ትዕግሥትን፣ በጎነትንና ራስን መግዛትን ገንዘብ የምናደርግበትን ኀይል ሰጥቶናልና ***«የድል ጾም»*** ይባላል:: የማስተማር ሥራውን ከመጀመሩ በፊት 40 መዓልት 40 ሌሊት እንደ ጾመ ለእኛም የደገኛ ሥራ መጀመሪያው ጾም መኾኑን አስተምሮናልና ዐቢይ ጾም ***«የሥራ መጀመሪያ ጾም»*** ይባላል:: ጾማችን ዋጋን ያስገኝልን ዘንድ በዚህ መንፈስ ትክክለኛውን መንገድ እናስይዘው:: የዘወትር ተሳታፊያችን ኃይለ ገብርኤል ዘሐና:- የነነዌ ሰዎች ለሦስት ቀናት ብቻ ባደረጉት ጾም ራሳቸውን፣ ያላቸውን ንብረትና አገራቸውን ከጥፋት ሲታደጉ እኛ በዓመት ውስጥ በትንሹ ለ215 ቀናት ያህል እየጾምን፣ ለ360 ቀናት ያህል እየቀደስን፣ ሰዓታትና ማሕሌት እየቆምን፣ በሥጋዊው አስተዳደር በኩልም ለሰላምና ልማት ብዙ ጥረት እየተደረገ የነነዌ ሰዎችን ዐይነት ሰላምና ደኅንነት ሊመጣልን ያልቻለው ለምንድን ነው? ሲል ይጠይቃል:: ሰላም ሳይሆን «ሰላም ነው» በማለት ራሳችንንና ሕዝቡን እንዳናታልል፣ የግልና የጋራ ጥፋታችንን ባለማመን፣ እርስ በርስ በመካሰስና ተስፋ በመቁረጥ ራሳችንን ከንስሐ እንዳናዘገይ ያሳስባል:: በመጨረሻም «ከነነዌ ሰዎች በመማር ጊዜ ገዳይ ንትርኮችን አቁመን ***እንደ ሕዝብ ንስሐ እንግባ***» በማለት ይመክራል::

እንግዲህ ይህች እትማችን የጥላቻንና አጉል ጥርጣሬን ብሉይ አስተሳሰብ አውልቶን ጥለን መግባባትንና መተማመንን እናጠናክር፤ ከኀይልና ከማስፈራራት አባዜ ተላቀን በሚዛናዊ አስተያየት፣ በሥርዐትና በጨዋነት እኛው በእኛው ተነጋግረን ችግራችንን እንፍታ፤ በየጊዜው ከምንዳክርበት የመከራ አዙሪትና አዘቅት ወጥተን የጋራ ቤታችንን በአንድነት እንገንባ፤ የምሕረት አቅማችንን እናሳይ፤ ዕርቅንና ሰላምን እናስፍን:: ለዚህም ሁላችንም የኀሊና ትንሣኤ እንነሣ፤ ለየራሳችን ሐላፊነቱን ወስደን ውስጣዊ ድክመታችንን በትክክለኛ ገጽታው ለመመልከት የሚያበቃ መንፈሳዊ ወኔ ይኑረን፤ ለራሳችን መመኪያ የሚኾንና ለትውልድ የሚያልፍ እንደ ኾን:- «ሥራችንን እንመርምር፤ በመንፈስ እንኑር፤ በመንፈስ የሚሠራውንም እንሥራ» /ገላ.5፥25/ ትላለች:: በዚህ መሠረተ ሐሳብ ላይ የሚያተኩረውን ዝግጅቷንም ይዛ ቀርባለች:: መልካም ንባብ::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሚያገኙት በመንፈሳዊነታቸው ብቻ ሳይሆን ተቋማቱ፣ መሪዎቻቸውና ተከታዮቻቸው ከራሳቸው አልፈው ለሌላው ኅብረተሰብም የሚጠቅሙ ተግባራትን ሲፈጽሙም ጭምር ነው። እነዚህ አካሎች ይህን ልዕልና ከሚቀዳጁባቸው ሁኔታዎች አንዱ ደግሞ ውሱን በሆነ ፖለቲካዊ ተሳትፎ /Limited political participation/ መርሕ መጽናት ሲችሉና በዚህ ተሳትፎዋቸውም ተከታዮቻቸውንና መላውን ኅብረተሰብ በተጨባጭ ሊጠቅም የሚችል ሥራ ሲያከናውኑ ነው። ለዚህም አንዱ ማሳያ ተቋማቱ፣ መንግሥትና ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ተቋማት የሚያወጧቸው ፖሊሲዎችና የሚወስዷቸው እርምጃዎች የኅብረተሰቡን ሰላማዊና ጤናማ አኗኗር የማያናጋ፣ ጠቃሚ ባህሉንና ልማዱን የማይጥስ፣ ያለበትን ችግር የማያባብስ ወዘተ መሆኑን መከታተልና አስፈላጊ ሲሆን ድምፃቸውን ማሰማታቸው ነው። ሁኔታው ጠቃሚ ሲኾን ደግሞ እገዛ ቢያደርጉና ቢያበረታቱ መልካም ነው። የእምነት ተቋማት ፖለቲካዊ ተሳትፎ በዋናነት ከመንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮዋቸው የሚመነጭ መሆኑን ማረጋገጥ ግን በጣም አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ ተቋማቱ የግለሰቦች የፖለቲካ አቋም ማስፈጸሚያ ከመሆን አያመልጡም። ከበጎ ጎኑ በመነሣት አንድ የቅርብ ምሳሌ ብጠቅስ ነገሩን የበለጠ የሚያስረዳልኝ ይመስለኛል።

*ታሪኩ በአጭሩ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የግሪክ ፓርላማ አንድ ሕግ ለማጽደቅ ዕቅድ ይዞ ነበር። ዕቅዱ በአገሪቱ በተለይም በከተሞች ያጋጠመውን የመቃብር ቦታ ጥበት ለማቃለልና በዚሁ ምክንያት ለሦስት ዓመት የመቃብር ቦታ በሊዝ /በኪራይ/ ለማግኘት የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለማስቀረት ይረዳል የተባለ የሕግ ረቂቅ ነው። የረቂቅ ሕጉ ማእከላዊ ጭብጥ የሙታንን በድን /አስከሬን/ ማቃጠልን ሕጋዊ ማድረግ ነው። ይህን ድርጊት በሕግ መልኩ ማውጣት ያስፈለገው ያለምክንያት አይደለም። ምክንያቱም ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በእርሷ በኩል በአገሪቱ ተጠብቆ በቆየው ክርስቲያናዊ ባህል የተነሣ ነው። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡ - «በትምህርታችንና በባህላችን አስከሬን ማቃጠል የተከለከለ ስለሆነ ይህን ሕጋዊ የሚያደርግ ሕግ ጸድቆ ሊወጣ አይገባም» በማለቷ በረቂቁ ላይ ውይይት ሲካሔድ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል። የግሪክ ዜጎች ከ95 በመቶ የማያንሱት የቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታዮች በመሆናቸውና በታሪካዊ ምክንያቶች የተነሣ የአገሪቱ መንግሥትና ፓርላማ የቤተ ክርስቲያኒቱን ይሁንታ ሳያገኝ ሕጉን ማውጣት የሚፈለገውን ውጤት እንደ ማያመጣ ያውቁ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታዮች ያልሆኑ ሰዎች እንኳ ድርጊቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ በይፋ የሙታንን አስከሬን ማቃጠል ቢፈልጉም አይችሉም ነበር። በመጨረሻም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር በተደረገ ሰፊ ውይይት «ቢያንስ የግሪክ ኦርቶዶክስ ምእመናን ያልሆኑ ሰዎች እንዲጠቀሙበት እናድርግ» ከሚል ስምምነት በመደረሱ ሕጉ ባለፈው ዓመት መጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ሊጸድቅ ችሏል።*

ይህን ምሳሌ ያነሣሁት የእምነት ተቋማት ከማኅበራዊና መንፈሳዊ ተልእኳቸው በመነሣት በተወሰነ መልኩ በፖለቲካዊ ሂደት የሚሳተፉበት ሁኔታ ሊኖር እንደ ሚገባ ለማሳየት ነው። ከዚህ በተቃራኒው ግን የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ ፖሊሲ በሚከተሉባቸው ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የእምነት ተቋማት በምንም መልኩ አቋም ባይዙ ይመረጣል። ምክንያቱም ከተከታዮቻቸው መካከል ፖሊሲውን የሚደግፉም የሚቃወሙም ስለሚኖሩና ይህም የውስጥ መከፋፈልን ሊያስከትልባቸው ስለ ሚችል ነው።

ሰማዕቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የፋሺስት ኢጣልያን ወረራና በንጹሐን ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመውን ጭፍጨፋ በመቃወም የያዙት አቋም በባሕርይው ፖለቲካዊ አቋም መሆኑ ባይካድም መነሻው ግን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኳቸው እንደ ነበረ ግልጽ ነው። እንዲያውም በወቅቱ ይህን አቋም ባያንጸባርቁ ኖሮ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ልዕልናቸው ዛሬ የምንመሰክርላቸውን ያህል ባልሆነ ነበር ብሎ መከራከር ይቻላል።

ብፁዕነታቸው በመንፈሳዊ ተልእኳቸው ፣ በሮም ካቶሊክ ፖፕ ቡራኬ ኢትዮጵያን ወርሮ መነኮሳትን፣ ሊቃውንትን ካህናትንና ምእመናንን እያረደ፣ አብያተ ክርስቲያናትን እያቃጠለ፣ ቅርሶችንና ቅርስ ንዋያተ ቅድሳትን እየዘረፈ የነበረውን የፋሽስት ኢጣልያ ሠራዊት አውግዘዋል። በማኅበራዊ ተልእኳቸው ደግሞ የግፍ አገዛዝን፣ ወረራን፣ ግድያን፣ ጭቆናንና ኢሰብአዊነትን በመቃወም ለአገር ሉዐላዊነት፣ ለነጻነት፣ ለፍትሕና ለእኩልነት ቆመዋል። በፋሽስቶቹ ፊት መሥዋዕት ሊኾኑ ቀርበው የተናገሩት የሚከተለውን ነበር፡- «ፋሽስቶች የአገራችንን አርበኞች ሽፍታ ቢሏቸው እውነት አይምሰላችሁ። ሽፍታስ ማለት ያለ አገሩ መጥቶ የሰውን ርስትና ክብት የሚቀማ፣ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያቃጥል፣ የክርስቲያንን ደም የሚያፈስ ይህ በመካከላችሁ የቆመው አረመኔው የኢጣልያ ፋሽስት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በርሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው!! የኢትዮጵያ መሬትም እንዳትቀበለው የተገዘተች ትሁን!!» ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በዚህ ጽናታቸው የኢጣልያን «ክርስቲያን ነኝ» ባይነትና ሥልጡንነት ፈተና ውስጥ ከተቱት። ለሃይማኖታቸው ያላቸውን ቅንዐት፣ መሥዋዕትነት ለተፈጸመበትና ለጨበጡት መስቀል ያላቸውን ስሜት፣ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ያላቸውን ታማኝነት አረጋገጡ። በፋሽስት መትረየስ ተደበደቡ። ዛሬ በዚህ ድርጊት ኢትዮጵያ ትኮራለች፣ ኢጣልያ ታፍራለች። ማርቲን ሉተር ኪንግ /ጁኒየር/ በአሜሪካ ጥቁሮች ላይ ይደርስ የነበረውን የዘር መድልዎ በመቃወም እስከ መታሰር የደረሰበትን የታሪክ አጋጣሚም ማስታወስ ይቻላል። ማርቲን ሉተር ኪንግ በዚህ እርምጃ ከሌሎች የእምነት ተቋሙ አገልጋዮች ተቃውሞ ቢቀርብበትም «ለሰው ልጆች እኩልነት መታገል መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግዴታዬ ነው» በማለት ባካሔደው ሰላማዊ ተጋድሎ ታሪክ የመንፈስ ልዕልናውን በክብር ያስታውሰዋል። */ማስታወሻ፡- ማርቲን ሉተር ኪንግ ለከሰሱት ካህናት ባልንጀሮቹ ከበርሚንግሐም እስር ቤት የጻፈላቸውን አስገራሚ ደብዳቤ ማንበብ የበለጠ ሐሳብ ይሰጣል። www.nobleprizes.com/noble/peace/MLK-jail.html/.*

## *የክርስትና ትምህርትን በማይቃረኑ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍና ልማታዊ አስተሳሰብን በመቅረጽ*

የእምነት ተቋማት በኢኮኖሚያዊ ዘርፍ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በሁለት መልኩ ለያይቶ ማየት ይቻላል። በአንድ በኩል የእምነት ተቋማት በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በቀጥታ የሚያደርጉት ተሳትፎ አለ። ተቋማቱ ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው አንድ አካል መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ የእምነት ተቋማት በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚሳተፉት መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎታቸውን ለማስፋፋት የሚያስችል ገቢ ለማግኘት ነው። በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች መሬታቸውንና ጥሪታቸውን እየሸጡ ገቢውን ወደ ማኅበሩ አምጥተው በአንድነት አገልግሎታቸውን ያስፋፉ እንደ ነበር ይታወቃል። የሐዋ.ሥራ 2፥45። ይሁን እንጂ ተቋማቱ ኅብረተሰቡን ከድህነትና ኋላ ቀርነት አረንቋ ለማውጣትና የአገርን ልማታዊ እንቅስቃሴ ከመደገፍም አኳያ የማይናቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል። በዚህ በኩል የካቶሊክ እምነት በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። ይሁንና ከክርስትና ትምህርት ጋር በሚቃረኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሳይቀር ትሳተፋለች እየተባለች ትወቀሳለች። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኩል በተለይ ከቅርብ ዘመናት ወዲህ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርትና ትውፊት ጋር በማይቃረኑና እግረ መንገዳቸውንም ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ አገልግሎት በሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ጠንካራ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ይህም ት/ቤቶችን፣ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን፣ የመኖሪያና የንግድ ሕንጻዎችን መገንባትንና ማከራየትን፣... ወዘተ ያጠቃልላል።

ሁለተኛው የእምነት ተቋማት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ተደርጎ የሚታየው ተቋማቱ ከኢኮኖሚ ልማት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡትን ትምህርትና የሚፈጥሩትን አስተሳሰብ የተመለከተ ነው። ይኼ ርእስ ጉዳይ በራሱ ሰፊ ማብራሪያን የሚጠይቅ በመሆኑ በዝርዝር የምንገባበት አይሆንም። ዋናው ጥያቄ ግን ሃይማኖቱ ሰዎች በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚኖራቸውን ተሳትፎ እንዴት ይመለከተዋል በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

## *ግንባር ቀደም የይቅርታና ዕርቅ መልእክተኛ የመኾን ማኅበራዊ ሚና*

ሦስተኛውና ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታችን ጋር በጣም አስፈላጊ ነው የምለው የእምነት ተቋማት ማኅበራዊ ሚና ነው። በጥቅሉ «ማኅበራዊ» የምንለው የእምነት ተቋማት ሚና ከባህል፣ ከኅብረተሰብ ሰላምና የተሻለ አኗኗር፣ ችግረኞችን ከመርዳትና ከመሳሰሉት ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ በኩል ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ ታሪካዊና ትልቅ ማኅበራዊ ተቋምነቷ የሚጠበቅባት መሠረታዊ ሚና የማስታረቅ፣ የማቀራረብና የማስማማት ድርሻዋ ነው። በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያናችን በምልጃዋ ዕርቅን፣ በዕርቁም ደግሞ ፍቅርንና ሰላምን ማስፈንዋ በክበረ ደሙ በመሠረታት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣት የባለሟልነት መብትዋ ነው። 2ቆሮ.5፥20።

የኢትዮጵያን ታሪክ በሚገባ የተረዳና ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ በቅርበት የሚከታተል ማንኛውም ሰው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚችለውን ቁልፍ የማረጋጋት፣ የማስታረቅ አገልግሎትዋን አስፈላጊነት በግልጽ ለማስተዋል ይችላል። ይህን እውነታም የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ያልሆኑ ዜጎች ሳይቀሩ የሚቀበሉት መሆኑ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚህ በኩል የምታደርገው ጥረት ከመንፈሳዊ ተልእኮዋ ብቻ ሳይሆን ከማኅበራዊና አገራዊ ሓላፊነቷም የሚመነጭ መሆኑን ያለጥርጥር የሚያስረዳ ይመስለኛል። በሥራ አጋጣሚ በልዩ ልዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተዘዋወርኩባቸው ትርብቀናት የተለያዩ እምነቶችን ከሚከተሉ በርካታ ሰዎች ጋር የመገናኘት ዕድል ነበረኝ። ከሁሉም ጋር በምናደርገው ውይይት በመጨረሻ የምንደርስበት አንድ መደምደሚያ ቢኖር የአገራችን የእምነት ተቋማትና መሪዎች ያለንበትን ሁኔታ ለማረጋጋትና ልዩነቱን ሁሉንም በሚጠቅም ሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ቁልፍ ሚና መጫወት የመቻላቸው እውነታ ነው። የእምነት ተቋማቱን በዚህ መንገድ የመምራት ግንባር ቀደም ሓላፊነት ደግሞ እንደ ብዙዎች ተስፋ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የወደቀ ነው።



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ይህ የብዙ ኢትዮጵያዊው ወገኔ አመለካከት ነው ብዬ አምናለሁ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ቀደም ሲል በታሪክ የነበራትን ቦታ እና በየደረጃው የሚገኙ አገልጋዮቿ አለመግባባቶችን በሰላምና በመስማማት ለመፍታት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያደረጉትን ወሳኝ እንቅስቃሴ ያስተዋለ ተመልካች ዛሬ ብዙ ቢጠብቅ የሚገርም አይኾንም። ከ1769-1855 እ.አ.አ በአገራችን የቆየውና እርስ በርስ የተላለቅንበት ዘመነ መሳፍንት ሊከሠት ከቻለባቸው ምክንያቶች አንዱ ጠበኞች የሚታረቁባት፣ የበደለ የሚገሠጽባት፣ የተበደለ የሚካሥባት፣ የሸሸ የሚማጥንባት፣ ምሕረትንና ፍትሕን የሚያገኙባት ታላቅ አገናኝ ተቋም /Cohesive Institution/ የኾነችው ቤተ ክርስቲያን በውስጥ መከፋፈልና በውጭ ተጽዕኖ በደረሰባት ጉዳት በመዳከሟ ነበር። በተለይም ደግሞ ለፖለቲካዊ ክፍፍሉ ርእዮተ ዓለማዊ መሠረት በመስጠት ይበልጥ ያከረረው በጸጋ እና ቅባት ተከታዮች የተፈጠረው ደም ያፈሰሰ ውዝግብ ነው። በዓለማችን ታሪክ በእምነት ተቋማት ልዩነት የተነሣ የተጫሩ ግጭቶች መኖራቸው ባይካድም በተቃራኒው በተቋማቱ ጥረት የረገቡ፣ በሰላም የተቋጩ ግጭቶች ብዛት ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። አበው ካህናት በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን፣ በተጎራባች የኅብረተሰብ አካላት እንዲሁም በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል የሚያጋጥሙ ግጭቶችን በመስማማት፣ በዕርቅና በይቅርታ እንዲፈታ በማድረግ የማይተካ ሚና እንደ ነበራቸው የታወቀ ነው። ቤተ ክርስቲያን በሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ዘንድ ከፍተኛ የመንፈስ ልዕልናን የተቀዳጀችበት አንዱ ምክንያትም ይኼው የማስማማት፣ የማስታረቅ፣ አንተም ተው፥ አንተም ተው፥ ሁላችሁም ተዉ፥ የማለት ሚዛናዊ ድፍረትዋ፣ የተጐዳው እንዲካስ፣ ያጠፋው እንዲታረም፣ አልፎም ዘላቂ መስማማት እንዲመጣ ለማድረግ ያሳየችው ቁርጠኝነትዋ ነው።

ታሪኩ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ ባይሆንም በደቡብ አፍሪካ የተፈጸመውን የይቅርታ ታሪክ ማስታወሱ የእምነት ተቋማትንና መሪዎቻቸውን የማስታረቅ ኀይል የሚያሳይ ነው። የደቡብ አፍሪካን የእውነትና የዕርቅ ኮሚሽን የመሩት ዴዝሞን ቱቱ አፓርታይድን በመደገፍ እና በመቃወም የሚታወቁ የእምነት ተቋማትና መሪዎቻቸው የአገሪቱ ሽግግር ወቅት እንደ ተጀመረ /እ.አ.አ በ1990/ ተሰባስበው በቅድሚያ እነርሱ ይቅር መባባላቸውን ያስታውሳሉ። «አፓርታይድን ደግፈው ሲሰብኩ የኖሩት የእምነት መሪዎች ይቅርታ ለመጠየቅ ሲመጡ ሌሎቻችን እንዴት ይቅርታን ልንነፍጋቸው እንችላለን» በማለትም ይጠይቃሉ። ዴዝሞን ቱቱ እንደ ሚሉት በዚያ ታሪካዊ ስብሰባ የእምነት መሪዎቹ ይቅር ተባብለው ታላቁን የይቅርታና የዕርቅ መልእክት በተግባር ማስተላለፍ ባይችሉ ኖሮ የአገሪቱ የፖለቲካ መሪዎችም በተለያየ አቅጣጫ ለመጓዝ ሰበብ /ማመካኛ/ ባገኙ ነበር። ቱቱ የደቡብ አፍሪካን የዕርቅ ጉዞ አስመልክተው በጻፉት መጽሐፋቸው «ዕርቅን የማያውቅ ኅብረተሰብ ተስፋ የለውም» ይላሉ። የይቅርታና የዕርቁ እርሾዎችም የእምነት መሪዎች መሆን እንዳለባቸው በስፋት ያብራራሉ። ዋናው መነሻችን የራሳችን

/ወደ ገጽ ፳፯ ዞሯል/

# ከመተናነቅ ወደ መተራረቅ - በፈረስ ሜዳ

**«ከጥፋት ወደ ፈጣሪ መመለሻው መንገድ በጣም አጭር፥ በጣም ቅርብ ነው፤ እሱም መጸጸት ነው።»**

*«...የታቦታቱ ጉዞ የሚወስደውን ጊዜ ከወሰደ በኋላ ታቦቱና አጃቢው በጣም ቀረቡ። ድባዎችና ጃንጥላዎች በዬቀለማቸው፥ ልብሰ ተክህኖ የለበሱት ካልለበሱት ተለይተው ለሽማግሌዎች ዐይን ሳይቀር መታየት፣ የከበሮው ድምፅ መሰማት ጀመረ።*

*ታቦቱ በፊታውራሪ አስጌ ሰፈር አቅጣጫ ሲደርስ ሰፈሩን ወደ ቀኝ ትቶ ቀጥታ ወደ ደቡብ የሚሄድ ከመሰለ በሁዋላ እንደገና መለስ ብሎ ወደ ፊታውራሪ መሸሻ ሰፈር አመራ።*

*«ወዲህ መምጣቱ ነው እንዴ?» አሉ ልጅ እጅጉ። ቀኛዝማች አካሉ ትንሽ እንደ መጣት ብለው ሚቆቻቸው እንዳይታይባቸው ኩታቸውን ወደፍንጫቸው ገፋ አደረጉ። ፊታውራሪ መሸሻ እስከዚያ ድረስ ሁሉ ጉዳያቸውንጂ ስለ ታቦቱ ሰው የሚተችውን በሙሉ አይከታተሉም ነበር። ታቦቱን ያጀበው ሕዝብ፦ «እግዚእ መሐረነ ክርስቶስ፥ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ፥ ሰአሊ ለነ ማርያም ምሕረተ ወልድኪ የሐውጸነ» እያለ በዜማ ምሕረት እዬለመነ ይጉዋዝ ነበር።*

*«ሁለት ታቦት!» አለ ከወታደሮቹ አንዱ እንደ ገና።*

*«አንዱ የዲማ ጊዮርጊስ ነው!» አሉ ባላምባራስ ምትኩ ደንግጠው። የዲማ ጊዮርጊስ ስም ሲጠራ ፊታውራሪም በጣም ደነገጡ። ያንጊዜ ብቻ አሳባቸው በፊታቸው የተዘበበውን ጦርነት ማሰላሰል ለቀቅ አድርጎ ወደ ዲማ ጊዮርጊስ መለስ አለና እንደ መሸበር ብለው «አምጣ ጠመንጃየን!» አሉ ፊታውራሪ። ጠመንጃቸውን ተቀብለው በትከሻቸው ሲይዙ መኳዋንንቱ ሁሉ ጠመንጃውን ከዬጋሻጃግሬው እዬተቀበለ ይዞ እንጻውሬ አጥማጅ ቀስ ብለው ወደ ፊታውራሪ ሰፈር የሚያዘግሙትን ሁለት ታቦቶች ይጠብቅ ጀመረ።*

*የዲማ ጊዮርጊስ፣ ገጻም በመሆኑ ድንግላዊ መነኩሴ ተሸክመውት የቢቸና ጊዮርጊስ ደብር፣ በመሆኑ ቄስ ተሸክመውት የዲማ መምህር በዲማ ጊዮርጊስ ግራ የቢቸና አለቃ በቢቸና ጊዮርጊስ ግራ ሆነው የሁለቱን ታቦቶች ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት በዬታቦታቸው ፊት ተሰልፈው የዲማ ገዳምና የቢቸና ደብር ካህናት ብቻ ሳይሆኑ ባካቢው ያሉ ገጠሮች ካህናትና ለበዓሉ የተሰበሰበው ቤተ ክርስቲያን ሳሚ ሁሉ በሁዋላ ተከትሎ ፈረስ ሜዳ ጠቦት ሁሉም አንድ ላይ «እግዚኦ» እያለ መጥቶ እፊታውራሪ መሸሻ ፊት ሲደርስ ቆመ። ከዚያ የፊታውራሪ አስጌ ሰራዊት በሁዋላ ተከትሎ መጣ። ወዲያው የዲማ ጊዮርጊስ መምህር አለቃ ጥዑመ ልሳን ነጠል ብለው ሁለት ሦስት እርምጃ ወደ ፊት ተራምደው ቆመው፦*

*«ይምሐረነ ወይሠሃለነ ይቀበነ ወይትመሐፀነነ እግዚአብሔር፥ ለበደለ ምሕረቱን ሊታመመ መድኀኒቱን ይስጥልን እግዚአብሔር። ወንድማችን ፊታውራሪ መሸሻ፦ - ዛሬ ጊዮርጊስ ከሩቅም ከቅርብም በደጁ የሚሰበሰቡትን ምእመናን በሚቀበልበትና የምእመናኑን ልመና ይዞ ወደ ፈጣሪ ፊት በሚቀርብበት የዓመት በዓሉ እርስዎን በደለኛውን እርስዎን እንዳባትዎ እንዳዳም የፈጣሪን ሥልጣን ለመካፈል ታጥቀው የተነሡትን ጥፋተኛ ተከትሎ ፈረስ ሜዳ ድረስ መምጣቱ ይገርምዎ ይሆናል። አዎ! እንደስዎ የክርስቲያንነትን ስም እንጂ ግብር ለማያውቁ ሁሉ፣ እንደስዎ የቅዱሳንን ባሕርይ ለማያውቁ ሁሉ ቢገርማቸው አያስገርምም። እግዚአብሔር በጣም የሚወደው ከፍጥረት ሁሉ አልቆ ባሪያው የፈጠረው አዳም የፈጣሪውን ሥልጣን በመመኘቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ሲኦል ቢወርድ እንደሱ እንደ በደለኛው ሞቶ ያዳምን ነፍስ ፍሊጋ ሲኦል ድረስ ወረደ። እንዲሁም ዛሬ እስዎ በፈጣሪ ሥልጣን ገብተው እሱ በረቂቅ ምሥጢሩ ሰማያዊት ነፍስን ከምድራዊት ሥጋ አንድ ላይ አዋሕዶ የፈጠረውን ፍጡር ለማጥፋት ታጥቀው ስለተነሡ በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይ ጭምር ሞተው እንዳይቀሩ ከዘላለማዊ ጥፋት ሊያድንዎ የሚወድዎ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፍሊጋዎን ተከትሎ መጥቶ እነሆ እፊትዎ ቆሞዋል። ምንም በደልዎ ኀያል ቢሆን፣ ይቅር ብለው ይቅርታ የለመኑ እንደ ሆነ፦ መሐሪ ነውና ይምርዎታል።» ብለው ወደነበሩበት ተመለሱ። ከዚያ የቢቸናው አለቃ ንዋይ እንዲሁ ሁለት ሦስት እርምጃ ቀደም ብለው ቆመው፦*

*«ጌታዬ ፊታውራሪ መሸሻ፣ ምንም እንኳዕዋ ወንድሜ መምህር ጥዑመ ልሳን ከተናገሩት ሌላ የምጨምረው ባይኖርና በላቸው ላይ መናገር ባይገባኝ በቢቸናው ጊዮርጊስ ስም ጥቂት ቃላት መናገር ስላለብኝ ከመጎሳደል እላቸው ያሉትን እደግመዋለሁ።*

*የርስዎንም ሆነ የሌላውን ነፍስ ከሥጋ አዋሕዶ የሥራ ፈጣሪ ስለ ሆነ የሥራውን ማፍረስም የሱ ሥልጣን ብቻ መሆኑን ምንም ዛሬ አዳምን ያሳተ ሰይጣን ዐይን ኅሊናዎን ቢሰውረው ከስዎ የተሻለ የሚያውቅ አለመኖሩን እናውቃለን። የስዎን የራስዎን ነፍስ እንኳዋ የኔ ናት ብለው ከሥጋዎ ለመለዬት ቢሹ በፈጣሪ ፊት ትልቅ በደለኛ ሆነው ይገኛሉ። ነፍስ ከእግዚአብሔር በቀር የማንም አይደለችም፤ የነፍስዎ ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ ዛሬ ታጥቀው የመጡለት ሥራ በፈጣሪ ፊት ከበደል ሁሉ የበለጠ በደል ነው። ብቻ እግዚአብሔር በቸርነቱ ተሳስተው በጥፋት መንገድ የሚሔዱትን አይተዋቸውም፤ ይከተላቸዋል፤ መመለሻ መንገድም ሠርቶላቸዋል። ይህ ከጥፋት ወደ ፈጣሪ መመለሻው መንገድ በጣም አጭር በጣም ቅርብ ነው፤ እሱም መጸጸት ነው። ስለዚህ ምንም በደልዎ ታላቅ ቢሆን ከተጸጸቱና ምሕረት ከለመኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመሐሪው ከእግዚአብሔር እንደሚያስምርዎ አይጠራጠርም። ዐይነ ኅሊናዎ ልቡናዎ በሀመፅ ተሸፍኖ እንጂ ብለው ወደ ጥፋትዎ እስኪሄዱ ድረስ ቅዱስ ጊዮርጊስ እዬተከተለ ወደ ፈጣሪዎ መመለሻውን መንገድ የመለከትዎታል።*

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ሲያስተምር፦ «ብዙ የበግ መንጋ ያለው ሰው ቢኖርና ከመንጋው መካከል አንድ በግ ቢጠፋው ብዙ መንጋውን ትቶ የጠፋውን አንድ በግ ፍሊጋ ይሔድ የለምን?» እንዳለው ሁሉ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ በብዙ ምእመናን ፈቃዳቸውን ለፈቃዱ ያስገዙ አማኞቹ በሩን ዘግቶ፣ ቅዳሴውንም አሲታጉሎ እስዎን ከምእመናን መካከል ተለይተው የጠፉትን አንዱን ፍሊጋ በዱር በገደል ተጉዞ እዚህ ድረስ መጣ። በመንበሩ ተቀምጦ ከሩቅ እዬመጡ የሚለምኑት ሊቀ ሰማዕታት ጊዮርጊስ እስዎን በደለኛውን ተከትሎ እስዎ ጠፍተው እንዳይቀሩ ሲለምንዎ ይቅርታ ያስጥዎ ዘንድ እስዎ አስቀድመው ይቅር እንዲሉ እነሆ በፊትዎ ቆሞ ይለምንዎታል!» ብለው ወደነበሩበት ተመለሱ።*

*ፊታውራሪ መሸሻ የዲማና የቢቸና ጊዮርጊስ ታቦቶች እፊታቸው በሙሉ ግርማ ቆመው ሁለቱ ሊቃውንት በደላቸው ከበደል ሁሉ በላይ መሆኑን በዬተራ እዬተቀባበሉ ሲገልጹላቸው፥ ያንለት ለመፈጸም ታጥቀው የመጡለት በደል በአዳም እስከ ዘራዝርእቱ ሞት ከአፈረደበት በደል የሚመዛዘን መሆኑን ከሊቃውንቱ አፍ ሲሰሙ በደላቸው ክርስቶስን ከመልዕልተ ሰማያት መንበረ ጸባኦቱ አስወርዶ በፍጡሮቹ እጅ መከራ እንዲቀበልና እንዲሞት ካደረገው ከታላቁ በደል የማያንስ መሆኑን ሲሰሙ ያንለት ሊፈጽሙት የፈለጉት ዐመፅ የክርስቶስ ሞት ብቻ የማይሽረው ሆኖ ሲኦል እንዲወርድ ካደረገው ካመፆች ዐመፅ የሚወዳደር መሆኑን ሁለቱ ሊቃውንት በምሁር አንደበት እዬተቀባበሉ ሲነግሩዋቸው ይህን ሁሉ በጊዮርጊስ ፊት ቆመው ሲሰሙ እግዚአብሔር በዕለተ ምጽአት በግርማ መለኮቱ ወርዶ በኀጥአን ስለሚፈርደው ፍርድ አባ ሞገሴ ሲሰብኩዋቸው የኖሩት ያንለት ልክ በላቸው የተፈጸመ መስሎዋቸው ይንቀጠቀጡ ነበር።*

*አለቃ ንዋይ ንግግራቸውን ጨርሰው ወደ ነበሩበት እንደ ተመለሱ ፊታውራሪ መሸሻ ጠመንጃቸውን ጥለው መጀመሪያ የዲማውን ጊዮርጊስ በተሸከሙት መነኩሴ እግር ወድቀው «ማረኝ ጌታዬ፣ አባዋቂ ባሪያህን ደንቆሮ ባሪያህን ማር፣ በዱር በገደል ስላንከራተትሁህ ማረኝ።» እያሉ ሲያማትሩ ቆዩና ከዚያ ተነሥተው እንደገና የቢቸናውን ጊዮርጊስ በተሸከሙት ቄስ እግር ወድቀው ያኑ ለዲማ ጊዮርጊስ ያቀረቡትን ልመና እዬመላለሱ ሲደግሙ ቆይተው ፊታቸውን ደረቅ መሬትና ደረቅ ግር በጫጭሮት ሲነሡ ፊታውራሪ አስጌ ጠመንጃቸውን በትከሻቸው ተሸክመው እግራቸው ላይ ሲወድቁ አዩ።*

*«ተቀበለው! ተቀበለው! ጠመንጃውን ተቀበለው!» አሉና ፊታውራሪ መሸሻ ዘቅ ብለው ፊታውራሪ አስጌን ከወደቁበት አንሥተው ሳሙዋቸው። «ይማሩኝ አባቴ ጌታዬ፣ በድፍረት ሳይሆን ባለውቀት በድንቁርና በደቈዎታለሁና ይማሩኝ ከልብዎ ይማሩኝ!» አሉ ፊታውራሪ አስጌ የፊታውራሪ መሸሻን እንገት ግራ ቀኝ እዬሳሙ።*

*«በውቀህም ይሁን ሳታውቅ የሆነው ሁሉ ይቅር፣ አንተም ማረኝ ልጄ ጌታዬ ማረኝ» አሉ ፊታውራሪ መሸሻ።*

*ከዚያ የዲማና የቢቸና ጊዮርጊስ ታቦቶች አንድ ላይ፣ ፊታውራሪ መሸሻና ፊታውራሪ አስጌ ጠመንጃቸውን ይዘው በታቦቶቹ ፊት አንድ ላይ ቆመው ሁለቱን ታቦቶችና ሁለቱን ፊታውራሪዎች ያጀበው ሕዝብ ፈረስ ሜዳን ሞልቶ መምህር ጥዑመ ልሳን ካሳረጉ በሁዋላ ካህናቱ ንኢብሎ በማለት ሕዝቡ በልልታና በጭብጨባ ደስታውን ገልጾ ፊታውራሪ መሸሻ የዲማ ጊዮርጊስን፣ ፊታውራሪ አስጌ የቢቸና ጊዮርጊስን አጅበው ወደ ያገራቸው ተመለሱ።»*

*ምንጭ፦ ሐዲስ ዓለማየሁ /ከበር ደክተር/፣ ፍቅር እስከ መቃብር ፣ 1992 ዓ.ም. ፣ ገጽ 166-171/።*



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «እግዚአብሔር ሲቆጣ አያነሣም በትር...»

## «የምክር፣ የመካሪ፣ የአስታራቂ፣ የተቆጪ መጥፋት የእግዚአብሔር ቁጣ ነው።»

/ኃ/ገብርኤል ዘሐና /

*በማኅበራዊ ሕይወት ሰዎች እርስ በርስ ከሚገናኙባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ጉርብትና ነው። ጉርብትና በሀገራችን ኢትዮጵያ ታላቅ ግምት የሚሰጠው ማኅበራዊ ትስስር ነው። ለደስታም ሆነ ለሐዘን ከወላጅ ከዘመድ ቀድሞ የሚደርስ ጎረቤት ነው። ጎረቤት እንደ የሁኔታው በአንድ ሰው ወይም ቤተሰብ ላይ የመልካም ግብር ወይም ተቃራኒውን ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ተጎራባቾች ከወላጆች ቀጥለው አስተማሪዎች ሊኾኑ ይችላሉ።*

*ዓላማዬ ስለ ጉርብትና ምንነት ላወጋችሁ ሳይሆን ጎረቤቶቼ የሆኑ ባልና ሚስት በልቡናዬ ያሳደሩትን ነገር ለዋናው ጽሑፌ መንደርደርያ ይኾነኝ ዘንድ ላጫውታችሁ ነው። እኒህ ባልና ሚስት ጎረቤቶቼ ለረጅም ጊዜያት ውስጥ ውስጡን ሲነታረኩ ሲጎሻሸሙ ቆይተዋል። ንትርኩ ገፍቶ አድጎ ለከፋ ጥል አበቃቸው። ጉዳያቸው ፍ/ቤት ደርሶ በሽምግልና እንዲታይላቸው ተብሎ ሽማግሌዎች ተጠርተው በደላቸውን ግራ ቀኙን በጥሞና ይከታተሉ ጀመር። ባል ሚስቱ በደለችኝ የሚለውን ተናገር ተባለ። «አትወደኝም፣ አታከብረኝም፣ ገንዘብ ታባክናለች፣ ያለ ሥራ ትዞራለች...» በማለት አለኝ የሚለውን ማስረጃ እያቀረበ በድላኛለች የሚለውን ዘረዘረ። ሚስትም በተራዋ ተጠይቃ «ገንዘብ አይሰጠኝም፣ ይሰክራል፣ በጊዜ አይገባም፣ ሰላም አይሰጠኝም፣ ይቀናል...» ስትል ዘረዘረች። ሁለቱም ተካሰሱ። ማን ይሆን እውነተኛው? የኾነው ኾኖ ይህ መካሰሳቸው ፍጻሜው ለአቅም ያልደረሱ ሦስት ልጆቻቸውን መበተን ነው። ምን ይሆን መፍትሔው?*

*ይህ ሽምግልና የተፈጸመው ባሳለፍነው ጊዜ በተፈጸመው ነነዌ ጾም ወቅት ነው። ለሽምግልና ተቀምጬ የባልና የሚስቱን የከረረ እሰጥ አገባ /ክርክር/ ሳዳምጥ መቅሠፍት የተዘጋጀባቸው የነነዌ ሰዎችና ይቅር ባይነትን፣ ዕርቅንና ሰላምን መውለድ አቅቷት የምታምጠው ሀገራችን ትውስ አለችኝ።*

እግዚአብሔር ነቢዩ ዮናስን፡- «ተነሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፥ ክፋታቸውም ወደ ፊቴ ወጥቷልና በእርስዋ ላይ ስበክ።» ብሎ አዘዘው። ት.ዮና.1፥2። ለጊዜው ነቢዩ ዮናስ ከራሱ ሰውኛ አመለካከት የተነሣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ ለመፈጸም ቢያንገራግርም ጽኑዕ በሆነች ሥልጣኑ ተይዞ በነነዌ ላይ ትንቢት ለመናገር በቅቷል። ነቢዩ ዮናስ ከዓሣ ሆድ ከወጣ በኋላ፡- «በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች» እያለ ጮኾ ትንቢት ተናገረ። /ት.ዮና.3፥4/።

ይህን የነቢዩ ዮናስን ቃል እንደ ሰሙ፡- «የነነዌም ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ለጾም ዐዋጅ ነገሩ፥ ከታላቁም እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ።» የነቢዩ ዮናስ ነገር በንጉሡ ዘንድ በተሰማበት ጊዜ በሚያስገርም ሁኔታ ንጉሡ ከዙፋኑ ተነሣ፣ መጎናጸፊያውን አወለቀ፣ ማቅ ለበሰ፣ በአመድ ላይ ተቀመጠ፣ ዐዋጁንም አስነገረ። በዐዋጁም መሠረት ከሰው እስከ እንስሳ ከታላቁ እስከ ታናሹ እንዳይሰማሩ፣ ውኃ እንዳይጠጡ፣ አንዳች ነገር እንዳይቀምሱ፣ ከዚህ ይልቅ ሰዎች ሁሉ በማቅ እንዲከደኑ፣ ወደ እግዚአብሔርም በብርቱ እንዲጮኹ ተደረገ። በዚህ መሠረት ለሦስት ቀናት በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን አዋርደው ጾሙ። «ወርእየ እግዚአብሔር ምግባሮሙ ከመ ነስሑ እምፍኖቶሙ እኩይ ወእግዚአብሔርኒ ነስሐ እምነ ዘነበበ እኩየ ይግበር ላዕሌሆሙ፤ እግዚአብሔርም ከክፉ ሥራቸው ተመልሰው ንስሐ እንደ ገቡ አይቶ በእነርሱ ላይ ያደርገው ዘንድ የተናገረውን ክፉ ነገር ከማድረግ ተመለሰ።» ዮናስ 3፥1-10።

የነነዌ ሰዎች ለሦስት ቀናት ብቻ ባደረጉት ጾም ራሳቸውን፣ ያላቸውን ንብረት፣ አገራቸውን ከጥፋት ታደጉ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሕግ በተደነገጉት ሰባቱ አጽዋማት በዓመት ውስጥ በትንሹ 215 ቀናት ያህል ይጾማል። በአንዳንድ የከተማ አድባራት 360 ቀናት ይቀደሳል፤ ሰዓታት ማሕሌት ይቆማል። በሥጋዊው አስተዳደር በኩልም ስለ ሰላም ብዙ ጥረት ሲደረግ ይታያል። ግን ይህ ሁሉ መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥረታችን ለምንድን ነው የነነዌ ሰዎችን ዐይነት ሰላምና ደኅንነት ያላመጣልን? በርግጥ በሀገራችን ምድራቱ በጥይት አረር አልታረሰች፣ መድፍና ታንክ አላጓራባት፣ ቤተ ክርስቲያኒቱም የዘወትር ሥርዐቷን መፈጸም አላቆመች ይሆናል። ይህን ተመልክተው ለጊዜው የሚደሰቱ ይኖራሉ። ግን አገልግሎቱ ፍቅርና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት ነው ወይ? ሕዝቡስ በኅሊናው /በልቡናው/ የሰከነ ሰላም አለው ወይ?

በብሉይ ዘመን ሰላም ሳይሆን ሰላም ነው በማለት ራሳቸውንና ሕዝባቸውን በማታለል ከንስሐ እንዳዘገዩ ሰዎች ራሳችንን ሳናታልል በመግቢያችን ላይ እንደ ጠቀስናቸው ባልና ሚስት በመካሰስ ትዳራቸውን ሊያፈርሱና ልጆቻቸውን ሊበትኑ እንደ ተነሡት ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችንንና አገራችንን ለጉዳትና ለጥፋት እንዳንዳርግ ከነነዌ ሰዎች ልንማር ይገባናል።

## ከነነዌ ሰዎች ምን እንማራለን?

### 1.ጥፋተኝነትን ማመን፡-

ነቢዩ ዮናስ ወደ አገራቸው ገብቶ ከኃጢአታቸው የተነሣ በሦስት ቀናት ውስጥ ነነዌ እንደ ምትገለበጥ ትንቢት በተናገረበት ወቅት ነገሩን የሰሙ ሁሉ አመኑ። የአገሩ ሰዎች «ድኻ መበደላቸው፣ ወደ ቤተ ጣዖት ገብተው ምስጋና ማቅረባቸው» በእግዚአብሔር ዘንድ ታውቆባቸው ሊያስቀጣቸው እንደ ሆነ በተነገራቸው ጊዜ እያንዳንዳቸው በየራሳቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ሕዝብ «አዎን ፥በድለናል» ነበር ያሉት። እግዚአብሔር ያለ ሥራችን ያለ ጥፋታችን ይህን አመጣብን አላሉም። በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኳቸው ባልና ሚስት ማየት የተሳናቸው ይህን ታላቅ ቁም ነገር ነው።

በአሁኑ ዘመን ዓለማችን ይልቁንም ሀገራችን አንድ ሁለት ተብለው በማይቆጠሩ ችግሮች ተመልታ በማማጥ ላይ ትገኛለች። ልዩ ልዩ ሥነ ምኅዳር፣ በርካታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ሀብቶች እያሉን በጣም ተቀራራቢ በሆኑ ዓመታት ድርቅ የሚመታን ለምንድን ነው? እውነት በዓል አብዝተን ስላልሠራን ነው? በዚህች አገር ድሀ አልተበደለም? ፍርድ በገንዘብና በወገን በሥልጣን ከለላ አልተጣመመም? እናቶች ገና ባልተወለዱ ልጆቻቸው ላይ የመግደል መብት እንዲሰጣቸው /ፅንስ ማቋረጥ/ አልጠየቁም? በአባይ ጠንቋይ ማታለያ ገንዘብ ለማግኘት ሲባል ንጹሐን ሕፃናት እንደ በግ አልታረዱም? መላ ዘመናቸውን ለቤተ ክርስቲያን ትምህርትና አገልግሎት የኖሩ የደከሙ መምህራን አስታዋሽ አጥተው አላለቀሱም? በጎሳ፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣ የማያውቁን ከሰብአዊ ርኅራኄ የተነሣ በበሽታ፣ በድርቅ፣ በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን የላኩትን ርዳታ የግል ኪሳችን ማደለቢያ አላደረግንም? ታቦታቱን፣ መጻሕፍቱን፣ መስቀሎቹንና ሌሎቹን ንዋያተ ቅድሳት አውጥተን አልሸጥንም? የመሥዋዕቱን ሥርዐት የክህነቱን ሥልጣን አላዋረድንም? ከእግዚአብሔር ይልቅ ምድራዊ ባለሥልጣን፣ ከነፍሳችን ይልቅ ሥጋችን፣ ከእውነት ይልቅ ሐሰት በልጦብን ከሌባው ጋር ሌባ፣ ከገብኛው ጋር ገብኛ፣ ከአጥፊው ጋር ተባባሪ አልሆንም? ከሁሉም በላይ መክበር የሚገባውን እግዚአብሔርን አልናቅነውምን? አልካድነውምን? በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑና በየመንደሩ በጠበል ፈውስ ስም ጥንቆላና ማታለል አልተፈጸመምን?

እነዚህንና ሌሎችን በየራሳችን የምናውቃቸውን ኃጢአታችንን አምነን ንስሐ ስንገባ እግዚአብሔር ይታረቀናል። ንስሐ ገብተን ከእግዚአብሔር ጋር ስንታረቅ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የኀሊና መታደስን እናገኛለን። «እኛም የበደለንን ይቅር እንድንል፥ በደላችንን አበሳችንን ይቅር በለን» /ማቴ.6፥12/ እያልን በየዕለቱ የምንጸልየውን ያህል በበደላችን ይቅር ተባብለን ዕርቅንና ሰላምን ለመፍጠር እንበቃለን። «ለሰዎች በደላቸውን ይቅር ብትሉ፥ ሰማያዊ አባታችሁም በደላችሁን ይቅር ይላችኋልና። ለሰዎች በደላቸውን ይቅር ባትሉ ግን ሰማያዊ አባታችሁ ይቅር አይላችሁም።» /ማቴ.6፥14-15/ እንዳለ። ከዚህ ውጭ ጥፋተኛነትን ሳያምኑ፣ አምነውም ንስሐ ሳይገቡ በዘልማድ ሰባቱን አጽዋማት ቢጾሙ፣ 360 ቀናት ቢቀደስ፣ ልቡና በክፋት ተመልቶ ምሕላ ቢደረስ ጥቅሙ ምን ይሆን? ደራሲው፦

> «ሁሉም በየቤቱ ሰይፉን እየሳለ፣
> አደባባይ ወጥቶ ሰላም ሰላም ካለ፣
> ሰው ራሱን እንጂ ማንን አታለለ፤»

እንዳለው እንዳይሆንብን ራሳችንን ዝቅ አድርገን፣ ጥፋተኝነታችንን አምነን ንስሐ ልንገባ ያስፈልጋል። ነቢዩ ዳንኤል ራሱን ዝቅ አድርጎ በዘመኑ በእስራኤል ላይ ለሆነው መከራና ምርኮ ምክንያቱ የራሱና የወገኑ ኃጢአት መሆኑን በእግዚአብሔር ፊት አምኖ ጸልዮአል። እኛም በአፍ ያይደለ በልባችን አምነን የጾምን የጸለይን እንደ ሆነ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንና ለአገራችን ሰላሟን፣ አንድነቷን፣ ክብሯንና ብልጽግናዋን ይሰጣል። በአብዛኛው ጾማችን፣ ጸሎታችን... በአጠቃላይ ንስሐችን በማኅበር የታወጀ /Mass Repentance/ ነው። ይቅር መባባላችንና መታረቃችንም እንዲሁ በይፋና ሁሉን ዓቀፍ መኾን ይገባዋል። ከዚህ ውጭ ልባችንን አጽንተን እንደ ነቢዩ ኤርምያስ ዘመን ሰዎች፦ «ክፉ ነገርም አይመጣብንም፤ ሰይፍንና ራብንም አናይም» የምንል ከሆነ እርሱ እግዚአብሔር የሌለውን እንዳለ አድርጎ መጥራት ይቻለዋል። ኤር.5፥12።

## 2. *አለመካሰስ*

የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔር ባወቀው ኃጢአታቸው መቅሠፍት እንደ ታዘዘባቸው ሲሰሙ፦ «ይህ የነ እገሌ ኃጢአት ነው» አላሉም። ሁሉም አንድ ሆነው አጥፍተናል ብለው ንስሐ ገቡ እንጂ።

በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችንና በሀገራችን ላይ ያለውም እውነታ ይህንኑ ሁኔታ ይፈልጋል። ባለፉት የመስቀልና የጥምቀት በዓላት በታየው ሁኔታና በአጠቃላይ በተለያዩ ጊዜያት በተፈጠሩት ግጭቶች ወገን እርስ በርሱ ደም ተፋሰሰ። በየመገናኛ ብዙኀኑ አንዱ ሌላውን ኰነነ። ከሰሰ። ተካሰሰ።

በዚህ ሁሉ የሕይወት መጥፋት፣ የአካል መጉደልና የንብረት መውደም እያንዳንዱ ሌላውን ከሰሰ። ማን ይሆን በሆነው ችግር ውስጥ ሁሉ ንጹሕ?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ዘመን



***የእግዚአብሔር ቁጣ*** *- እስከ መቼ በሰው ኃጢአት ሌሎች ፍጥረታት ይቀጣሉ? /ዘጸ.9 እና 10/*

ጸፎችና ፈሪሳውያን «ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች» የተባለችቱን ሴት ለክስና እግረ መንገዳቸውም ጌታን ለመፈተን ይዘው ቀረቡ። ጌታም የክሳቸውን ነገር ከሰማ በኋላ፦ «ከእናንተ መካከል ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት።» አላቸው። ዮሐ.8፥4-9። ይህን ቃል ከጌታ በሰሙ ሰዓት ሁሉም አፍረው ተመለሱ። ማን ነው ወንድሙን የሚከስ? ማን ነው ሌላውን ከመክሰሱ በፊት ራሱን በውስጣዊው ዐይኑ የተመለከተ? በእውነት በዚህች አገር ያለን ሰዎች ሌላውን በምን ከስበት ነገር ምን ያህል ራሳችንን መርምረናል?

በመሠረቱ መካሰስ ፈቃደ እግዚአብሔር አይደለም። ሰውን ሲከስ የተገኘው /ከሳሽ የተባለው/ ዲያብሎስ ነው። ኢዮ. 1፥9፤ 2፥3። ሰውን ከመክሰስ የራስን ሕይወት በንስሐ አስተካክሎ እግዚአብሔር የሁሉን ልቡና ወደ በጎ እንዲመልስ መጸለይ፣ ለሀገር ለወገን ለቤተ ክርስቲያን በጎ የሆነውን ሥራ እንዲሠራ መለመን ተገቢ ነው። በእርግጥ በገሃድ የምናውቀው ነገር እንኳን ቢኖር በግልጥ ተወያይቶ መፍትሔ ከመፈለግ ውጭ ክፉውን በክፉ በመቃወም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ማቆም አንችልም። እርስ በርሳችን ብንነቃቀፍና ብንካከስ ፍጻሜያችን ጥፋት ይሆናል። ለክስ የምናውለውን ጊዜና አቅም በንጹሕ ልቡና ሆነን ለበጎ ሥራ እናውለው።

## 3. *ተስፋ አለመቁረጥ*

ነቢዩ ዮናስ ትንቢት በተናገረበት ወቅት ነነዌ ለጥፋት የቀራት የሦስት ቀናት ዕድሜ ብቻ ነበር። ለብዙ ዘመናት ነዋሪዎቿ የፈጸሙት ኃጢአት የበደል ጽዋቸውን ሞልቶ ሊያጥለቀልቃቸው ጫፍ ላይ የደረሰበት ሰዓት ነበር። ሕዝቡ ግን ተስፋ አልቆረጠም። ከባለ ሥልጣኖች የሚሰጠውን ትእዛዝም አልጠበቀም። ጥፋት በደጃቸው ቆሟልና ፈጥነው ንስሐ ገብተው ጾምን ዐወጁ። ንጉሡም ሳትነግሩኝ፣ ሳልሰማ ሳይል በሰማበት ሰዓት እንደ ሕዝቡ ሁሉ ጥፋቱን አምኖ ንስሐ ገባ። የሕዝቡን የጾም ዐዋጅ አጸና። ይልቁንም፦ «እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ተመልሶ ይጸጸት እንደ ሆነ ከጽኑ ቁጣውም ይመለስ እንደ ሆነ ማን ያውቃል» በማለት ተስፋ እንዳ ይቆርጡ አበረታታቸው። ዮና. 3፥9።

በሀገራችን ከግለሰብ እስከ ኅብረተሰብ፣ ከቤት እስከ አደባባይ፣ ከሥጋዊ እስከ መንፈሳዊ፣ ከአስፈጻሚ መሥሪያ ቤት እስከ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከአንዲቷ አጥቢያ እስከ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ለቁጥር የታከቱ፣ እንደ ተጎለጎለ ልቃቂት ውል አልባ የመሰሉ ችግሮች ይኖራሉ። እነዚህን ችግሮች በመመልከት በሀገራቸውም በቤተ ክርስቲያናቸውም ተስፋ የቆረጡ ሊኖሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ለሁሉም መፍትሔ አለው። በእምነት በርትተን ስለ ኃጢአታችን በፍጹም ልቡና ወደ እግዚአብሔር በንስሐ ብንመለስ እርሱ የተቆረጠውን ይቀጥላል። የደረቀውን ያለመልማል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ዘመን ሰዎች በእግዚአብሔር ማመንን፣ መፍትሔ ከእርሱ መፈለግን እንደ ሞኝነት ቆጥረውታል። እግዚአብሔር ራሱ በነቢዩ ኤርምያስ አንደበት፦ «ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና። እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል። የተቀደዱትንም ጉድጓዶች ውኃንም ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል» በማለት እንደ ተናገረው እግዚአብሔርን በሥራቸውም ሆነ በልባቸው በመካድ በሰብአዊ ፍጡር አቅም ሊገኝ የማይችለውን ሰላም ሊያስገኙ ይሯሯጣሉ። ኤር.2፥13። ሰዎች ቢያምኑም ባያምኑም አገራችን የተደቀነባትን ችግር እግዚአብሔርን ካልያዝን በስተቀር መፍታት ከቶ አይቻለንም። የዚህንም እውነታ እስካሁን የተደረጉ የተለያዩ የሰላም ድርድር፣ የጉልበት ፍጥጫ... የመሳሰሉት ባስገኙት ውጤት ታይቷል። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች እያደር ሆድ ከማጎሽ በስተቀር ምን አስገኙ?

ሐዋርያው «የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?» እንዳለው ባላመኑት ሰዎች ሳንገረም ተስፋችንን አጠንክረን በጾም በጸሎታችን በፍቅር፣ በይቅር ባይነት፣ በተስፋና በትሕትና ሆነን እግዚአብሔርን እንለምነው። ሮሜ.3፥3። እርሱ በነቢዩ ኤልሳዕ አንደበት፦ «ነፋስ አታዩም፣ ዝናም አታዩም። ይህ ሸለቆ ግን ውኃ ይሞላል፤ እናንተም





© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከብቶቻችሁም እንስሶቻችሁም ትጠማላችሁ:: ይህም በእግዚአብሔር ዐይን ቀላል ነገር ነው::» በማለት እንደ ተናገረው እንዳደረገውም በችግሮቻችን መብዛትና መደራረብ ተስፋ ሳንቆርጥ እርስ በርስም ሳንካሰስ በእምነት ወደ እርሱ ተመልሰን ብንለምነው የጎደለንን የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል:: 2ኛነገ. 3፥17-18::

እዚህ ላይ አጽንዖት ሰጥተን ልናስተውለው የሚገባን ነገር አለ:: የቱንም ያህል ችግሮቻችን ቢበዙ፣ የቱንም ያህል የቆዩና ስር የሰደዱ ቢሆኑ፣ የቱንም ያህል ለችግራችን እውነተኛ መፍትሔ የሚሆነውን ነገር የሚያጣጥሉ ሰዎች ቢበዙ እግዚአብሔር አፋቸውን ሳይሆን ልባቸውንና ሥራቸውን ለእርሱ ያስገዙ ጥቂት ሰዎችን ቢያገኝ ምሕረቱን ያደርጋል:: «... በሰዶም በከተማይቱ ውስጥ ዐሥር ጻድቃን ባገኝ ስፍራውን ሁሉ ስለ ዐሥሩ አላጠፋትም::» እንዲል:: ዘፍ.18፥26-33::

ተስፋ ባለመቁረጥ በእምነት ጸንተን፣ በፍቅር ሆነን፣ ሁላችን ለራሳችን፣ ለወገኖቻችን፣ ለሀገራችን፣ ለቤተ ክርስቲያናችን... የሚገባንን በእውነት ከሠራን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሠራል:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንን የቅዱስ ጳውሎስን የአቴና አገልግሎት እንመልከት::

ቅዱስ ጳውሎስ ቤርያ በተባለች ሥፍራ እያስተማረ ሳለ ከተሰሎንቄ የመጡ አይሁድ ቢያሳድዱት ወደ አቴና ሄደ:: ሲላስና ጢሞቴዎስ ከቤርያ ወደ እርሱ እስኪመጡ ድረስ በአቴና ከተማ እየተመላለሰ ይመለከታት ነበር:: በዚህ ሰዓት:- «ጳውሎስም በአቴና ሲጠብቃቸው ሳለ በከተማው ጣዖት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ተበሳጨ በት::» የሐዋ.ሥራ.17፥16::

ይህን ዐረፍተ ነገር በዝርዝር ነጥቦች እንመልከተው::

## ሀ. «*በከተማው ጣዖት መሙላቱን ተመለከተ*»

ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና የቆየው ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም የከተማይቱን ችግር ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም:: በከተማይቱ ብዙ መካናተ ጣዖታት ተተክለው፣ ሰው ቀኑን ሙሉ በጣዖታት ቤት ተገኝቶ ሲሰግድላቸው፣ ለእያንዳንዱ ፍጥረትና ክሥተት ጣዖታት ተሰይመውለት አየ:: አካባቢውን ማስተዋል የሥራ መጀመርያው አደረገ::

ሰዎች ሥራ ሊሠሩ የሚችሉት በሀገራቸው፣በቤተ ክርስቲያናቸው፣ በቤታቸው፣በትዳራቸው፣ በሥራ ገበታቸው ያለውን ችግር ሲመለከቱ ነው:: መመልከት ማለትም እነዚህ ችግሮች ሊያስከትሉት የሚችሉትን ነገር መረዳት ነው:: በአሁኑ ጊዜ በግል ሕይወታችን፣ በአካባቢያችን /በየአጥቢያችን/፣ በሀገራችን ምን ዐይነት «*ጣዖታት*» /ችግሮች/ አሉ? ከራሳችን ጋር፣ ከአካባቢያችን ጋር፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን፣ በመሥሪያ ቤታችን፣ በሀገራችን ምን ያህል ጊዜ ኖረናል? ይህን ያህል ጊዜስ ስንኖር በእነዚህ ቦታዎች የሞሉ ችግሮቻችንን ምን ያህል ተረድተናል? «*ከተማ*» ሰውነታቸው፣ «*ከተማ*» ቤተ ክርስቲያናቸው፣ «*ከተማ*» አገራቸው ከጣዖታት በከፉ ችግሮችና መከራዎች ተመልታ የጭንቅ ምጥ እያማጠች ሳለ በጊዜያዊ ደስታና ችግር ጎሊናቸው ናውዞ በስንፍና አልጋ ላይ የተኙ አሉ:: እነዚህም «መስማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፣ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም፤ በዐይናቸው እንዳያዩ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈወሳቸው የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል፣ ዐይናቸውንም ጨፍነዋል» ተብሎ:: የተ ነገረባቸው ዐይነት ሰዎች ናቸው:: ኢሳ. 6፥9-10፤ ማቴ.13፥14-15::

ቅዱስ ጳውሎስ የአቴናን ችግር የተረዳው ሥራዬ ብሎ ስለ ተመለከተ ነው:: እኛም ያሉብንን ችግሮች ከልባችን ልንረዳ የምንችለው ያገባናል፣ ጉዳያችን ነው፣ በሰውም በእግዚብሔርም ዘንድ ያስወቅሰናል ብለን ስናስብ ብቻ ነው:: ያለበለዚያ ዐይንና ጆሮ በአንድ አካል ላይ እያሉ ሳይተያዩ እንደ ሚኖሩ ሁሉ እኛም ችግሮቻችን መላ ሕይወታችንን ወርሰውት ሳለ ሳናያቸው የአስከፊ ውጤታቸው ሰለባዎች እንሆናለን:: በሚያስገርም ሁኔታ በአቴና ከተማ በዚያን ወቅት በርካታ አይሁድ ነበሩ:: አይሁድ ከሌላው ኅብረተሰብ ተለይተው ለእግዚአብሔር የቀረቡ፣ ሕጉን ሥርዐቱን እንጠብቃለን፣ እናስጠብቃለን ሲሉ የነበሩ ሰዎች ናቸው:: ከእግዚአብሔር ዘንድ ሳልሆን ወግና ልማዳቸውም እጅጉን ይቀኑ እንደ ነበር በወንጌል ተጠቅሷል:: ይሁን እንጂ በሚኖሩባት በአቴና ከተማ ከመጠን በዝተው ስለነበሩት ጣዖታት ደንታ አልነበራቸውም፤ ይህን የሚያዩበት ውስጣዊ ዐይናቸው ጨልሟልና:: በሀገራችንም ያለው እውነታ ይኸው ነው:: በመንፈሳዊውና በሥጋዊው ዕውቀት የረቀቁ፣ አንቱ የተባሉ አያሌ ምሁራን በምድራችን ቢኖሩም የአገሪቱን ሕዝብ ነፍስና ሥጋ አስጨንቀው የያዙ ችግሮችን ገና ማየት አልቻሉም:: አንዳንዶቹ አይተናል ቢሉም የራስ ባልሆነ ዐይን ገጽታው ነው::

## ለ. «*መንፈሱ ተበሳጨበት*»

በከተማው የመላው ቤተ ጣዖት፣ በየክሥተቱ የተሠየሙት ጣዖታት፣ መላ ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውንና ሰውነታቸውን ሳይቀር ለአማልክቱ የሚሠዉት ሰዎች ሁኔታ በአግራሞት ሳይወስደው አበሳጨው:: ወደ ዘላለም ሞት በሚያመራቸው መንገድ እየተጓዙ ያሉትን በተመለከተበት ሰዓት እንደ ልዩ የጉብኝት ቦታ ወይም እንደ አስደናቂ የዓለም ኪን አልቆጠረውም:: ፍጹም አግባብነት ባለው ቅንዓት ቀናባቸው::

እውነትን የሚያውቁ፣ እውነትን የያዙ፣ ለእውነት የሚሠሩና የሚኖሩ ሰዎች ከራሳቸው አልፈው በወገናቸው፣ በአገራቸውና በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ የሚሆነው ክፉ ነገር ያስቀናቸዋል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኛ እንደ ሌለው መንጋ ከበረቱ ወጥቶ ሲቅበዘበዝ ለንጥቂያ፣ ለእርድ፣ ለመከራና ለሐዘን፣ ለረኀብ፣ ለድህነት፣ ለበሽታና ለድንቁርና ሲጣል አይቶና ሰምቶ «ከራስ በላይ ነፋስ» በሚል ጎሊና የላቸውም:: እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚቀናው መልኩ ለመላው ሕዝብ ዘር፣ ቀለም፣ ቋንቋና እምነት ሳይለያቸው ለሁሉ ይቀናሉ:: የብዙኃኑ ሥቃይና ብሶት ይጋባባቸዋል እንጂ በምንቸገረኝነት ግዴታቢስ አይኾኑም:: ነቢዩ ኢሳይያስ:- «ሕፃን ተወልዶልናልና ወልድም ተሰጥቶናልና» ብሎ ብሉየ መዋዕል ወልድ በግእዘ ሕፃናት የመወለዱን ነገር በተናገረበት ምዕራፍ የዚህ ሁሉ መንሥኤው እግዚአብሔር ለወገኖቹ የቀናው ቅንዓት መሆኑን «የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል::» በማለት ገልጧል:: ኢሳ.9፥7:: የእግዚአብሔርን ጸጋ ገንዘብ ያደረጉ ሰዎችም እንደ እርሱ ለወገናቸው ይቀናሉ::

በዚህች ምድር ላይ እንደ ጳውሎስ ሥጋዊው ጥበብ ከመንፈሳዊ ጥበብ የተሟላላቸው አንቱ የተባሉ ሰዎች በርካቶች ናቸው:: ግን ማን ነው የወገኑ መራብ፣ መሰደድ፣ መታረዝ፣ በበሽታ መወረር፣ ደም መፍሰስ፣ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ እውነቱና ንዋያተ ቅድሳቱ እንዲሁም ሥርዐቱ መበረዝ፣ የሰላሙ መናጋት ያስቀናው? ምናልባት መልካም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለመረዳት መነካከስና መነቃቀፍ፣ መካሰስና መሰዳደብ፣ መገዳደልና መደባደብ ያለበትን እንስቃሴያቸውን ሰዎች እንደ ቅናት ሊቆጥሩት፣ ይህን ድርጊታቸውንም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቅሰው ተአማኒነት ለማግኘት ከብሉይ መዝዘው በሐዲስ ኪዳን እምብርት ላይ ሊተክሉ ይፈልጉ ይሆናል:: «ዐይን ስለ ዐይን ቀርቶ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» የሚለው ቃለ ኃይል የማይዋጥላቸው ናቸው::

በውኑ ለራሱ ሳይሰስት እኛን አብልቶና አጠጥቶ ያጠገበን፣ ሳይለብስ ያደመቀን፣ ሳይማር ለሊቅነት ያበቃን፣ የከብት ጭራ ተከትሎ በቀን ኪሎ ሜትሮችን በእግሩ እየገሠገሠ በምድር በሰማይ ለመሽከርከርና ለመብረር ያበቃን ወገናችን ውለታና አሁን ያለበት የመንፈሳዊና የሥጋዊ ኑሮው መዝቀጥ ያስቀናናል? ቀንተናል የምንል ሰዎች ካለንስ ቅንዓታችን በጀርባ ስውር ግላዊ ጥቅም ከማንገብ ምን ያህል የጸዳ ነው? ያልቀናን ሰዎችስ መቼ ነው የምንቀናው? ቀንተንስ መቼ ነው ማንንም ሳንከስ በሰላም ማስርያ የመንፈስ አንድነትን ገንዘብ አድርገን በከተማችን የመላብንን ችግሮች የምናስወግደው? በተለይም በዕውቀት፣ በገንዘብ፣ በሥልጣን ከፍ ካለ ቦታ ያለን ሰዎች መርዶክዮስ በእስራኤል የሞት ዐዋጅ ከአርጤክስስ ዘንድ በታወጀበት ወቅት: - «አንቺ በንጉሥ ቤት ስለ ሆንሁ ከአይሁድ ሁሉ ይልቅ እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ:: በዚህ ጊዜ ቸል ብትዪ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ሥፍራ ይሆንላቸዋል:: አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ» ሲል ለአስቴር የላከውን ጽኑዕ መልእክት ልብ ማለት ይበጃል:: እግዚአብሔር ሲ. ቆጣ ዕውቀታችን፣ ገንዘባችንና ሥልጣናችን አያድኑንምና::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

### ሐ. ለሥራ ተነሣ

ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና ካለው አምልኮ ጣዖት የተነሣ መንፈሱ ተበሳጭቶበት ከንፈር በመምጠጥ ብቻ አላቆመም:: በከተማይቱ ከሚኖሩ አይሁድ፣ ከታዋቂ የግሪክ ሰዎች ጋር በተለይም በፍልስፍናቸው ከታወቁ የኤፊቆሮስ ወገንና አስጦኢኮች ከተባሉት፣ በአርዮስፋጎስ የፍርድ ቤት ፈራጅ ከነበረው ከዲዮናስዮስና ደማሪስ ከተባለችው ሴት ጋር ተነጋገረ፣ አስተማረ::

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ እንበል፤ ቅዱስ ጳውሎስ በትውልዱ አይሁዳዊ ቢሆንም በዜግነት ግሪካዊ ሳይሆን ሮማዊ ነው:: የግሪክ ጣዖታት በመጀመርያ ለቁጥር የበዙ ናቸው:: ሁለተኛም ጣዖታቱ በዚያች ምድር ለብዙ ዓመታትና ትውልዶች ሲመለኩ የኖሩ ናቸው:: ይህ ሁሉ ኾኖ ሳለ እነዚህን በመቃወም ለማስተማር በመንፈሳዊ ወኔ የተነሣው አንድ ቅዱስ ጳውሎስ ብቻ ነው:: ይኼ ሁሉ ተስፋ አላስቆረጠውም:: በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ በከተማይቱ የመሉ ጣዖታትን በተመከለተበት ወቅት:- ጊዜ ገዳይና ተነሣሽነትን አቀዝቃዥ የሆኑ ጥያቄዎችን አላነሣም:: ከእግዚአብሔር ጋር የሚቻለውን ያህል ሊሠራ ተነሣ እንጂ:: በዘመናችን ላሉብን ሥጋዊና መንፈሳዊ ችግሮቻችን ስፍር ቁጥር በሌላቸው እርባና ቢስ ጥያቄዎች መነታረኩ ጊዜንና ገንዘብን ያባክናል፣ ተነሣሽነትን ያቀዘቅዛል:: በመላምት ሐሳቦችና በእነርሱ ላይ በተመሠረቱ ድምዳሜዎች ወቃሽና ተወቃሽን ማብዛት ይከሠታል:: ዛሬ ላይ ቆመን ሳንሠራበት ትላንት ጊዜው፣ ዕውቀቱ፣ ንቃተ ኅሊናው፣ ባህሉ፣ ፖለቲካው፣ ኢኮኖሚው የፈቀደላቸውን ሰዎች ገበና ለማውጣትና ለመውቀስ መፍጨርጨር በእውነቱ መልካም ዛሬን ማስናቅና በከንቱ ማሳለፍ ነው:: ለሀገራችንም ሆነ ለቤተ ክርስቲያናችን ከመቶና ሁለት መቶ ዓመታት በፊት የነበሩ ሰዎችን መውቀስ ሥልጣኔ ሳይሆን በየትኛውም ውድ ዋጋ ሊገኝ የማይችለውን ጊዜ በከንቱ ማጥፋት ነው:: ከዚህ ይልቅ እነዚያ ከብዙ ዓመታት በፊት የነበሩ ሰዎች በድለዋቸዋል የምንላቸውን ወገኖቻችንንና አገራችንን ዛሬ /የሠለጠነው ዓለም ከሰው እልፎ እውሬ እሠልጥኖ በሰላምና በፍቅር የሥራው ተባባሪ የድካሙ አጋዥ አድርጎ አብሮ በሚኖርበት ወቅት/ ምን ሠርተን የቀደመውን ቁስል ጠባሳ እናጥፋ ማለቱ ሥልጣኔ ነው::

ምናልባት ከችግሮቻችን መብዛትና ሥር መስደድ የተነሣ መፍትሔ ለማግኘት፣ በሰላምና በፍቅር እግዚአብሔር በተፈራበት ኅሊና እንሥራ ሲባል የማይሆንና የማይቻል የሚመስለን ልንኖር እንችላለን:: ቅዱስ ጳውሎስም ሊያስተምር በተነሣበት ወቅት ለአቴና ሰዎች እንዲሁ ነበር የመሰላቸው:: አንዳንዶቹ «ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል?» አሉ:: ሌሎቹም «አዲሶችን አማልክት የሚያወራ ይመስላል::» አሉ:: የተቀሩትም የሙታንን ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ አፌዙበት:: ይሁን እንጂ ሐዋርያው ይህ ሁሉ መለያየት ካለመረዳት መሆኑን ስለ ተገነዘበ በእግዚአብሔር ፈቃድ ጸና፤ በአርዮስፋጎስ ሁሉ ሳይቀር ጸንቶ አስተማራቸው:: በመሆኑም ብዙዎች ተባብረው በጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ:: «ለማይታወቅ አምላክ» ብለው ለማይታወቅ ጣዖት በሰገዱበት አገር፣ እስከዚያን ድረስ ሳያወቁት እርሱ ግን አስቀድሞ በመፍጠር፣ በመመገብ፣ በመጠበቅ ላወቃቸው አምላክ ለክርስቶስ ሰገዱ::

እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ አንድ ራሱን ኾኖ ችግሮች በበዙበት፣ ጠላቶችና ፌዘኞች በበረከቱበት በባዕድ አገር ይህን መሰል ለውጥ ያመጣበት ምሥጢሩ በተስፋ፣ በትዕግሥትና በዓላማ እንዲሁም ከሁሉም በላይ ለሰው ልጅ ታላቅ ክብርና ፍቅር በመስጠቱ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ የጣዖታቱን ብዛት፣ የፌዘኞቹን ኃይል ባዕድነቱን ተመልክቶ ተስፋ ቢቆርጥ ኖሮ አቴናና ጣዖቶቿ እንደ ተጣበቁ ይኖሩ ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስ በሌላው ሀገር ይህን መሰል ታሪክ ብቻውን ከፈጸመ እኛስ ብዙዎች ሆነን መልካምና ክፉውን ላየንባት አገራችን ምን ልንሠራ እንችል ይሆን? ቸርነት የባሕርይው የሆነ እግዚአብሔር በእምነትና በእውነት ለሚጠሩት የቅርብ አምላክ ነው:: ስለዚህ ተስፋ አንቁረጥ:: ምንም እንኳን ችግሮቻችን እንደ ተራራ የገዘፉ ቢሆኑ የሰናፍጭ ቅንጣትን ያህል እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ካለን ደግሞ ይወገዱልናል::

## 4. ለጊዜ ዋጋ መስጠት:-

የነነዌ ሰዎች ከነአገራቸው ሊገለበጡ የቀሯቸው ሦስት ቀናት ብቻ ናቸው:: በነዚህ ቀናት ውስጥ መፍትሔ አልባ በሆኑ ርእስ ጉዳዮች በመጨቃጨቅ ጊዜን ከማገደል ይልቅ ጾምን ዐወጁ:: ያለቻቸውን ሦስት ቀናት አክብረው ጾሙባት፣ ጸለዩባት፣ ንስሐ ገቡባት፣ ራሳቸውን በፈጣሪያቸው ፊት የይስሙላ ያይደለ በእውነት አዋረዱባት:: ለትንሿዋ ጊዜ ዋጋ ሰጥተው ባደረጓት ንስሐ ታላቂቷን ነነዌን ከመገልበጥ አዳኗት::

ያሉንን ጊዜያት ለራሳችን፣ ለደጊቱ ሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ሰላም፣ ፍቅር፣ ዕድገትና ብልጥግና ልናመጣባቸው ምን ያህል ዋጋ ሰጥተን እንሠራባቸዋለን? የሥራ ሰዓቶቻችን፣ የጾም፣ የቅዳሴና የምሕላ ጊዜዎቻችን ምን ያህል ትኩረት ይሰጣቸው ይሆን? በሀገር፣ በቤተ ክርስቲያን የሚታወጁ የውይይት፣ የምሕላ ወቅቶች ጊዜያዊ መልስ ለመስጠት ተብለው መደረግ የለባቸውም:: እንዲህ ከሆነ ታላቅ የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በጊዜ መጫወት ይሆናል:: ፈያታዊ ዘየማን /በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ሽፍታ/ በሽፍትነት ከጨረሰው ጊዜው ይልቅ ከጌታ በስተቀኝ ለተሰቀለበት ጥቂት ጊዜ ዋጋ ሰጠ:: ስለ ቀደመው በደሉ ሁሉ በማያዳግም ሁኔታ ንስሐ ገባባት:: በደሉ ሁሉ ተደምስሶለት «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ::» ተባለ::

ያለፈው ጊዜ መማርያ ከመሆን በቀር ትርፍ የለውም:: የምትጠቅመን አሁን ያለችው ጊዜ ናት:: አገራችንን፣ ሕዝባችንን፣ ቤተ ክርስቲያናችንን ከሁሉም በላይ ኹናኝና አጽዳቂ እግዚአብሔር እያለ እንደሌለ በመቁጠር ሌላውን በመበደልም ሆነ በሌላው ላይ በመፍረድ በድለናልና ፈጥነን ንስሐ እንግባ:: ያን ጊዜ እንደ ነነዌ የተቃጣብን መቅሠፍት ሁሉ ይጠቃለልልናል::

ባልና ሚስቱ መደማመጥ፣ መነጋገርና መረዳዳት አቃታቸው:: ተካሰሱ:: ሁለቱም በየራሳቸው «ተበደልኩ» ብለው የሚያስቡትን እንጂ የበደሉት ነገር እንዳለ ማሰብ ተሳናቸው:: ትዳራቸውን ለማፍረስ ለክስ በቆሙበት ወቅት እንኳን አሳዳጊ አልባ ሆነው የሚበተኑና ለልመና የሚዳረጉ ልጆቻቸውን ማሰብ አልቻሉም:: ይህ የአገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን ሕይወት ገጽታ ነው:: አበው ሲተርቱ:- «እግዚአብሔር ሲጣላ አያነሣም በትር፣ ምክር አሳጥቶ ያደርጋል ድንግርግር» ይላሉ:: የምክክር፣ የአመካከር፣ የዕርቅ የአስታራቂ፣ የተቆጪ መጥፋት የእግዚብሔር ቁጣ ነው:: እግዚአብሔር የነነዌ ሰዎችንና የቅዱስ ጳውሎስን የአቴና አገልግሎት መካሪ አድርጎ ሰጥቶናል፤ እንጠቀምበት:: በንስሐ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ እርሱም ይመለስልናል:: የአንድ እጅ ጣቶች በርዝመትና በእጥረት፣ በውፍረትና በቅጥነት፣ በማጌጥና ባለማጌጥ ሳይለያዩ በአንድነት ጸንተው የቀረበውን በማራቅ የራቀውን በማቅረብ አንድ አካልን /ሰውነትን/ እንደ ሚያገለግሉት ሁሉ እኛም በጎሳ፣ በፖለቲካ አቋም ልዩነት፣ በእምነት፣ በባህል፣ በዕውቀት... ልዩነታችን ሳንጋጭ ተባብረን ደጊቱ አገራችን ኢትዮጵያን፣ ከነ ችግሩ ደግና ትዕግሥተኛ የኾነውን ሕዝባችንን እናገልግል:: በተለይም አሁን ያለንበት ጊዜ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 40 መዓልትና 40 ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ ጾሞ የሰው ሁሉ ጠላት የሆነውን ዲያብሎስን ድል ያደረገበትን የምናስብበት የጾም ጊዜ ነው:: በጾማችን ፍጻሜ እንደ ሕዝበ እስራኤል:- «ስለምን ጾመን አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን አንተም አላወቅህም?» ከማለት እንድንድን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ የነነዌን ሰዎች አርአያ እናድርጋቸው:: ኢሳ. 58፥3:: ቅዱስ ጳውሎስ በኦሪት ስለ ነበሩት ሰዎች:- «ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» እንዳለ እኛም ያለ ልዩነት በእግዚአብሔር ፊት በድለናል:: ኃጢአት በመሥራት፣ በመተባበር፣ኃጢአተኛው ከመንገዱ ይመለስ ዘንድ ባለመገሠጽ በድለናል:: ሮሜ.3፥22-23:: የዘመመውን ለማቅናት፣ የኀበጠውን ለማስተካከል፣ የጎደለውን ለመሙላት ብዙ ሮጠን አንዳች አላተረፍንም:: መፍትሔው:- በዚህ በጾማችን ከነነዌ ሰዎች በመማር አለቃ፣ ሎሌ፣ ምሁር፣ ያልተማረ፣ ካህን ጨዋ፣ ሳንባባል ሁላችንም እንደ ምእመንም እንደ ሕዝብም የማስመሰል ያይደለ እውነተኛ ንስሐ እንግባ:: ይኸውም ልባችንና አንደበታችን አንድ ኾኖ በደላችንን ወደ ፈጣሪያችን እናመልከት:: በልባዊ ይቅርታ መተማመንን፣ ዕርቅንና ሰላምን እንፍጠር:: ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን:: አሜን::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ምሕረት እና ይቅር ባይነት

/ኃይለ ሚካኤል ዘማርያም/

የዕብራይስጡ ራሐምና የግሪኩ ኤሌኦስ ምሕረት የሚለውን የአማርኛ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አገላለጽ «ምሕረት» ማለት «አንድን ሰው ይቅር ማለት ወይም በችግሩ ጊዜ መርዳት» ማለት ነው፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም «ምሕረት የሚለው ቃል ሣህል የሚለው የግእዝ ቃል ነው ካሉ በኋላ ትርጉሙንም «ቀጥታ፣ ልዝብታ፣ ሐዘኔታ፣ ርኅራኄ፣ ይቅርታ፣ ዕርቅ፣ ፍቅር ነው» ብለውታል፡፡ ሁሉም ወገኖች ግን በአንድ ነገር ይስማማሉ፤ አንድን በደል የፈጸመ ሰው አቅም በፈቀደ መጠን መበቀልና ብድራትን መክፈል እየቻሉ በይቅርታ ማለፍና በርኅራኄ መተው ምሕረት እንደ ሆነ፡፡

## 1. እግዚአብሔር መሐሪ ነው

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምሕረት የባሕርይ ገንዘቡ ነው፡፡ ሰዎች ቢምሩ ወይም ይቅር ቢሉ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ይቅርታ የማድረግ ጸጋ /ችሎታ/ ተጠቅመው ነው፡፡ ይህ ጸጋ ለሁላችንም ተሰጥቶ ሳለ እንኳን የበደሉንን ይቅር ባለማለታችን የምንኩራራ አለን፡፡ የተቀበሉትን አለማቀበል ምንኛ ሞኝነት ነው! አምላካችን ግን ቢምርም ቢቀጣም በሥልጣኑ የሚገባ የለም፡፡ ነገር ግን «ኮናኔ በርዕት ፈታሒ በጽድቅ» ነው፡፡ ፍጹም መሐሪ ነውና በእውነት ይምራል፥ ይቅርም ይላል፡፡ ሰዎች መሐሪነቱን ያውቁ ዘንድ አስቀድሞ «ስምየሰ መሐሪ ወመስተሣህል፤ ስሜ መሐሪና ይቅር ባይ ነው» ሲል ዐውጇል፡፡ ዘጸ.34÷6፡፡ ንጉሥ ዳዊትም «አቤቱ÷ አንተ መሐሪና ይቅር ባይ ነህ» ሲል አመስግኖታል፡፡ መዝ.86÷5፡፡

## 2. እግዚአብሔር ምሕረትን /ይቅርታን/ ይወዳል

ምሕረት የባሕርይ ሀብቱ የሆነ ልዑል እግዚአብሔር ምሕረትን ይወዳል፡፡ በእርሱ ፊት መልካም ከሆኑ ነገሮች መካከል ምሕረት ማድረግ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ አንዳንዶቻችን በተትረፈረፈ መሥዋዕታችን ልመናችን የሚሰማልን፣ ፈቃዳችን የሚፈጸምልን ይመስለናል፡፡ ይሁን እንጂ ተታለናል፡፡ ሕያው አምላካችን ከመሥዋዕታችን ይልቅ ይቅርታችንን ይወዳል፤ «መሥዋዕትን አይደለም ምሕረትን እወዳለሁ፡፡» ብሏልና፡፡ ማቴ.9÷13፡፡

## 3. እግዚአብሔር ስንት ጊዜ ይቅር ይላል?

አምላካችን ይቅርታው ብዙ ነው፡፡ ለቁጥር በሚያታክቱ አጋጣሚዎች በኃጢአት ስንወድቅ ኖረናል፡፡ ዕለት ዕለትም በብዙ ነገር እንስታለን፡፡ እርሱ ግን በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ በየትኛውም ኃጢአት ለወደቅነው ይቅርታውን አይነፍገንም፡፡ ንጉሥ ዳዊት ይህን ስላወቀ «አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ» ሲል ጠይቆታል፡፡ መዝ.50/51/ ፥1፡፡ በዚህ ምሕረት ከተጠሩት መካከል ቅዱስ ጳውሎስ አንዱ ነበር፡፡ እናም እንዲህ አለ፦ «ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለ ሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፡፡» ኤፌ.2 ፥4-5፡፡ ባለ ብዙ ምሕረት የሆነ ቸሩ እግዚአብሔር እኛን ይቅር ለማለት የቁጥር ወሰን አላበጀም፡፡ «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና ይነሣማል፡፡» ምሳ. 24 ፥16፡፡

## 4. በምሕረቱ እንጠቀም ዘንድ አምላካችን ጠርቶናል

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መሐሪነት በተረዳ ነገር አናውቅም፡፡ ብናውቅ እንኳን መፍቀሬ ምሕረት /ምሕረትን የሚወድ/ መኾኑን አልተረዳንም፡፡ ይህን ብንገነዘብ እንኳን በምሕረቱ ባለጠጋ መሆኑን ስለ ምንዘነጋ ለኃጢአታችን ይቅርታ የምንጠይቀው ጥቂት ጊዜ ነው፡፡ በሌላ ፈተና ስንሰናከል ግን «አሁንስ ይቅር አይለንም» ብለን እንሸሸዋለን፡፡ የሚበቀለንም እየመሰለን እንደ ቂመኛ አምላክ እንቆጥረዋለን፡፡ እርሱ ግን «መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፥ ኃጢአትህንም አላስብም፡፡ አሳስበኝ፥ በአንድነትም ሆነን እንፋረድ፤ እንድትጸድቅ ነገርህን ተናገር፡፡» ይላል፡፡ ኢሳ.43 ፥25-27፡፡ እኛ ኃጢአታችንን አምነን እንናዘዝ እንጂ እርሱ ይቅር ይለናል፡፡ ተመለሱ ካለን የኃጢአት መንገድ መመለስ ብቻ ነው የኛ ድርሻ፡፡ ከዚያም መናዘዝ፡፡ «እኔንም የበደሉኝን፣ ያመፁብኝንም ኃጢአታቸውን ሁሉ ይቅር እላለሁ» የሚል ኪዳን ተሰጥቶናልና፡፡ ኤር.33 ፥8፡፡ ይህን አምላካዊ ግብዣ በማክበር አባታችን አዳም፣ ቅዱስ ዳዊት፣ ንጉሥ ሕዝቅያስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ባለሽቱዋ ማርያም በኃጢአታቸው ተጸጽተውና ተናዘው ምሕረትን አግኝተዋል፡፡ ለአብነት እነዚህን ጠቀስን እንጂ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ያገኘን ብዙዎች ነን፡፡ እስኪ ርቀን የቆምን ወደ እርሱ ቀርበን ይቅርታውንና ቸርነቱን እንቅመስ፤ «ጣእሙ ወታእምሩ ከመ ሔር እግዚአብሔር፤ እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ ቅመሱ፣ እዩም» እንዳለ፡፡ መዝ.33/34/ ፥8፡፡

## 5. ምሕረትና ሰዎች

የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ እርስ በእርሱ ሲካሰስና ሲጣላ ኖሯል፡፡ በመሆኑም ሙሉ ታሪኩ ከክርክር፣ ከጥል፣ ከመቃቃርና ከመከፋፋት ጸድቶ አያውቅም፡፡ ይህ ክፉ ድርጊቱም የሚኖርባትን ምድር መዓዛ አገልምቶታል፡፡ መቃረኑና መጠላላቱ ወደ ከፋ ደረጃ ደርሶ ሕይወታቸውን እንዳያበላሽ ሰዎች የይቅርታ ሰው እንዲሆኑ ታዘዙ፡፡ የበደሉንን እንድንምር ሁላችንም ከሰማይ አባት ተነገረን፡፡ ታራቂነትም ላይኛ ዪቱ ሕግ ሆና ተሰጠችን፡፡ «ላይኛ ዪቱ ሕግ ግን ታራቂና እሺ ባይ ናት» እንዲል፡፡ ያዕ.3 ፥17፡፡ ጥንቱኑ ስንፈጠር የበደሉንን ሁሉ ይቅር ማለት የሚያስችል የእግዚአብሔር ጸጋ ለሁላችንም ተሰጥቶናል፡፡ በቂም፣ በኩርፊያ፣ በበቀል መጋረጃ የጋረድነውን ልባችንን በይቅር ባይነት ገለጥ ብናደርገው የልባችንን ገጸ ምሕረት እናገኘዋለን፡፡ ይህን የሰጠን አምላክ በአልኾኝነትና በቸልተኝነት ያዳፈነውን ጸጋ እንጠቀምበት ዘንድ ስለሚፈልግ፦ «ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፡፡» አለን፡፡ ቆላ.3 ፥12፡፡

## 6. ማንን ይቅር እንበል?

6.1 ***ራሳችንን፦*** ከሌሎች ጋር ከምንፈጽመው ጥልና ክርክር ይልቅ ከራሳችን ጋር የምንቃረንባቸውና የምንጣላባቸው ጊዜዎች ይበዛሉ፡፡ ይህን ከራስ ጋር የሆነ ጥል ከእኛና ከእግዚአብሔር ውጭ ሰዎች ላያውቁብን ይችላሉ፡፡ ለጠነሰስነው ክፉ ሐሳብ፣ ለተናገርነው ልብ ሰባሪ ንግግርና ለፈጸምነው በደል ራሳችንን ወቅሰን ይቅር ማለት ካልቻልን ሕይወታችን መራራና ሰላም የለሽ ይሆንብናል፡፡ በዚህ ምክንያት ዘወትር ራሳችንን ወቃሾችና የሌሎችን ሰላም አዋኪዎች እንሆናለን፡፡ ብሶትን አምቆ ለብቻ በማብሰልሰል መኖር የዚህ ችግር ሰለባዎች ያደርገናል፡፡ ራሳቸውን ከሚያጠፉ ሰዎች መካከል ከፊሎቹ ራሳቸውን ይቅር ማለት ያልቻሉ ናቸው፡፡ ይቅርታ ግን ከራስ ይጀምራል፡፡ ራሳችንን ይቅር ማለት ካልቻልን ሌሎችን ይቅር ለማለት አንችልም፡፡ ስለዚህ በመጀ መሪያ ራሳችንን በምሕረት መጎናጸፊያ እናስጊጥ፤ ***«ምሕረትን ልበሱ»*** ተብለ ናልና፡፡ ቆላ.3 ፥12፡፡ ***«ምሕረትን መልበስ»***፡- ይቅርታን ማድረግ፣ በቸርነት፣ በትሑት ልብ፣ በየውሃት፣ በትዕግሥት መመላለስ ነው፡፡ 1ጴጥ.2 ÷9፤ ኤፌ. 4 ፥2፡፡

6.2 ***የትዳር ጓደኞቻችንን፦*** በጋብቻ ውስጥ ግጭት ሊፈጠር አይችልም አይባልም፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ከትዳር ጓደኞቻችን ጋር ልንቃረን እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ በኩርፊያና በቂም የተሞላ ጎጆ ሥቃይ ከበዛበት ወሕኒ ስለ



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ማይሻል ምንጊዜም ለይቅርታ መዘጋጀት ይመረጣል፡፡ ባልና ሚስት ይቅር ባለመባባላቸው የተነሣ ስንት ጎጆ ፈርሷል፡፡ የተበተኑትን ልጆችና በዚህም ሳቢያ የሚደርሰውን ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ቤት ይቁጠረው፡፡ ለምን እንደ ዚህ ሆነ? የምሕረትና የይቅርታ አቅዋም በእጅጉ የሚያስፈልጋቸው ባለ ትዳሮች አካላቸው በእልኸኝነት እየተንቀጠቀጠ፣ እንደበታቸው የበቀልን እሳት ስለሚተፋ ነው፡፡

እስኪ የመጀመሪያዎቹን ባለ ትዳሮች አዳምንና ሔዋንን መለስ ብለን እንመልከት፡፡ አዳም ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ ዕፀ በለስን እንደ በላ ብናምንም ለመብላቱና ለሞቱ ምክንያት የሆነችው ግን እናታችን ሔዋን ናት፡፡ «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ፡፡» ዘፍ.3፥12፡፡ አዳም ግን ለውርደቱና ለሞቱ ምክንያት የሆነችኝ ሔዋን ባለቤቴ ናት ብሎ ይቅር ሳይላት አልቀረም፡፡ በፍጹም ይቅርታ ይቅር ብሏታል፡፡ በርግጥ እርስዋን ተቆጥቶ ሰዶ ሰዐት ጠብቆ ጸሎት ሊያደርግ ቢል እርስዋን አጓዶ ይዞ ታርቆ ካላመጣት በቀር ልመናው ቅቡል እንደ ማይሆን በመልአኩ ተነግሮት ይህንኑ ፈጽሟል፡፡ በዚህ ይቅርታ ላይ በተመሠረተው አንድነታቸው ላይ ስለ ቀደመ በደሉ ባፈሰሰው መሪር እንባና በተገባለት ቃል ኪዳን የተወለደው ጌታ ነው ኋላ ቤዛ የኾናቸው፡፡

የትዳር ጓደኞቻችን የሚያስከፋ ንግግር ሊናገሩን ይችላሉ፡፡ ከነበርንበት የክብር ወንበር ወርደን ለመንኮታኮታችንም ምክንያቶች የሚሆኑበት ጊዜ አለ፡፡ ለትዳር ጓደኞቻቸው መታመምና መሞት ብቸኛ ተጠያቂ የሚሆኑ ባለትዳሮችም አይታጡም፡፡ ይሁን እንጂ ከጥል ወደ ፍቅር፣ ከውርደት ወደ ክብር፣ ከሕመም ወደ ፈውስ፣ ከሞትም ወደ ሕይወት መሸጋገር የሚቻለው በይቅርታ ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ይቅር በመባባላቸው ጥላቸው በፍቅር፣ ውርደታቸውም በክብር፣ ሞታቸውም በሕይወት ተለውጧል፡፡

ባለትዳሮች የሆን ሁሉ ይህን ልንከተል ይገባል፡፡ በንግግር ያስቀየሙንንና በተግባር የበደሉንን የትዳር ጓደኞቻችንን ይቅር እንበላቸው እንጂ መራራ አንሁንባቸው፡፡ አምላካችን «መራርነት ከእናንተ ዘንድ ይወገድ» ይለናል፡፡ ኤፌ.4፥31፡፡

6.3 ***ልጆቻችንን፡-*** ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች፣ የባልና ሚስትን አንድነት የሚያጠብቁ ማሰሪያዎች፣ ትዳርን የሚያጣፍጡ ቅመሞች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለአካለ መጠን እየደረሱ በሚሔዱበት ጊዜ ወላጆቻቸውን ከማስደሰት ይልቅ የሚያሳዝኑ፣ ከመርዳት ይልቅ የሚመዘብሩ ልጆች አይታጡም፡፡ ይህም ከሚችሉት በላይ ኾኖ ልጆችና ወላጆችን እስከ መቃቃር አድርሶ ይሆናል፡፡ ወላጆችም ልጆቻቸው የተናገሯቸውን ክፉ ቃልና በደላቸውን በማስታወስ ከልጆቻቸው ጋር ሊወዛገቡ ይችላሉ፡፡ በተለይ በክርስቲያናዊ ቤተሰቦች

ይቅርታ ግን ከራስ ይጀምራል፡፡ ራሳችንን ይቅር ማለት ካልቻልን ሌሎችን ይቅር ለማለት አንችልም፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ራሳችንን በምሕረት መጎናጸፊያ እናስጊጥ፣ ***«ምሕረትን ልበሱ»*** ተብለናል፡፡ /ቆላ.3፥12/

ውስጥ ይህ ችግር ሥር ሰዶ መታየቱ ያሳዝናል፡፡ በልጆቻችን የተበደልን የዛሬ ወላጆች ብቻ አይደለንም፡፡ የቀደሙት ወላጆችም ተበድለው ነበር፡፡ ነገር ግን ይቅር ብለዋል፡፡

የዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አባት የሆነው ያዕቆብ ወጣት ሳለ በብልሃት የወንድሙን ምርቃት ወስዷል፡፡ አባታችን ይሥሐቅ ይህን ካወቀ በኋላ ግን በያዕቆብ ላይ አላቄመም፡፡ በይቅርታ አለፈው እንጂ፡፡ ዘፍ.27፥1-40፡፡ ልጆቻችን ስላታለሉን ይቅር ሳንላቸው የተቀመጥን ሁሉ አባታችን ይሥሐቅን አብነት እናድርግ፡፡ በሉቃስ ወንጌል 15፥11-13 ታሪኩ የተጠቀሰለት አባካኝ ልጅም የአባቱን ይቅርታ አግኝቷል፡፡

የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነት ለማሳየት በምሳሌነት በተጠቀሰው በዚህ ታሪክ ውስጥ አባትየው ልጁ ያባከነውን ገንዘብ ሳያስብ ይቅር ማለቱን እንመለከታለን፡፡ ይልቁንም ኀልቶ የወጣው ልጁ ከጠፋበት መገኘቱ፣ ከኮበለለበት መመለሱ ነው፡፡ ዛሬ በብዙ ቤተሰብ ውስጥ አባካኝ ልጆች ለወላጆቻቸው ሐዘን ሆነዋል፡፡ ወላጆችም እነዚህ ልጆቻቸው ያባከኑትን ሀብት በኀሊናቸው በማመላለስ ልጆቻቸውን ከልብ ይቅር ማለት ስላልቻሉ የቤተሰብ ሰላም ይደፈርሳል፡፡ የልጆች ሕይወትም ለበለጠ ችግር ተጋልጧል፡፡ በወላጆችና በልጆች መካከል ባለው አለመግባባት የቤተሰቡ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ሕይወት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ ወላጆች ለይቅርታ መዘጋጀት አለብን፡፡ የልጆቻችንን አበሳ በይቅርታ አልፈን ሕይወታቸውን፣ አስተሳሰባቸውን በአዲስ መልኩ ለማነፅ መሥዋዕትነት መክፈል ይጠበቅብናል፡፡ አባታችን እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዳለ እኛም ልጆቻችንን ይቅር እንበላቸው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፡- «እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡» ኤፌ.4፥32፡፡

6.4 ***ወላጆቻችንን፡-*** ልጆች ሁል ጊዜ ከወላጆቻቸው መልካም ነገር ስለ ሚጠብቁ መራራ ንግግር ሲናገሯቸውና ሲያስቆጧቸው አብልጠው ይጎዳሉ፡፡ በራሳችን ሲደርስ ጥዝጣዜውን ዐውቅነው እንጂ ወላጆቻችንም ከእኛ መልካም ነገር ጠብቀው በበደልናቸው ጊዜ የሚጎዱት በዚሁ መጠን ነው፡፡ ወላጆቻችን ሰው እንደ መሆናቸው ቢበድሉንም እኛን በብዙ አጋጣሚዎች ከስሕተታችን መልሰው ማስተማራቸውን በማሰብ ይቅር እንበላቸው፡፡

ዮናታን የተባለው የንጉሥ ሳኦል ልጅ ዳዊትን ከልቡ ከመውደዱ የተነሣ ሳኦል ዳዊትን ፈጽሞ ሊገድለው እንዳሰበ ለማወቅ ለዳዊት ፈቃድ ሰጥቶ አሰናብቶት ነበር፡፡ በንጉሡ ግብር ላይ ዳዊት አለመገኘቱን ያወቀው ሳኦል ልጁ ዮናታንን ዳዊት የት እንደ ሔደ ሲጠይቀው «መሥዋዕት ለመሠዋት ፈልጎ ፈቃድ ስለ ጠየቀኝ ፈቅጄለት ወደ ወንደሞቹ ሔዷል» ብሎታል፡፡ ዳዊት ከእርሱ እንዳመለጠ የተረዳው ሳኦል ልጁ ዮናታንን ሊገድል ጦሩን ወረወረበት፡፡ ነገር ግን በጋሻው መከቶም ቢሉ ስቶትም ቢሉ አልወጋውም፡፡ 1ሳሙ.20፥1-42፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን ሳኦል ከፍልስጤማውያን ጋር ፍልሚያ ጀመረ፡፡ አሁን ዮናታን አባቱ ያደረገበትን የግድያ ሙከራ አስቦ አባቱን የተቀየመ ይመስለናል፡፡ በፍጹም፡፡ ከዚህ ይልቅ ለአባቱ ይቅርታ አደረገለት፡፡ ከአባቱም ጎን ቆሞ ሲፋለም በጊልቦአ ተራራ ላይ ሞተ፡፡ 1ሳሙ.31፥1-3፡፡

የተለያየ በደል በወላጆቻችን ተፈጽሞብን ሊሆን ይችላል፡፡ በወላጆቻቸው አማካይነት ከትንሹ በደል እስከ ሞት የመከራ ጽዋ የቀመሱ ልጆች አይታጡም፡፡ ይቅርታ ማድረግ ግን መንፈሳዊ ግዴታችን ነው፡፡ ልቡ በፍቅርና በምሕረት የተሞላው ዮናታን ምሳሌያችን ሊሆን ይገባል፡፡ ዛሬ ወላጆቻችን በድለውናል ብለን ብናቄምባቸውም ራሳችንን በተለያዩ ነገሮች ከማበላሸታችን በፊት ለነበረን አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊና መንፈሳዊ ግንባታ ብዙ ችግሮችን ያዩብን መኾናቸውንም አንዘንጋ፡፡ ትላንት የተበደልነው በደል አልፏል፡፡ ነገን ለምን በታመመ ልብ እንቀበለዋለን፡፡ ሞልቶላቸው የተድላና ደስታ ኑሮ የሚመሩትን ወላጆችና ልጆች ፍቅርስ በማየት ለምን ራሳችንን እንደ ዕድለ ቢስ እንቆጥራለን፡፡ ዛሬውኑ ታሪካችንን መለወጥ እንችላለን፡፡ በይቅርታ ስሜት አዲስ የሕይወት ምዕራፍ እንክፈት፤ አባትና እናትን ማክበር ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ በደላቸውን ይቅር ማለት ነውና፡፡

6.5 ***ተቀናቃኞቻችንን፡-*** በዚህ ጽሑፍ ተቀናቃኞች ስንል ከባላንጣዎች ይለያሉ፡፡ ባላንጣዎች ከኛ ጋር በሐሳብ ቢለዩም ባይለዩም የፍጻሜ ሐሳባቸው ለጥፋት ነው፡፡ ተቀናቃኞች ግን በክፊልም ሆነ በምልዓት ከኛ ሐሳብ ጋር ሊቃረኑ ይችላሉ፡፡ ተቃርኖአቸው ግን ለመልካም ነገር ነው፡፡

የፖለቲካ ቡድኖች በፕሮግራም፣ በፖሊሲና በአፈጻጸም ብቃት፤ ተማሪዎች በአካዳሚያዊ ውጤት፣ ነጋዴዎች በትርፍ፣ አርሶ አደሮች በምርታማነት፣



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዳሯ እሳት መሐሏ ገነት

ቤተ ክርስቲያን በእምነት አንዲት ተብላ ብትጠራም እንደ ሕዝቡ ብዛት እንደ ሀገሩ ስፋት ለጸሎት፣ ለመሥዋዕት በጠቅላላው ለሥርዐተ አምልኮ መፈጸሚያ እንዲሆኑ የተተከሉ ቅዱሳት መካናት፣ አብያተ ክርስቲያናት /ቤተ መቅደሶች/ ይባላሉ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት የሚመሩና የሚሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ገዳም፥ ደብር፥ ገጠር በሚባሉ ሦስት ታላላቅ ሥራቶች ይከፈላሉ።...

ቤተ ክርስቲያን የሚደበረው ሰፊ ታሪክ ያለው ከሆነ ወይም በሕዝቡ ፍላጎት፡ በቀድሞው ዘመን ደግሞ በንጉሥ ትእዛዝ ነበር። በሚደበርበት ጊዜ ሁለት ዐይነት አፈጻጸም ያለው ሲሆን አንደኛው ንጉሡ ከቦታው ላይ ደርሶ የመንግሥት ልብሱን ከለበሰ በኋላ እምቢልታ እያስነፋ፣ ነጋሪት እያስጎሰመ የሚደበረውን ቤተ ክርስቲያን በመዞር፦ «ይህ ቦታ ዳሩ እሳት መሐሉ ገነት ይሁን፡ ከዛሬ በኋላ ማንኛውም አገረ ገዥ የዚህን ደብር ክብር እንዳይገስና በአሉን እንዳይቀማ በጳጳሱ አንደበት ይወገዝ!» ሲል ጳጳሱም «ይህ የንጉሡ ቃል እንዲጸና በጴጥሮስ በጳውሎስ ሥልጣን አውግዘናል» ብሎ ንጉሡ የተናገረውን ኃይለ ቃል ሁሉ በውግዘት ያጸናዋል። «በስሕተት ለገደለ መማፀኛ ይሁን» ብሎ ንጉሡ ሲናገር ጳጳሱም መርቆ ያሳርጋል።

አንድ ቤተ ክርስቲያን ከተደበረ በኋላ ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን አስተዳደር የሚመራው አለቃው ነው። ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን በክልሉ ውስጥ የማዘዝ ሥልጣን የለውም። ... በዚህም የተነሣ በአንድ የደብር ክልል ውስጥ ወታደር እንዲገባ አይፈቀድለትም። ... በሌላም በኩል አንድ ሰው በስሕተት ሰው በመግደል ሸሽቶ ከደብሩ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ገብቶ ከደወለ /ከተማፀነ/ ገዳይን በመያዝ ነገሩ ተጣርቶ ለመንግሥት ከቀረበ በኋላ የደብሩ ካህናት የሟችን ቤተሰብ መስቀል ይዘው በመለመን ገዳይን ከሟች ቤተሰብ ጋር በገደብ ካስታረቁ በኋላ ስለ ወንጀሉ መንግሥትን ለምነው በይቅርታ እስረኛውን ያስፈቱ ነበር።

*ምንጭ፦ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል /ብላቴን ጌታ/፣*
*ዝክረ ነገር፣ 1962 ዓ.ም።*

ሹሞቹ በአስተዳደርና ወታደሮች በጀግንነት፣ ... ይፎካከራሉ፤ ይቀናቀናሉ።

ራስንና ወገንን ወደ ተሻለ ሕይወት ለማድረስ በሚደረገው መተጋገል ውስጥ ጤናማ ማኅበራዊ ግንኙነታችን የማይጎዳበት ሁኔታ እንዲኖር ያስፈልጋል። በጤናማ ልዩነት በመፋጨት መቻቻልና ከሰላማዊው የሐሳብ መፋጨት በሚወጣው ብርሃን አገርን መገንባት ቀርቶ መካረር፣ ክፉኛ መቀናናትና ለመጠፋፋት መሯሯጥ ተገቢ አይደለም። ከእኛ በተሻለ በብቃታቸው ለሚበልጡን መንገድ መዘጋትም ምቀኝነት ብቻ ሳይሆን የተሻለውን ነገር ላለመቀበል ማመፅ ነው።

ንጉሥ ዳዊት በእስራኤል ላይ በነገሠበት ዘመን ከነበረው አስተዳደር የተሻለውን ሊያመጣ እንደ ሚችል ይናገር የነበረው አቤሴሎም የሕዝቡን ልብ ሰረቀ፤ ሕዝብ የተሻለ አስተዳደር ይፈልጋልና። ይህን ያወቀው አቤሴሎም ጥርጊያ መንገዱን ማስተካከል ያዘ። ንጉሥ ዳዊት የእስራኤላውያን ልብ ወደ አቤሴሎም እንደ ሸፈተ ሲያውቅ ቤተ መንግሥቱን ለቆ ሸሸ። በነበረው ብቁ ጦር ታግዞ አቤሴሎምን ማስወገድ ይችል ነበር። መተላለቁን አልወደደምና ከመጠፋፋት ዘወር አለ። 2ሳሙ.15፥1-37፤ 2ሳሙ.18፥14።

እንደ አኪጦፌል ባሉ ክፉ ባልንጀሮች ይመከር የነበረው አቤሴሎም ግን ነውረኝነቱ ሳያንሰው ኀራ ለኀራ የሚንከራተተውን አባቱን ሊወጋ ጦር አሰለፈ። ዳዊትም ለመከላከል ውጊያ ራሱን አዘጋጀ። ወደ ፍልሚያ ለተመመው ሠራዊቱ ያስተላለፈው መልእክት ግን ለተቀናቃኙ አቤሴሎም የሰጠውን ምሕረት ከማገባረቁም በላይ የብዙዎቻችንን ልብ በሐዘን የሚነካ ነው፦ «ለብላቴናው አቤሴሎም ስለ እኔ ራሩለት።» 2ሳሙ.18፥5 እና 33። ውጊያው ተፋፍሞ እልቂት ኾነ፤ 20,000 ያህል ሰዎችም ሞቱ። አቤሴሎምም በፍልሚያው ላይ በጦር ተወግቶ ሞተ። ቅዱስ ዳዊት ባለሚሎቹ በተቀናቃኙ አቤሴሎም ላይ ካገኙት ድል ይልቅ በአቤሴሎም ሞት በእጅጉ አዝኗል። «ልጄ አቤሴሎም ሆይ፥ ልጄ፥ ልጄ አቤሴሎም ሆይ፥ በአንተ ፋንታ ሞቼ ኖሮ ቢሆን፥ ልጄ አቤሴሎም፥ ልጄ ሆይ» እያለ በታላቅ ድምፅ ጮኾ አልቅሶለታል። ሕዝቡም የድሉን ብሥራት በሰማበት ቀን «ንጉሡ ስለ ልጁ አዘነ» /1ሳሙ.19፥2/ ሲባል ስሜቱ ወደ ሐዘን ተለውጧል። የዳዊት ይቅርታና ምሕረት ግን ከሞቱ የቀደመ ነው።

በሥራ አፈጻጸም ብቃትና ውጤት፣ በትርፍ፣ በአገልግሎት፣ በዕውቀትና በአስተዳደር ብቃት የሚቀናቀኑንን ሰዎች በክፉ ለመተቸትና ለማጥፋት እንሩጥ። አባታችን ዳዊት ግን ከትክክለኛው የመቀናቀን መንፈስ አፈንግጦ ወደ ጠላትነት የተቀየረውን አቤሴሎንም ምሯል። እኛም ይህን ወደ መሰለው ተግባር ልናዘነብል ይገባል። አለበለዚያ ምሕረት ባላደረግንበት መጠን ጨካኝ እሳት ያቃጥለናል። «አንተም ጨካኝ ነበርከ ጨካኝ አዘዘብህ፤ እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ» እንደ ተባለለት።

6.6 ***መሪዎቻችንን፦*** በየትኛውም ወቅት የሚነሡ መሪዎች ከመሪነታቸውና ከሕዝብ አባትነታቸው ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ የጭካኔና የማን አለብኝነት ተግባር በሕዝባቸው ላይ ሊፈጽሙ ይችላሉ። እነኝህን መሪዎች የሥልጣን ሰይፍ ያስታጠቃቸው እግዚአብሔር ነው። ይህ የሥልጣን ሰይፍ አፎቱ ሁለት ወገን ነው። ባለሥልጣናቱ ዛሬ በሚፈጽሙት በጎም ይሁን ክፉ ተግባር በጊዜው መልስ ይሰጡበታል። ሕዝቡ ግን እንደዚህ የመሰሰሉትን መሪዎች አስመልክቶ የሚበጀውን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ለማግኘት በፍጹም የይቅርታ ስሜት አምላኩን መማፀን ይኖርበታል።

ለግድያ ጭምር ያሳደዷቸውን መሪዎች በሚያስደንቅ ምሕረት ይቅር ካሉ ሰዎች መካከል ቅዱስ ዳዊት ደማቅ ታሪክ ያለው ሰው ነው። ንጉሥ ሳኦል በዳዊት ላይ ያልፈጸመው በደል የለም። ሊገድለው ጦር ወርውሮበታል። እጮኛው ሜሮብን ለሌላ ሰው መዳሩ ሳያንስ ሚስቱ ሜልኮልን ለጋሊምማዊው ፊልጢ ሰጥቶበታል። 1ሳሙ.25፥44 ። በረኀብ፣ በጥም፣ በእርዛት፣ በመጠለያ እጦትና በስደት እንዲጠበስ አድርጎታል። ቁጥሩ በርካታ የሆነ ጦር ይዞ አሳዶታል።

የዳዊት መልስ ግን ጸሎትና ይቅርታ ነበር። ሳኦል ከአንድም ሁለት ጊዜ በዳዊት እጅ ወድቆ ሳለ በምሕረት አልፎታል። 1ሳሙ.24፥1-22፤ 1ሳሙ.26፥6-25። ዳዊት ሳኦልን ለመበቀል ባያስብ እንኳን የጦር አለቆቹ ይገድለው ዘንድ ሞግተውት ነበር። እግዚአብሔር እንደ ልቤ ያለለት የይቅርታ ማኅደር ዳዊት ግን እጁን እግዚአብሔር በቀባው ንጉሥ ላይ አላነሣም፤ ለሁላችንም በሚያስደቅ መልኩ በይቅርታ ተወው እንጂ። እግዚአብሔር የተበቃዮችን ክንድ ሳይሆን የመሐሪዎችን ድካም ይደግፋልና የሳኦልን ግፍ ቆጥሮ ጣለው። ከሳኦል ፍጻሜ ይልቅ የዳዊት መጨረሻ እንዴት ያማረ ነው!

ክርስቲያን አብነት የሌለው ሕዝብ አይደለም። ንጉሥ ዳዊትን የመሳሰሉ የይቅርታ ሰዎች ምሳሌዎቻችን ሊሆኑ ይገባል። መሪዎች በፈጸሙብን ግፍና በደል ልባችን የጠቆረ ሁሉ ልባችንን በምሕረት አጥበን ልንገኝ ግድ አለብን። እነርሱን ይቅር ማለታችን ለነገው መልካምና ፍጻሜው ያማረ ሕይወት ተቀዳሚ ነገር ነው፤ ተበድለው ሳለ በይቅርታ ለሚያልፉ ተበዳዮች እግዚአብሔር ብድራትን ይከፍላልና።

6.7 ***ሕዝባችንን፦*** የዓለማችን ውበት የጠወለገው የሕዝብ መሪዎች ለተሾሙለት ሕዝብ ፍትሕን፣ ነጻነትን፣ ቸርነትን፣ ምሕረትን ማድረግ ባለመቻላቸው ነው። አምባገነን መሪዎች ሕዝብ በመልካም ሲቃወማቸው ለቅጣት፣ ለብቀላና ለጥፋት ይፋጠናሉ። ይህን በነፈርዖንና በነሳኦል ሕይወት ማየት እንችላለን።

ከሕዝባቸው ጋር ያለውን መቃቃርና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ጥል ልባዊ በኾነ የመቀራረብና የመተማመን መንፈስ፣ በይቅርታ ከፈቱ ግን በሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን በምሕ





© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ረት ላይ የነገሡ ተብለው ይወደሳሉ::

ይህ ደግሞ ተደርጎ የማያውቅ አዲስ ተግባር አይደለም:: ታሪክ መቀየሩ አይቀርምና ተሳዳጁ ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሠ:: ይህ የምሕረት ሰው ግን ለበቀል አልቆመም:: ትላንት ሲረግመው ከነበረው ሳሚ ወልደ ጌራ ጀምሮ እስከ አሳዳጁ የሳኦል ቤተሰብና የጦር አለቆች ድረስ ምሕረትና ይቅርታ አድርጓል:: 2ሳሙ.3፥12-21፤ 2ሳሙ.9፥1-13፤ 2ሳሙ. 19፥19-23:: ዛሬ ያሉ መሪዎች ሁሉ ይህን አሰረ ፍኖት መከተል አለባቸው:: ለሕዝባቸው ይቅርታ የሚያደርጉ መሪዎች ሁሉ ነገን በስጋት ሳይሆን በተስፋ ይጠብቁታል:: ጨክኖ ከመሳቀቅ ምሮ መታረቅ አይበጅምን?

6.8. ***አገርን፡-*** ክብር ይግባውና አምላካችን እግዚአብሔር አገርን ሳይቀር ይምራል:: በቅዱስ መጽሐፍ ብዙ ጊዜ «ኢየሩሳሌምን ምሬያለሁ» ሲል እንሰማዋለን:: የሰማይ መላእክትም፡- «ጌታ ሆይ፥ እነዚህን ሰባ ዓመት የተቈጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው?» እያሉ ስለ አገር ምሕረት ይማልዳሉ:: ዘካ.1፥12::

ከሌሎች አገሮች ጋር አገርን እያነጻጸሩ መኮነን ተገቢነት የለውም:: «አገሬ ይህን አላደረገችልኝምና ስለ አገሬ አይገደኝም» ብሎ አገርን ማኩረፍ አስፈላጊ አይደለም:: እያንዳንዱ ሰው ለሀገሩ የሚጠቅበትን ካደረገ በኋላ ነው ከአገሩ መጠበቅ ያለበት:: «አገሬ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን ምን አደረግኹላት በል» መባሉ ለዚህ ነው::

በመሆኑም ሕዝብና የሕዝብ መሪዎች ከሀገራቸው ጋር ልባዊ ዕርቅ መፍጠር አለባቸው:: ሰዎች በደሉን ማለት ሀገር በደለችን ማለት አይደለም:: ለሀገር ልባዊ ምሕረትና ይቅርታ ሳያደርጉ የሚደረግ ሩጫና ልቅሶ ፍሬ አልባ ነው:: ሀገሩን የማይምር ሁሉ የሀገሩ አጥፊ ነው:: ስለዚህ የአንድ ሀገር ልጆች በፍቅርና በሰላም ተባብረው ለሀገራቸው ምሕረትን ሊያደርጉ፣ መንፈሳቸውን ከፍ አድርገው፣ በልዩነታቸው ተቻችለው ለሀገራቸው ሰላም፣ ዕድገትና ብልጽግና መነሣት ይገባቸዋል::

## 7.ይቅር የምንለው ምንን ነው?

### 7.1 የተቀየምንበትን ሐሳብ /ንግግር/፡-

እንደበት እሳት ነው:: ዐመፀኛ ብልት ሆኖ የሰውን ልጆች እርስ በእርሳቸው ሲያፋጅ ኖሯል:: በተናገሩት ንግግር ልባችንን ያቆሰሉ ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: እኛ ግን ክፉ ንግግርን ይቅር ብሎ በማለፍ ምሕረታችንን ለነዚህ ሰዎች ልንሰጥ ያስፈልገናል:: «ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል» ተብሏልና:: ማቴ. 12፥41:: ስለዚህ ታማን፣ ተሰደብን፣ ተጻፈብን፣... ብለን ከወገኖቻችን ጋር የተቃረንን ሁሉ ይቅር መባባል አለብን::

### 7.2. ድርጊትን፡-

ሌሎች እኛን ካሳዘኑባቸው ነገሮች መካከል ክፉ ድርጊት አንዱ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ፡- ተደብድበን፣ ተዘርፈን፣ ታስረን፣ ተከድተን ልባችን ያዘነብን እንኖራለን:: በዚህ የተነሣ ተቃቅሮ በባላንጣነት እየተያዩ መኖር ግን አይጠቅመንም:: እኛ ይቅር እንበል:: ሌላው የአምላካችን ድርሻ ይሆናል::

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለገረፉት፣ለገፈፉትና ለሰቀሉት አይሁድ ይቅርታ አላደረገምን? «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው::» ሲል ይቅርታን ለምኖላቸዋል:: ሉቃ.23፥34::

ደካማ ሥጋችን ቢፈትነንም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በሐሳብ፣ በቃልና በድርጊት የበደሉንን ሰዎች ይቅር ለማለት መሮጥ አስፈላጊ ነው:: እንግዲህ «እኛም የበደለንን ይቅር እንድንል፤ በደላችንን አበሳችንን ይቅር በለን» የሚለውን ጸሎታችንን ተግባራዊ እናድርግ:: ማቴ.6፥12::

## 8. መቼ ይቅር እንበል ?

### 8.1 በጊዜው ፡-

*ይቅርታ ማድረግ አስፈላጊና መንፈሳዊ ግዴታችን ነው:: ከተለያዩ ወገኖች ጋር በየምክንያቱ የምንፈጥረውን መቃቃርና ግጭት የሚያባብሰው ጨርሰን ይቅር አለማለታችን ብቻ አይደለም:: ይቅር የምንልበትን ጊዜ አለማወቃችንም ጭምር ነው:: ይቅርታ የሁል ጊዜ ተግባር ነው:: ይበልጥ ደግሞ በጣም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሲፈጽሙት ማትረፊያ ይሆናል:: የቂም መወጫ ሁኔታዎችን ካመቻቸንና የብቀላ ጥማታችንን ካረካን በኋላ የምናደርገው ይቅርታ ፈርዖናዊ ይቅርታ ነውና ልባዊ አይኾንም፤ መተማመንንና እፎይታን አያጎናጽፈንም:: ስለዚህ ይቅርታችን ለራሳችን፣ ለቤተሰባችን፣ ለአገራችንና ለዓለማችን ወሳኝ የሆነበትን ወርቃማ ጊዜ ሳንጠቀምበት እንለፍ:: የምንገኝበት ጊዜ የምሕረትና የይቅርታ አቅዋም በእጅጉ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው:: ሁከትና ግርግር፣ ጦርነትና እልቂት እንዲያከትም ስሕተቶቻችንን በይቅርታ ማረም፣ አእምሯችንንና ልባችንን ከቂምና በቀል ማጽዳት ያሻናል:: ጠባችን የሐሳብ ልዩነት አይደለም:: አለመተማመንና መፈራራት ነው:: ጊዜ የለንምና ተጠብቆ በቆየን የአገራችን ዕርቅና ይቅርባይነት ባህል በመነጋገር ዛሬውኑ መንገድ ፈልገን እንተማመን:: ባለመተማመናችን ሳቢያ በውስጣችን በሚፈጠረው መንቃት /መስነጣጠቅ/ ገብቶ በሚቆራኘን ርኩስ መንፈስ ምክንያት በጠና ከመታመማችን በፊት እንዳን::*

### 8.2 ከመጸለያችን በፊት፡-

የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን በጸሎት አማካይነት እግዚአብሔርን ሳናነጋግር አንውልም:: አናድርም:: በጸሎት አማካይነት ካቀረብናቸው ጥያቄዎች ግን ስንቶቹ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሰው ምላሽ አግኝተንባቸዋል? ብዙዎቹ ወይም አንዳንዶቹን እስከ አሁን ምላሽ አላገኘንባቸው ይሆናል:: ችግሩ ምንድን ነው? በርግጥ እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ አለው:: ይሁንና በቂምና በጥል ከጠቆረ ልብ የሚሰሙትን ልመናዎች እግዚአብሔር ስለ ማይቀበላቸውም ጭምር ነው:: ስለዚህ ይቅርታ ዕለት ተዕለት ከሚከወነው ጸሎት በፊት ይደረግ መባሉ ለጸሎታችን ተሰሚነት የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ያመላክታል:: ጌታ ባስተማረን ጸሎት ላይ «እኛም የበደሉንን ይቅር እንደ ምንል በደላችንን ይቅር በለን» የሚለው ቃል መገኘቱ ይቅርታ ቅድመ ጸሎት የሚከወንና በጊዜ ጸሎትም ሊፈጽሙት የሚገባ መሆኑን ያጠይቃል:: ማቴ.6፥12::

### 8.3 መባችንን ለእግዚአብሔር ከማቅረባችን በፊት

ጧፍ፣ ዕጣን፣ ዘቢብ፣ መገበርያ ይዘን ወደ እግዚአብሔር መቅደስ መገሥገሣችን መልካም ነው:: የልኡካን መቀደሻ አልባሳት፣ መንጠላእትና ምንጣፎችን ለእግዚአብሔር ቤት መስጠታችን፣ በሌላም በኩል በሞያችን፣ በጉልበታችን ቤተ ክርስቲያንን ማገልገላችን ደጎና ነው::

ነገር ግን የተጣላናቸውንና ያቄምንባቸውን ሰዎች በደል ይቅር ሳንል የቱንም ያህል መሥዋዕት ይዘን በልዑል አምላክ ፊት ብንቀርብ የሚቀበለን አይሆንም:: «ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ» ያለው ጌታ ያመጣነውን መሥዋዕት ለእርሱ ከማቅረባችን በፊት ለሰዎች ይቅርታ እንድናደርግ ይሻል:: «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ::» ማቴ.5፥23-25::

## 9.እንዴት ይቅር እንበል?

### 9.1 እንዲሁ በደስታ፡-

ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከራሱና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታርቆ ምሕረትና ይቅርታ ያደረገለት እንዲሁ በጸጋው ነው:: «እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው:: ዮሐ.3፥16:: ከይቅርታ ሁሉ ትልቁ እንዲሁ በደስታ የምናደርገው ይቅርታ ነው:: እውነትን ይዘን ራሳችንን ስንመረምር በሐሳብ፣ በንግግርና በሥራ ብዙ ጊዜ ፈጣሪያችንን በድለናል:: ሳስታወስነው ኃጢአታችን ተጸጸትን እንጂ ብዙዎቹን ረስተናቸዋል:: እርሱ ግን እነዚያን ሁሉ ደመሰሰልን:: ለሠራነውም ኃጢአት እንዲሁ የሆነ ምሕረት ሰጠን:: እኛም እንዲሁ በብላሽ ያገኘነውን በከንቱ /በብላሽ/ እናድርግ:: በዳዮቻችን ይቅርታና ካሣ ይዘው ወደኛ እስኪ መጡ ለምን እንዘገያለን? እንዲሁ በደስታ እንማራቸው:: ያን ጊዜ በሥራቸው ይጸጸታሉ:: ቅዱስ ጳውሎስ እንደ መከረን በራሳቸው ላይ የእሳት ፍሕም እንሰበስባለን:: የሐዋ.12፥21:: የቤተ ልሔሙ ዳዊት ሳኦልን ሲምር እንዲሁ አልነበረምን!! የዳዊት ልጆች ነንና ያን ታሪክ እንድገም፤ «የሚምር በደስታ ይማር» ተብሎ ተጽፏልና:: ሮሜ.12፥8::

### 9.2 ይቅርታን በመቀበል፡-

ይህኛው የምሕረት መንገድ ደግሞ የበደለን ሰው በፈጸመብን ጥፋት ተጸጽቶ ይቅርታ ሲጠይቀን ይቅርታውን ተቀብለን ምሕረት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

**ከተበያዩ ወገኖች ጋር በየምክንያቱ የምንፈጥረውን መቃቃርና ግጭት የሚያባብሰው ዉርሰን ይቅር ስለማለታችን ብቻ ስይደለም:: ይቅር የምንልበትን ጊዜ ስለማወቃችንም ጭምር ነው:: ይቅርታ የሁል ጊዜ ተግባር ነው::**

የምና ደርግበት መንገድ ነው:: በባሕርዩ መሐሪና ሰውን ወዳጅ የኾነ ልዑል እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን እንድንጸጸትና ንስሐ ገብተን ይቅርታ እንድንጠይቀው ይሻል:: ለምሕረት የሚፋጠነውም ይህን ጊዜ ነው፤ «መተላለፍህን:- ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኀጢአትህንም አላስብም:: አሳስበኝ፥ በአንድነትም ሆነን እንፋረድ፤ እንድትጸድቅ ነገርህን ተናገር» ሲል የገባልን ቃል ይህን ያስረግጣል:: ኢሳ. 43፥25-27::

ከዘመናችን አሳዛኝ ክንውኖች አንዱ የበደሉንን ይቅርታ ለመጠየቅ አሻፈረኝ የማለታችንን ያህል የተበደልነውም ይቅርታ ስንጠየቅ ልባችንን ከአድማስ ደንጊያ ይልቅ አጽንተን አካላችን እየተንቀጠቀጠ፣ እንደበታችን የበቀልን እሳት እየተፋ እምቢ ማለታችን ነው:: ለመሆኑ ይቅርታ መጠየቅ መዋረድ ይመስለን ይሆን? ይቅርታ ማድረግስ ሞኝነት ነው? ይቅርታ የትሑታንና የአስተዋዮች መገለጫ ነው:: ይቅርታ አድራጊም ሆነ ጠያቂ ሰው የመቃቃርን አስከፊነት የተረዳና የመፈቃቀርን ብርሃን ያየ ከፍ ያለ የመንፈስ ልዕልናና ወኔ /higher moral ground/ ያለው ሙሉ ሰው ነው:: ስለዚህ ይቅርታ ስንጠየቅ ይቅር እንበል:: «ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፤ ቢጸጸትም ይቅር በለው::» ተብሏል:: ሉቃ.17፥3::

*9.3 በካሣ-* መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከዘለዓለም ባርነት ወደ ሚደነቅ ልጅነት፣ ከሞትም ወደ ሕይወት ያሸጋገረን ሥጋውን ቆርሶ፣ ደሙን አፍስሶ፣ ነፍሱን ክሦ ነው:: እርሱ ንጹሐ ባሕርይ ሆኖ ሳለ እንደ ኃጢአተኛ ሞቶ ስለ እኛ ራሱን ቀጣ:: ከዚህ በኋላ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጠብ ልዩነት ተወገደ፤ እርሱ ክሦ አድኖናልና::

አንዳንድ ጊዜ ለተበደሉ ሰዎች የሚሰጡ ካሣዎች በበዳይና በተበዳይ መካከል ያለውን ደም ሲያደርቁ ይስተዋላሉ:: ይህ ልምድ ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ ነበር:: ለምሳሌ:- «ሁለት ሰዎች ቢጣሉ አንዱም ሌላውን በድንጋይ ወይም በጡጫ ቢመታው ያም ባይሞት ነገር ግን ታሞ በአልጋው ላይ ቢተኛ ተነሥቶም በምርኩዝ ወደ ሜዳ ቢወጣ የመታው ንጹሕ ነው:: ነገር ግን ተግባሩን ስላስፈታው ገንዘብ ይክፍለው ዘንድ ያስፈውሰውም ዘንድ ግዴታ አለበት::» ይላል:: ዘጸ.21፥18-19:: ድንግል የሆነችውን ሴት አግብቶ ከክብር ካሳነሣት በኋላ ክብር አላገኘሁባትም በማለት ስም የሚያጠፋ ባልም ይክስ ዘንድ ታዟል:: ዘዳ.22፥13-19:: በአጭሩ በዘመነ ብሉይ ካሣ የተለመደ ነበር::

ዘመነ ሐዲስ የምሕረትና የይቅርታ ዘመን ነው:: ቢሆንም ተበዳዩ ፈጽሞ የማይመለስና የበዳዩም በደል በግፍ፣ በድፍረትና በማን አለብኝነት የተፈጸመ ከሆነ የሚጣልበትን ቅጣት ተቀጥቶ ከበደለው ሰው ጋር መታረቅ ግድ ሆኗል:: ካሣ ቁሳዊ ብቻ ሳይሆን በበደልናቸው ወገኖች ፊት ስለ በደላችን ማፈር፣ ስናለቅስ፣ ስንጸጸት፣ ስንቆጭ መታየትም ነው:: ይህም የይቅርታን ዋጋና ለይቅርታ ሲባል መከፈል ያለበትን ሁለንተናዊ መሥዋዕትነት ያመላክታል::

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያሳዘናቸውን አንድ ምእመን በጋራ ቀጥተውት ነበር:: ነገር ግን ከቀጡት በኋላ የከፈለውን ካሣና የተቀጣውን ቅጣት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይቅር ሊሉት ስላልቻሉ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መቀጣቱ ሲሉ ይቅር እንዲሉት አሳስቧቸዋል:: «እንደዚህ ላለ ሰው ይህ ከእናንተ የምትበዙት የቀጣችሁት ቅጣት ይበቃዋልና እንደዚህ ያለው ከልክ በሚበዛ ሐዘን እንዳይዋጥ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል:: ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ:: ስለዚህ ደግሞ ጽፌ ነበርና በሁሉ የምትታዘዙ እንደ ሆናችሁ የእናንተን መፈተን ዐውቅ ዘንድ አሳቤ ነበር:: እናንተ ግን ይቅር የምትሉትን እኔ ደግሞ ይቅር እለዋለሁ:: እኔም ይቅር ካልሁ ይቅር ያልሁትን ስለ እናንተ በክርስቶስ ፊት ይቅር ብዬአለሁ:: በሰይጣን እንዳንታለል የእርሱን አሳብ አንስተውምና::» 2ቆሮ.2፥6-11::

ሐዋርያው ይቅር አለማለትን ከሰይጣናዊ ሐሳብ ጋር እንዳነጻጸረው ልብ እንበል:: ሰይጣን የሰው ልጆችን ዕርቅና ፍቅር ስለ ማይፈልግ ይቅርታ እንዲጠየየቁ ወይም ሰላም እንዳይፈጥሩ ሁሌ ይተጋል:: በዳዮችን በማስታበይና ተበዳዮችንም ለእምቢታ በማስጨከን በይቅርታ ድልድይ ላይ ትልልቅ የማሰናከያ ዐለት እያኖረ ነው:: እኛ ግን ዕንወቅበት:: ልብን ከቂምና ከበቀል አለማጽዳት፣ ይቅርታ አለመጠየቅና ይቅር አለማለት ሰይጣናዊ ሐሳብ ነውና አንታለል:: ስለ በደላችን የተጣለብንን ቅጣት ካሣ ከፍለን ፍቅራችንን እናድስ:: በመታረቃችን የምናገኘው ትርፍ ዛሬ ከተቀጣነው ቅጣት ወይም ከከፈልነው ካሣ /ቁሳዊም ይሁን መንፈሳዊ/ ጋር ሲነጻጸር ምንም አይደለምና:: ተበዳዮችም የቅጣቱን /የካሣውን/ መብዛትና ማነስ ሳይሆን የበደለንን ሰው ይቅርታ እናደርግለት ዘንድ እስከ መጨከን ድረስ መታዘዙን በማስተዋል ይቅር እንበለው::

## 10.ስንት ጊዜ ይቅር እንበል?

በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ስንት ጊዜ ነው የማረን? ሁላችንም ቆጥረን ለማንዘልቃቸው ጊዜያት ምሕረትን ከፈጣሪያችን ተቀብለናል:: እርሱ ሐሳባችንን እንኳ ስለ ሚመረምር ሲምረን የተናገርነውንና የሠራነውን ብቻ ሳይሆን ያሰብነውንም ክፉ ሐሳብ ይቅር ይላል:: ሰዎች በሐሳባችን ያለውን ሐሜት፣ ምኞት፣ ጥላቻ፣ ትዕቢት፣ ስርቆት፣ ንቀት፣ መለያየት፣ አስመሳይነትና አመንዝራነት ቢያውቁ ኖሮ በየስክንዱ ሳንጣላ አንውልም ነበር:: ክብር ይግባውና ልዑል እግዚአብሔር ይህን አበሳ በእኛና በእርሱ መካከል ተሸፍኖ እንዲኖር አድርጓታል:: እናም ስንበድለው ዘወትር ይምረናል:: እኛስ ስንት ጊዜ ይቅር እንበል?

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ አንድ ቀን ጌታን «ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?» ብሎ ጠየቀው:: አሁን ለስምዖን ጴጥሮስ ሰባት ጊዜ ይቅር ማለት በጣም ብዙ መሆኑ ነው:: የምሕረት ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ምላሽ ምንኛ ደስ ይላል:: «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም::» ሉቃ.17፥3::

አሁን ጌታ የበደሏችሁን ለ490 /7»70= 490/ ጊዜ ብቻ ይቅር በሉ ሊል ፈልጎ አይደለም:: ይቅርታ ፍጹም ብዙና የሁል ጊዜ መሆኑን ሊነግረን ፈልጎ ነው:: ስንቶቻችን ነን የበደሉንን ሰዎች ለ490 ጊዜ እንኳ ይቅር ያልን? ማንም ሰው 490 ጊዜ አልበደለንም:: አንድ ጊዜ፥ ሁለት ጊዜ እጅግ በጣም ቢበዛም ከመቶ ጊዜ በላይ አልተበደልንም:: እኛ ግን አንዴም ይቅር ማለት ተስኖናል:: ከአንዴና ከሁለቴ በላይ እርም ያልንም አንጠፋም:: «ስንት ጊዜ ይቅር ብዬዋለሁ» በማለት የትላንት ይቅርታችንን የምንቆጥርም አለን:: ኧረ ጌታ ስንት ጊዜ ይቅር ብሎናል:: ትላንት ይቅር ያልኳችሁ ይበቃችኋል ቢል በዚህች የሰቆቃ ምድር ላይ ውሎ የሚያድር ሰው ይኖር ይሆንን? አይታሰብም:: ሁላችንም ኃጢአተኞች ከመሆናችን የተነሣ ዕለት ዕለት እያሳዘነው ነው:: እርሱ ግን ዘወትር ይቅር እያለ ዕድሜ ለንስሐ ዘመን ለፍሥሐ እየቸረ ያኖረናል:: ስለዚህ ለምሕረታችን ቁጥር ሳንወስን የበደሉንን ይቅር እንበል፤ በዳዮችም ባጠፉን ቁጥር ይቅርታ መጠየቅን አንተው::

## 11. የይቅርታ ጠላቶች

***11.1 ክፉ የማሸነፍ ስሜት /ለይቅርታ አለመሸነፍ/-*** ከሌሎች ጋር ይቅር ላለመባባላችን ትልቁ ምክንያት በዳዮቻችንን በክፉ ለማሸነፍ መውተርተራችን ነው:: በዘገየን ቁጥር ከይቅርታ መሸሻችንን አንዘንጋ:: ሁሌም አሸናፊ የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ግን ይህን አላስተማረንም:: እርሱ ራሱ በፍቅሩና በዘለዓለማዊ ይቅር ታውና ቸርነቱ ለሰቀሉት አይሁድ ምሕረትና ይቅርታን አድርጓል:: በክፉ ማሸነፍን ለሰዎች አልፈቀደም:: ማሸነፋችን ሁሉ በመልካም እንዲሆን ይወዳል:: ምሕረት ማድረግ ደግሞ በመልካም ማሸነፍ ነው::





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ይቅርታ የሚያደርጉ ሁሉ በክፉ ባለ ማሸነፋቸው በክፉ አይሸነፉም:: ስለዚህ ይቅርታ በማድረግ በክፉ የማሸነፍ ስሜታችንና ተነሣሽነታችንን እንግደል:: «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ::» ተብሎ ተጽፏልና:: ሮሜ. 12፥21::

*11.2 **እልከኛነት**:-* ለበጎ ነገር እልከኛ መሆን መልካም ነው:: ለአገልግሎት፣ ለንስሐ እልከኛ ሆነው ለፍጻሜ የሚተጉ እንዴት የታደሉ ናቸው:: ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ይወዳልና ለመልካም ነገር የሚቀኑ እልከኛ አድርጎ ፈጥሯቸዋል:: «የሚወደውንም እልከኛ ያደርገዋል» ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው:: ሮሜ.9፥18::

በሚያሳዝን መልኩ ብዙዎቻችን እልካችንን የምንገልጠው ላልተገባ ነገር ነው:: ኃጢአትን ለመሥራት፣ ላለመታረቅ እልከኞች መሆናችን ጀግንነት አይጠደለም:: ይህን ቁርጠኝነትና እልክ ከኃጢአት ለመሸሽ፣ ለዕርቅና፣ ለመልካም ነገር ብናውለው እንዴት መልካም ነበር! ይህን ባለማድረጋችን ግን ትጋታችን ሁሉ ከንቱ ሆኗል:: ምክንያቱም «እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው::» ስለ ተባለ:: 1ሳሙ.15፥23::

*11.3 **ቂመኛነት**:-* ቂመኛነትን የሚጠየፈው ልዑል እግዚአብሔር ሰዎች ቂመኛ እንዳይሆኑ «በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ» ሲል አዟቸዋል:: ዘሌ.19፥18:: ሰዎች ግን በየምክንያቱ ቂምን በልባቸው አቁማዳ በማዘል ይገኛሉ:: የሰውነታችን ማእከላዊ መዝገብ የሆነው ልባችን በቂም ጠጠር ስለ ተሞላ ይቅርታ ቦታ አጥቷል:: ተሸክመነው በምንዞረው ቂም የተነሣ ጸሎታችንም ፍሬያማ አልሆነልንም:: «ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት» እንዲሉ:: «ኤዶምያስ በይሁዳ ቤት ላይ... ቂም ይዞአልና እጄን በኤዶምያስ ላይ እዘረጋለሁ፤ ከእርስዋም ሰውንና እንስሳን አጠፋለሁ» የሚለው የአምላካችን ቃልም ቂመኛነታችን ለእኛና ከእኛ ጋር ላሉት /ለእንስሶቻችን ሳይቀር/ ጥፋት ምክንያት መሆኑን ይነግረናል:: ሕዝ.25፥12-14::

ስለዚህ ቂመኛነታችን ለይቅርታ ወደር የሌለው ጠላት ብቻ ሳይሆን አጥፊያችንም እንደ ሆነ ማወቅ ይገባናል:: ከነሰንኮፉ አውጥተውን እንጣለውና ለይቅርታ ቦታ እንስጥ::

*11.4 **በቀለኛነት**:-* አይተን፣ ሰምተን፣ አንብበን የወረስናቸው መልካም ባህሎች አሉን:: ዓለም በዚህ ተደንቋልና በየጊዜው ወደ ቅድስት አገር ወደ ኢትዮጵያ ይተማል::

ከቀደምቶቻችን የወረስነው የመበቃቀል ባህል /ጥቁር ደም/ ግን የቱን ያህል እንደ ጎዳን አስተውለናል? ይቅር እንዳንባባል አንቆ የያዘን ክፉ የመበቃቀል ባህላችን ነው:: በብዙ ነገራችን የሚያደንቀን ዓለም በበቀለኛነታችን የተነሣ ኢትዮጵያውያን መገዳደል፣ መተላለቅ፣ መበቃቀል ባህላቸው ነው እያሉ ያሙናል::

በክፉ ሥራችን ሳይበቀለን እስከ ዛሬ ያቆየን ቸር አምላክ ግን «አትበቀል::» ብሏል:: ዘሌ.19፥18:: መገፋታችን በዝቶ ከጽዋው ቢፈስ እንኳን ወደ እርሱ እንድናመለክት እንጂ ብዙ ስለ ተገፋችሁ ተበቀሉ አይለንም:: «ራሳችሁ አትበቀሉ፤ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ በቀል የእኔ ነው::» ይለናል:: ሮሜ. 12፥19::

ሳኦልን መበቀል እየቻለ በይቅርታ ያለፈው ዳዊት ረጅምና ሰላማዊ ሕይወት ኖሯል:: የወንድሙ አሣሄልን ደም ለመመለስ አበኔርን ተበቅሎ የገደለው ኢዮአብ ግን አሳዛኝ አሟሟት ሞቷል:: 2ሳሙ.2፥18-32፤ 2ሳሙ.3፥12-39፤ 1ነገ. 2፥28-32::

ስለዚህ ከይቅርታ፣ ከዕርቅና ከሰላም እየጎተተ ወደ ኋላ ያስቀረንን ክፉ የበቀለኛነት ባህል /ጥቁር ደም/ ከልባችንና ከምድራችን ማስወገድ ይገባናል:: ያን ጊዜ ምሕረትና ይቅርታ ቦታ ያገኛል::

*11.5 **የአስታራቂዎች አለመኖር**:-* እኛ እም ላካችንን በድለን በኃጢአታችን ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም በተጣላን ጊዜ የኛን ሥጋ ነስቶ በመስቀል ላይ ቤዛነትን ከፈጸመ በኋላ ከራሱ ጋር አስታረቀን:: በመሆኑም አስታራቂዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ክብር ይሰጣቸዋል::

ቅዱሳን መላእክትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን ዘወትር ከፍ ከፍ የምናደርጋቸው ለእርሱ ባላቸው ታማኝነትና ተጋድሎ ብቻ አይደለም:: ከእርሱ ጋር የተጣሉትን ሁሉ ለማስታረቅ በሚያደርጉት ምልጃና ልባዊ ልቅሶ ነው፤ ምክንያቱም አስታራቂዎችን ይወዳልና::

እኛም ሰዎች ሲጣሉ የማስታረቅ ግዴታ አለብን:: ዳሩ ግን የአስታራቂነት ተግባራችንን ስለ ተውን ብዙዎች በጥል፣ በኩርፊያና በጠበኛነት ይኖራሉ:: ይህ ብቻ አይደለም:: እናስታርቅ ብለን የቆምነውም ከተጣዮቹ ለአንዱ በመወገናችን የአንዱን ነገር ለሌላው በማቀበልና መካረሩን በማባባስ የችግሩን መፍትሔ እናዘገያለን:: የአንዱ ከሌላው መጣላት ለእኛ ሥጋዊ ትርፍ መሰብሰቢያ የሆነልንም አንታጣም:: ይህን የዐመፃ ጥቅም ላለማጣትም ስንል ማስታረቁን ትተነዋል:: ወይም በእሳት ላይ ቤንዚን የመጨመር ዐይነት ተግባር እንፈጽማለን:: ይህ ሁሉ ነገር አስታራቂዎች እንዳንሆን ስላደረገን ይቅር አለመባባል ተንሰራፍቷል:: ይህ ሥራ ግን የእግዚአብሔር ልጆች ሥራ አይደለም:: የተጣሉትን በማስታረቅ ከብፁዓን ኅብረት እንግባ:: የእግዚአብሔር ልጅነታችንንም እናስመስክር:: «የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና::» ማቴ. 5፥10::

## 12. ይቅር አለማለትና ችግሮቹ

ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ይቅርታ ባለማድረጋቸው የሚታወቁ ብዙ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ምሕረት አልባ ሰዎች ይቅርታ ባለማድረጋቸው የተነሣ ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን እየጎዱ ቆይተዋል፤ ይቅርታ አድራጊዎች ከጠቀሙና ከተጠቀሙ ምሕረት አልባዎች መጎዳታቸውና መጉዳታቸው የማይቀር ነውና:: ይቅርታ ባለማድረግ ከሚታወቁት መካከል በጥቂቶቹ ታሪክ መማር እንችላለን::

### 12.1 ቃየን

አንዳንድ ሰዎች ራሳቸው በድለው መልሰው ደግሞ ተበዳዩን ይበቀላሉ:: በአቤል ንጹሕ መሥዋዕት ተቀባይነት ማግኘት የቀናው ቃየን በወንድሙ ላይ መቅናቱ ሳያንስ በድንጋይ ቀጥቅጦ ገድሎታል:: ቃየን ከዚህ በኋላ ምን ሆነ? /ዘፍ.41-8/::

*12.1.1 **ተረገመ**:-* እግዚአብሔር ለሰው ትልቅ ክብር አጎናጽፎታል:: ቀድሞ የእጁ ሥራ ኋላም የደሙ ዋጋ ነውና በሰው ሞት ደስ አይለውም:: ራሱ በሞት ለጠራው አልዓዛር እንባውን ማፍሰሱ ይህን ያረጋግጣል:: ዮሐ.11፥35:: ስለሆነም አቤልን የገደለውን ቃየንን ረገመው፤ እንዲህ ሲል:- «ምን አደረግህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል:: አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ሁን::» ዘፍ.4፥10-11:: አንዳንዶቻችንን ምንም ያላደረጉንን ሰዎቹ እያሳደድን፣ እየሰደብን፣ እየከሰስንና እየገደልን ነው፤ ለምን? ወደ ምሕረት ካልተመለስን የተረገምን እንሆናለን::

*12.1.2 **ኩብላይና ተቅበዝባዥ ሆነ**:-* ይቅር የማይል ሰው ሰላምና መረጋጋት ስለ ሌለው ኩብላይና ተቅበዝባዥ ይሆናል:: ይቅር ብለው የሰከነ ሕይወት መኖር ሲችሉ ምሕረትን በጭካኔ ለውጠው ልባቸው ያሰበውን በመፈጸማቸው የኩበ ለሉና የሚቅበዘበዙ ሰዎች አሉ:: ከእነርሱ መካከል አንዱ ሆነን ይሆን? «ቃየን በምድር ላይ ኩብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ» እንደ ተባለ ዛሬም ይቅርታ የሌላቸው፣ ልባቸው ከቂምና ከበቀል ያልጸዳ፣ በቁጣና ጭፍን እልኸ የሚኋዙ ሰዎች በሐሳብና በአካል እንደ ኮበለሉና እንደ ተቅበዘበዙ ይኖራሉ:: ዘፍ.4፥12::

### 12.2 ስምዖንና ሌዊ

ሴኬም የተባለ ወጣት የያዕቆብን 13ኛ ልጅ ዲናን ክክብር በማሳነሱ በአባቱ በኤሞርና በያዕቆብ ቤተሰብ መካከል ፍጥጫ ነገሠ:: የሴኬም አባት ኤሞር ግን ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ ዲናን ለልጁ ለሴኬም ይድሩለት ዘንድ አባትዋን ያዕቆብንና ወንድሞቿን ጠየቀ:: በልባቸው ሌላ የሞት ድግስ የደገሱት የያዕቆብ ልጆች ግን ሴኬምና በዚያች አገር ያሉ ወንዶች ሁሉ ቢገዘሩ ፈቃደኛ እንደ ሚሆኑ ገለጹ:: በዚህ ስምምነት መሠረት ሴኬማውያን በሙሉ ተገዘሩ::

በሦስተኛው ቀን ቁስል እንዲጸና ያወቁት ስምዖንና ሌዊ ሰይፋቸውን መዝዘው ወደ ሴኬማውያን መንደር ገቡ:: «ተገዝረናልና ወደ ፊት ከእስራኤላውያን ጋር ተጋብተን በሰላም እንኖራለን» ብለው በመዘለል የተቀመጡትን ወንዶች ሁሉ ገደሉ:: ሴኬምም ከአባቱ ኤሞር ጋር ተገደለ:: ዘፍ.34፥1-29:: በመጨረሻ ምን ተከሠተ?



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

### 12.2.1 መጠላት

ስምዖንና ሌዊ በቅናትም ይሁን በማን አለብኝነት ተነሥተው የሴኬምን ወንዶች ከጨፈጨፉ በኋላ የያዕቆብ ዘር በከነዓናውያንና በፌርዛውያን ዘንድ የተጠላ ሆነ:: አባታችን ያዕቆብ ይህን ሲገልጽ:- «በዚች አገር በሚኖሩ በከነዓናውያንና በፌርዛውያን ሰዎች የተጠላሁ ታደርጉኝ ዘንድ እኔን አስጨነቃችሁኝ፤» ነበር ያለው:: ዘፍ.34፥30::

የበደልናቸውንም ሆነ የበደሉንን ይቅር ሳንል ሌላ እርምጃ በወሰድንባቸው ቁጥር ራሳችንን፣ ቤተሰባችንንና ማኅበረሰባችንን በሌሎች ዘንድ የተጠላንና የተጠሉ እናደርጋለን:: በደለኞችን ከመገሠጽ ይልቅ ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው፣ ባልንጀሮቻቸውና ጎሳዎቻቸው ስለሆኑ ብቻ ዝምታን የሚመርጡና ለበለጠ መቃቃር ምክንያት የሚሆኑ ሰዎች ካሉ ደግሞ በሌላው ዘንድ መጠላቱ የከረረ ይሆናል:: በክርስትና ሕይወት ሳይበድሉ መጠላትና መንገላታት ያሸልማል:: በደል ፈጽሞ መጠላትና መንገላታት ግን ሕይወትን በሰቀቀን ሲመላ ከሰማይ ለሚታዘዝ ቁጣም ጭዳ ያደርጋል:: 1ጴጥ.2፥19-20::

የክርስቲያን ዐይን ግን አጥርቶ ማየት ይገባዋል:: በጥቂት በደለኞች ብዙዎችን መጥላትና መግፋት ተገቢ አይደለም:: እንኳን ምንም በደል የሌለባቸውን ንጹሐንን የበደሉንን እንኳን እንጠላ ዘንድ ለክርስቲያኖች አልተፈቀደም::

### 12.2.2 ጭንቀት

ከዚያች ዕለት ጀምሮ አባታችን ያዕቆብ በሴኬም ያሳለፈው ጊዜ በጭንቀት የተሞላ ነበር:: «ከዛሬ ነገ ሴኬማውያን የበቀል ጦራቸውን ሰብቀው ያጠፉኝ ይሆንን?» እያለ ተጨንቋል:: «እኔን አስጨነቃችሁኝ፤ እኔ በቁጥር ጥቂት ነኝ፤ እነርሱ በእኔ ላይ ይሰበሰቡና ይመቱኛል፤ እኔም ከወገኔ ጋር እጠፋለሁ::» እንዲል:: ዘፍ.34፥31::

ከተጣሏቸው ሰዎች ጋር ምሕረትንና እርቅን ከመመሥረት ይልቅ ጥልንና ብቀላን የሚገነቡ ሰዎች ዘመናቸውን የሚጨርሱት በፍርሃትና በጭንቀት ነው:: ራሳቸውን በመደበቅና በመጠበቅ ከጥቃት ቢያመልጡም ቤተሰቦቻቸውና ወገኖቻቸው ላይ የሚያስከትሉት ጭንቀት ታላቅ ነው:: ይህን ጭንቀት የቀመሱ ሰዎች ሕመሙን በሚገባ ያውቁታል:: ፍርሃትና ጭንቀት ደግሞ ሕይወትን ያጎመዝዛሉ::

ያዕቆብ ሊሞት ሲል ልጆቹን ሰብስቦ ነበር፤ የወደፊት ዕጣ ፈንታቸውን ሊነግራቸው:: ያን ሁሉ መጠላትና ጭንቀት በሌዊና በስምዖን የተነሣ ተቀብሏልና «ቁጣችሁ ርጉም ይሁን» ብሏቸዋል:: «በምክራቸውም ነፍሴ አትግባ» ሲልም ተናግሮባቸዋል:: «እከፋፍላቸዋለሁ፤ በእስራኤልም እበታትናቸውማለሁ» ብሎአቸዋል:: ዘፍ.49፥5-7::

ይቅር ባለማለታችን የሚረግመን እግዚአብሔር ብቻ እንዳይመስለን:: የገዛ ወገናችንም ያደረስንበትን ሰቆቃ ቆጥሮ ሊረግመን ይችላል:: ያዕቆብ ስምዖንና ሌዊን እስከ መርገም የደረሰው ያለ ርኅራኄ በገደሏቸው ሴኬማውያን ምክንያት እጠፋ ይሆንን እያለ ተጨንቆ ነበርና ነው::

### 12.3 ፈርዖን

ፈርዖን «ሕዝቤን ልቀቅ» በተባለ ጊዜ እምቢ አለ:: ይባስ ብሎ የጭቆና በትሩን የግፍ አገዛዙን አጸና:: ሕዝበ እስራኤልን ይቅር ብሎ ከመልቀቅ ይልቅ በጭካኔና በእምቢተኛነቱ በመጽናቱ ተከታትሎ የወረደው የእግዚአብሔር መቅሠፍት ለሌሎችም ተርፏል::

#### 1.2.3.1 በአዝርዕት፣ በአትክልትና በዕፀዋት ላይ

ሰዎች እርስ በእርሳቸው ሲጨካከኑና ዘአልቦ ምሕረት /ምሕረት የለሽ/ ሲሆኑ እግዚአብሔር የተሰማውን ሐዘን በአዝርዕት፣ በዕፀዋትና በአትክልት ላይ ይገልጣል:: ፈርዖን ይቅርታን ባለማድረጉ በምድረ ግብጽ አዝርዕት፣ ዕፀዋትና አትክልት ላይ ጥፋት ታዟል:: ዘጸ. 9፥22-26፤ ዘጸ.10፥12-16:: ይቅር ባልተባባልን ቁጥር ይህ ሊሆን ግድ ነው:: ይህን ተከትሎ የሚመጣው የረኀብ ሰይፍ ደግሞ ይብ ሳል:: እስከ መቼ በኛ ጥፋት ግዑዛን ፍጥረታት ይቀጣሉ:: ይህ ሁሉ እንታረቅ ዘንድ አይደለምን?

### 12.3.2 በእንስሳት ላይ

የፈርዖን ምሕረት አልባነት ለቤት እንስሳትም ጥፋት ምክንያት ሆኗል:: ዘጸ.9፥1-8:: እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ ይመለስ ዘንድ ሲያሳስበው ከእርሱ ባነሱ ሥጋዊና ደማዊ እንስሳት ላይ ቁጣውን ይልካል:: ይህ የኾነው ትክክለኛውን ጥፋተኛ አጥቶ እንዳይመስለን፤ እርሱንማ ያውቃል:: ነገር ግን እንደ ማይናገር በታጋሽነቱ ዝም የሚል አምላክ እንደ ማያውቅም በርኅራኄው ሰውን ሳይቀጣ ያልፋል:: ይቅር እንባባልና ምንም የማያውቁትን እንስሳት እንታደግ:: ለራሳችንም ሆነ ለአገራችን ያላቸው ጠቀሜታ የጎላ ነውና ቢጠፉ እንጎዳለን::

### 12.3.3 በሰው ላይ

ይቅርታን የማያውቀው ፈርዖን ለግብጻውያን ሁሉ የበኩር ልጆች ሞት ምክንያት ሆነ:: ዘጸ.12፥29-30:: በዚህ አላበቃም:: ፈርዖን ከእግዚአብሔር በታዘዘ ቁጣ ተንበርክኮ ሕዝቡን ቢለቅም ወዲያው ተመልሶ ልቡን አደነደነ:: እግዚአብሔርም የትዕቢቱን ጽናትና ተግዳሮቱን ተመልክቶ አብረውት ከሮጡት ሠራዊቱ ጭምር በኤርትራ ባሕር ውስጥ አሠጠማቸው:: ዘጸ.14፥26-31::

እኛ ይቅር ያላልናቸውን ወገኖች እግዚአብሔር ባሕሩን ከፍሎ፣ ከማዕበሉ ከልሎ ሊያሻግራቸው ይቻለዋል:: የኛ መጨረሻ ግን ዘግናኝ እንዳይሆን:: የኛ ይቅር አለመባባል ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን ይዞ ይጠፋል:: ይቅርታን የማያውቅ ወገን በመጨረሻ መጥፋቱ አይቀርም::

### 12.3.4 ጨካኙ አበዳሪ

ጌታ በማቴ.18፥23-35 በሰጠው ምሳሌያዊ ትምህርት ላይ የተገለጸው አበዳሪ ለበደሏቸው ሰዎች ምሕረት የማያደርጉ ጨካኝ ሰዎችን ብቻ አያመላክትም:: ምሥጢራዊ ትርጉሙ ለዚህ ቢሆንም አፍዓዊ ትርጉሙ ምስኪን ተበዳሪዎቻቸውን ስለ ማይምሩ ጨካኝ አበዳሪዎች ያመለክታል:: ለኛ ቢመጣ ብዙ ቁም ነገር መሥራት የማይችለው ብር ለተበዳሪዎቻችን ትልቅ ጥቅም ሊኾን ይችላል:: ታድያ ተቸግረው ስናይ ስለምን አንተውላቸውም!

አምላካችን ስንቱን በደላችንን ትቶልን የለ? ለእኛም ያስጨነቀንን ዕዳችንን ደምስሶልናል:: መቸገራቸውን እያየን ብንከሳቸው፣ ብናሳስራቸውና ብናስቃያቸው ግን አምላካችው ዝም አይልም:: «ጌታውም ተቆጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚያሠቃዩት አሳልፎ ሰጠው::» እንደ ተባለለት አበዳሪ ያደርገናል:: ማቴ.18፥34::

## 13. የይቅርታ ትርፎች

**የመንፈስ ደስታ**:- ብዙዎቻችን መንፈሳዊ ደስታን በሌለበት ቦታ እየፈለግነው ነው:: መንፈሳዊ /ውስጣዊ/ ደስታ ግን ያለው በይቅርታ አድራጊዎች ልብ ውስጥ ነው:: የበደሉንን ሰዎች ይቅር የምንል ከሆነ ደስታ ወደ እያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ይገባል:: ሌሎች በእኛ ላይ ስለ ፈጸሙት በደል ምሕረት ማድረጋችንን ባሰብን ቁጥር የመንፈስ ደስታችን ይጨምራል:: ጸሎታችን በቂም አለመተብተቡን ማወቃችንም ሌላው የደስታችን ምንጭ ነው:: አይሁድ ቅዱስ እስጢፋኖስን በድንጋይ ሲወግሩት እርሱ ግን ለነሱ ይቅርታን ከአምላክ ዘንድ ይለምንላቸው ነበር:: የሐዋ.ሥራ 8፥54-60:: የዚህ ንጹሕ ሰማዕት ሞት በደስታ የታጀበ ነበር:: ያጣነውን ደስታ ማግኘት እንፈልጋለንን? መልካም! አሁኑኑ የበደሉንን በደስታ እንማር:: ያኔ ደስታን በእውነት እናገኘዋለን:: የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚገኘው በመንፈሳዊ /ልባዊ/ ይቅርታ ነውና:: ገላ.5፥22::

**13.2 የመንፈስ ሰላም**:- ፍርሃት፣ ጥርጣሬ፣ ድንጉጥነትና መረበሽ ይቅር በማይሉ ሰዎች ላይ ይበረታሉ:: የይቅርታ ሰዎች ካልሆን ስንበላ፣ ስንተኛ፣ ስንሠራ፣ ስንጓዝ ወዘተ ሰላም አይኖረንም:: የምሕረት ሰዎች ስንሆን ግን ሰላማችን ይበዛል:: የትም ቦታ እንሁን፣ ሰላም ይኖረናል:: ከማንም ጋር እንሁን፣ አንፈራም:: እንተማመናለን:: አለበለዚያ የበደልነው ወይም የበደለን ሰው ይተናኮለናል እያልን እንሰጋለን:: በቂመኛነታችን የተነሣም የጸሎታችንን አለመደመጥ በማሰብ እንታወካለን:: «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር::» ኢሳ.48፥22::

ታድያ ለምን ሰላምን በምሕረት ውስጥ አንፈልጋትም:: «ኅሥሣ ለሰላም ወዴግና።.. ሰላምን ሻ፣ ተከተላትም»



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

/ዲ.ን ደረጀ ጅማ/

# ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን

## በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት ውስጥ

## የቅድስና ሕይወት በወጣትነት (በብቸኝነት)

*ባለፈው እትማችን ምእመናን ስለ ቅድስና በተለያየ መንገድ /እንደ ተሞክሯቸው መጠን/ የሰጡትን ገለጻ አቅርበን ነበር:: ቅድስና እስከ ኅልፈተ ዓለም የሚነሡ ክር ስቲያኖች መንፈሳዊ ተጋድሎ በማድረግና የእግዚአብሔርን አጋዥነት በማግኘት ሊኖሩት የሚገባ ሕይወት እንደ ሆነ ባለፈው ጽሑፋችን ውስጥ ተገልጧል:: ከዚሁ ጋር ቅድስና በግል ሕይወት፣ ከማኅበረሰቡ ጋር በሚደረግ መስተጋብር፣ ለቤተ ክርስቲያን በሚፈጸም አገልግሎትና የቅድስና ምንጭ ከሆነው ከልዑል እግዚአብሔር ጋር ባለ ግንኙነት የሚንጸባረቅ እንደ ሆነ የተለያዩ አስተያየት ሰጪዎችን ምላሽ መሠረት በማድረግ ለማየት ሞክረናል:: ቀጣዩን ክፍል እንደ ሚከተለው ይዘንላችሁ ቀርበናል:: መልካም ንባብ::*

የሰው ልጆች በዚህች ዓለም የተፈቀደላቸውን የዕድሜ መጠን ፈጽመው ወደ ሰማያዊ ሕይወት ከመ መለሳቸው በፊት በተለያዩ የሕይወት ቆይታዎችና ውጣ ውረዶች ውስጥ ያልፋሉ:: ለምሳሌ:- ለአካለ መጠን ደርሰው ጋብቻቸውን በመፈጸም የትዳር ሕይወት ከመጀመራቸው አስቀድሞ የተወሰነ ጊዜ በብቸኝነት ማሳለፋቸው ግድ ነው:: ይህ ብቸኝነት ያለ ማግባት ውሳኔ ካላቸው እስከ መጨረሻው ይጸናል:: ትዳር የመሠረቱትም ቢሆኑ የትዳር ጓደኞቻቸውን በሞት ሲያጡ እና በኀጆአቸው መሐል ሳንካ ሲፈጠር የብቸኝነትን ሕይወት ለመምራት ይገደዱ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ በሚ መሩት የብቸኝነት ቆይታ ውስጥ የቅድስናን ሕይወት መኖር ይጠበቅባቸዋል፤ ቅድስና በየትኛውም የኑሮ መስክ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታ ነውና::

«እውን በብቸኝነት እየኖሩ በቅድስና የተሸለመ ሕይወትን መምራት ይቻላል ወይስ አይቻልም?» የብዙዎች ኅሊናዊ ጥያቄ ነው:: ኀለማየሁ ውቤ ይባላል:: ወጣትና የአዲስ አበባ ነዋሪ ነው:: እንዲህ ይላል:- «በመሠረቱ የቅድስና ሕይወት ከባድ ነው:: ይሁን እንጂ በወጣትነት ወይም በብቸኝነት ሕይወት ውስጥ በቅድስና ለመኖር ይከጠብዳል ወይም ይቀላል ለማለት የየግላችን ሁኔታ ወሳኝ ነው::» ወጣት ዮሴፍ ስሜ ደግሞ የነገሌ ቦረና ነዋሪ ነው:: ቅድስና በወጣትነት ሕይወት ውስጥ ያለውን ክብደት ሲገልጽ:- «የቅድስና ሕይወት ከባድ ቢሆንም በወጣትነታችን ልንኖረው እንችላለን:: እርግጥ እንደ የሰዉ ሊለያይ ይችላል:: የቅድስና ሕይወትን ለመኖር የግል ውሳኔ፣ ጽናት፣ ቃሉን ማወቅና ረድኤተ እግዚአብሔር ያስፈልገናል እንጂ ልንኖረው እንችላለን::» የልዩ ልዩ መንፈሳዊ መጻሕፍት ደራሲ የኾነችው ክርስቲና ደግሞ «ቅድስናችንን ከየትኛውም የዕድሜ ደረጃ ጋር ማላመድ አለብን» ትላለች::

ሰዎች ነጻ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የተፈጠሩ የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ናቸው:: በብቸኝነት ቆይታቸው ውስጥ የቅድስናን ሕይወት ለመምራትም ይሁን ላለመምራት ወሳኞቹ ራሳቸው ናቸው:: ራሳቸውን አበርተው በሕይወቱ ልኑር ካሉ ይችላሉ:: «አልችልም» በማለት መንፈሳቸውን ካሸመደመዱ ደግሞ በርኩሰት እየመላለሱ መዳከር የዘወትር ተግባራቸው ይሆናል:: ከቅድስና ላፈነገጠው ጉዞአቸው ግን ማንም ተጠያቂ አይ

---

እንዲል መዝሙረኛው:: መዝ. 33/34÷14:: ልባችንን ከቂምና ከበቀል እናጽዳ፣ ይቅርም እንበል፤ ያን ጊዜ ሰላማችን ይበዛል::

*13.3 ምርቃት:-* እኛ የለመድነው ወዳ ጆቻችን ሲመርቁን ነው:: ይቅርታ ግን የበደሉን ሰዎች ሳይቀሩ አፋቸውን ከፍተው እንዲያመሰግኑን ያደርጋል:: የእሴይ ልጅ ዳዊት የሚያሳድደውን ሳኦልን ይቅር በማለቱ ሳኦል ልቡ ተነካና እንደዚህ አለ፤ «ልጄ ዳዊት ሆይ ÷ ቡሩክ ሁን፣ ማድረግን ታደርጋለህ፣ መቻልንም ትችላለህ::» 1ሳሙ.26÷25:: ከዚህም ሌላ ሳኦል በዳዊት ይቅርታ መንፈሱ ተነክቶ አንብቷል:: ሁላችንም የምሕረት ሰዎች ብንሆን በጉስቁልናችንና በሞታችን ሊሳለቁ የተሰለፉትን ሰዎች በጸጸት ተሞልተው እንዲያለቅሱ እናደርጋለን:: ያኔ አፍዓዊ ያልሆነ ልባዊ ምርቃታቸው ያረሰርሰናል::

*13.4 ይቅርታ:-* ማናችንም ብንሆን ልዑል እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን እንፈልጋለን:: የእርሱን ምሕረት እንቀበል ዘንድ ብዙ መንገዶችን የሰጠን አምላክ «የበደሏችሁን ማሩና ይቅር እላችኋለሁ» ሲል ቃል ገብቶልናል:: «በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት፤ እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም::» ማር.11÷25-26:: ይህን እውነት ቢመረንም እንዋጠው:: ይቅር ካላልን ይቅር አንባልም:: ከማርን ግን ምሕረትን እናገኛለን::

*13.5 ብፅዕና:-* አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «ብፁዕ» የሚለውን ቃል «የታመነ፣ የተመሰገነ፣ ሥራውና ልቡ የቀና የተከናወነ፣ ክቡር፣ ምስጉን፣ ምሩቅ፣ ቡሩክ፣ ቅዱስ፣ ጻድቅ፤ ቸር የእግዚአብሔር ሰው» ብለው ይተረጉሙታል:: /ኪ.ወ.ክ÷ 281/:: እነዚህን መሆን የማይፈልግ ሰው ይኖራል ተብሎ አይጠረጠርም:: ይቅር ብለን ከብፁዓን ኅብረት እንግባ፤ የማይምሩ ሁሉ ብፅዕና አይገባቸውም:: «የሚምሩ ብፁዓን ናቸው» የተባለው ለይቅርታ አድራጊዎች ነውና:: ማቴ.5÷7::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሆንም፡፡ ተወቃሾቹ ራሳቸው ብቻ ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው አስተያየት የሰጠችው ወ/ት ነጻነት አበረ የሚከተለውን ብላለች፡- «በወጣትነት ወይም በብቸኝነት ሕይወት ስንኖር እግዚአብሔር ለኃጢአት አያዘጋጀንም፡፡ እርሱ ያዘጋጀን ለጽድቅ ነው፡፡ ፍትወቱ በውስጥ ካየለ ቅድስናን በብቸኝነት ሕይወት ውስጥ መተግበር ይከብዳል፡፡ ለቅድስና ተቃራኒ የሆነውን ሕይወት እየፈለግነውና ልባችን ተከፍሎ የምንኖር ከሆነ ብቸኝነታችን ፈታኝ ይሆንብናል፡፡ ነገር ግን ዓላማ ካለንና ዓላማችን ላይ ወስነን ከተጓዝን በብቸኝነት ሕይወታችን ውስጥ አቅማችን የቻለውን የቅድስና ኑሮ መኖር እንችላለን፡፡»

ጊዜው የተለያየ ቢሆንም የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍና የንጉሥ ዳዊት ልጅ አምኖን በብቸኝነት ሕይወታቸው ውስጥ የዝሙት ፈተና ገጥሞአቸው ነበር፡፡ ያ ክፉ የዝሙት ፈተና የጣለው ግን በምኞት የተቃጠለውንና ኃጢአትን ለማድረግ የተዘጋጀውን አምኖንን ነው፡፡ በዝሙት ምኞት ባልተከበበውና ራሱን ለኃጢአት ባላዘጋጀው ዮሴፍ ላይ ፈተናው ድል የመንሳት ኃይል አልነበረውም፡፡ ዘፍ. 39፥7-12፤ 2ሳሙ.13፥1-14፡፡ ሁለት ወጣቶች በአንድ ዐይነት ፈተና ተፈተኑ፡፡ ራሱን ለቅድስና ያዘጋጀው ፈተናውን አለፈ፡፡ ያላዘጋጀው ግን ወደቀ፡፡ በሥጋና በነፍስም ተጎዳ፡፡

በወጣትነት ወይም በብቸኝነት ቆይታ ውስጥ ለሚፈጸሙት ከቅድስና ሕይወት ያፈነገጡ ድርጊቶች የመጀመሪያና የመጨረሻ ተጠያቂዎች ራሳቸው ድል የተነሱት ሰዎች ቢሆኑም ፈተናዎች መኖራቸው ግን አይዘነጋም፡፡ ወጣት አበባው ደስታ የተባለ የደሴ ነዋሪ ያለው ይህን ነበር፡- «እርግጥ ወጣትነት ላይ ብዙ ፈተና ይኖራል፡፡ ነገር ግን *«በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ»* በሚለው አምላካዊ ቃል ይህን ትእዛዝ ለማክበር ስንል የወጣትነት /የብቸኝነት/ ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር በመስጠት የተቀደሰ ሕይወትን መምራት ይገባናል፡፡ በሌላው ዕድሜ ቅድስና አያስፈልግም ማለቴ ሳይሆን ይበልጥ ቅድስናን መለማመድ ያለብን በወጣትነት ዕድሜያችን ነው፡፡ የቅድስና ሕይወትን በእሳት ዘመናችን እንምራ ብለን ስንነሣ ግን ብዙ ፈተናዎች እንደ ሚያጋጥሙን የታመነ ነው፡፡»

በወጣትነት የሚገጥሙንና የቅድስና ሕይወትን እንዳንመራ የሚገዳደሩን ፈተናዎች በወጣትነት ዘመን ማየላቸው ወጣትነት በራሱ ለመፈተን ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት ዕድሜ በመሆኑ ነው፡፡ በዕድሜም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት ወጣኒ በሆኑት ላይ ፈተናዎች ሁሉ ሠልጥነው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ተጋድሎው መራራ ነው፡፡ ፈተናዎችም መልካቸውንና ጊዜያቸውን እየቀያየሩ ወጣቶችን ወይም ብቸኞችን ከቅድስና መስመር ገፍተው ለማስወጣት ይጣደፋሉ፡፡ ቶሎ ለመጣል ከውስጥ ከውጭ ሆነው ይተኩሳሉ፡፡ ተፈታኞቹ በተዘናጉበት ወቅት ቆርጦ ለመጣል ሲሉ ደግሞ አድብተው ይቆያሉ፡፡ በመሆኑም ወጣትነት ወይም ብቸኝነት ፈተና የማያጣው ሕይወት ነው፡፡

የወጣቶች ተቀዳሚ ፈተና ምን እንደ ሆነና ብዙ ጊዜ ከየት እንደ ሚነጭ ከራሱ ሕይወት በመነሣት ማብራሪያ የሰጠው ዲ/ን ዘርዐ ዳዊት እንዲህ ይላል፡- «ከውስጤ እየተነሡ ከሚፈትኑኝ ፈተናዎች አንዱ የሐሳብ ዝሙት ነው፡፡ ይህን መሰሉ ክፉ ሐሳብ በውስጤ እየተመላለሰ በወጣትነቴ የቅድስናን ሕይወት እንዳልኖር ይፈታተነኛል፡፡ ይሁን እንጂ በመጨረሻ የማገኘው ምንድን ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብና ከእርሱ ጋር ከመኖር ውጭ ምንም እርካታ የማገኝበት ነገር እንደሌለ ሳውቅ በሰውነቴ የሚመላለሰውን ሐሳብ እቃወመዋለሁ፡፡» የዲ/ን ዘርዐ ዳዊትን ሐሳብ የሚጋራው ወጣት ዓለማየሁ ውቤም፡- «ዝሙት ወጣቶች የቅድስና ሕይወትን እንዳይኖሩ የሚፈታተናቸው ክፉ ጠላት ነው፡፡» ብሏል፡፡

እንደ ሚታወቀው ወጣትነት የልጅነት ዕድሜ ተጠናቆ በአካል፣ በአእምሮ፣ በሥነ ልቡና የሚበስልበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም በሕፃንነትና በልጅነት በሥራ ላይ ያልነበሩ ሆርሞኖች በሰውነት ውስጥ ተግባራቸውን ይጀምራሉ፡፡ እነዚህ ሆርሞኖች በሚያስከትሉት አካላዊ፣ ስሜታዊና ሥነ ልቡናዊ ተጽዕኖ አማካይነት ከወጣትነት ዕድሜ በፊት ታስበው የማያውቁ ሐሳቦችና ምኞቶች በኅሊናና በልቡና ውስጥ መመላለስ ይጀምራሉ፡፡ ሁሉም ምኞቶች ሥጋዊና ለኃጢአት የሚያዘጋጁ ናቸው ለማለት ባያስደፍርም እንደ ሐሳበ ዝሙት ያሉት ግን በብዙዎቹ ዘንድ የማይቀሩ ናቸው፡፡ በኅሊና ኅዳና የሚመላለሰውን የዝሙት ሐሳብ ወደ ልቡና ጓዳ አስገብቶ ማስቀመጥ ግን አንድ ቀን ለታሰበም ይሁን ላልታሰበ ስብራት ይዳርጋል፡፡

ስለዚህ ክፉ የኅልማሳነት ምኞት ገና ብቅ ሲል መቃወም ያስፈልጋል፡፡ ተቃውሞው ግን በቃልና በአንደበት ብቻ ሳይሆን በሥራና በእምነት ሊሆን ይገባዋል፡፡ «በእምነት ተቃወሙት» እንዲል፡፡ 1ጴጥ.5፥9፡፡ «ክፉ ምኞትን በረድኤተ እግዚአብሔር አሸንፌዋለሁ» የሚሉ ሁሉ ያሸንፋሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ሸሽት መረሳት የለበትም፡፡ ዓለማችን በታሪኳ የለመደችው መሸሽ የፈሪዎች መኾኑን ነው፡፡ በክርስትና ሕይወት ደግሞ ከክፉ ምኞትና ፈተና ሸሽተው የሚያመልጡ ጀግኖች ይባላሉ፡፡ በመሆኑም ክፉውን ምኞት እየተቃወሙ መሸሽ ማትረፊያ ነው፡፡ «ከክፉ የኅልማሳነት ምኞት ግን ሸሽ» ተብሎ መጻፉ ለዚህ ነው፡፡ 2ጢሞ. 2፥22፡፡ ወጣቱ ዮሴፍ ከዝሙት መዳፍ ያመለጠው በመሸሹ አይደል?

ወጣቶች ወይም በብቸኝነት ያሉ ሰዎች ሁሉ ዘወትር ከራሳቸው ኅሊና በሚፈልቅ ሐሳበ ዝሙት ምክንያት የቅድስና ሕይወታቸው ይፈተናል ብሎ መደምደም ግን አይታሰብም፡፡ ምክንያቱም የራስ ምኞትና ተነሣሽነት ሳይኖር ከሌላ ሰው በሚመጣ የዝሙት ጥያቄና ፈተና መፈተን አለና፡፡

ወ/ሮ ንግሥት አጎናፍር በመምህርነት ገጠር ተመድባ ስትሠራ የገጠማትን ፈተና እንዲህ ነበር የገለጠችው፡፡ *«ገጠር ውስጥ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርት ሳለሁ በርእሰ መምህሩ በኩል ተፈትኜ ነበር፡፡ ነፍሱን ይማረውና ይህ ሰው ፍጹም ዓለማዊ ስለነበር የሥጋ ፈቃዱን ብቻ ፈጽሞ መኖር ይፈልጋል፡፡ ፈቃዱን እንድፈጽምለት በመጨቅጨቅ የሥራ ጫና በመፍጠር፣ ሌሎች ፈተናዎችን ከፊቴ በመደቀን በእኔ ውስጥ ወደ ሌለው በእርሱ ግን ወደ ታሰበው ዝሙት ይጋብዘኝ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን ከዚያ ፈታኝ ችግር ነጻ አውጥቶኛል፡፡»*

እውነትም ብእሲተ ጲጥፋራ ዮሴፍን በዝሙት ስትፈትነው በዮሴፍ ልቡና ውስጥ ግን ሐሳበ ዝሙት አልነበረም፡፡ አምኖንም ትዕማርን በሥጋ ብልጠት ሲቀርባት በእርሷ ኅሊና የእርሱን መሰል ምኞት አልነበረም፡፡ የሚጠነቀቁና በዝሙት ሊጥሏቸው የሚያደቡትን ፈታኝ ሰዎች በንቃት የሚከታተሉ ወጣቶችና ሌሎች ሰዎች የዝሙትን ፈተና ድል ነስተው በቅድስና ሕይወት እንደ ተሸለሙ መቆየት ይችላሉ፡፡

ራሳቸውን ከዝሙት ኃጢአት ጠብቀው የሚኖሩ ወጣቶች አሉን፡፡ በሚያሳዝን መልኩ ደግሞ ዝሙትን እንደ ኃጢአት ባለመቁጠር ወይም ፈተናውን መቋቋም አቅቶን አልያም በአካባቢያችን የሚከናወነውን ክፉ ተግባር እንደ ጀብዱ አብነት አድርገን ብዙዎቻችን በዚህ ክፉ ኃጢአት ተሰነካክለናል፡፡ ይህ ደግሞ በሌላው የሕይወታችን ክፍል የደከምንለትን መንፈሳዊ ድካም መናቢስ አድርጎብናል፡፡ አሁን ባለንበት

**ቅድስና በየትኛውም የኑሮ መስክ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታ ነው፡፡**



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሁኔታ ደግሞ በተለይ ሩቅ ሆነው ለሚመለከቱን፣መንፈሳዊ ታሪካችንንና ሀብታችንን ለሚያውቁቱ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ምን ነካቸው ሳያሰኝ አይቀርም፡፡ ግሪካዊቷ ክርስቲና ትዝብት አዘል አስተያየቷን በዚህ መልኩ ገልጣ ነበር፡- «*I have noticed that in Ethiopia there are many young men and women who have a very spiritual life. They fast, pray and go to church every time. However I understood that some of them have a sexual life with out being married and with different partners. I am surprised and I couldn't understand how people who are so spiritual allow to commit such bad sin!* በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው ብዙ ወንድና ሴት ወጣቶች እንዳሉ አስተውያለሁ፡፡ ይጾማሉ፣ ይጸልያሉ፣ ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶች ወጣት ወንዶችና ሴቶች ከጋብቻ በፊት በሚፈጸም ፈቃደ ሥጋ ከተለያዩ ሰዎች ጋር እንደ ሚተዋወቁ ተገንዝቤያለሁ፡፡ በጣም መንፈሳዊ ሰዎች ይህን መጥፎ ኃጢአት ለመፈጸም መፍቀዳቸው ያስደንቀኛል፡፡ ለምን ይህ እንደ ኾነ ሊገባኝም አልቻለም፡፡» አያይዛም «የሚጾሙ፣ የሚጸልዩ፣ የሚያስቀድሱና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱ አንዳንድ ወጣቶች በተቃራኒ ፆታ ግንኙነት በኩል ያለው የሕይወታቸው ገመና ሲፈተሽ በዚህ ነውር መሞላቱ ያሳዝናል፡፡ እነዚህ ወጣቶች በሕይወታቸው ውስጥ ሁለት ክፍል አላቸው፡፡ አንደኛው የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ክፍል ሲሆን ሌላው ደግሞ በተቃራኒ ፆታ ችግር የተሞላው የሕይወታቸው ክፍል ነው፡፡ እርግጥ በመንፈሳዊና በተቃራኒ ፆታ ግንኙነት መካከል ያለውን ሁኔታ በጋብቻ አስተካክሎ የቅድስና ሕይወትን መምራት ይቻላል፡፡ መንፈሳዊ የሆኑ ወጣት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በቤት ውስጥ እንደ ማንኛውም ወንድ ወይም ሴት ሆነው በቤተ ክርስቲያን ግን እንደ መላእክት ቢመስሉ ምንም ዋጋ አያገኙም፡፡ ይህን መሰሉ አሳዛኝ ልማድ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ዘንድ ያለ አይመስለኝም፡፡» ብላለች፡፡

መ/ር ፈቃዱ ሣህሌ ይባላል፡፡ የሐረር ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ በሌላ አካባቢ ያሉ ወጣቶች ችግር ሊሆን ቢችልም የተወሰኑ የሐረር ወጣቶች የቅድ ስና ሕይወት እንዳይኖሩ እንቅፋት የሆነ ባቸውን ችግር ሲገልጽ፡
- «*በዚህ አካባቢ ከሚኖረው ወጣት መካከል የተወሰነው ጫት በመቃሙ በሚኖረው ግላዊና ማኅበራዊ መስተጋብሩ ለቅድስና ሕይወት የማይመች ጉዞ ይጓዛል፡፡ በሱሰኝነት ሕይወት ውስጥ ለቅድስና መሰናከሉ ብዙ ነው፡፡ ይህ እኛ ራሳችን ያመጣነው ችግር ነው፡፡ እንዲሁም በእናት ላይ የሚወረወሩ አጸያፊ ስድቦች በአካባቢው እንደ ምርቃት ይቆጠራሉ፡፡*» ብሏል፡፡ ነገሌ ቦረና በሚባለው የጠረፍ ከተማ የሚኖረው ዮሴፍ ስሜ የመምህር ፈቃዱ ሣህሌን ሐሳብ ሲያጠናክር፡- «በልዩ ልዩ የባዕዳን ውጥንቅጥ ባህል መንፈሳዊና ማኅበራዊ እሴቱ የተቀየጠ ትውልድ የቅድስናን ሕይወት ለመምራት ሊያስጨንቀው ይችላል፡፡ » ብሏል፡፡

ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር በሚደረግ የተቀራረበ ኑሮ የባህል፣ የቋንቋና የማኅበራዊ ሕይወት መስተጋብር ጠቃሚ የሆነውን ብቻ መውሰድ የብልህ ትውልድ ድርሻ ነው፡፡ በጥራዝ ነጠቅነት ያለ ምርጫ ሲቀበሉ መኖር ግን በመጨረሻ ላይ ስም አጠራርን ያጠፋል፡፡ በተለይ ክርስቲያን የተሰጠውን ሁሉ የሚቀበል ያገኘውንም የሚሰበስብ መሆን የለበትም፡፡ ሲቀበልም ሆነ ሲሰበስብ መርጦ ነው፡፡ መርጦ መውሰድን ከአምላኩ ተምሯልና፡፡ ሥጋውንም ሆነ ነፍሱን የማያረክሱ ነገሮች ምርጫው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ያገኙትን ሁሉ መሰብሰብ ግን ራስን ለመርሳት ቅድስናንም ለመጣል መጣደፍ ነው፡፡ ሕጉ ብርሃንና ሕይወት የሆነ ጌታ እግዚአብሔር ልጆች እናት አባታቸውን በሐሳብ፣ በቃልና፣ በድርጊት ያከብሩ ዘንድ ማዘዙ ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ከሚያስገኘው መንፈሳዊ በረከት በተጨማሪ በቤተሰብና በማኅበረሰብ ውስጥ መተሳሰብና መፈቃቀርን ስለ ሚያስገኝ ነው፡፡ ዘጸ.20፥12፡፡ ታድያ እናትን ሊሰሙት በሚከብድ ቃል መስደብ ከየት መጣ? ይህ ልምድ በአገራችን ከተሞች ያሉትን ወጣቶች እንደበት አርክሶ አልቆመም፡፡ ነገ ወጣት ወደ ሚሆኑ ሕፃናት ሁሉ ተዛምቷል፡፡

እናት አባቱን በመታዘዝና በማክበር ቅድስና ለማግኘት ከሚተጋው ወጣት ባላነሰ መልኩ ወላጆቹን እየረገመ የሚረክሰው ጎበዝ በዝቷል፡፡ የአንደበት ኃጢአት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ወጣቶች ፈተና ሆኗል፡፡ የምዕራባውያንም ሆነ ዐረባውያን «የባህል ወረራ» አገራዊና ባህላዊ እሴቶችን በማሳጣት አልተወሰነም፡፡ ሃይማኖታዊ ጉዟችንም ላይ መሰናክሎችን እያኖረ ነው፡፡ ወሪ/ት ክርስቲና እንዲህ ነበር ያለች ው፡
- «*The so called modern life has changed the time table of every body. For instance some sunday people want to sleep. They don't want to get up and go to church. They will go and make some sport instead of going to church. I have seen here in Addis Ababa at 4 in the sunday morning people who were running on the street. I don't know these people go to church or not. But I could notice that it is the influence of western life* – ዘመናዊ ተብዬው ሕይወት የብዙዎችን ጊዜ አነዋወር ለዋውጦታል፡፡ ለምሳሌ፡- በአንዳንድ ሰንበታት ሰዎች ተነሥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሔድ ይልቅ መተኛት ይፈልጋሉ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ፋንታ አንዳንድ የአካል እንቅስቃሴ ይሠራሉ፡፡ እሑድ ማለዳ ዐሥር ሰዓት በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ሰዎች እየሮጡ እንደ ነበር አይቻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ ግን የምዕራባውያን ተጽዕኖ እንደ ሆነ ላስተውል ችያለሁ፡፡» ትላለች፡፡

«የምትውላቸው ጓደኞች ማንነት በወጣትነት ለሚኖርህ የቅድስና ሕይወት የጎላ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ጓደኞችህ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ከሆኑ ሕይወቱን ትኖር ዘንድ ያበረታቱሃል፡፡ አለበለዚያ ችግር ነው» የወጣት አበባው አስተያየት ነበር፡፡ ጓደኛ ምረድ ነው፡፡ በመልካም አለበለዚያም በክፉ ይስልሃል፡፡ መዝ.17/18/፥25-26፡፡ በክፉ ባልንጀራ ተስሎ ከቅድስና ላለመለየት መጠንቀቅ በጎ ነው፡፡ «ከባልንጀሮቻችሁ ተጠንቀቁ» ተብለናልና፡፡ ኤር. 9፥4፡፡ ሔዋን ከአዳም ጋር በመልካም ባልንጀርነት ሳለች የቅድስና መዓዛዋ ገነትን ያውድ ነበር፡፡ ከእባብ ጋር የጀመረችው ባልንጀርነት ግን የቅድስና መዓዛዋን አሳጣት፡፡ ዘፍ.3፥12-4፡፡ በእምነት ከሚመስሉት እስራኤላውያን ባልንጀሮቹ ጋር ሲውል ቅድስናን አጥብቆ ይከተል የነበረው ሶምሶን ከፍልስጤማውያን ሴቶች ጋር በመሠረተው ግንኙነት ቅድስናውን አጣ፡፡ በመልአኩ፡- «ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና» ተብሎለት ነበር፡፡ መሳ.13፥5፡፡ ቅድስና ናዝራዊነት ነውና፡፡ ራሱም «ከእናቴ ማኅፀን ጀምሬ ለእግዚአብሔር የተለየሁ ነኝ» ብሎ ነበር፡፡ መሳ.16፥17፡፡ ቅድስና ለእግዚአብሔር መለየት ነውና፡፡ አብሮ የዋላቸው ጓደኞቹ ግን ቅድስናውን እንዲጥል ምክንያት ሆኑ፡፡ እርሱም ቃላቸውን በመፈጸም ተባበረ፡፡ በቅድስና ዘመኑ የነበረው ጉልበት ከቅድስና ሕይወት በራቀ ጊዜ ርቆታል፡፡ ይህ እውነት ዘወትር ይኖራል፡፡ ወጣቶች ከቅድስና ሕይወት በራቅን ቁጥር መንፈሳዊ ጉልበታችን ይከዳናል፡፡ ቀስ በቀስ ደግሞ የሥጋ ጉልበታችን ይቀልጣል፡፡ ከዳዊት ጋር የዋለው ዮናታን እውነተኛ ፍቅርን በሥራና በእውነት ሲ

**«ቅድስናችንን ከየትኛውም የዕድሜ ደረጃ ጋር ማላመድ አለብን፡፡»**



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያይ /1ሳሙ.20፥35-42/ አኪጦፌልን ባልንጀራ ያደረገው አቤሴሎም ግን ቅድስናውን ብቻ አይደለም ያጣው፤ ሕይወቱንም ገብሯል:: 2ሳሙ.17፥1-4:: የአምኖንም ውድቀት የተጀመረው ከውሎው ነው:: መልካም ባልንጀራ ወደ ቅድስና ሲመራ ክፋው ደግሞ መልካሙን የቅድስና አመል ያጠፋል::

«በወጣትነት ሳንቲሞችም ሊያሳስቱህ ይችላሉ» ይላል ወጣት ዓለማየሁ:: አያይዞም:- «እጅህ ላይ ገንዘብ ሲኖር ዓለማዊ ነገሮች ሊያምሩህ ይችላሉ:: ሌላው ደግሞ የሴት ጓደኛ መያዝ ያምርሃል:: ጓደኛ ስትይዝ ደግሞ «እነ እገሌ ከጓደኞቻቸው ጋር ይህን ፈጸሙ» የሚል ወሬ ሰምተህ ትፈተን ይሆናል ወይም በጓደኛህ ትፈተናለህ:: በመጠጥም ተገፋፍተህ የምትፈተንባቸው ጊዜያት አሉ:: አንተ የቅድስናን ሕይወት ለመምራት ስትነሣ ኋላ ቀርና «ፋራ» የሚሉህ ሰዎች ይኖራሉ:: አንተ ግን ከእግዚአብሔር አለመለየትና በቅድስና መኖር አላዋቂነት እንዳልሆነ ታውቃለህ:: ይህን የሚሉ ብቻ ሳይሆኑ የሚያስቡትም ማስተዋል የጎደላቸው አላዋቂዎች ናቸው::»

ወጣቶች ከኪሳቸው አውጥተው የሚፈልጉትን የሚያደርጉበት ብር ይፈልጋሉ:: ይህን የወጣቶች ፍላጎት የተረዱ አንዳንድ ወላጆች በቻሉት መጠን ለልጆቻቸው የኪስ ገንዘብ ይሰጣሉ:: የገንዘብ ልውውጥ ባለበት ቦታ ልጆቻቸውን በሐላፊነት የሚያስቀምጡም አሉ:: በአገባቡ ለሚኖሩት መልካም ነው:: ነገር ግን በወጣትነት የዕድሜ ክልል የሚፈትነው የንዋይ ፍቅርና አባካኝነት ወጣቶችን ከቅድስና ሲያርቅ ይታያል:: እርሱን የመሰሉ ወጣቶች በገንዘብ የሚፈጽሙት እኩይ ተግባር እንደ መነሻ ሊሆናቸው ይችላል:: ያሻኝን ላድርግ ማለትም አንዱ ችግር ነው:: በዚህ ምክንያት የሱስ ተገዥ ከሆኑ ደግሞ ችግሩ የከፋ ነው:: የቅድስና ሕይወታቸውን እጃቸው ላይ ባለው ገንዘብ አማካይነት የሚያቆሽሹ ወጣቶች ጉዳታቸው ሦስትዮሽ ነው:: በአካል፣ በመንፈስና በኢኮኖሚ ይጎዳሉ:: ጦሱ ለቤተሰብም መትረፉ ግድ ነው:: «አባቴ ሆይ፥ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው:: ገንዘቡንም አካፈላቸው:: ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሔደ:: ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ:: ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ረኀብ ሆነ፤ እርሱም ይጨነቅ ጀመር» ተብሎ የተጻፈለት ወጣት በዚህ መሰሉ ችግር ውስጥ ያለፈ ነበር:: ሉቃ.15፥11-14:: የወላጆች ቁጥጥርና ማስተማር፣ የወጣቶችም ታማኝነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ይህን ችግር ይዋጋሉ::

ከተቃራኒ ፆታ ጓደኞቻቸው /እጮኛዎቻቸው/ ጋር ከጋብቻ በፊት ፈቃደ ሥጋን ባለመፈጸም እስከ ጋብቻ ድረስ በንጽሕና ለመቆየት የወሰኑ ወጣቶች ሁሉ ወጣት ዓለማየሁ እንዳለው ይፈተናሉ:: ፈተናው ከራሳቸውም ሆነ ከጓደኞቻቸው ሊመጣ ይችላል:: የሌሎችን አሳፋሪ ድርጊት መስማትም ወጣቶችን ሊገፋፋ ይችላል:: ምኞቱ ባይኖራቸው እንኳን በሌሎች ክፉ ሥራ ሊጨነቁ ይችላሉ:: እንኳን እኛ «ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በዐመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበር::» /2ጴጥ.2፥7-8/ ተብሎ ተጽፎለታል:: ክብር፣ ሥልጣኔና ዕውቀት እግዚአብሔር የተጠየፈውን ኃጢአት መፈጸም የሚመስላቸው ሰዎች ደግሞ የእነርሱ ሥራ ተባባሪ ያልሆነውን ሰው ሊንቁ፣ ሊያቃልሉ ይችላሉ:: ይህ ትችትና ዘለፋ ከሚኖሩት የቅድስና ኑሮ ፈቀቅ የማያደርጋቸው ብርቱ ወጣቶች አሉ:: በመሰደባቸውና በመተቸታቸው እየተሸማቀቁ ለሚንቀጠቀጡና ኅሊናቸው ለሚዋዥቅባቸው ወጣቶች ግን ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ይላቸዋል:- «በዚህም ነገር ወደዚያ መዳራት ብዛት ከእነርሱ ጋር ስለ ማትሮጡ እየተሳደቡ ይደነቃሉ:: ግን እነርሱ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ለተዘጋጀው መልስ ይሰጣሉ::» አካሔዳቸውን ካላስተካከሉ በፈራጁ ጌታ ፍርድን ይቀበላሉ:: ትችትና ዘለፋ ግን በቅድስና ሕይወት ያሉትን ክርስቲያኖች መዋግደ ኅሊና ውስጥ ገብተው ቅድስናን እንዲተዉ ማድረግ አይችሉም:: ወሳኙ ባለቤቱ ነውና::

ወ/ት ነጻነት አበረ ደግሞ «አጓጉል ፊልሞችን ማየት፣ ለፈተና በሚያጋልጡ ቦታዎች መቀመጥና ለመዝናናት ብሎ ርቆ መሔድ አላስፈላጊ ከሆኑ እይታዎች ጋር ተደማምረው ቅድስናን ሊሸረሽሩ ይችላሉ::» ትላለች:: «እነዚህ ነገሮች ሊያዝናኑኝ ይችላሉ ብዬ አስብ ይሆናል:: ነገር ግን ለፈተና የሚዳርገኝ መስሎ ከታየኝ ለዚህ መሰሉ ነገር ኋላ እደርሳለሁ ብዬ ፍላጎቴን መግታት እችላለሁ:: ይህ የራሴ ከሆነ ሰው ጋር ነጻ ሆኜ የምደርስበት ይሆናል:: ዛሬ ያንን አድርጌ ፈተና ላይ ከምወድቅ ራሴን ገትቼ ኋላ ከሚመጣው ችግር ራሴን መጠበቅ አለብኝ::»

ከስሜት ሕዋሳታችን ሁሉ የላቀ መረጃ የሚሰበስበው ዐይናችን እንደ ሆነ የዓለማችን ሊቃውንት ከደረሱበት ሰነበቱ:: የምናያቸውና የምንሰማቸው ነገሮች ጠብቀን በቆየነው የቅድስና ሕይወት ላይ የሚያሳድሩት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም:: ለቅድስና ሕይወት ከማይመቹ ቦታዎች፣ ኃጢአትን እንዴት እንደ ምንፈጽም ክፉ ምሪት ከሚሰጡ እይታዎችና የሚደመጡ ነገሮች መሸሽ የቅድስና ሕይወትን ጠብቆ ለመቆየት ይረዳል:: አለበለዚያ በጸጋ እግዚአብሔርና በብዙ ትጋት የተጠበቀ ቅድስና ለጥቂት ጊዜ በታዩና በተሰሙ ነገሮች እንዲሁም ፈታኝ ቦታዎች አማካይነት መፈራረሱ አይቀርም:: ወጣቱና ኀያሉ ሶምሶን ተምና ወደ ተባለች ፍልስጤማዊ መን ደር ባይሔድ ፍልስጤማዊቷን ሴት ባላገኝ:: ነገር ግን ሔደ:: በእይታው በገባ ምኞት /መሻት/ ነፍሱ ተወጋ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የቅድስና ክብሩን ተራ በተራ ማጣት የጀመረው:: መሳ.14፥1-31::

ከነጻነት አበረ ሐሳብ ጋር የሚዛመድ አስተያየት የሰጠን ወጣት ዓለማየሁ ውቤ በበኩሉ እንዲህ ብሏል:- «ዓለም ከባድ ነች፤ ብዙ ፈተና አላት፤ በአለባበስ ትፈትንሃለች፤ ብዙ እኅቶቻችን ዛሬ ርቃናቸውን ገልጠው እየሔዱ ነው፤ ይህ ደግሞ ለባሹንም ሆነ ተመልካቹን ለፈተና እየዳረገ ነው:: ዐይንህ ያያል:: ለድርጊት ባትበቃም ውስጥህ ሊመኝ ይችላል:: ምኞቱም ሆነ ድርጊቱ በቅድስና ሕይወትህ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም::» በሰዎች ባሕርይ ላይ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ የዓለማችን ሊቃውንት እንደ ሚናገሩት ከሆነ ወንዶች በከፊልም ሆነ በምላት የተራቆተ የተቃራኒ ፆታ ሰውነት ካዩ ክፉኛ ይፈተናሉ:: ከነባራዊ እውነታ ማስረጃ መጥቀስ ቢያስፈልግ የተራቆተች ሴት ፎቶም ሆነ ሥዕል በብዛት ሲሸመት የሚታየው በወንዶች ነው:: ይህን የወንዶች ደካማ ጎን ያወቁና ደካማ መንፈስ ያላቸው ሴቶች ሰውነትን በሚያራቁት ወይም በሚያሳይ አለባበስ መታየት ከጀመሩ ቆይተዋል::

በዚህ የተነሣ በገዛ አለባበሳቸው የጥቃት ሰለባ የሚሆኑ ሴቶች ቁጥር ጨምሯል:: ይህን በመሰለ አለባበስ ለሚታዩ ሴቶች ማኅበረሰቡ እየሰጠ ያለው ግምት መልካም ነው:: ለማለት አይቻልም:: በአለባበስ ምክንያት በሚነሡ ምኞቶችና በሚፈጸሙ ኃጢአቶች የተነሣም የብዙ ወንድሞችና እኅቶች የቅድስና ሕይወት ተጎሳቍሏል:: በኃጢአት ላይ ለመወሰን የተዘጋጁትንም በማመንታት እንዲቆዩ እያደረገ ነው:: ሌሎችን ለመፈተን ብለው ሳይሆን ለመዋብና ራሳቸውን ደስ ለማሰኘት ብለው ይህን መሰል አለባበስ የሚጠቀሙ አሉ:: በየትኛውም ምክንያት ይሁን ችግሩ አለ:: በአንድ ወቅት ንጉሥ ዳዊት ቤርሳቤህ ሰውነቷን ስትታጠብ አይቷት ነበር:: እርሷ ግን ፈጽሞ አላየችውም:: በዚህ እይታ የተፈተነው ንጉሥ ከምኞት አልፎ ከእርሷ ጋር በዝሙት ወድቋል:: 2ሳሙ.11፥18:: ይህንና ይህን ተከትሎ በፈጸማቸው ኃጢአቶች ታላቁ ንጉሥ ብዙ ነገር አጥቷል:: በየትኛውም ዘመን የሚነሡ ወጣቶች የሚያዩትን፣ የሚሰሙትን፣ የሚያነቡትንና የሚውሉበትን ቦታ ካልመረጡ በመተላለፋቸው የተነሣ ቅድስናቸውን ሊያጡ ይችላሉ:: በሥጋ የሚታጨደው መከራም መረሳት የለበትም::

ወጣቶች ለዓላማቸው ከታመኑ፣ ራሳቸውንም በሥራ ከጠመዱና በጾም፣ በጸሎትና በስግደት ከበረቱ ፈተናዎችን ሊቋቋሙ ይችላሉ:: ቃለ እግዚአብሔርን ማወቅና ለቅድስና ሕይወት ከማይመቹ ቦታዎች፣ እይታዎችና የሚደመጡ ነገሮች መራቅ ደግሞ የብርታት ምንጭ ይሆናል:: እግዚአብሔርን በሥጋና በነፍሳቸው ከሚያከብሩ ባልንጀሮች ጋር መዋልም ከፈተና ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን የተቀደሰ ኑሮን ለመጀመር፣ በቅድስና ለመጽናት ይጠቅማል:: እንዲሁም የባዕዳንን ባህል ተቀብሎ ከመሮጥ ይልቅ ጥቅሙንና ጉዳቱን በአንክሮ መመርመር አስፈላጊ ነው፤ የሚበጀውን ለመውሰድ ጎጂውንም ለመጣል ይጠቅማልና:: ለዚህ ሁሉ ረድኤተ እግዚአብሔርን እየተማፀኑ የወጣትነትንና የብቸኝነት ሕይወትን በቅድስና ሕይወት ለማሸብረቅ መጋደል መልካም ነው::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

*ይቀጥላል::*





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ሰባቱ ኪዳናት

*ባለፈው እትማችን ሰባቱ ኪዳናት የሚገኙበትን የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊን 59 አንቀጾች ዝርዝር ይዘት፣የሰባቱ ኪዳናትን ማንነት ተመልክተናል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ከሰባቱ ኪዳናት አንዱ የኾኑትን የዘወትር ኪዳናት ይዘት እንዳስሳለን:: መልካም ንባብ::*

*(መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው)*

በዘወትር መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልደት እስከ ዕርገት ያደረገው የማዳን ጉዞ በስፋት ተሰብኳል:: «ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኀያል፣ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተወልደ እማርያም እም ቅድስት ድንግል ተሠሃለነ እግዚኦ፤ ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኀያል፣ የማይ ሞት ሕያው፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ፤ አቤቱ ይቅር በለን፤» ይህ እንግዲህ ከድንግል ማርያም የተወለደው መድኀን ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ኀያልነቱ፣ ሕያውነቱ /ዘላለማዊነቱ/፣ ክቡርነቱና ገናናነቱ የተገለጸበት ነው:: በአጠቃላይ ኀያልነቱ፣ ዘላለማዊነቱ፣ ጌትነቱ ሁሉ የተለየ እንደ ሆነም ያስረዳል:: ሰው ኀያል፣ ልዩ፣ ክቡር፣ ገናና... ቢባል የተለየ የባሕርይ ገንዘቡ ሳይሆን ከእግዚአብሔር በገድል በትሩፋት የሚቸረው ነው::

በዚህም ላይ የሰውን ልጅ ህብታም ቢሉት ድኀነት፣ ጻድቅ /እውነተኛ/ ቢሉት ሐሰት፣ ኀያል ቢሉት ድካም ይስማማዋል:: እግዚአብሔር ግን ድኀነት የሌለበት ባዕለ ጸጋ፣ ሐሰት የሌለበት እውነተኛ፣ ድካም የሌለበት ኀያል ነው:: ይህ ኀያል አምላክ በሰው ልጅ የፍቅር ሰንሰለት ተስቦ እኛን መውደዱና ማፍቀሩ ለሞት አድርሶታል:: «ፍቅር ስሐቦ ለወልድ ኀያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት፡ ኀያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞት አደረሰው::» /ቅዳሴ ማርያም/:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ» /ፊልጵ.2፥8/ ሲል እንደ ገለጸው ጌታችን ለእኛ ፍቅር ሲል ለአምላክነቱ የማይገባውን ሕማምና ሞት ተቀብሏል::

አይሁድ እንደ አንበሳ ሲያገሱ እንደ ግስላ ሲደነፉ በነበረበት በዕለተ ሞቱ የቁርጥ ቀን ወዳጆቹ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የአይሁድን ትችትና ግድያ ሳይሰቀቁ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋውን ከቅዱስ መስቀሉ አውርደው ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው አዲስ መቃብር ለመቅበር ይቀርባሉ:: እነርሱም ተፈቅዶላቸው ከመስቀል ካወረዱት በኋላ፡- «ሞትከኑ መንሥኤሆሙ ለምውታን፡ ደከምከኑ መጽንዒሆሙ ለድኩማን፡ ሙታንን የምታሥነሳቸው ሞትክን /ሞትክ ወይ/፡ የደከሙትን የምታጸናቸው ደከምክን /ደከምክ ወይ/፡» እያሉ ሲገንዙት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐይኖቹን ግልጥልጥ አድርጎ «እንደ ዕሩቅ ብእሲ ለምን እንዲህ እያላችሁ ትገንዙኛላችሁ? ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኀያል፣ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፡... እያላችሁ ገንዙኝ» ብሏቸው በዚህ መልኩ እንዳመሰገኑት ተጽፏል:: /መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ 1988 ዓ.ም፣ ገጽ 24/:: ይህም ቃል ነገረ ሃይማኖትን ያስተምረናል::

ቅዱስ የሚለው ቃል መሠረታዊ መገኛው «ቀደሰ» የሚለው የግእዝ ግስ ነው:: በትርጉም ረገድ፡- ለየ፣ አከበረ፣ አነጻ፣ አመሰገነ የሚል ፍቺ ይኖረዋል:: ታድያ በመጽሐፈ ኪዳን «ቅዱስ እግዚአብሔር፤ ልዩ የሆነ እግዚአብሔር» በማለት የተቀመጠው ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኀያልነቱ የተለየ መሆኑን የሚገልጽ ነው:: የጌታችን ልዩነቱ፣ ገዥነቱ እና ጌትነቱ እንደ ምድራውያን ነገሥታት በጉልበት፣ እንደ አሪት ካህናት በሀብት፣ እንደ ጣዖታት በሐሰት አይደለም:: ገዥነቱ እና ጌትነቱ የባሕርዩ ስለሆነ በተጥባበ ሥጋ ከተገኘ ማንኛውም ሥልጣንና የጌትነት ክብር የእርሱ የተለየ እንደ ሆነ ቃሉ ያስረዳል::

***«ልዩ ኀያል»*:-** በሚል ገላጭ የተቀ መጠው የእኛ አምላክ ኀያልነቱ ከኃይል መልአካዊ እና ኃይል ሥጋዊ ተለይቶ የባሕርዩ ነው:: ስለ ኀይል መልአካዊና ሥጋዊ የሉቃስ ወንጌል አንድምታ ምዕራፍ 1፥26 ይመልከቱ::

***ቅዱስ ሕያው*:-** «ልዩ ሕያው» እያሉ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ እንዲገንዙት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘዘው ቃል በውስጡ የሚከተለውን ፍሬ ነገር ያስጨብጠናል:: በዚህ ዓለም ሕይወት እንስሳዊ /የእንስሳት ሕይወት/፣ ሕይወት ሰብአዊ /የሰው ሕይወት/፣ ሕይወት መልአካዊ /የመላእክት ሕይወት/ አለ:: የእንስሳት ሕይወት በተፈጥሮ ይሰጣል፡ በሞት ይወሰዳል እንደ ተወሰደም ይቀራል:: የሰው ሕይወት በተፈጥሮ ይሰጣል፡ በሞት ይወሰዳል፡ በትንሣኤ ዘጉባኤ ይመለሳል:: የመላእክት ሕይወት በተፈጥሮ ይሰጣል፡ እንደ ተሰጠ ይቀራል:: ምክንያቱም መላእክት እንደ ሰዎች እና እንስሳት ሥጋዊ ሞት የለባቸውም::

***ጽኑዑ ክቡር*:-** ለእግዚአብሔር ባሕርይ የሚስማሙ ገጸተ ባሕርይ ናቸው:: የሰውን ልጅ ንጹሕ ቢሉት ጽድቅና ኃጢአት ይስማማዋል:: ነጭ ልብስ፡ - ጥቁር ቀለም፣ ቀይ ቀለም ቢቀቡት ሁሉን ይቀበላል:: ሰውም አንድ ጊዜ ወደ ኃጢአት አንድ ጊዜ ወደ ጽድቅ ሲል ይኖራል:: ለእግዚአብሔር ባሕርይ ግን ጽድቅ እንጂ ኃጢአት አይስማማውም:: «እስመ ንጹሐት እማንቱ ጠባዕያቲሁ ለእግዚአብሔር ዘእንበለ ነውር፡» እንዲል:: «አንተ ግን አንተ ነህ፡ ዘመንህ አያልቅም::» እንዳለ ቅዱስ ዳዊት:: መዝ. 101፥27:: ኀያል፣ ልዩ የማይሞትና ዘላለማዊ ለሆነው እግዚአብሔር ምልጃ እንደ ሚቀርብለት በመጽሐፈ ኪዳን እንዲህ በማለት ተገልጿል፡- «ተሠሃለነ እግዚኦ፡ አቤቱ ይቅር በለን::» ይህ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረት /ይቅርታ/ የሚጠየቅ መሆኑን ያመለክታል:: በዚህ ላይ ሊተኮር የሚገባው ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምልጃ የሚቀርብለት፣ የሰዎ ችን ጸሎት ተቀብሎ ይቅርታ የሚያ ደርግ ቸር አምላክ መሆኑን ነው::

ዘር ብእሲ ምክንያት ሳይሆነው ከድንግል ማርያም የተወለደው አምላካችን መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ግዕዘ ሕፃናትን ሳያፈልስ፣ እንደ ሕፃን እያለቀሰ ጡት እየለመነ የድንግል ማርያምን ሐሊበ ድንግልናዋን /የድንግልናዋን ወተት/ እየጠባ አድጓል:: በዚህም ዘመን የማይቆጠርለት አምላክ ዘመን ተቆጥሮለታል:: 30 ዓመት ሲሆነው በባሪያው በቅዱስ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቋል:: ስለዚህ በመጽሐፈ ኪዳን በድኅነት ሥራ ቅደም ተከተል ልደቱን ሰብኮ ጥምቀቱን እንዲህ ሲል ያስከትላል፤ «ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ፣ በዮርዳኖስ የተጠመቀ»

ታድያ ክብር ይግባውና በዮርዳኖስ የተጠመቀው በራሱ በደል ኖሮበት፣ ለድምሳሴ ኃጢአት አለመሆኑን ሲያስረዳ፡- «ኀያል፣ ልዩ ዘላለማዊ» ይለዋል:: ይህ ጥምቀት የሚያስፈልገው ለእርሱ ሳይሆን ከጸጋ እግዚአብሔር ለተራቆተው የሰው ልጅ መሆኑን ማጤን ያሻል:: ኀያል የሆነው አምላክ ለአርአያ /ለአብነት/ ተጠምቋል:: ይሁንና እርሱ ግን ልዩ ኀያል፣የማይሞት /ዘላለማዊ/ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ ልጅነትን፣ በስቅለቱ ነጻነትን አስገኝቶልናል:: በርባን ተፈቶ በፈንታው ክርስቶስ የተሰቀለው ስለዚህ ነው:: የጌታችን ጥምቀቱና ስቅለቱ በመጽሐፈ ኪዳን በአንድ አንቀጽ ውስጥ ቀርበዋል:: «ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል፡ በዮርዳኖስ የተጠመቀ፣ በእንጨት መስቀል ላይ የተሰቀለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ፣ ኀያል፣ ሕያው /ዘላለማዊ/ አምላክ ነው::» ሮሜ.9፥9::

በዕለተ ስቅለቱ መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ምሕረቱን ለቋንጃ ቆራጩ ፈያታዊ ዘየማን አድርጓል:: ለቋንጃ ቆራጩ ሽፍታ ያደረገውን አምላካዊ ይቅርታውን መሠረት በማድረግ በዕንጨት መስቀል ላይ የተሰቀለው የባሕርይ አምላክ ለኃጢአት፣ ለበደልና መተላለፍ ምሕረትና ይቅርታ ሊጠየቅ እንደ ሚገባ ሲያመላክት፡- «ተሠሃለነ እግዚኦ፡ አቤቱ ይቅር በለን» ይላል:: ከድንግል ማርያም የተወለደው፣ በዮርዳኖስ የተጠመቀው እና ለቤዛ ዓለም በመልዕልተ መስቀል የተሰቀለው አምላክ ይወዳቸው ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ እና ያገለግሉት ለነበሩት ቅዱሳት አንስት ብርሃነ ትንሣኤውን መግለጹ ይታወቃል:: ዮሐ.21፥21:: በመጽሐፈ ኪዳን ከሦስት ቀን በኋላ ሞትን አሸንፎ መነሳቱን ሲያስተነትን እንዲህ ይለናል፡- «ዘተንሥአ እሙታን አመሣል



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስት ዕለት፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ» በማለት ብርሃነ ትንሣኤውን ይነግረናል፡፡

በፈጸመው ቤዛነት ለነፍስም ለሥጋም ከሦ ትንሣኤውን ገሃድ ያደረገው ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ በተለያዩ ጊዜያት ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጸ እያስተማራቸው እያጽናናቸው ቆይቶ በ40ኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐርጓል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን የምትጠቀምበት መጽሐፈ ኪዳን ነገረ ዕርገቱን፣ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ዕሩይ /እኩል፥ ትክክል/ መኾኑን ፍንትው አድርጐ ሲሰ ብክ «በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ፡ በአባ ቱም ቀኝ ተቀመጠ፡፡» ይላል፡፡

በመጨረሻ ለጻድቃን ዋጋ ለኃጥአን ፍዳ ሊሰጥ ቸሩ አምላክ ወደዚህ ዓለም እንደ ሚመጣ በነቢያት በትንቢት ተነግሯል፡፡ በሐዋርያትም ተሰብኳል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ መምጣቱን ሲገልጽ ደግሞ፡- «ዳግመኛም በጌትነት ይመጣል በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ» ይላል፡፡ በጥቅሉ የመጽሐፈ ኪዳን መግቢያ ጌታ ከልደቱ እስከ ዕርገቱ ያደረገውን፣ ከዕርገቱ በኋላ ለፍርድ እንደ ሚመጣና የፍርድ ሥራ እንደ ሚሠራ ተብራርቶ ተቀምጧል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ በኪዳን ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልደት እስከ ዕርገት ያደረገውን የድኅነት ሥራ ትሰብካለች፡፡ ነገረ ምጽአቱን ታዘክራለች፡፡ በዚህም ልደቱን፣ ጥምቀቱን፣ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዕርገቱን፣ ዳግም ምጽአቱን እያሰቡ ይኖራሉ፡፡ ዘወትር ማለዳ ወደ ኪዳን ሲሔዱ በዕዝነ ልቡና ኪዳኑን አድምጠው ከነፍሳቸው አዛምደው መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት በምስጋና ይጀምራል፡፡ መንፈቀ ሌሊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤውን የገለጠበት፣ የጌታ ጠላት የሆኑ አይሁድ ያፈሩበት እና በሌላ ወገን ደግሞ በምድር ያሉ ደቀ መዛሙርቱ እና በሲኦል ያሉ አዳም እና ልጆቹ የተደሰቱበት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ክፍል በአብዛኛው *«ምስጋና»* ሲቀርብ እናስተውላለን፡ «አቤቱ፥ ሁሉን ለፈጠርኽ ለማትመረመር ለአንተ ስውነታችንን እና ቀርባለን /እናስገባለን/፡፡ አቤቱ፥የነግህ ምስጋናን እናቀርብልሃለን፡፡»ከዚህ በማስከተል የኢየሱስ ክርስቶስን ሁሉን ዐዋቂነቱን፣ ኀያልነቱን፣ ቸርነቱን፣ ፈጣሪነቱን፣ የቅድመ ዓለም ልደቱን ይተነትናል፡፡ «የፍጥረቱ ሁሉ ዕውቀት፣ ኀያል የምትሆን አንተ፣ ይቅርታህ የበዛ ፈጣሪ፣ ነፍስን የፈጠርኽ፣ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ከአብየተወለድህ አንተን እናመሰግንሃለን፡፡» ይላል፡፡

እነዚህ የሕይወት ቃላት መሠረት የሚያደርጉት ቅዱስ መጽሐፍን ነው፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስውነትን ማስገዛት እንደ ሚገባ ተነግሯል፡፡ «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፡፡» /ፊልጵ. 2፥10/ እንዲል፡፡ ምስጋና የሚቀርብለት መሆኑ፣ ኀያልነቱ፣ ቸርነቱ፣ ፈጣሪነቱ በጥቅሉ «ዓለሙም በእርሱ ሆነ» ተብሎ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ መጽሐፈ ኪዳን መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡



ኦ ዘገነዙከ በሰንዱናት በእንተ:ኣነ ስምዓነ አምላክነ ወመድኃኒነ /ጌታችንን እንደ ገነዙት/

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ቃል መሆኑ፣ በቅዱሳን ላይ በረድኤት አድሮ መኖሩ፣ በቅዱሳን መላእክት ምስጋና እንደ ሚቀርብለት፣ ምስጋና ይግባውና ዕሩቁ ብእሲ /ፍጡር/ አለመሆኑ፣ በፈጣሪነት የማይታዩ ፍጥረታትን መፍጠሩ፣ በሥጋዊ ጥበብ የማይ መረመር መሆኑ በገለጻ መልክ ቀርቧል፡፡ «የብቻው የአብ ቃል የምትሆን፣ በቅዱሳን አድሮባቸው የሚኖር፣ አርምሞ ጽርዓት በሌለበት በሊቃነ መላእክት ቃል የምትመሰገን፣ አለቆች ያሏቸው ሠራዊተ መላእክት የሚያመሰግኑህ፣ «በእጅ ያልተፈጠርኸ፣ የማይታዩትን ፍጥረታት የፈጠርህ፣ የማትመረመር ፈጣሪ ንጹሕ ቅዱስ፡፡» ይላል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ ቃል ስለ መሆኑ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ፡- «በመጀመሪያ ቃል ነበር፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፡፡» ይለናል፡፡ ዮሐ1፥1፡፡ በቅዱሳን አድሮ መኖሩን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ፡- «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን ለነቢያት ተናግሮአል፡፡» /ዕብ.1፥1/ ማለቱ በነቢያት ላይ በረድኤት ማደሩን ያመለክታል፡፡ «ሁሉ በእርሱ ሆነ» በማለት ቅዱስ ዮሐንስ የሰበከውን መለኮታዊ ቃል በመጽሐፈ ኪዳን፡- «የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረታት የፈጠርህ» በማለት ማጠናከሩን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

እንግዲህ መጽሐፈ ኪዳን በመጀመሪያ የጌታን የድኅነት ሥራ ከዘረዘረ በኋላ ለዚህ የቸርነት ሥራው መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና እንደ ሚገባው ሲያመለክት፡- «አቤቱ፥ፍጹም ምስጋና ለአንተ እናቀርባለን፡፡» ይላል፡፡ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ፈርሶ በምትኩ ዕርቅ ሰላም መስፈኑን ሲተነትን ደግሞ፡- «እኛ ቤተ ሰዎችህ አገልጋዮችህ እናመሰግንሃለን» በማለት በምስጋና ጀምሮና ነገረ ድኅነትን አመልክቶ በምስጋና ይደመድማል፡፡

*አምላከ ብርሃን /የብርሃን አምላክ/:* - በማለት የመጀመሪያው ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃናትን የፈጠረ ወይም «ለይኩን ብርሃን፣ ብርሃን ይሁን» /ዘፍጥ.1፥3/ በማለት የብርሃን አምላክ መሆኑን ይገልጣል፡፡ በጥንት ዘመን ደገኛው አብርሃም በጥበብ መንፈሳዊ አምላኩን መፈለጉ ይታመናል፡፡ በውኃ፣ በነፋስ፣ በእሳትና በፀሐይ ያደረገው አምላኩን የመፈለግ ምርምር፡- «አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ፡ የፀሐይ አምላክ ሆይ፥ ተናገረኝ» ከማለት አድርሶታል፡፡ በመጽሐፈ ኪዳን አብርሃም የተማፀነው የብርሃን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የብርሃን አምላክ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የሕይወት መገኛ፣ የዕውቀት መጀመሪያ እርሱ ነው፡፡ ለሰዎች በሕይወት መመላለስ መሠረቱ እርሱ ነው፡፡ የዕውቀት ሁሉ መጀመሪያ ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ሲያብራራ፡- «የብርሃን አምላክ ሆይ፥ የሕይወት መገኛ፣ የዕውቀት መጀመሪያ /መኖሪያ/፣ ከደገኛው ክብር አስቀድሞ የዐረቦኑን ክብር የሰጠኸን፣ ነፍስን የፈጠርህ» በማለት ተገልጿል፡፡ እነዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚገልጹ ቃላት መሠረታቸው ከላይ እንደ ተመለከትነው ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ የብርሃን አምላክነቱን በደረቅ ግንባር ላይ ዐይን በመፍጠር፣ የሕይወት መገኛ መሆኑን ለማጠየቅ ከሞተ አራት ቀን የሆነውን አልዓዛርን በማስነሣት፣የዕውቀት መጀመሪያነቱን ሕፃናተ አእምሮ የነበሩ ሐዋርያትን በዕውቀት መንፈሳዊ ማበልጸጉ ከላይ ለተገለጸው ፍሬ ነገር ዐይነተኛ ማሳያ ይሆናል፡፡ ዮሐ.9፥5፣ ዮሐ.11፥25፣ 1ቆሮ.1፥36፡፡

*«መንፈስ ቅዱስን በመስጠት የሚጠቅም»*፡ ጌታችን፡- «እኔ እሔዳለሁ፡ አጽናኙን መንፈስ ቅዱስ እልክላችኋለሁ፡ እርሱ በመጣ ጊዜ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ነበራችሁና ትመሰክራላችሁ» ብሎ እንደ ተናገረ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጸጋን የሚሰጥ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ የሚያመላክት ነው፡፡

በማስከተል የተገለጸው ደገኛ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ለትሑታን ጥበብን የሚገልጽ መሆኑ ነው፡፡ ሰዎች ጠቢብ ቢባሉ ከእግዚአብሔር ባገኙት ዕውቀት ነው፡፡ የጸጋ ሁሉ መገኛ እግዚአብሔር ነው፡፡ በቅዱሳን ላይ በብሉይ ኪዳን በረድኤት በማደር ማስተማሩ፣ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በአካል ከሥት ሆኖ ማስተማሩ፣ የዓለም ሁሉ መነሻ መሆኑ እንዲሁም በትሑት ሰብ እና ሆነው የሚጸልዩ ምእመናንን ጸሎት የምትቀበል እርሱ እንደ ሆነ እና ለአብ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጅ እንደ ሆነ ሲያስረዳ፡- «የጥበብ መገኛ፡ የቅዱሳን ምመህር፡ ረዳት የምትሆን፣ የዓለም መሠረት፣ የንጹሐንን ጸሎት የምትቀበል ተቀዳሚ ተከታይ የሌለህ ወልድ ዋህድ» ይለዋል፡፡

«የንጹሐንን ጸሎት የሚቀበል» በማለት የተነገረው ቃል በንስሐ ከኃጢአት፣ ከቂምና በቀል በይቅርታ ንጹሐን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በመሆን ሰዎች የሚያቀርቡትን ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሚቀበለው ለማስረዳት:: «ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት» እንዲሉ ሰዎች ከቂምና ከበቀል የነጻ ሕይወት ሳይዙ እንባቸውን ቢያፈሱ፣ ቢወድቁ ቢነሡ፣ ቢጸልዩ እግዚአብሔር አይቀበልም:: «እስመ ዘያነብር ቂመ ወበቀለ ውስተ ልቡ ኢውክፍት ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር፤ ቂምና በቀልን በልቡ ውስጥ የሚያኖር ጸሎቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የላትም::» ተብሎ እንደ ተጻፈ መጽሐፈ ኪዳን ሰዎች ከቂምና በቀል ጸድተው መጸለይ እንደ ሚገባቸው ሥርዐተ ጸሎትን ያውጅልናል:: እንዲሁም የንጹሐን ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር ተቀባይነት እንዳለው ያረጋግጥልናል:: ለዚህ ሁሉ ደገኛ ግብሩ ከሰው ወገን ምስጋና እንደ ሚገባው ሲገልጽ ደግሞ «አንተን እናመሰግንሃለን» ይላል::

### ቀዳሜ በኩር

በኵር፣ ከሰው ወይም ከከብት ወገን ማኅፀንን የሚከፍት፣ በመጀመሪያ የሚወለድ ማለት ሲሆን ብዙውን ጊዜ ለወንድ ፆታ ይነገራል:: «እግዚአብሔር ከግብጽ ባርነት እስራኤልን ስለ አዳነ የእስራኤል በኵር ሁሉ የእግዚአብሔር ሆነ ይላል::» ዘጸ.12፥12:: በሐዲስ ኪዳን ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለድንግል ማርያም የበኵር ልጅ በመሆኑ እና በሙሴ ላይ በረድኤት አድሮ የሠራውን ሕግ ለመፈጸም በቤተ መቅደስ መሥዋዕት ቀርቦለታል:: ሉቃ 2፥7-27:: ዓለምን ፈጥሮ የሚታየውንና የማይታየውን ስለ ሚገዛ የፍጥረት በኵር /የፍጥረት አለቃ/ ተብሎአል:: ቆላ. 1፥15:: እንዲሁም ሞትን በሞቱ አሸንፎ ብርሃነ ትንሣኤውን ስለ ገለጸልን በትንሣኤው «በኵረ ምውታን» /የሙታን በኵር/ እንለ ዋለን:: ቈላ.1፥18:: ራእ. 1፥5::

ይህ ቀዳማዊ የሆነ የአብ አካ ? ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕር ፡ ነውር ነቀፋ የሌለበት ሰው ወዳጅ መሆኑን:- «አብ ንጹሕ ዘአልቦ ነውር፤ ነውር ነቀፋ የሌለብህ ልዩ አባት» ይለዋል:: መጽሐፈ ኪዳን እንደ መሰከረልን እኛም እንደ ምናምነው ጌታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ልዩ አባት ነው:: በአምላክነቱ በቸርነቱ መሐሪ፣ ደግ፣ ነቀፋ የሌለበት ማን እንደሱ አለ:: ይህን የመሰለውን ቸርነቱን ለማን እና እንዴት እንደ ሚሰጥ ሲያብራራ:- «ብል የማይበላው፣ ነቀዝ የማያበላሸው ገንዘብ ያለህ፣ በፍጹም ልቡናቸው ለሚያምኑብህ የምትሰጥ» ይላል:: ይኸውም በፍጹም ልቡ ለሚያምንበት ሰው ጸጋ እግዚአብሔር እንደ ሚሰጠው ያስገነዝባል::

በዓለመ መላእክት በቅድስና የሚኖሩ ብርሃናውያን መላእክት «ቀዳሜ በኩር» የሆነውን አምላክ ምን ያህል እንደ ሚወዱትና ያላቸውን ተስፋ ሲያስረዳ:- «ዘያፈትዎሙ ለመላእክት የሐውጽዎ ለዘእም ቅድመ ዓለም ብርሃን፤ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ብርሃን ባሕርይህን ያዩት ዘንድ መላእክትን ደስ የሚያሰኛቸው::» ይለናል::

ቅዱሳን መላእክት በመንበሩ ፊት ኾነው ጌታችንን መልሰው መላል ሰው ቢያዩት አይጠግቡትም:: «ስለዚህ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ብርሃን ባሕርይህን ያዩት ዘንድ መላእክትን ደስ የሚያሰኛ ቸው፤» አለ:: ለምሳሌ:- ለአንድ ሰው «አ ዲስ ነገር መጣ፣ ወጣ» ብለን ብንነግረው ያንን አዲስ የተባለውን ነገር እስኪያየው ድረስ ይቸኩላል:: ካየው በኋላ ግን ይሰለ ቸዋል፣ ይጠግበዋል፤ እርሱን ግን ቢያዩት አይሰለቹም::

መጽሐፈ ኪዳን ወደ ረቂቅ የመላእክት አገልግሎት በመዝለቅ ድንቅ ድንቅ የምስጋና ተምኔት መኖሩን እንደ ሚነግረን:- ቅዱሳን መላእክት ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ እግዚአብሔርን አመስግነውት አንዱን ሰዓት ለአራት ከፍለው የሩቡን እንኳን ያህል ያመሰገኑት አይመስላቸውም:: ይህ ከሰዎች ሕይወት ጋር ሲነጻጸር ሰው አምላኩን ከማመስገን ምን ያህል መራቁን በግልጽ ያመላክታል::

ሌላው በመጽሐፈ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ፈቃድ፣ በባሕርይ አባቱ ፈቃድ እና በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ለሰው ያደረገውን ቸርነት ይነግረናል:: «በእኛ የነበረውን ጨለማ በአባትህ ፈቃድ ያራቅኸልን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ያመጣኸን፣ ከሞት አድነህ ሕይወትን የሰጠኸን፣ ለኃጢአት /ለዲያብሎስ/ ከመገዛት ነጻ ያወጣኸን፣ በመስቀልህ በሰማይ ወዳለው ወደ አባትህ ያቀረብከን::» ይላል:: በማስከተል ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ በነቢያት ላይ በረድኤት አድሮ ሰውን ማረጋጋቱን በወንጌል ደግሞ የሕይወት መንገድ መምራቱን በዚሁ ክፍል ይገልጻል፤ «አቤቱ፥ በወንጌል የሕይወትን መንገድ መራኸን፤ በነቢያት አረጋጋኸን::» ይላል:: እንግዲህ መጽሐፈ ኪዳን እንዲህ ዐይነት ትምህርት የያዘ በመሆኑ ኪዳን ስናደርስ በማስተዋል ልናደምጥና ልንከታተል ይገባል::

### ከሁሉ በላይ መሆኑ

ቃለ እግዚአብሔር፣ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል ትክክል የሆነ የባሕርይ አምላክ ነው:: የፍጥረታት አስገኝ /ፈጣሪ/ በመሆኑ ከፍጥረት ሁሉ የበላይ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል:: መጽሐፈ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዓለምን እንደ ሚገዛ በጥልቀት ይሰብካልና፤ «ከአብ ጋር እንደ አብ ሁሉን የምትገዛ፣ የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትህ የዘላለም ነው::» ይላል:: መጽሐፈ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስን ዘላለማዊነት የሚነግረን ከቅዱስ መጽሐፍ ተነሥቶ እንደ ሆነ ማጤን ያስፈልጋል:: ነቢዩ ዳዊት «ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ::» /መዝ.89፥2/ ይላል:: በሐዲስ ኪዳን ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በበኩሉ:- «እርሱ ዓለምን ፈጠረ፤ ነገር ግን በጊዜ አይወሰንም» በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ዘላለማዊነት ጽፎልናል:: 2ኛ ጴጥ.3፥8::

መጽሐፈ ኪዳን የጌታን ዘላለማዊነትን ብቻ ሳይሆን የሚነገረን ለዘላለማዊነቱ የሚገባውን ክብር ጭምር ነው:: ከምንም በላይ ለእርሱ የከንፈራችንን ፍሬ ምስጋና ማቅረብ እንደ ሚገባን ሲያመላክተን ደግሞ:- «አቤቱ፥ አምላካችን ሆይ፥ ክቡር መንግሥት የአንተ ነውና ፍጻሜ የማይፈጸም ምስጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን::» ይለናል:: ስለዚህ መጽሐፈ ኪዳን እነዚህን የሃይማኖት ፍሬ ነገሮችን በመያዙ በማስተዋል ልንረዳውና ልንጠቀምበት ይገባል:: ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## ወቅታዊው የቤተ ክርስቲያን ...

/ከገጽ ፱ የዞረ/

ታሪክና ያለንበት እውነታ ቢሆንም የእ፡ ንዴዜሞን ቱቱ ተሞክሮ ራሳችንን እንድንመለከት የሚጋብዘን ነው::

ዴዝሞን ቱቱ ስለ ሩዋንዳ ጉብኝታቸው ሲያስታውሱም በአገሪቱ ብዙ ሰዎች ያለፈውን ስሕተት በሙሉ በፍርድ ቤት ፍትሕ ለማረም ይመኙ እንደ ነበር ይገልጻሉ:: «ባለጊዜ» «ቀን በጣለው ላይ» የሚሰጠውንና ነገ ደግሞ ሌላው ባለተራ በባላንጣው ላይ የሚደግመውን *የ«በቀል ፍትሕ» /Retributive Justice/* *በ«ተሐድሶ ፍትሕ» /Restorative Justice/* መተካት ካልተቻለ አገሪቱ ከገባችበት የበቀል አዙሪት እንደ ማትወጣ ለሩዋንዳውያን መንገር ለቱቱ ግዴታቸው ነበር:: አድርገውትማል:: ከዚህ አዙሪት የመውጫው ብቸኛ መንገድም ዕርቅና ይቅርታ ብቻ መሆኑን ተናግረዋል:: ለዚህም ይመስላል መጽሐፋቸውን NO FUTURE WITHOUT FORGIVENESS የሚል ርእስ የሰጡት::

በቤተ ክርስቲያናችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ስለ መፈጠራቸው የማንበብ ዕድል ባይገጥመኝም ቀደም ባሉት ዘመናት ግን ሊጠቀሱ የሚችሉ ታሪኮች መኖራቸው እሙን ነው:: የአንዳንድ ነገሥታትን አምባገነንነትና የጭካኔ ተግባር የተቃወሙ፣ ለጦርነት የተሰላለፉ የአካባቢ ገዢዎችን ማልደውና በፍቅር ተቆጥተው ያስታረቁ ወዘተ.. የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንደ ነበሩ ማስታወሱ በራሱ በቂ ምሳሌ ነው:: እኒህን አብነቶች እየቀነጫጨብኩ ያቀረብኩት የቤተ ክርስቲያን የማስማማት፣ የማስታረቅና የመገሠጽ ሐላፊነት አዲስ ነገር አለመሆኑን ለመጠቆም ያህል ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ቤተ ክርስቲያን ለብቻዋም ሆነ ከሌሎች የእምነት ተቋማት ጋር በመሆን በአገራችን ልዩ ልዩ ቦታዎችና ምክንያቶች የሚነሡ ግጭቶችንና አለመረጋጋቶችን በሰላም፣ በውይይት፣ በዕርቅ፣ ሁሉም ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ የሚፈቱበትን መንገድ በማፈላለግ ተግባሯ ልትገፋበት እንደ ሚገባ ለማስታወስ ነው:: ይህም መላው ምእመናንዋና የአገሪቱ ዜጎች ከታላቋ ቤተ ክርስቲያን አጥብቀው የሚፈልጉትና የሚጠብቁት ወቅታዊ ሚና ይመስለኛል::

ቤተ ክርስቲያን መሪ አስታራቂ መሆን አለባት ሲባል አጥፊውንም ተጎጂውንም በደፈናው ታረቁ ትላለች ማለት አይደለም:: ማስታረቅ የተቃረኑት ወገኖች እርስ በርስ እንዲተማመኑ፣ ሁሉም ወገኖች ጥፋታቸውን በዝርዝርና በትክክል እንዲያምኑ ማድረግን፣ ለነዚህ ጥፋቶች የዳረጉትን ሁኔታዎች መመርመርን፣ ተጎጂውም በአግባቡ የሚካሥበትን፣ ከጭፍን እልህና ከቂም በቀል የሚጠበቅበትን መንገድ ማፈላለግን ወዘተ.. የሚያጠቃልል ታላቅ ታማኝነትንና የመንፈስ ልዕልናን የሚጠይቅ ሐላፊነት ነው:: ይህን የመሰለ መስማማትና ዕርቅ በዴዝሞን ቱቱ አገላለጽ *«መታደስን የሚያመጣ ፍትሕን»* ያጎናጽፋል:: አገራችን ከዚህ መሰሉ ፍትሕ ተጠቃሚ እንድትሆን ቤተ ክርስቲያናችን ያላት ታላቅ ሚና በማንምና በምንም የማይተካ ነው::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ

/መምህር ደጀኔ ሺፈራው/

*ባለፈው እትማችን፡- ማለትም በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም ላይ ኅብስቱን ወደ ቅዱስ ሥጋነት ወይኑን ወደ ክቡር ደምነት ከሚለውጡት የምስጋና ጸሎቶች መካከል የታላቁን አባት የቅዱስ ባስልዮስን ጸሎት በሚገባ ተመልክተናል፡፡ በአሁኑ እትማችን ደግሞ የተቀረውን በሚከተለው መልኩ ከነገረ ድኅነት አንጻር ለማየት እንሞክራለን፡፡ የምንጀምረውም ከጸሎተ መባእ ዘሐዋርያት ነው፡፡*

## ጸሎተ መባእ ዘሐዋርያት

በዚህ ጸሎት ንፍቁ ካህን መሥዋዕቱን ዐሥራቱን ስላመጡ ሰዎች ይጸልያል፡፡ ከዚህም ጋር በማያያዝ ይኸን ሁሉ ለመስጠት እየፈለጉ ልባዊ ምኞት እያላቸው እጅ ስላጠራቸው /ስለ ቸገራቸው/ ሰዎችም ምኞታቸውን መባ አድርጎ እንዲቀበልላቸው ይጸልያል፡፡ ዐሥራት ያለው ከዐሥሩ መካከል አንዱ የእግዚአብሔር በመሆኑ ነው፡፡ ቀዳምያት የሚባለው ደግሞ፡- ከአዝመራው የመጀመሪያውን ፣ ከእንስሳትም ከልጅም ቀድሞ የተወለደውን ለእግዚአብሔር መስጠት ስለሚገባ ነው፡፡ መሥዋዕት የተባለው ደግሞ ለአማናዊው መሥዋዕት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ለቅዱስ ቊርባኑ የሚሆን ስንዴውንና ወይኑን በማምጣታቸው ነው፡፡ ደጋግ ምእመናን መሥዋዕቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጡት ከዐሥር አንዱን /ዐሥራቱን/ ለእግዚአብሔር ከሰጡ በኋላ ከተቀረው ከዘጠኙ ላይ ነው፡፡ ይህም ትልቅ መሥዋዕትነት ነው፡፡ ስለ እነርሱ በመስቀል ላይ ተሠውቶ ድኅነታቸውን ለፈጸመላቸው ጌታ የሚሰስቱት ነገር የለም፡፡ ሕይወታቸውን፥ ገንዘባቸውን፥ ትዳራቸውን፥ ጊዜአቸውን፥ ዕውቀታቸውን፥ ጉልበታቸውን ሁሉ መሥዋዕት አድርገው ያቀርቡለታል፡፡ «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፣ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው፡፡» እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ ሮሜ.12፥1፡፡

ዲያቆኑም «መባ ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ» ብሎ ያውጃል፡፡ በዚህን ጊዜ ሕዝቡ በጠቅላላ «የወንድሞችንና የእኅቶችን የእኛንም መባና ቊርባን ተቀበል» እያሉ ይጸልያሉ፡፡ ንፍቁ ካህን ደግሞ ጸሎተ መባን ለሁለተኛ ጊዜ ይጸልያል፡፡ በቤተ ክርስቲያን የሚቀርበው መባ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ምክንያቱም መባ ማለት ስጦታ ማለት በመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስም አብ የሰጠን የአዲስ ኪዳን መባ ነው፡፡ ይኸንም ራሱ ጌታችን፡- «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡» በማለት ነግሮናል፡፡ ዮሐ.3፥16፡፡ ለምሳሌ፡- መባ ሆኖ የሚቀርበውን ጧፉን፣ ዕጣኑን ብንመለከት የምሳሌውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ ጧፍ እየነደደ /እየሞተ/ ለሌላው ብርሃን ይሆናል፡፡ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ሞቶ የሕይወት ብርሃን ሆኖልናል፡፡ እርሱም «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤» ብሏል፡፡ ዮሐ.8፥12፡፡ ዕጣኑም በእሳቱ እየተቃጠለ /እየሞተ/ መዓዛ ይሰጣል፡፡ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ሞቶ መዓዛ ሕይወት ሆኖልናል፡፡ ቀዳምያቱም ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብም ለእናቱ ለድንግል ማርያምም ተቀዳሚ የበኲር ልጅ ነውና፡፡ ማቴ.1፥25፤ ሉቃ.2፥7፤ ዕብ.1፥6፡፡

## ጸሎተ እንፎራ

ጸሎተ እንፎራ ማለት ጸሎተ ኅብስት ማለት ነው፡፡ ይኸን ጸሎት የሚጸልየው ዋናው ካህን ነው፡፡ የሚጸልየውም በኅብስቱና በወይኑ ላይ ነው፡፡ «መምህሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ ከቀዳማዊ አብ ጋር አንድ የምትሆን ንጹሕ የሚሆን የአብ ቃል የማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ቃል ከሰማያት የወረድህ የሕይወት ኅብስት አንተ ነህ፡፡ ስለ ዓለሙ መዳን ነውር የሌለበት መሥዋዕት እንድትሆን መናገርን አስቀደምህ፡፡» የሚለውን ኃይለ ቃል እየጠቀሰ ይማልዳል፡፡ ይህም «በመጀመርያው ቃል ነበረ፤» ዮሐ.1፥1፡፡ «ከሰማይ የወረደ ሕያው ኅብስት እኔ ነኝ፤» /ዮሐ.6፥51/ ከሚለው የወንጌል ቃል ጋር አንድ ነው፡፡ «አስቀድመህ ተናገርከ» ማለቱም አስቀድሞ በነቢያት አድሮ መናገሩን ማናገሩን ለመጥቀስ ነው፡፡ ይኸውም ነቢዩ ኢሳይያስ፡- «ተጨነቀ፣ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፥ ልመታረድ እንደ ሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደ ሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም፡፡» ብሎ መናገሩን ለማመልከት ነው፡፡ ኢሳ.53፥7፡፡ «ነውር የሌለበት» በማለትም በባሕርዩ ንጹሕ መሆኑን ይመሰክራል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ነገረ ድኅነትን ነው፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር መጥምቀ መለኰት ቅዱስ ዮሐንስ፡- «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤» በማለት ከመሰከረው ጋር አንድ ነው፡፡ ዮሐ.1፥29፡፡

ካህኑ በዚህ ጸሎት የሚማፀነው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኰት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኰት እንዲሆንለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ኅብስቱንና ጽዋውን በማኅፈድ እየሸፈነ «ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በውስጡ በኖርህበት መቃብር አምሳል በዚህ በተባረከ ጻሕል ላይ አኖርን፡፡ እጆቼንም ሥጋህን እንደ ገነዙት እንደ ዮሴፍና እንደ ኒቆዲሞስ እጆች አድርጋቸው፡፡» የሚለውን የመግነዝ ጸሎት ይጸልያል፡፡ በዚህም ጻሕሉ የመቃብሩ ማኅፈዱ ደግሞ የመግነዙ ምሳሌ መሆኑን አስረድቷል፡፡ በጸሎቱም ዮሴፍን እና ኒቆዲሞስን አንሥቷል፡፡ እንደ እነርሱ እንዲያደርገውም ተማፅኗል፡፡ ዮሴፍ፥ ኒቆዲሞስ ጌታን ያገኘው መከራ ሁሉ እኛን ያገኘናል ብለው ሳይፈሩ ከጲላጦስ ተካስው፥ ከመስቀል አውርደው «ሞትን ያሸነፍከው ሆይ፥ ያንተ ሞት ምን ዐይነት ሞት ነው?» እያሉ ከማድነቅ ጋር ገንዘውታል፤ ስመውታል፤ አክብረውታል፡፡ ጌታም በመለኰቱ ሕያው እንደ ሆነ ለማጠየቅ ዐይኑን ግልጽልጽ አድርጎ «ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ሆይ፥ ሥጋዬን እንደ ሳማችሁ፥ እንደ ገነዛችሁና እንዳ ከበራችሁ እኔም በሰማይ እስማችኋለሁ፥ አከብራችኋለሁ» ብሏቸዋል፡፡ ካህኑ ፍትሐት ዘወልድን ካነበበ በኋላ ዋናው ዲያቆን በእንተ ቅድሳት የሚለውን የምልጃ ጸሎት ይጸልያል፡፡

## ጸሎተ ዕጣን

ዲያቆኑ የምልጃውን ጸሎት ከጨረሰ በኋላ፡- ዋናው ካህን አምስት ቆቀር ዕጣን አዘጋጅቶ እየባረከ ጸሎተ ዕጣንን ይደግማል፡፡ በጸሎቱ ውስጥም፡- «የወዳጅህን የአቤልን ቊርባን፥ የሔኖክንና የኖኅን የአብርሃምንም መሥዋዕት፥ የአሮንና የሳሙኤልን የዘካርያስንም ዕጣን እንደ





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ወደድህ እንዲሁም ይህን ንጹሑን ዕጣን ከኔ ተቀበል።» እያለ ይማፀናል። ይህም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ እንደ ተመለከትክ ወደ እኔና ወደ መሥዋዕቴ ተመልከት ማለቱ ነው። ዘፍ.4፥4። ኖኅን በተመለከተም፡- «ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ፥ ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ ከንጹሐን ወፎችም ሁሉ ወሰደ፥ በመሠዊያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ። እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ፤» ተብሎ ተጽፏል። ዘፍ.8፥20። የሌሎቹም ይኸንኑ የመሰለ ነው። ምሳሌነታቸውም ጌታችን ለድኅነተ ዓለም በመስቀል ላይ ለፈጸመው መሥዋዕትነት ነው። የመሠዊያው ምሳሌነት ደግሞ በቀራንዮ ለተተከለው መስቀል ነው። በመጨረሻም፡- «ነባቢት መሥዋዕትን ወደ ውስጠኛዪቱ መጋረጃና የዘላለም ማደሪያህ ወደ ምትኾን ወደ ቅድስተ ቅዱሳንም ውስጥ የምታገባ የበረከትን መሥዋዕት እንሠዋ ዘንድ ስጠን።» ብሎ ይጨርሳል። ትርጉሙም፡- «ምስጋናህ ወደ ሚነገርበት ቤተ መቅደስ፥ አንድም ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ተብለህ ወደ ምትመሰገንበት መንግሥተ ሰማያት የምታገባ መክበሪያ ነባቢ የምትሆን /የምትናገር/ መሥዋዕትን /ሥጋህን እና ደምህን/ በባለሟልነት ሁነን እንሠዋ ዘንድ መሠዋቱን ስጠን፤» ማለት ነው። ሥጋውን እና ደሙን ነባቢት መሥዋዕት ማለቱ ሕያው መለኮት የተዋሐደው በመሆኑ ነው።

ከዚህ በኋላ ካህኑ መብራት የያዘውን ዲያቆን ከፊት አስቀድሞ የቅዱስ ጳውሎስን መጽሐፍና መስቀል የያዘውን ዋናውን ዲያቆን ደግሞ ከኋላ አስከትሎ ሦስት ጊዜ ታቦቱን ይዞራል። ሦስት ጊዜ መሆኑ የሥላሴ ምሳሌ ነው። መብራት የያዘው ዲያቆን የዮሐንስ መጥምቅ ምሳሌ ነው። ቄሱ የጌታ፣ ከኋላ የሚከተለው ዲያቆን ደግሞ የእስጢፋኖስ ምሳሌዎች ናቸው፤ ምክንያቱም ከጌታ ስድስት ወር ተቀድሞ መጥቶ መንገድ የጠረገ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ነውና፤ ከጌታም በኋላ ከሌሎቹ ቀድሞ ሰማዕትነትን የተቀበለው ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነውና።

ካህኑ በዑደቱ ጊዜ፡- ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን፥ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን፥ ሊቀ ጳጳሱን፥ ኤጲስ ቆጶሳቱን፥ ቀሳውስቱን፥ ዲያቆናቱን፥ ምእመናንን፥ በቀናች ሃይማኖት ሁነው የሞቱትንና ያረፉትን፥ የቤተ ክርስቲያንን አባቶች በጸሎቱ ያስባል። ይህም የሚገባ ነው። ምክንያቱም አባቶች ልጆቻቸውን በጸሎት

> ደጋግ ምእመናን መሥዋዕቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጡት ከዐሥር አንዱን /ዐሥራቱን/ ለእግዚአብሔር ከሰጡ በኋላ ከተቀረው ከዘጠኙ ላይ ነው። ይህም ትልቅ መሥዋዕትነት ነው። ስለ እነርሱ በመስቀል ላይ ተሠውቶ ድኅነታቸውን ለፈጸመላቸው ጌታ የሚሰስቱት ነገር የለም። ሕይወታቸውን፥ ገንዘባቸውን፥ ትዳራቸውን፥ ጊዜአቸውን፥ ዕውቀታቸውን፥ ጉልበታቸውን ሁሉ መሥዋዕት አድርገው ያቀርቡለታል።

እንደ ሚያስቡ ሁሉ ልጆችም እስከ ፓትርያርክ ድረስ ያሉትን አባቶች በጸሎት ማሰብ አለባቸው። ለምሳሌ: - ጻድቁ ካህን ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በሚጸልይበት ጊዜ በውጭ የቆሙት ሕዝብ፡- «መሥዋዕቱን ተቀበልለት፤ ባላወቀው ኃጢአት አትቅሠፈው፤» እያሉ ይጸልዩለት ነበር። ሉቃ.1፥10። ይኸን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ፤ በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምሥጢር እንድነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ /ስለ አባቶች/ ጸልዩ፤ ልናገር እንደ ሚገባኝ ያሀል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ።» ብሏል። ቈላ.4፥2-4። በኤፌሶን መልእክቱም፡- «በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ /ከልባችሁ/ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን /ስለ ደጋግ ሰዎች/ ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር /ትርጓሜ/ በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ /ኃይለ ቃል ተሰጥቶኝ አፌን ሞልቼ እናገር ዘንድ/ ስለ እኔ ለምኑ፤ ስለ ወንጌልም በሰንሰለት መልእክተኛ የሆንሁ፥ መናገር እንደ ሚገባኝ ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ።» ብሏል። ኤፌ.6፥18-20።

## ንስግድ

ካህኑ በጸሎት በቡራኬ ያከበረውን ዕጣን እያጠነ በመንበሩ ፊት ሦስት ጊዜ እየሰገደ «ንስግድ'» እያለ ሕዝቡን በዜማ ያዝዛል። ሕዝቡም፡- «ሦስት ሲሆኑ አንድ ለሚሆኑ ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም፤» እያለ በዜማ ይመልሳል። ከዚህም ቀጥለው በመቀባበል፡- «የመለኮት ማደርያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ላንቺ ይገባል። አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ለምኚልን። ቡሩክ ከቤተ መቅደስ የተቀበላትን የእሳትን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ። ኃጢአትን የሚያስተሠርይ፣ በደልንም የሚያጠፋ ይኸውም ካንቺ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ራሱን መሥዋዕትና ዕጣን አደርጎ ላባቱ ያሳረገ። ይኸውም ካንቺ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ክርስቶስ ሆይ ፥ቸር ሰማያዊ ከሚሆን አባትህ ጋር ከማሕየዊ ቅዱስ መንፈስህም ጋር እንሰግድልሃለን። መጥተህ አድነኸናልና።» ይላሉ።

ካህኑ የሚያጥንበት ጥና የእመቤታችን፥ፍሕሙ የመለኮት ፥ ዕጣኑ የትስብእት ምሳሌዎች ናቸው። በጥናው ውስጥ ፍሕሙ ዕጣኑን መዋሐዱ፥ በድንግል ማርያም ማኅፀን መለኮት ሥጋን መዋሐዱን ያመለክታል። ጥናው ከላይ መያዣው አንድ ሆኖ ሦስት ሐብል አለው። መያዣው አንድ መሆኑ የአንድነት ምሳሌ ሲሆን ሐብሉ ሦስት መሆኑ ደግሞ የሦስትነት ምሳሌ ነው፤ ሥላሴ በመለኮት አንድ በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ናቸውና።

በዚህ ክፍል ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድኅነተ ዓለምን ለመፈጸም እንደ ንጹሕ ዕጣን መሥዋዕት ሆኖ ራሱን እንዳሳረገ ይናገራል። ጌታችን ድኅነተ ዓለምን የፈጸመው ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ፥ ራሱ መሥዋዕት ፥ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ ሆኖ ነው። «ለአባቱ ያሳረገ፤» ሲል «መሥዋዕትን የሚቀበል አብ ብቻ ነው፤» ማለት አይደለም። አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም መሥዋዕት ተቀባይ ናቸው። ጌታችን በወንጌል፡- «እኔ እና አብ አንድ ነን፤» ያለው ለዚህ ነው። ዮሐ. 10፥30። «ለአብ ያሳረገ፤» ሲል በአብ ህልውና ወልድ መኖሩን መርሳት አይገባም። «አብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። /አለ/። ወልድም በአብ በመንፈስ ቅዱስ





© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ህልው ነው:: መንፈስ ቅዱስም በአብ በወልድ ህልው ነው:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በህልውና /በአኗኗር/ አንድ ናቸው::» የሚያሰኘው ምሥጢር ይህ ነው:: ራሱ ጌታችንም በወንጌል :- «እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምኑምን? ... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤» ብሏል:: ዮሐ.14፥10-11:: እንግዲህ:- «ለአባቱ ያሳረገ» ማለት የኢየሱስ ክርስቶስን መሥዋዕትነት አብ የወደደውና የፈቀደው መሆኑን ያመለክታል:: ለዚህም ነው:- ጌታችን: - «አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ፤» ማለቱ ነው:: ይህም በፈቃድ አንድ መሆናቸውን ያረጋግጥልናል:: ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ከመሞቱ በፊት ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንዲት በሆነች ፈቃዱ እንደሚሞት ሲያጠይቅ:- «ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ /ነፍሴን ከሥጋዬ አዋሕጄ አነሣት ዘንድ/ አኖራለሁና /እሞታለሁና/፤... እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ /እሞታለሁ እንጂ/ ከእኔ ማንም አይወስዳትም /የምሞተው ያለ ፈቃዴ አይደለም/:: ላኖራት ሥልጣን አለኝ፥ ዳግምም ላነሣት ሥልጣን አለኝ::» ብሏል:: ዮሐ. 10፥17-18::

ቅዳሴው ስለ ክርስቶስ መሥዋዕት መሆን ከተናገረ በኋላ ዓለምን ለማዳን ሲል ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አለማነሱን ሲናገር :- «ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንሰግድልሃለን፤» ብሏል:: ከዚህ በኋላ ካህኑ አራቱን ማእዝን ያጥናል:: ሴቶቹንም ወንዶቹንም ይባርካል:: ካህናቱንም እያጠነ:- «ቄሱ አባቴ ሆይ፥ ክብርት በምትሆን በጸሎትህ ታስበኝ ዘንድ እለምንሃለሁ::» ይላቸዋል:: እነርሱም:- «የመልከ ጼዴቅን መሥዋዕት፣ በበኩር ቤተ ክርስቲያን የሚኖሩ የአሮንና የዘካርያስንም መሥዋዕት እንደ ተቀበለ እግዚአብሔር መሥዋዕትህን ይቀበል፥ የዕጣንህንም መዓዛ ይቀበል፥ ክህነትህንም በእውነት ይጠብቃት::» ብለው ይመልሱለታል:: መሥዋዕቱ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፥ ዕጣኑም እርሱ ነው:: ካህኑ አራቱን ማእዝን ካጠነ በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ተመልሶ አንድ ጊዜ መንበሩን ይዞራል:: ቀጥሎም በሥጋ ወደሙ ላይ ሦስት ጊዜ እያዞረ ያጥናል:: ይህም ከሥጋውና ከደሙ መዓዛ መለኮቱ እንዳልተለየው ለማጠየቅ ነው:: ከዚህ በኋላ ንፍቁ ካህን «እግዚአ አእምሮ»ን ያነባል:: በንባቡ ውስጥም በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ድኅነት ለመግለጥ: - «በመስቀልህም ሁልጊዜ እንመካ ዘንድ፤» የሚለውን ኃይለ ቃል ይናገራል:: ከእርሱም በመቀጠል:- ነገረ ድኅነትን የሚመሰክሩ ከጳውሎስና ከሌሎች ሐዋርያት መልእክት እንዲሁም ከግብረ ሐዋርያት ተውጣጥቶ ይነበባል::

ምንባባቱ ከተነበቡ በኋላ ቄሱ በታቦቱ ፊት ቆሞ:- «እግዚአብሔር አምላክነ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አቡነ አብርሃም:: ወህየንተ ይስሐቅ ወልዱ ዘአስተዳሎከ ወአውረድከ ሎቱ ቤዛሁ በግዓ:: ከማሁ ተወከፍ እግዚኦ መሥዋዕትነ ወመዓዛ ዝንቱ ዕጣንነ:: የአባታችንን የአብርሃምን መሥዋዕት የተቀበልህ አምላካችን እግዚአብሔር ስለ ልጁ ስለ ይሥሐቅም ፈንታ ቤዛ ሊሆነው በጉን አዘጋጅተህ ያወረድህለት አቤቱ፥ እንዲሁ መሥዋዕታችንን እና የዚህን የዕጣናችንን መዓዛ ተቀበል::» እያለ ይማፀናል::

አባታችን አብርሃም ልጁን ይሥሐቅን ለመሠዋት በመሠዊያ ላይ ባጋደመው ጊዜ:- እግዚአብሔር ስለ ይሥሐቅ ፈንታ የሚሠዋውን በግ ሰጥቶታል:: አብርሃም ልጁ ይሥሐቅ «የሚሠዋው በግ የት አለ?» ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ: - «በጉን እግዚአብሔር ያዘጋጃል፤» ብሎ እንደ እምነቱ ተደርጎለታል:: እግዚአብሔር ባመለከተው ጊዜ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ የተያዘ በግ አግኝቶ በይሥሐቅ ፈንታ ሠውቶታል:: ለይሥሐቅ ቤዛ ሆኖ የተሠዋው በግ ለቤዛ ዓለም በመስቀል ላይ ለተሠዋው አምላክ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው:: ዕፀ ሳቤቅ ደግሞ የእመቤታችን ምሳሌ ናት:: ለዚህ ነው ቄሱ አብርሃምንና መሥዋዕቱን እያነሣ የሚማፀነው::

## ዝ ውእቱ

ቄሱ «ደኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተመላሽ ቅድስት ሆይ፥ ደስ ይበልሽ፤» እያለ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም እንድታማልደው ከተማፀነ በኋላ:- «ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት ወዝ ውእቱ ጊዜ ዕጣን ኅሩይ ጊዜ ስብሐቱ ለመድኃኒነ መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ:: የማመስገን ጊዜ ይህ ነው፤ ሰው ወዳጅ መድኃኒታችን ክርስቶስን ማመስገኛ ጊዜ የተመረጠ የዕጣን ጊዜም ይህ ነው::» ሕዝቡም:- «ማርያም ዕጣን ናት፥ ዕጣን እርሱ ነው፤ በማኅፀንዋ ያደረው ከተመረጠ ዕጣን ሁሉ የሚሸት ነውና የወለደችው መጥቶ አዳነን::» ይላል:: እመቤታችን ዕጣን መባሏ መዓዛ ድንግልናዋን ያመለክታል:: ጌታችን ደግሞ ዕጣን መባሉ ከላይ እንደ ተገለጠው ስለ መሥዋዕትነቱ ነው:: አንድም ምዑዝ ባሕርይ መሆኑን ይገልጣል:: ለአዳም ልጆች በሙሉ በቤዛነቱ መዓዛ ሕይወት የሆነን ዕጣን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በአዳም ምክንያት ሞት የሸተተው ዓለም ሕይወት የጎበኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

በዚህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ያለው ሽቱ እንደ ሆነ፥ ኃጢአትን እንደ ሚያስተሰርይ፥ ለቅዱስ ሚካኤል ምሕረት፣ ለቅዱስ ገብርኤል ብሥራት፣ ለድንግል ማርያም ሰማያዊ ሀብት፣ ለቅዱስ ዳዊት ልቡና፣ ለንጉሥ ሰሎሞን ጥበብ፣ ለነቢዩ ሳሙኤል ነገሥታቱን እየቀባ የሚሾምበት የሽቱ ቀንድ፣ ለቅዱስ ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ፣ ለቅዱስ ዮሐንስ ድንግልና፣ ለቅዱስ ጳውሎስም መልእክት እንደ ተሰጣቸው፥ እመቤታችን መዓዛ ያላት ሽቱ መሆኗንና የማኅፀንዋ ፍሬም ከዕጣን ሁሉ እንደሚበልጥ፥ እርሷንም አብ እንደ ወደዳትና ለልጁ ማደርያ እንድትሆን በቅድስና ሽልሞ እንዳስጌጣት፥ ለሙሴ ሕግ፥ ለአሮን ክህነት፥ ለካህኑ ዘካርያስም የተመረጠ ዕጣን እንደ ተሰጣቸው ይናገራል::

ጌታችን ሽቱ መባሉ ራሱን የቻለ ምሥጢር አለው:: አንደኛው ጌታ ምዑዝ ባሕርይ መሆኑን ያመለክታል:: ሁለተኛው ደግሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ነቢያት እነ ሳሙኤል ሽቱ እየቀቡ ነገሥታቱን ይሾሙ እንደ ነበረ ይታወቃል:: ይህም ምሳሌነት አለው:: ምሳሌነቱም ጌታ ሁሉን የሚያከብርና የሚሾም መሆኑን ያመለክታል::

በበዓለ ኀምሳ ማለትም ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ በ«ዝ ውእቱ» ፈንታ *«ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፥ ሞቶ ሞትን አጠፋው፥ በመቃብር ላሉ የዘላለም ዕረፍት የሚሆን ሕይወትን ሰጠ::» ይባላል:: ከዚህ በኋላ ኪዳን ይደርሳል::*

*ይቆየን ::*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የማኅበረ ቅዱሳንን
ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አዳኙ

/ፍቅረ ሥላሴና መብዐ ሥላሴ/

እሑድ ማለዳ ላይ ነው:: ዳኘው የአዕዋፍ ድምፅ ሲሰማ ከመኝታው ተነሣ:: ከቆጡ ቁጭ እንዳለ ትራስ አድርጎት ያደረውን የተጨማደደ እጀ ጠባቡን ለብሶ አረንጓዴ ቁምጣውን ታጠቀና ከአልጋው ወረደ:: በዕለተ ሰንበት ተኝቶ ማርፈዱን አልወደደውም:: አባቱ ይህን ቢያውቁ እንደ ሚያዝኑበት ስለ ስጋ ፈጥኖ ለመነሣት ወሰነ:: አባቱ ሊቀ ኅሩያን በለጠ ኅበዝ ገበሬ÷ ትጉህ ካህን ናቸው:: በአንጻሩ የክርስትና አባቱ ፊታውራሪ ኃይሌ የታወቁ አዳኝና አርበኛ በመሆናቸው የዳኘው ዝንባሌ እንደ እርሳቸው መሆን ነው:: አባቱ በግብርናውም ሆነ በአዳኝነቱ ባይከፋም በዳኘው ደስታቸው እጅግም ነው:: ምነው ቢሉ እርሳቸው የቤተ ክርስቲያኑን ትምህርት እንዲዘልቅ ይፈልጉ ነበርና:: የክርስትና አባቱ ሃይማኖቱን እንዲማር የሚቻላቸውን ቢያደርጉም በሌላውም «አይዞህ የኔ ጀግና!!» እያሉ ስለሚያበረታቱት ባገኘው አጋጣሚ ፊታውራሪን ማስደሰት ያጓጓዋል::

ሊቀ ኅሩያን በለጠ ልጃቸው ዳኘው መንፈሳዊ ጥበብን እንዲማር በአራት ዓመቱ ነበር ወደ ደብረ ሐዋርያት ቅዱስ ሚካኤል የላኩት:: እርሱም ቢሆን ትምህርቱን ወዶት ነበር፤ ያጠናውን ማስታወስ እያቃተው ተቸገረ እንጂ:: ጸሎት ዘዘወትርን እንኳ በቃሉ አጥንቶ ለመዝለቅ መንፈቅ ፈጀበት:: ከዘወትር ጸሎት ሁሉ «ሰላም ለኪ» ብቻ ከልቡ ዘልቃ ገብታለች:: ብቻውን ሲኾን በለሆሳስ እየደጋገመ ያዜማታል:: በስተቀር ግን ወንጌለ ዮሐንስ ንባብ ቤት ገብቶ ሲያጠና ውሎ ማታ ላይ ሲጠየቅ ግራ እየገባው ሲጨነቅ ከእርሱ በኋላ የጀመሩት ልጆች ሲበልጡት ታናሽ ወንድሙ አምባዬ እንኳ ሳይቀር... ሲያፌዝበት ልቡ ስለ ተከፋ፤ ዓመት የለፋበትን ትምህርቱን ትቶ ወደ ወላጆቹ ቤት ተመለሰ...::

ወላጅ አባቱ ትምህርቱን በማቋረጡ ቢያዝኑም የክርስትና አባቱ: - «አንተ እንግዲህ ስጦታህ ግብርና ነው» ብለው ወደ ግብርና እና አረኝነት አሠማሩት:: እያደገ ሲሔድ አደን አስተማሩት:: ወደ ጫካ ይዘውት ይወጡና የዱር እንስሳቱ የተሠማሩበት ሜዳ ላይ ሲደርሱ እርሳቸው መሽገው፣ ጠመንጃቸውን ሰድረው እንስሳዋን ማነጣጠሪያው ቀለበት ውስጥ አስገብተው ግንባሯ ላይ መትተው ሲጥሏት ... እንዴት እንደ ሚነጣጠር... እንዴት እንደ ሚመታ ተማረ:: ዳኘው አደኑ እንደ ትምህርቱ አላስቸገረውም:: የክርስትና አባቱ ለአደን በወጡ ቁጥር በቆሙበት አልመው፣ አነጣጥረው፣ ሲተኩሱና ግዳይ ሲጥሉ.... አይቷል:: ላንድ ግዳይ ከአንድ ጥይት በላይ አያበላሹም:: እርሱም ያሳዩትን ስልት በቶሎ ቀሰመው:: የክርስትና አባቱ ይኽን ባዩ ጊዜ እጅግ ተደሰቱ:: አጭር ምንሽር ሸለሙት:: ምነው ቢሉ ከአምባዬ ይልቅ ልባቸው ለዳኘው ያደላ ነበር:: በዚያ ላይ ደግሞ የቄስ ትምህርት እምቢ ብሎት ወንድሙም የዕድሜ እኩዮቹም ይቀልዱበት ነበርና ከእነርሱ የተለየ ችሎታውን የሚያስመሰክርበት ስላገኙ እጅግ አስደሰታቸው::

ዳኘው አዳኝ ብቻ ሳይሆን በግብርናውም ትጉህና ታታሪ ሆነ:: ሌት ተነሥቶ በሬ ጠምዶ እርሻ ከጀመረ በሬዎቹ ካልደከሙ በቀር ዕረፍት አያምረውም:: ክረምት ወራት ላይ ወደ በረሐ እየወረደ ያርሳል::

ዛሬ ዳኘው በጠዋት ወደ አደን ለመሔድ ወስኗል:: የክርስትና አባቱ ፊታውራሪ ኀይሌ አጭር ምንሽር ከሸለሙት ጊዜ አንሥቶ በዐይኑ የሚዞረው የዱር አውሬ ማደን ነው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፊታውራሪ በጠና ስለ ታመሙ ዳኘው ጠበል እያመጣ ሲያስታምማቸው ከርሟል:: እርጅና ስለ ተጫጫናቸው ከቤት መውጣትም ተስኗቸዋል:: አደን ቀረ:: የሚወዱትን የሚዳቋና የአጋዘን ሥጋ አጡ... ከዚህ የተነሣ ዳኘው በተለይም በአዘቦት ቀን በማለዳ ተነሥቶ ወደ ዱር ለመሮጥ ያልማል:: መሣሪያውን ከተሰቀለበት አውርዶ ጠራረገውና ዝናሩን ታጥቀ:: ያሉትን ጥይቶች ቆጠረ፤ ስድስት ብቻ ናቸው:: «የሚያስተማምን አይደለም ግን ይበቃል» አለ በልቡ:: አፉን ለመሻር ወደ ጓሮ ዘለቀና እሸት ፈልፍሎ እየቃመ ጉዞውን ጀመረ:: ወደ ጫካው በኩል ሲያመራ በማዶ የሚታየውን የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተሳለመ::

ከተራራው ራስ የደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የማሕሌት ዝማሬ ደምቆ ይሰማል:: መዘምራን «የክብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማየት ጸድቃን በውስተ ገነት...» እያሉ በያሬዳዊ ዜማ ስለ ሰንበት ክብር ይመሰክራሉ:: ሥርዐተ ቅዳሴው ተፈጽሞ ታቦቱ ወደ ዐውደ ምሕረት ሊወጣ ነው:: ይህንኑ ለማብሠር ዲያቆን አምባዬ ከትልቁ ጥድ ሥር ካለው ድንጋይ ላይ ተንጠራርቶ ገመዱን በመያዝ ደውሉን ከወዲያ ወዲህ በማላጋት ይደውላል:: ሕዝበ ክርስቲያኑ ወደ ዐውደ ምሕረት ሰብሰብ ማለት ጀምሯል:: ፊታውራሪ ኀይሌ ከቤተ መቅደስ እንደ ወጡ ወደ ሰንበቴ አዳራሽ አመሩ:: ማኅበርተኞቹ ተሰብስበው ጠበል ጠዲቅ ለምእመናን እያደሉ ነው:: ፊታውራሪ ዳኘውን ፍለጋ ከወዲያ ወዲህ አማተሩ፤ ሊያዩት አልቻሉም:: እንዳልመጣ ስለ ገመቱ ዲያቆን አምባዬን ጠሩና ልጅ ወደ ቤት እንዲልክበትና እንዲያስጠራው ነገሩት::

⁂ ⁂ ⁂

ዳኘው ግዳይ ለመጣል እየገሠገሠ በልቡ የክርስትና አባቱ እንደ ሚመርቁት ሲያስብ ደስ አለው:: ማለዳ ላይ የሰማውን «የክብርዋ ለሰንበት...» የሚለውን ዜማ በልቡናው ያዜማል:: በአእምሮው የወንድሙ መንፈሳዊ ትጋትና የዜማ ችሎታ ውልብ አለበት:: እንደ ወንድሙ በ«ቄስ ትምህርት ቤት» የቀሰመውን ዕውቀት ጠንቅቆ ባይዝም ወንድሙ ሲያዜም መስማት ደስ ይለዋል:: ወንድሙን ሲያስብ ፊታውራሪ ቤተ ክርስቲያን ፈልገው ሲያጡት እንደ ሚጨነቁ በማሰብ ለመፍጠን ወሰነ:: አካባቢውን አማተረ፣ ያለወትሮው ጸጥ ረጭ ብሏል:: ጸጥ ማለቱን አልወደደውም:: ሰንበት መሆኑን አስቦ ለራሱ ፈገግ አለ:: «አራዊቱ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ሊሳለሙ ሔደዋል ማለት ነው» እንደ ማፌዝ ቃጣው:: «ለካ ሰንበትን ያላከበርኩ እኔ ነኝ፤ እነሱማ ስለሚያከብሩ መሆን አለበት እንዲህ የጠፉት፤ ለሁሉም ወደ ወንዙ አፋዛኘ ልሒድ» በማለት ወደ ወንዙ አቅጣጫ መገሥገሥ ጀመረ:: እየሮጠ ሳለ ከወንዙ ማዶ እጅብ ብለው ውኃ የሚጠጡ ሚዳቆዎችን አሻግሮ ተመለከተ:: ዕቅዱ ግብ ሊመታ ነው:: ቁልቁለቱን ተንደርድሮ ወርዶ አድፍጦ ለማነጣጠር የሚችልበትን ቦታ መርጦ አንድ አለት ድንጋይ አጠገብ በርከክ አለ:: እርሱ ቦታ ከመያዙ እጅብ ብለው ቆመው የነበሩት ሚዳቋዎች ድንገት ደነበሩ:: ሁሉም በየፊናቸው እየሮጡ ተበታተኑ:: ከኋላቸው ሁለት ነብሮች እየፎገሉ ሲከተሏቸው ሲያይ ገረመው:: ሁሉም በርግገው ወደ ደኑ ገብተው ጠፉት::

ዳኘው በሚዳቋዎቹ መበርገግ እየተበሳጨ፣ «ዛሬ አይቀናኝም ማለት ነው» ብሎ ሳይጨርስ አንዲት ሚዳቋ እቋጥኙ ሥር ብቻዋን እንደ ተንበረከከች አስተዋለ:: «ተመስገን» አለ በረዥሙ እየተነፈሰ:: ፊታውራሪን የማስደሰት ህልሙ እንደገና በልቡ ተቀሰቀሰ:: «ይህች ለሰንበት ድካሜ እግዚአብሔር ያዘጋጀልኝ ናት» ብሎ አሰበና ለመተኮስ ተመቻቸ:: አጭር ምንሽሩን አነጣጥሮ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ አልሞ ተኰሰ:: ለጥቂት ሳታት:: ገረመው:: ለወትሮው ጥይቱ መሬት አትወድቅም ነበር:: «ርቄ ይሆናል» ብሎ አስቦ እያደባ ተጠጋ:: ቀረብ ብሎ አደፈጠና አልሞ ተኰሰ:: አሁንም አልመታትም፤ እንደገና ትንሽ ጠጋ ብሎ ለሦስተኛ ጊዜ ሞከረ፤ አልመታትም::

ያባከነውን የጥይቱን ዋጋ በማሰብ ተናደደ:: «ከአደኔም ሳልሆን ከጥይቱም ሳልሆን ፊታውራሪ ምን ይሉኝ! መቼም በቀሩኝ ሁለት ጥይቶች እሷን መጣል አያቅተኝም» ብሎ ከነበረበት ቦታ ተነሣና ተጠጋ:: በደንብ ልመታት እችላለሁ ብሎ ቦታ መርጦ በርከክ ብሎ አለመ... ተኰሰ... አሁንም አልመታትም::

ዳኘው ከመበሳጨት ይልቅ ግራ ተጋባ:: «ዛሬ ምን ሆኛለሁ ወይስ



© ማኅበረ ቅዱሳን   www.eotcmk.org

የምትታየኝ ምትሀት ናት እንዴ» ብሎ አሰበ፤ በጣም ተደነቀ፥ ጥይቱን አባክኗል:: ግዳዩንም አልጣለም:: «እሷስ እንዴት ነው የጥይት ድምፅ እየሰማች የማትበረግግ... መቼም አራት ጥይት ተኩሼ ባዶ እጄን አልመለስም፤ የቀረ ችኝን በግንባሯ ለቅቄ አሳርፋታሁ» ብሎ እንደገና በርከክ አለ:: ተመቻቸ... አለመ... አነጣጠረ:: «ከዚህ ርቀት መቼም አልስታትም» ብሎ አሰበ፤ እርግጠኛም ሆኖ ተኮሰ:: ሆኖም ጥይቱን በማባከኑ አዘነና ትንሽ ጠጋ ብሎ በድንጋይ ለመምታት ወሰነ::

ሚዳቋዋ ከተንበረከከችበት አልተ ንቀሳቀሰችም:: «ከተጠጋሁ በደቦል ድን ጋይ እጥላታለሁ ወይም የሆነችውን ማየት አለብኝ» በማለት አይታው እንዳ ትበረግግ እየተጠነቀቀ ቀስ ብሎ ወደ ቋጥኙ ተጠጋ:: መቶ ርምጃ ያህል ሲ ቀረው ስትንቀሳቀስ አያት:: በደንብ ለማስተዋል እንዲመቸው የበለጠ ተጠ ጋ:: ሰውነቱን አንዳች ፍርሃት ይሁን ደስታ ያላወቀው ስሜት ወረረው:: እን ባውም ባይኑ ሞላ:: ጥይት ከማባከኑ ይልቅ አሁን በሚያየው ነገር ተደነቀ:: ለካስ ሚዳቋዋ ያን ያህል የጥይት ድምፅ እየሰማች ያልበረገገችው በምጥ ተይዛ ኖሯል::

ወንዙን ተሻግሮ አጠገቧ ሲደርስ በሙሉ ተገላግላ እንቦሳዋን በምላሷ እየላሰች ነበር:: ሚዳቋዋን እያስተዋለ የእግዚአብሔርን ሥራ አደነቀ:: እግ ዚአብሔር ሚዳቋዋን በጭንቅ ሰዓት እንዴት ከጥቃት እንደ ጠበቃት፣ እርሱም በሰንበት ወጥቶ ተአምር እንደ ተገለጠለት እያሰበ ብዙ ቆየ:: እጆቹን ዘርግቶ ወደ ሰማይ አቀና... ከዚያም በቆመበት ቦታ ለአምላኩ ሰገደና ጸሎት ጀመረ... «አቤቱ፥ እግዚአብሔር ሆይ፥ ሥራህ እንዴት ግሩም ነው? ፍጥረታትን ሁሉ የምትመግብ ሁሉን የምትመራ አንተ ነህ፤ ሁሉን በጥበብ ሠራህ...»

ከደኑ በኩል የሰማው ድምፅ ዳኘውን ከተመሥጠው መለሰው:: ... እየዘለለ ጥሻውን አልፎ ወደ እርሱ የሚሮጠውን አውሬ ሲያይ ደነገጠ፤ ሚዳቆዎቹን ካስበረገጉት ነብሮች አንዱ ነው:: እርሱም እንደ ዳኘው ግዳይ አልቀናውም:: ተቆጥቷል:: ከርቀት ሚዳቋዋንና ዳኘውን አይቶ ያመለጠውን ለማካካስ እየመጣ ነው::

ዳኘው ምንሽሩን አስተካክሎ ደገነ... ሲያስበው ምንም ዋጋ የለ ውም:: ጥይቱን ጨርሷል:: ምናልባት አንዲት ብቻ ነው የቀረችው፤ እሷኑ ተኩሶ ከሳተው አለቀለት:: ምን ማድ ረግ እንዳለበት ግራ ገባው:: ነብሩ ወደነሱ ሲቀርብ ቀስ እያለ መጠጋት ጀመረ:: ዳኘው በዚህ የጭንቅ ሰዓት አጠገቡ አይዞህ ብሎ የሚያበረታታው የለም፤ የሚያደርገው ቅጡ ጠፋው:: ልቡ በአፉ ልትወጣ የቀረበች መሰለው:: ወደ ሰማይ አንጋጠጠ::

«አቤቱ አምላኬ፥ እንዴት ታደርገኝ ይሆን? በሰንበት ምድር አደን ብዬ ወጥቼ እኔው ታዳኝ ሆንኩኝ» በደመ ነፍስ በልቡ የሚያውቃትን የእመቤታችንን ጸሎት መድገም ጀመረ....

«ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ...» የጀመረውን መፈጸም እያቃተው እንደገና ይጀምራል:: «እናታችን ማርያም ሆይ፥ ማርያም ሆይ... ሰላም ላንቺ ይሁን እያልን እንሰግድልሻለን... እንማልድሻለን... ከክፉ አውሬ ታድኚን ዘንድ ተማፅነንብሻል... ስለ አባትሽ ስለ ኢያቄም ስለ እናትሽ ስለ ሐና ብለሽ አድኚኝ...» ቀና ብሎ ወደ ነብሩ ተመለከተ፤ ደርሷል...

አዳኙ መዳፍ ውስጥ ገባሁ ብሎ አሰበ:: ከአሁን አሁን ደረሰብኝ እያለ በሚጨነቅባት ቅጽበት ከበስተኋላው የጥይት ድምፅ ሲሰማና ነብሩ ተመቶ ሲወድቅ ሲያይ ድንገት መብረቅ የወረደ መሰለው:: ዳኘው ያየውን ነገር ማመን ስላልቻለ ጭንቅላቱን እግሩ ላይ እንደ ደፋ ፈዝዞ ቀረ:: ወደ ኋላው ዞሮ ማን እንደ ተኮሰ ለማየት አቅም አልነበረውም:: ...

«ብቻህን ሊያውም በሰንበት ለምን ወረድክ ልጄ?» የክርስትና አባቱን ድምፅ ሰማ:: ለካስ ፈታውራሪ ቤተ ክርስቲያን ፈልገው አስፈልገው ቢያጡት እመንደር እንደ ደረሱ ምንሽሩም እተቀመጠበት ባይኖር ብቻውን ለአደን እንደ ወጣ፣ ጠርጥረው ሊ ፈልጉት መምጣታቸው ነበር::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

---

# መንፈሳዊ የምክክር...

/ከገጽ ፴፰ የዞረ/

## 2. ድኅረ ምርመራ /ተከታታይ/ መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት

- ይህ የምክክር አገልግሎት በተለይ ሰዎች ተመርምረው ውጤታቸውን ካወቁ በኋላ የሚሰጥ አገልግሎት ነው:: ብዙውን ጊዜ በዚህ ተጠቃሚ የሚሆኑት ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች ናቸው::

## የዚህ አገልግሎት ዓላማም:-

- ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸው ሰዎች በየዕለቱና በየቦታው የሚገጥማ ቸውን ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ችግ ሮችን የመቋቋም ዘዴን እንዲያዳብሩ መርዳት፤
- የተከሠተውን ችግር ተቀብለው ጤናማ ጠባዕያትን በማዳበር የወደፊት ኑሮን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ድጋፍ መስጠት፤
- ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩ ሰዎች ለተጨማሪ አደጋ ራሳቸውን እንዳያጋ ልጡ ለማድረግና የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከል ኅብረተሰቡን በማስተማር በኩል ያላቸውን ከፍተኛ ሐላፊነት ማሳወቅና ተግባራዊ እንዲያደርጉትም በመንፈሳዊና ሥነ ልቡናዊ መንገድ ድጋፍ ማድረግ፤
- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቤተ ክርስ ቲያን ታሪክ ችግር ያጋጠማቸውን ሰዎች በመጥቀስ እንዴት ችግራቸውን እንደ ተወጡት በማስረዳት እነርሱም ያላቸውን አቅምና ልምድ በመጠቀም ለገጠማቸው ችግር መፍትሔ እንዲ ያመነጩ ማገዝና መርዳት፤
- አእምሯቸው ከሐሳብና ከጭንቀት እንዲ ላቀቅና ዕለታዊ ሥራቸውን በትክክል እንዲያከናውኑ፣ ዕቅድ እንዲያወጡና በዚያ መሠረት እንዲኖሩ ማበረታታ ትና ማገዝ፤
- በጎ ተግባራትን በሚያልፍ ዕድ ሜ በቅደው የማያልፍ ሥራን ለማከ ናወን እንዲችሉ መርዳት፤ ይህም ማ ለት ከመደበኛ ሥራቸው ውጭ በተለ ያዩ ማኅበራዊና መንፈሳዊ አገልግ ሎቶች እንዲሳተፉ ማበረታታት፤
- ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲ ሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መርዳት፤ ይህም ሞተ ዕረፍትን በጸጋ ለመቀበል ይረዳቸዋል:: በአጠቃላይ እነዚህንና ሌሎች ተዛማኝ ነጥቦችን አመካካሪው ዓላማ አድርጎ ሊነሣ ይችላል::

## መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት ለማን ይሰጥ?

መንፈሳዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት አገልግሎቱን ፈልገው ለሚመጡ ሰዎች ሁሉ ሊሰጥ ይቻላል:: በተለይ ግን:-

- ለወጣቶች /ለሰንበት ትምህርት ቤት አባላትና አገልጋዮች/
- ለተጋቢዎች:- ጋብቻቸውን ከመፈጸማ ቸው በፊት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠ ረተ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ እን ዲያርጉ ማበረታታት:: በተለይ በዚህ ረገድ አበ ነፍሶች ልጆቻቸው ጋብቻ ለመፈጸም ሲመጡ ቅድሚያ ይህን ምርመራ እንዲያደርጉ የምክክር አገልግሎት ሊሰጧቸው ወይም ደግሞ ሊያሰጧቸው ይገባል::
- ቫይረሱ ጋር አብረው ለሚኖሩ ሰዎች
- ለኤድስ ሕሙማን
- በኤድስ ምክንያት አሳዳጊ ላጡ ሕ ፃናት፤

## አገልግሎቱ የት ይሰጥ?

አገልግሎቱ በዋናነት በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በተመካካሪዎች ቤት በመሔድ እና የኤድስ /የጤና ተቋማት/ ሕሙማን ከሆኑ በተኙበት ሆስፒታል በመገኘት ሊ ሰጥ ይችላል::

## ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚከሠቱ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ችግሮች

ብዙውን ጊዜ ሰዎች ቫይረሱ በደ ማቸው ውስጥ መኖሩ ከተነገራቸው በኋላ የሚከተሉት ሥነ ልቡናዊና ማኅበ ራዊ ችግሮች ይታዩባቸዋል:: እነዚህም ችግሮች:- ድንጋጤ፣ ጭንቀት፣ ፍር ሃት፣ ቁጣ፣ ሐዘን፣ የጥፋተኝነት ስሜ ት፣ ራስን ማግለል፣ የባዶነት ስሜት፣ የመደበት ስሜት፣ ተስፋ የመቁረጥ

/ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል/





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «ደባ ተውኔት መንፈሳዊ ይዘትም ኾነ ፋይዳ ይጎድለዋል።»



*የተውኔት ርእስ - ደባ*
*ተውኔት ድርሰት - ዘሚካኤል*
*አስተያየት /ሂስ/ - ፍቅረ ሥላሴ*

በቅድሚያ ወንድማችን ዘሚካኤል «ድፎ» ተውኔትን ደርሶ በማቅረቡ አመሰግነዋለሁ። ማኅበረ ቅዱሳን ደግሞ አባላቱን አሰባስቦ በማዘጋጀት ለመድረክ በማብቃቱ ይህን ጥበብ ለሰጠንና በዚህም እንድንተጋ ላደረገ ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው እላለሁ። ለሁሉም ያለኝን አድናቆትና ወንድማዊ አክብሮት ለመግለጽ እወዳለሁ። ዘሚካኤል ጀማሪ ደራሲ እንደ መሆኑ መጠን ሊበረታታ ይገባዋል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ለትችት ሳይሆን ገንቢ ሂስ ለመስጠትና ለማነጽ በመሆኑ አስተያየቴን ሳቀርብ በትሕትና ነው። በሐመር መጽሔት 14ኛ ዓመት ቁጥር አንድ *«ደባ ቴአትር ሲቃኝ»* በሚል ርእስ በዲያቆን ኤርሚያስ በዛብህ የተሰጠውን አስተያየት አንብቤዋለሁ። በጸሐፊው በተነሡት ሐሳቦች በተወሰነ ደረጃ የምስማማ ቢሆንም የማልስማማባቸውን ነጥቦች በዚህ ጽሑፍ አቅርቤያለሁ።

### የተውኔቱ ርእስ

የተውኔቱ ርእስ የተውኔቱን ማእከላዊ ጭብጥ መሠረት ያደረገ ይመስላል። ርእሱ ማን በማን ላይ ምን ዓይነት ደባ ፈጸመ? የሚል ጥያቄ እንዲያጭር ታስቦ እንደ ተሰጠ ማስታወቂያው ያመላክታል። የተውኔቱ ማስታወቂያ «በዓለማዊ ጥበብ የተከፈነ... » በሚል ተውኔቱን እንድንመለከት ይጋብዛል። አንድ ርእስ የጉዳዩን ማእከላዊ ነቁጥ የሚያመለክት፣ በታዳሚው ዘንድ ስሜትን የሚስብ ቢሆን ይመረጣል። ርእሱ እነዚህን ነጥቦች ያሟላል ሊባል ቢችልም ለመንፈሳዊ ተውኔት የሚገባ ርእስ ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ ቢነሣ የኔ መልስ አይገባም የሚል ነው። ለምን ቢባል ርእሱ መንፈሳዊ መልእክት ያዘለ፣ በመንፈሳዊ መድረክ የሚነሡ ጥያቄዎችን የሚያጭር ባለ መሆኑ ነው። «ደባ» የሚለው ቃል አንዳች የተንኰል፣ የሤራ ውጥን እንዳለና በቤተ ክርስቲያን ላይ ደባ እየተፈጸመ ነው ብለን እንድንሰጋ የሚያደርግ ነው። ይህ ደባ ያለ የነበረና የሚኖር ነው። በመንፈሳዊ ዐይን ስናየው የደባው ባለቤት ዲያብሎስ ነው። በእኔ አስተያየት የተውኔቱ ርእስ ቤተ ክርስቲያን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የማትናወጥ መሆኗን መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን የሚያስረግጥ መሆን ነበረበት። ማቴ.16፥18።

### የተውኔቱ ታሪክ

የተውኔቱ ታሪክ የሚያጠነጥነው በዋናው ባለታሪክ በሚክያስ በተቃራኒው ታምሩ ዙሪያ ነው። ሚክያስ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚተጋ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ነው። ታምሩ ደግሞ የራሱን ዓላማ ለማራመድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የተጠጋ መናፍቅ መሳይ የቅርስ ዘራፊ ነው።

መጋረጃው ሲከፈት ስናይ ስለ እናቱ ሞት እያሰበ ተዝካራቸውን መሠረት በማድረግ ጠበል ጸዲቅ አዘጋጅቶ ረጅም መነባንብ ያሰማናል። ግርማ ይገባል። ሌሎችም ይገባሉ። ፃዘን ይመጣሉ... ወዘተርፈ። በዚህ ሒደት ስለ ሰበካ ጉባኤ አባላት ምርጫ ውይይት ይደረጋል። የታምሩ ደግነት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያተረፈው ወዳጅነት ይነገረናል። ድርጊያው የሚጀምረው በዚህ ሲሆን የተውኔቱ መሠረታዊ ግጭት በቅርስ ዘረፋ ዙሪያ የሚውጠነጠን ነው ጉዳይ ነው። የቅርስ ዘረፋ ጉዳይ ወቅታዊ ነው። ይሁን እንጂ የቅርስ ዘረፋ በተውኔቱ በተነሣው መልኩ በቁንጽል የሚታይ ነገር አይደለም።

ሁለቱ ባለታሪኮች ሚክያስና ታምሩ ፊት ለፊት ሲገናኙና ሲፋጠጡ እናያቸውም። ትግላቸው በደጋፊዎቻቸው በኩል ነው። የሚክያስ ወዳጆች ግርማና ዘገየ በተለያየ ምክንያት ታምሩን ይደግፋሉ። ሡናይና ሌሎች ደግሞ በሚክያስ ጎራ ተሰልፈው የታሪኩን ሂደት ያራምዳሉ። በተውኔቱ መደምደሚያ ላይም ሁለቱም እንደ ተፋጠጡ እናያለን። ባለታሪኮቹ በቤተ ክርስቲያን በተለምዶ የምናያቸው ሰዎች ናቸው። በእውኑ ዓለም ስንመለከት የዚህ ዐይነት ታሪክ የሆነ ወይም ሊሆን የሚችል ነው ማለት ይቻላል። ነገር ግን በዚህ ተውኔት ሊዳሰሱ የሚገባቸው ብዙ ውስብስብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አልተዳሰሱም።

በታሪኩ ሒደት የአንዳንዱ ትዕይንት አስፈላጊነት ጎልቶ አይታይም። በታሪኩ መሠረታዊ ጭብጡ፣ በዋና ባለታሪኮች መካከል ያለው የጥቅም ሆነ የፍላጎት ግጭት ጎልቶ ሳይወጣ በተወሰኑ ነጥቦች ዙሪያ በሚያጠነጥኑ ጉዳዮች ብቻ እየተውተረተረ ታሪኩ ይገባደዳል። በተውኔቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ትዕይንቶች ሙሉ በሙሉ ዓለማዊ አስተሳሰብ የነገሡባቸው ናቸው። በተለይ የታምሩ ስብከት፣ የሕይወት ፍልስፍናውና ስለ ቤተ ክርስቲያን ካለው አመለካከት በተቃራኒው የተሰለፉት ባለታሪኮች የሚገባ መልስ ሳይሰጡት ወይም ማንም ምንም ዐይነት አስተያየት ሳይሰነዝርበት ያልፋል።

በእኔ አመለካከት ታምሩ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ያን ሁሉ ርኩሰት እንደ ተናገረ ታሪኩ መፈጸሙ ያሳዝናል። በተለይ በሁለቱ ገጸ ባሕርያት አንደበት የሚነገረው ርኩሰት በመንፈሳዊ ጉባኤ ሊነገር የማይገባው፥ ቢነገር እንኳ በትክክል መልስ ሊሰጥ የሚችል፣ እውነቱን ይዞ ፊት ለፊት የሚሟገት ባለታሪክ ባለበት መኾን ነበረበት። ከአቀራረብ አንጻር ሲገመገም በአመዛኙ ሲታይ የአንዳንድ ባለታሪኮች ንግግር በጣም ረጅም ነው። ተውኔት ሲባል ንግግር ብቻ ይመስል በአንድ ትዕይንት ውስጥ አንድ ባለታሪክ በዛ ያለ ንግግር ሲያደርግ ይደመጣል። ይህ ደግሞ ተውኔቱን አሰልቺ አድርጎታል። ታሪኩ መቼና የት ተፈጸመ የሚለው በግልጽ አለመውጣቱ ችግሩን ያድበሰብሰዋል። ተውኔቱ የችግሩ ምንጭ ምን እንደ ሆነ ለመጠየቅ አይሞክርም። ይህም በመሆኑ ቢያንስ በአእምሮአችን ምስል ከሣች በኾነ መልኩ አልቀረበም። እዚህ ላይ የቅርስ ዘረፋና የመናፍቃን የቅሰጣ ተግባር የተያያዙ መሆናቸውንና ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቦታና በጊዜ ተወስነው የሚከወኑ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም።

### የተውኔቱ መልእክት

ዲ/ን ኤርሚያስ በጽሑፋቸው እንደ ገለጹት የተውኔቱ መልእክት፦ «ሁላችንም ቤተ ክርስቲያንን ከመናፍቃንና ከተንኰለኞች ተግተን እንጠብቅ» የሚል ነው ብለዋል። ተውኔቱ የእግዚአብሔር ቸርነት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዕለት ዕለት የማይለይ መሆኑን አበክሮ በማስረገጥ ለታዳሚዎቹ /ለምእመናን/ በማያሻማ ሁኔታ አላቀረበም። የቅርስ ዘረፋ እንደ ማዕበል ነው። ቤተ ክርስቲያን በማዕበል የማትናወጥ መርከብ ናት። የዲያብሎስ አሽከሮች የሆኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ ደባ ለመፈጸም የሚፈልጉ ግለሰቦች ይሁኑ ድርጅቶች ይኖራሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ኃይሎች ቤተ ክርስቲያንን ሊያስጉት እንደ ማይችሉ ምእመናን ተስፋ ያደርጉ ዘንድ የተውኔቱ መልእክት መሆን ነበረበት። «ደባ» ተውኔት መንፈሳዊ ጠባይ አለው ተብሎ ከሚታለፍ በስተቀር በእኔ አስተያየት ተውኔቱ በአንድ ደባ ዙሪያ ሰ የ ጠነጥን ተጀምሮ የሚፈጸም፣ የታምሩ ፍልስፍና የገነነበት፣ ተንኮሉና ደባው በተከሠ ተው አጋጣሚ /በሕግ አስከባሪዎች ትጋት/ ሲጋለጥ የሚታይበት ነው። ተውኔቱ ስለ መን ፈሳውያን ወጣቶች፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ያነሣል ሊባል ቢችልም ባመዛኙ ሲታይ መንፈሳዊ ይዘትም ሆነ ፋይዳ ይጎድለዋል ለማለት ይቻላል። ተውኔቱ ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የመሠረታት አምላካችን መድኀኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠብቃት መሆኑን፣ የቅዱሳን አባቶች ተጋድሎ የማያቋርጥ መሆኑን በግልጥ አላሳየንም። በርግጥ ሚክያስ ይጸልያል። ጸሎቱ በእምነት ጽናት የሚደረግ የተጋድሎ ጸሎት ሳይሆን በቀቢጸ ተስፋ የተዋጠ ይመስላል።

በእኔ እምነት አንድ ተውኔት መንፈሳዊ ነው ሊባል የሚገባው ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት አድርጎ፣ በመንፈሳዊ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ ለተመልካች /ለምእመናን/ ሕይወት ጽድቅና አብነት የሚሆን መልእክት ሲያስተላልፍ ነው። ይኸውም ክፋትና ኃጥእ ሲወድቅ፣ጽድቅና ጻድቅ ሲያሸንፍ በማሳየት የሚደመደም ነው። የደባ ተውኔት አብነት ምንድን ነው? ተመልካች ከአዳራሹ ሲወጣ ምን ይዞ ይወጣል? ባለንበት ዘመን የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች ይዘረፋሉ .... ይህን ዝርፊያ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ ምን እናድርግ? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ መልስ አልተሰጠንም ... በዚህ ወቅት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ምን ያድርጉ? የማኅበረሰብም ሆነ የግለሰብ የጋራና የግል ሚና ምንድን ነው? የሚለው የተምታታ ይመስላል። የተውኔቱ ዓላማ በተመልካች ኀሊና ጥያቄ ማጫር ከሆነ ያንንም በሚገባ አሳክቷል ማለት ይከብዳል። በዓለም ከንቱ ተንኰል የተካነው ባለታሪክ ዓለማዊ ከግቡ ባይደርስም አልወደቀም።

ተውኔቱን በሃያሲ ዐይን ብንመለከተው አንዳንዶቹ ባለታሪኮች ራሳቸውን የሚያውቁና መንፈሳዊ ዓላማቸውን በውል የተረዱ አይመስሉም። መሪ ተዋናዩ ሚክያስ ታምሩን የሚጠረጥር ይምስላል። ለምን ጠረጠረው? እንዴት?... ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትም ሆነ ሌሎቹን ለማሳመን ቀርቶ ለራሱ ምክንያት የለውም። የሰማቸው ወሬዎች አሉ። ሡናይ ያገኘው መረጃ ነበር። ግን ከሚክያስ እጅ አልገባም። ጠፍቷል። ሚክያስ ከታምሩ ጋር በራሱ ጥበብ ገትሮ ተዋግቶ ድል ለመምታት ብቻውን የሚፍጨረጨር ይመስላል። ይህ ደግሞ ባንድ እጅ እንደ ማጨብጨብ ይቆጠራል። ከዚህ ጋር በማያያዝ በሰበካ ጉባኤ ምርጫ ላይ የአንድ ሰው መሳተፍ ሆነ አለመሳተፍ ምን ያህል ለውጥ ያመጣል? የቤተ ክርስቲያንን ቅርስ ለማስጠበቅ የሰበካ ጉባኤ ተመራጭ መሆን ወሳኝ ነው ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ። እነዚህም በተውኔቱ በሚገባ አልተመለሱም።

ቀደም ሲል በማኅበረ ቅዱሳን የተለያዩ ተውኔቶች ተዘጋጅተው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የባህል ማእከል፣ በሕፃናትና ወጣቶች ቴአትር እንዲሁም በሌሎች መድረኮች ቀርበ ዋል። /ለአብነት፡- *«የአምላክ ባለሟል»*፣ *«የተ ከፋፈለ ልብ»*፣ *«ናቡቴን»* መጥቀስ ይቻ ላል.../። የአሁኑ «ደባ» ተውኔት በአቀራረብ ቴክኒኩ ከሌሎቹ የተሻለ ቢሆንም በይዘቱ ግን ብዙ ነገሮች ይጎድሉ ታል። በተለይ አንዳንድ አቀራረቦቹ ዓለማዊ ተውኔት አስመስለውታል። የዓለምን ጥበብ እንዳለ ገልብጦ ወደ መንፈሳዊ መድረክ ማምጣት ትልቅ ስሕተት ይመስለኛል። በመድረክ ዝግጅት፣ በተዋንያን የትወና ከሂል ደረጃ ጥሩ ጅምር ታይቷል ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ መንፈሳዊ ሥራ በመንፈሳዊ ጥበብ መታነጽ አለበት። መንፈሳዊ ሥራ ለመሥራት እግዚአብሔርን አጋዥ ማድረግ ያስፈልጋል። በጸሎት የፈጣሪያችንን ፈቃድ በመጠየቅ፣ የአባቶችን ምክር በመቀበል ሕጸጽ የሌለበት ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል። ወስብሐት ለእግዚአብሔር






© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ሰማዕቱ አባ ገብረ እንድርያስ -የጦር መኰንን እና መነኮስ



/ጌታቸው በቀለ/

*አገራችን ኢትዮጵያ ያለ ሃይማኖት የኖረችበት ጊዜ የለም:: በቤተ መንግሥትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የታሪክ መጻሕፍትና መዛግብት ተጽፈው፣ ተጠብቀው ከጊ ዜያችን የደረሱት በቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ቅትልት /ተጋድሎ/ ነው:: ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን አገልግለው፣ ለአገራቸው መልካም ሥራ ሠርተው፣ ስማቸው በትውልዱ ዘንድ ሕያው ሆኖ ሲወደስ ይኖራል:: የታሪክ ድርሳናትም ይዘግቡታል:: የታሪክ ድርሳናት ከዘገቧቸው ሰማዕታት አባቶች መካከል አንዱ አባ ገብረ እንድርያስ ነው::*

አባ ገብረ እንድርያስ በ15ኛው ምእት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የኖረ የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮስ ነው:: አባ ገብረ እንድርያስ የቀድሞ ሥራው ውትድርና ነበር:: አባ ገብረ እንድርያስ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሐረሩ ኤሚር ማኅፉድ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ ያደረሰውን መከራ በመቃወም እንደ ሙሴ ከወገኖቹ ጋር መከራ መቀበልን መርጦ ከማኅፉድ ጋር ተዋግቶ ሰማዕትነትን ተቀብሏል:: ለመሆኑ አባ ገብረ እንድርያስ ማነው? እነሆ፥ የዚህን ታላቅ አባት ታሪክ እናስነብባችኋለን::

በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት /1500-1533 ዓ.ም/ የነበረው ይማም ማኅፉድ በዐረብኛ ቋንቋ «ኤሚር» ወይም «ይማም ማኅፉዝ» በአማርኛ ቋንቋ «ማኅፉድ» ወይም «ማፉድ» ተብሎ ይጠራል:: የሐረር ኤሚር ነበር:: ከዐፄ እስክንድር /1470-1486 ዓ.ም/ና ከዐፄ ናዖድ /1486-1500 ዓ.ም/ ጀምሮ ክርስቲያኖችን እየወጋ፣ ሀብት ንብረታቸውን እየዘረፈ በመውሰድ አብያተ ክርስቲያናትን በመዝረፍና በማቃጠል ለ25 ዓመታት ሙሉ ክርስቲያኖችን ሲያስጨንቅ ኖሯል:: ማኅፉዝ ክርስቲያኖችን በጦርነት እንዲወር ድ ጋፍ የሚያደርጉለት ዐረቦች ናቸው:: ከሐረር ባላባትነቱ በተጨማሪ የዘይላን ወደብ በራሱ ቁጥጥር ሥር አድርጎ ነበር:: በዚሁ ወደብ አማካይነት ዐረቦቹ አዳዲስ መሣሪያ በየጊዜው ይሰጡት ነበር:: በማናቸውም ረገድ እንዲቋቋምና እንዲደራጅ ይረዱት ነበር::

ደብረ ሲና አጠገብ «ማፉድ ከተማ» ተብሎ በማኅፉድ ስም የተሰየመ «ማፉድ ገቢያ» የሚባል አካባቢ መኖሩን የታሪክ ጸሐፊው ክቡር አቶ ተክለ ጻድቀ መኩሪያ «የግራኝ አሕመድ ወረራ» በሚለው መጽሐፋቸው አስፍረውታል::

ማኅፉድ ዐረቦቹ ለሚያደርጉለት ርዳታ በበኩሉ ከኢትዮጵያ ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስ እንደ ገጸ በረከት እያደረገ በመላክ ያስደስታቸው ነበር:: ማኅፉድ በወቅቱ የበላይነት ከነበራቸውና እስልምናን በጅሃድ መንፈስ ለማስፋፋት ይጣጣር ከነበረው ከኦቶማን ቱርክ እስላማዊ መንግሥት ጋር በነበረው ቀረቤታ በየጊዜው የሚላኩለትን የጦር መሣሪያዎች በመጠቀም በኢትዮጵያ ምዕራብ ደጋማ ግዛቶችና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ በርካታ ወረራዎችንና ዘረፋዎችን አካሒዷል::

ዐፄ ልብነ ድንግልም በማኅፉድ ድርጊት ተበሳጭተው በ1508 ዓ.ም ጦራቸውን አስከትተው ከማኅፉድ ጋር ለመዋጋት ወደ ይፋት ሔዱ:: በመጽሐፍ ቅዱስ እስራኤላውያንን ምድያማውያን ለሰባት ዓመት ካደረሱባቸው መከራ ነጻ እንዲወጡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ስለ ሆነ ጌዴዎንን አሥነስቶ ጠላቶቻቸውን ድል አድርጓል:: /መሳ.6፥1-15/:: ማኅፉድም በክርስቲያኖች ላይ ካጸናባቸው መከራ ነጻ እንዲወጡ እግዚአብሔር ወታደሩን አባ ገብረ እንድርያስን አሥነሳው:: አባ ገብረ እንድርያስም ዐፄ ልብነ ድንግልን ተከትሎ ዘመተ::

ፖርቱጋላዊው የታሪክ ጸሐፊ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ስለ ጦርነቱ እንዲህ ሲል ያትታል:- «የቤተ መንግሥቱ ሰዎች እየዘፈኑ ስሙን የሚያነሡት /የሚፎክሩበት/ ማኅፉዝ የተባለ የእስላሞች አዛዥ ክርስቲያኖችን ለመውጋት የሚነሣው በዐቢይ ጾም ወቅት ነው:: ዐቢይ ጾም የሕዝቡን ኃይል እንደ ሚቀንሰው ስለ ገመተ 25 ዓመት ሙሉ የንጉሡ ነገሥቱን ግዛት የሚደፍረውና በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ አደጋ የሚያደርሰው በጾም ወራት ነበር::» ብሏል::

ጦረኛው ማኅፉድ በክርስቲያኖች ላይ ካለው ጥላቻ የተነሣ ጦርነት የሚያውጀው በዐቢይ ጾም መሆኑን ነጋ ወልደ ሥላሴ «ባለታሪክ ኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ገልጸውታል:- *«ማኅፉድ ዐቢይ ጾምን ምክንያት እያደረገ በዐፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ወረራ አካሒዷል:: ዐፄ ናዖድም ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ዘምተው ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀሩ የማኅፉድን ሠራዊት ድል አድርገውታል::*

*ማኅፉድ በዐፄ ናዖድ የደረሰበትን ሽንፈት ካረሳሳና ከአዘናጋ በኋላ ከቱርኮቹ ባገኘው ርዳታ ለወረራ በድጋሚ ተነሣ፤ ቱርኮችም ማኅፉድ በክርስቲያኖች ላይ በሚያደርሰው ጥቃት የተነሣ «የዘይላ ሼክ» ብለው ሾሙት:: ለብዙ ጊዜ በጠላትነት ይመለከተው የነበረውን የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ለመውጋት በድጋሚ ለወረራ መጣ:: በኢትዮጵያ ላይ የቱርክ ጥይት ነደደ::*





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

*ማኅፋድ ክርስቲያኖችን ለማጥቃት ዐቢይ ጾምን እንደ ምቹ ጊዜ የሚቆጥርበት ምክንያት ምእመናን በዚህ ወራት በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቸው ተሰባስበው፣ በጾም በጸሎት ተወስነው፣ ከእግዚአብሔር የሚገናኙበት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሀገራቸው የሚጸልዩበት ወቅት ስለኾነ ነው::*

*«ጾም ክርስቲያኖችን ስለሚያደክማቸው ማጥቃት እችላለሁ፤» ብሎ የተነሣው ማኅፋድ በተከታታይ ለሠላሳ ዓመታት ያህል ወረራ ያካሄደው በዐቢይ ጾም ወቅት ነበር:: ማኅፋድ በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኙ አብዛኛዎቹን የኢትዮጵያ ግዛቶች ምድረ በዳ አድርጓቸዋል:: በርካታ ክርስቲያኖችን ገድሏል:: አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥሏል:: ሕዝበ ክርስቲያኑም «በዐቢይ ጾም ጦርነት አይበጀንም፤ ይልቁንም ሁሉን ማድረግ ወደ ሚችለው ወደ እግዚአብሔር እንጸልይ» ብለው መታገሣቸው ማኅፋድን የልብ ልብ ቢሰጠውም ፍጻሜውን ግን አላሣመረውም:: /ኀጋ ወልደ ሥላሴ፤ ባሕታሪክ ኢትዮጵያ፤ ገጽ 118 - 119/::*

ዐፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ24ኛው ዓመት ማኅፋድ ክርስቲያኖች በሚገኙበት ገብቶ የተለያየ ሥቃይ አድርሶባቸዋል:: በፈጠጋር አውራጃ በገባ ጊዜ ክርስቲያኖቹ ማኅፋድ ከሚያደርስባቸው መከራና ሥቃይ ፋታ ለማግኘት ሸሽተው በየጋራ ሸንተረሩ ሲደበቁ ማኅፋድ እየተከታተለ ከየተደበቁበት እያወጣ ገደላቸው፤ ገዳማት አድባራቱን አወደመ፤ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍትን አቃጠለ፤ የታሪክ ሰነዶች የእሳት እራት ሆኑ፤ ካህናቱ ገዳማቸው ሲቃጠል ሲያዩ እሳት ውስጥ እየገቡ አለቁ፤ ምእመናንን የሚያጠምቅ፣ ሕፃናትን የሚባርክ ካህን ጠፋ::

ማኅፋድ የገደለውን ገድሎ፣ የአጠፋውን አጥፍቶ የማረከውን ሕዝብ:

- «የሚቀጥለው ዓመት በጾማችሁ ወቅት ስለምመጣ ለፈረሶቼና ለሠራዊቴ የሚሆን ብዙ እህል አምርታችሁ ጠብቁኝ» ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ አሰናበታቸው:: ወታደሩን ግን:

- «እናንተ የንጉሣችሁን እንጀራ የምትበሉ ነገር ግን አገሩን በደንብ የማትጠብቁ ናችሁ» ብሎ እየተሳለቀ የማረካቸውን ገደላቸው:: በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ መከራ ተፈራረቀባቸው::

አባ ገብረ እንድርያስ ያለበትን የክርስቲያኑን ጦር ማኅፋድ አይቶ:

- «እኔ እዚሁ ለመሞት ቆርጫለሁ፤ አንተ ግን በፈረስ አምልጥ» ብሎ አጠገቡ ለአለው ለአጼሉ ንጉሥ /ለሡልጣን መሐመድ/ ስለ ነገረው ሡልጣኑ አመለጠ:: ማኅፋድ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ከሰልፉ ውስጥ ወጥቶ ጐልዮድ እንዳደረገው ሁሉ:- «ከመካከላችሁ አንድ ሰው ከእኔ ጋር ለመዋጋት የሚደፍር እንዳለ ይምጣና ይሞክረኝ::» ብሎ ጠየቀ:: አባ ገብረ እንድርያስም «እኔ አለሁ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አለ» ብሎ ማኅፋድን ሊገጥመው ወጣ:: ጦርነቱን ገጠሙ:: አባ ገብረ እንድርያስ ተንደርድሮ ሔዶ የማኅፋድን አንገት በጐራዴ ቀላው:: ማኅፋድ ወዲያው ሞተ:: ጦርነቱ በክርስቲያኑ ጦር አሸናፊነት አከተመ:: ወራሪው የማኅፋድ ሠራዊትም ተሸነፈ:: ማኅፋድና ሠራዊቱ ድል ሆኑ::

የሚደንቀው ነገር በመልእክት ተላልከውና ተስማምተው ይሁን ወይም እንደ አጋጣሚ ማኅፋድ በተሸነፈበት ቀን የሕንዱ የፖርቱጋል አገረ ገዥ ሎፖ ሶአርስ /LOPO- SOARES/ በመርከብ በድንገት መጥቶ ማኅፋድ ከዐረቦች ጋር እንደ ግል ንብረቱ ይዞት ሸቀጥና መሣሪያ የሚለዋወጥበትን የዘይላን የወደብ ከተማ ክርስቲያኖቹ እንዳይጠቀሙበት አቃጥሎ፣ አፈራርሶ ተመለሰ::

ማኅፋድ ሞቶ ሡልጣን መሐመድም ከሸሸ በኋላ የክርስቲያኑ ጦር እስከ ዘከራ ከተማ ደርሶ ማኅፋድ የዘረፋቸውን ንብረቶች አስመልሶ ሠራዊቱ በደስታ ወደ ሥፍራው ተመለሰ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የወጣቱን ንጉሥ ነገሥትና የመነኩሴውን ዝና ቤተ መንግሥቱም ሕዝቡም አደነቁ፤ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ:: /ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ *የግራኝ አሕመድ ወረራ*፤ ገጽ 103-104/::

ማኅፋድን ድል ያደረጉት አባ ገብረ እንድርያስ ከዐፄ በእደ ማርያም /1460- 1480 ዓ.ም./ ጀምሮ ከሹመት ወደ ሹመት እየተዛወሩ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል የደረሱ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሰው ናቸው:: በጥበብና በትምህርት ብቻ ሳይሆን እንደበተ ርቱዕ /ንግግር ዐዋቂ/ ነበሩ:: ይሁንና በዐፄ ናዖድ ዘመን ምላሳቸው ተቆርጦ ነበር:: ፖርቱጋላዊው የታሪክ ተመራማሪ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ በመጽሐፉ እንደ ገለጸው:- «አባ ገብረ እንድርያስ በጣም የተከበረና ብዙ ገቢ ያለው መነኩሴ ነው:: ከዚህ የጀብዱ ሥራ /ማኅፋድን ድል ከማድረጉ/ በተጨማሪ ብዙ ታላላቅ ሥራዎችን ለሀገሩም፣ ለቤተ ክርስቲያኑም ሠርቷል:: ንግግርም ዐዋቂ ነው:: ፖርቱጊዞችን፣ የሚወድ ቤተ ክርስቲያንን የሚረዳ አባት ነው:: ነገር ግን ይህ ሰው በጣም ማውራት ስለሚወድ ዐፄ ናዖድ ምላሱን አስቀነጠበው::» ይላል::

የታሪክ ምሁሩ ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ደግሞ:- «አባ ገብረ እንድርያስ በ15ኛው ምእት ሁለተኛ አጋማሽና በ16ኛ መጀመሪያ አጋማሽ ላይ የኖረ የደብረ ሊባኖስ መነኩሴ ነው:: ከመመንኩሱ በፊት ሥራው ውትድርና ነበር:: በውትድርና ሥራው ላይ በነበረ ጊዜ ውሸት በመናገሩ ምላሱ ተቆረጠ:: ከዚያ በኋላ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብቶ መነኮሰ::» በማለት ያስረዳሉ:: */ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት፣ ቁጥር 12፣ ያልታተመ/::*

አባ ገብረ እንድርያስ እስከ ግራኝ አሕመድ መነሣት ድረስ ቆይተዋል:: ግራኝ በከፈተው ጦርነት ብዙ ሕዝበ ክርስቲያን በመሞታቸው፣ እርሻዎች ሳይታረሱ በመቅረታቸው፣ ረኀብና ድህነት በመስፋፉ፣ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት በመውደማቸው፣ ወራሪው ሠራዊት በያዛቸው ቦታዎች የሚኖረው ሕዝበ ክርስቲያን ሃይማኖቱን እንዲለውጥ፣ እምቢ ያሉት ደግሞ እንዲሰየፉ መገደዳቸው አባ ገብረ እንድርያስን ሰላም ነሳቸው:: ስለዚህም ከራስ ወሰን ሰገድ ጦር ጋር ሆነው ከግራኝ አሕመድ ጋር ተዋግተዋል:: በካህንነታቸው ሠራዊቱን እያስተማሩ፣ ጸሎት እያደረጉ በሀገራቸው ላይ የመጣውን ወራሪ ኃይል ለመመከት ከወገኖቻቸው ጋር ሆነው በጦር ሜዳ ተዋግተው ሰማዕትነትን ተቀብለዋል:: የአባ ገብረ እንድርያስን አሟሟት በተመለከተ ሙሴ ረኔ ባሴት ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ በተረጎመው የዐረብ ፋቂህ መጽሐፍ እንዲህ ተገልጾአል:- «አባ ገብረ እንድርያስ ሀገሩን ላለማስደፈር፣ የቤተ ክርስቲያኑንና የክርስቲያኑን ሕዝብ ክብር ለመጠበቅ በጦር ሜዳ ተዋግቶ በዘጠና ዓመቱ ሞተ::» ይላል:: /ዐረብ ፋቂህ፤ ገጽ 260-267/::

በዚያን ዘመን የነበሩ ባለሥልጣናት በአብዛኛው የቤተ መንግሥቱንና የቤተ ክህነቱን ተግባር ደርበው የሚሠሩ ናቸው:: አባ ገብረ እንድርያስም በመጀመሪያ ዘመናቸው የታወቁ ተዋጊ የጦር መኮንንና ሀገረ ገዥ ሆነው ሲኖሩ በኋላም መንኩሰዋል:: በዚህም ዐይነት የሽማግሌና የመነኩሴ አርበኛ ነበሩ::

የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ:- «ሰውን ብትታገልና ብትዋጋ ታሸንፈዋለህ፤ ቤተ ክርስቲያንን ግን ለማሸነፍ አይቻልም:: ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ትዋጋለች፤ ተሸንፋ ግን አታውቅም:: ዲያብሎስ ዝናሩን አራገፈ፣ ቀስቱንም ጨረሰ፣ ቤተ ክርስቲያንን ግን አልጐዳትም» እንዳለ ማኅፋድም የተለያዩ መከራዎችን በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ ቢያደርስም እርሱ ግን አለፈ:: ቤተ ክርስቲያን ግን አለች:: ወደፊትም ትኖራለች::

*የሰማዕቱ አባ ገብረ እንድርያስ የሩጫው ቅድሚያ፣ የድካሙ በረከት ከእኛ ጋር ይሁን:: አሜን::*





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# እልፍኝ እና ሥዕል ቤት ቤተ መንግሥት እና ታቦት

በኢትዮጵያ የሕንፃ አብያተ ክርስቲያናትና መማጠኛ ሥዕል ቤቶች በአብያተ መንግሥታት ዙሪያ መተከል ሥራት ነበር:: በአዲስ አበባ የእንጦጦ ደብረ ማርያም እና የእንጦጦ ራጉኤል አብያተ ክርስቲያናት መሬት ተባርኮ መሠረታቸው ሲተከል /1877 ዓ.ም/ የእንጦጦ ቤተ መንግሥት ሥራም እየተካሔደ ነበር:: «በ1889 ዓ.ም በእምዬ ምኒልክ እልፍኝ /በታላቁ ቤተ መንግሥት/ አጠገብ የሥዕል ቤት ሥዕለ ማርያም ሥዕለ ስቅለት ያለባት፣ ሰዓታት ቋሚዎች የሚቆሙባት፣ ምሕላ የሚያዝባት ነበረች:: አልፎ አልፎ እየተቀደሰባት፣ ከሌሊቱ ስምንተኛው ሰዓት ጀምሮ ከመዓልቱ /ከቀኑ/ እስከ አንድ ሰዓት ድረስ ንጉሥ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ የሚጸልዩባት ነበረች:: በቀረው ግን መዓልቱን ሁሉ እስከ 12 ሰዓት ድረስ መነኮሳቱ፣ ሊቃውንቱ፣ መኳንንቱ፣ መሳፍንቱ፣ ወይዛዝሩ፣ መበለታቱ እንደ ፈቃዳቸው፣ እንደ ትሩፋታቸው ሲጸልዩ የሚውሉባት ሲያ ይዋት ልብ የምትስቅል ሥዕል ናት:: ዐፄ ምኒልክ ወደ ዐድዋ ሲዘምቱ «በደኅና የተለስኩ እንደ ኾን ከዚያው ላይ ታቦት አስገብቸ አስቀድሳለሁ» ብለው ብጽአት አድርገው ነበር:: ከዚያም ካጠገቡ ቅዳሴ የሚያስማ፣ መጽሐፍም የሚደገምባት ሥራዋ ያማረ አምስት መስኮት ባለመስታወት አራት ደጃፍ ያለበት ቤት /በኋላ ደብረ መንክራት ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት/ ሠሩ:: በሁዳዴም በፍልሰታም ጦም ከዚያች ሥፍራ ንጉሠ ነገሥቱም ንግሥቲቱም እቴጌ ጣይቱ ፈጣሪያቸውን ደጅ ይጠኑባታል:: ከዘመቻው ገብተው ከርመው በጥቅምት 1889 ዓ.ም እልፍኝ ገብርኤል የሚባል፣ ከዚያም ከእልፍኙ አጠገብ እጅግ ሥራዋ ያማረች፣ የሕንድ ሠራተኞች እየጠረቡ፣ እያለዘቡ አድሰው ሠሩዋት:: በዚሁ ጊዜ ግን አንድ ማለፊያ እልፍኝ፣ የግብር ማግቢያ ቤተ ንጉሥ እልፍኝ ሰገነት አጠገብ ተሠርቷል::» /ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ 1959 ዓ.ም፣ ገጽ 123፣ 191፣ 193፣ 278፣ 333/:: በ1917 ዓ.ም የተመሠረተው መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ /በተለምዶ «ግቢ ማርቆስ»/ እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ንጉሠ ነገሥቱና ቤተሰቦቻቸው፣ ሊቀ ጳጳሱ፣ አልፎ አልፎም ጳጳሳቱ የሚጸልዩበት፣ የሚቀድሱበት ሥዕል ቤት ኋላም ቤተ ክርስቲያን ኾና በቀድሞው ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት /የዛሬው አ.አ.ዩ/ ቅጥር ግቢ የሚገኝ ነው:: በኢዮቤል (ብሔራዊ) ቤተ መንግሥት ደግሞ የእመቤታችን ጽሌ የሚገኝባት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴና ንጉሣውያን ቤተሰቦች የሚማጠኑባት /ከ19 54-1966 ዓ.ም/ ሥዕል ቤት /ዛሬ በጾመ ፍልሰታ ይቀደስባታል/ አሁንም ድረስ እንዳለች ይታወቃል:: /መጋቤ ሥርዐት አባ ዐሥራተ ማርያም ደስታ/::

/ወደ ገጽ ፴፯ ዞሯል/

# አስቸኳይ የርዳታ ጥሪ ለግሮት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

የግሮት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በአምባሰል ወረዳ በ022 ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ክልል ውስጥ ትገኛለች:: ከአዲስ አበባ 488 ኪ.ሜ. ርቀት ግሸን ማርያም ጥግ ሐሙሴት ከተባለው አንሥቶ በግምት በእግር 15 ኪ.ሜ. ተጉዘን ግሮት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንደርሳለን::

ግሮት ቅድስት ማርያም የተመሠረተችው በ434 ዓ.ም. በዐፄ ኢዮአብ ዘመነ መንግሥት /425-435 ዓ.ም/ መሆኑን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያለው ቅርስ ይገልጻል:: እስከ 917 ዓ.ም. ድረስ በገጠር ሥርዐት ትተዳደር ነበር:: በ917 ዓ.ም ዐፄ ድልነዓድ /917-927 ዓ.ም/ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ጀርባ ደብረ እግዚእ ከሚባለው ቦታ ላይ በግምት 80 ኪሎ ሜትር ርቀት፣ በሰማይ ላይ ሥዕለ ማርያምን አዩ:: በርካታ ካህናትና ሠራዊት አስከትለው በአካባቢው ሲደርሱ በወቅቱ ብቸኛ የሆነችውን የእመቤታችንን ተአምር በማየታቸው «ግረት ለማርያም ይደሉ፡ ለማርያም ስግደት ይገባል» ብለው ሰግደው፣መባ ሰጥተውና አመስግነው ታሪኳ እንዲጻፍ አድርገዋል:: «ግረት» ማለት መገዛት ሲሆን «ይደሉ» ማለት ይገባል ማለት ነው:: እርሳቸውም ጥር 21 ቀን 918 ዓ.ም. «ሀገረ ግረት ቅድስት ማርያም» ብለው ቤተ ክርስቲያኗን አሠርተውና አስደብረው «መሐሷ ገነት ዳሯ እሳት ትሁን» ብለው ከ300 በላይ አገልጋይ ካህናትና መሪጌቶች መድበው ሔደዋል::

ከዚህ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኗ በስተ ሰሜን በኩል ባለው ጨፌ የዐማኑኤል ጠበል ፈልቆ ብዙ ሕሙማን ሲፈወሱበት በመታየቱ የጥንት ባለመሬቶች «አካባቢያችን የበሽተኞች መጠራቀሚያ ሆነች» ብለው በጋሻ ደፈኑት:: ጠበሉም ውስጥ ለውስጥ ሔዶ ከቤተ መቅደሱ ውስጥ ፈልቆ ብዙ ተአምራት በመሥራት ላይ እያለ 1444 ዓ.ም. ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀሉን ይዘው በዚሁ ቦታ ዐርፈው ነበር:: የጠበሉን ተአምራት የእመቤታችንን አማላጅነት አይተው የኀደለውን አሟልተው የመስቀሉን አጣኝ የነበረውን አለቃ አድርገው ሹመው ሔደዋል::

በ1463 ዓ.ም የዐፄ በእደ ማርያም ቤተ መንግሥታቸው በዚሁ ሰበካ ድቡ ከተባለው ቦታ ስለነበር የሚያስቀድሱት በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ነበር:: በዚሁ ዘመን አንድ ካህን በመንገድ ሲሔድ ጠርተው ዝክር ዘክርልን አሉት:: እርሱም እሺ ብሎ ዘከረ:: ከዘከረ በኋላ «እህል ቅመስ» ሲሉት ጊዜው የችግር ወቅት ስለነበር እሺ ብሎ እህል ቀምሶ ወደ ግሮት ቅድስት ማርያም ሔደ:: ቀኑ የኅዳር ማርያም ስብሰባ ስለነበር ዐፄ በእደ ማርያም ሊያስቀድሱ መጡ:: በዚሁ ሰዓት የቅዳሴው መግቢያ በደረሰ ጊዜ ንጉሡ ሊያስቀድሱ ገቡ:: ይሁን እንጂ ካህናቱ ቅዳሴ ሊገቡ አልቻሉም:: ንጉሡም «ለምን ቅዳሴ አትገቡም፡ ሰዓቱ ደርሶአል» አሉ:: ቄሱም አይቀድስ፥ ፈጣሪውን ፈራ፡ አይተወው፥ ንጉሡን ፈርቶ ፈራ ተባ እያለ ለንጉሡ ነገራቸው:: ንጉሡም «እንዴት ምግብ ትበላለህ? የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ ክቡር ደም እያለልህ!!» ብለው ተቆጡ:: «ይህን ቄስ ስቀሉት!» ብለው እርሳቸው ካህን ስለነበሩ ቅዳሴ እንደ ገቡ ከምህላ ጸሎት ሲደርሱ ከመቅደስ ካለው ጠበል መሐል ትልቅ ጥቁር እባብ ወጥቶ ከእግር እስከ ራሳቸው ተጠመጠመባቸው:: በዚህ ጊዜ በጣም ደንግጠው ወደ እመቤታችን አመለከቱ:: እንዲህም አሉ:-

«ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ማርያም እምነ ናስተበቍዐኪ እምአርዌ ነዓዊ ተማኅፀነ ብኪ በእንተ ሐና እምኪ ወኢያቄም አቡኪ ማኅበረነ የዐም ድንግል ባርኪ፡ እመቤታችን ማርያም ሆይ፥ ሰላም ላንቺ ይሁን እያልን እንሰግድልሻለን፡ እንማልድሻለን፡ ከአዳኝ አውሬ ታድኘ ዘንድ ተማፅነንብሻል፡ ስለ እናትሽ ስለ ሐና ብለሽ ስለ አባትሽ ስለ ኢያቄም ብለሽ ድንግል ማኅበራችንን ዛሬ ባርኪልን» ብለው ጸለዩ:: በዚህ ጊዜ እባቡም ለቆአቸው ሔዶአል:: ከቅዳሴው ከወጡ በኋላ «ነአኩተከን» ደርሰዋል:: በዚህም «ሰላም ለኪ፣ና ነአኩተከ» ለምእመናን የዘወትር ጸሎት እየተጠቀምንበት ይገኛል:: ንጉሡም ቄሱ ካልተሰቀለ እንዳይሰቀል ትእዛዝ ቢሰጡም ወታደሮች ቸኩለው በወይራ ላይ ሰቅለውት ተገኘ:: ቄሱ የተሰቀለባት ወይራ አሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ትገኛለች:: ጠበሉን ግን በጋሻ ደፍነውት ዛሬ ከገደሉ ላይ ወጥቶ ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸውን እየፈወሰ ይገኛል:: ጠበሉን ያለ አጥማቂ ካህን በመጠቀም ነው ፈውስ የሚገኘው:: ንጉሡ ስማቸው በእደ ማርያም የተባለው እናታቸው ያለ አዋላጅ ብቻቸውን ወልደዋቸው ሳለ:- «ምነው ብቻሽን!» ቢሏቸው «አንድ ቀይ ሴት ሰውነቴን ስለ ዳሰሰችኝ በሰላም ወልጄለሁ» አሏቸው:: በዚህም ምክንያት «ይህማ በማርያም እጅ ተወለዱ» ማለት ነው ሲሉ በእደ ማርያም አሏቸው:: ዐፄ በእደ ማርያምን ያስተማሯቸው ኢትዮጵያዊው የዋድላ መንገድ ቅኔ ደራሲ የሐንስ ገብላዊ ናቸው::

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከ1966 ዓ.ም. በፊት ሰፊ የሆነ መሬት ነበራት:: በዚህ መሬት ላይ የሰፈሩና በግብርና የሚተዳደሩ በርካታ አገልጋይ ካህናት


/ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል/



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እልፍኝ እና ሥዕል ቤት...

/ከገጽ ፴፯ የዞረ/



ግኮሞ ናሬቲ ከአንድ ወጥ የጥድ ዕንጨት ያሠራው የዐፄ ዮሐንስ ዙፋን

***በመቐለ ዐፄ ዮሐንስ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ይገኝ የነበረው ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል ሁኔታ ግን ከእኒህም ለየት ይላል፤ እንዴት? በምን?***

እንደ ምን ሰንብታችኋል የተወደዳችሁ አንባብያን፡ ባለፉት ሦስት ተከታታይ እትሞቻችን ከትግራይ ክልል የጉዞ ዘገባችን ቀዳሚ የኾነውን የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ኮሌጅ አመሠራረት፣ የሥራ ክንውንና የወደፊት አቅጣጫ እንዲሁም የተቋሙ መሥራችና የትግራይ ህገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩትን የብፁዕ አቡነ ዮሐንስን ዜና ሕይወትና ሥራዎች ስናስነብባችሁ መቆየታችን ይታወሳል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ከዚያው ከመቐለ ሳንወጣ እግረ መንገዳችንን ለአፍታ ቆይታ ያደረግንበትን የዐፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት እናስቃኛችኋለን:: መልካም ንባብ::

የቅዱስ ፍሬምጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ኮሌጅ ቆይታችንን በግማሽ ቀን ውስጥ ነበር ያጠናቀቅነው:: ከመቐለ ሳንወጣ ለመጎብኘት ካቀድናቸው ታሪካዊ ሥፍራዎች መካከል የዐፄ ዮሐንስ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት አንዱ ነበር:: ወደ ቤተ መንግሥቱ መቅረጸ ምስልና መቅረጸ ድምፅ ይዞ መግባት ስለማይቻል የተለመደ ጓዛችንን መሸከም አላስፈለገንም- ቅሬታ ቢሰማንም:: ይህም ኾኖ የመንፈሳዊ ኮሌጁ አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሐላፊ ሊቀ ትጉሃን ላእከ ታረቀ የመደቡልን መኪና አልተለየንም ነበር:: እንደ መኪናዋ ሁሉ ምቾት የሚሰጠው የአሽከርካሪዋ የአቶ የማነ ሥዩም ጨዋታና ወግ፣ በማኅበረ ቅዱሳን የመቐለ ንኡስ ማእከል ጸሐፊ የወጣት የማነ ሃይሉ ያልተቆጠበ ድጋፍ ድካምን የሚያስረሱ ናቸው::

*የ«ሃፀይ ዮሃንስ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት»* በተለምዶ *«ማይላሐም»* እየተባለ በሚጠራው የከተማዋ ሰሜናዊ ምሥራቅ ክፍል ይገኛል:: ቤተ መንግሥቱ ዙሪያው በዐጸዶች የተከበበና ውስጡ ከጊዜ በኋላ አስፋልት በተነጠፈለት መሬት ላይ የተጠንጣለለ፣ የቀደመ ግርማውን እንደ ያዘ ያለ ኪነ ሕንጻ ይታይበታል:: በአስጎብኚው እንደ ተገለጸልን በራስ መንገሻ ሥዩም ጊዜ ግንቡና የወለል ቤቱ ከተደረገለት የሲሚንቶ ተኩስ በቀር ዕድሳት /ጥገና/ አያውቀውም:: በዘመናችን የሕንጻ አሠራር የቤተ መንግሥቱ ርዝመት ሦስት ደርብ /ፎቅ/ ሊወጣው እንደ ሚችል ቢገመትም ከምድር ቤቱ ጋር የንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን የተሠየመበት አንድ ደርብ ብቻ ነው ያለው::

የምድር ቤቱ በቋሚ ምሰሶዎች ወደ ጎን በረድፍ የተከፈሉ ሦስት አዳራሾች አሉት:: በዋናው በር ሲገባ የመጀመሪያው መደዳ ለሠራዊቱ፣ መካከለኛው ለካህናቱ፣ ሦስተኛው ደግሞ ለመኳንንቱ የግብር አዳራሽ ኾነው ያገለግላሉ:: ንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋናቸው ሲወርዱ በመጀመሪያ የሚያገኙት ሠራዊቱን ነው፤ ይህም ከደኅንነት ጥበቃ አንጻር መኾኑ ተገልጾልናል:: ዙፋኑና ወደ ዙፋኑ የሚያወጣው ደረጃ ከአንድ ወጥ የጥድ እንጨት ተቀርጾ የተሠራ ነው:: አጠቃላይ መጠኑ አነስተኛ ቤትን የሚያክል ሲኾን በአፍሪካ ደረጃ መሰሉ እንደ ሌለ ይነገራል:: ተመልካቾቹን እየተዟዟረ የሚመለከት ሕይወት ያለው የሚመስል የዐፄ ዮሐንስ ሥዕለ ገጽ ዙፋኑ በሚገኝበት ክፍል መውጫ ላይ ተመልክተናል:: ከጥድ እንጨት የተሠሩት ነገሮች ሁሉ ቫርኒሽ የተቀቡ ያህል አንጸባራቂ ገጽታ ቢኖራቸውም የጥንት ይዞታቸው እንጂ ዕድሳት ተደርጎላቸው እንዳልኾነ ተረድተናል::

የዐፄ ዮሐንስን ቤተ መንግሥትና ዙፋናቸውን የሠራላቸው ጃኮሞ ናሬቲ የተባለ ኢጣሊያዊ አናጢ ነው:: ጃኮሞ ናሬቲ የኢጣልያ ንጉሣዊ መንግሥት በ1852 ዓ.ም በደንብ ከተቋቋመና የአሰብን ወደብ በእጁ ካደረገ በኋላ በሚሲዮናዊነት፣ በንግድና በሞያ አገልግሎት በኩል ገብተው ባለሟል ከኾኑትና ለኢጣልያ መስፋፋት የምርመራና የስለላ ሥራ ከሠሩት የላዛሪስት ሚስዮናውያኑ ከእነ ጁሴፔ ሳፒቶ፣ ፒየጃና ስቴላ አንዱ ነበር:: ናሬቲ በ1862 ዓ.ም ቤተ መንግሥታቸውንና ዙፋናቸውን ሠርቶ ንጉሠ ነገሥቱን ካስደሰታቸው በኋላ የሰሎሞንን ኒሻን ሸልመውታል:: ከዚያም ወዲህ ከአገሩ ቋንቋ ውጭ ዐረብኛም አማርኛም እየደበላለቀ በመናገር በበዓል ቀን እንግዳም በመጣ ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት ጃኖ ወይም ኩታውን አደግድጎ ወጣ ገባ እያለ ሲያስተናብር ብዙ የውጭ አገር ሰዎች እንዳዩት በመጽሐፋቸው ገልጸውታል:: እንዲያውም በአንድ ወቅት ከሚላኖ የመጡትን <የንግድ ምርመራ ማኅበር> መልእክተኞችን ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ለማገናኘት ባደረገው ጥረት ንጉሠ ነገሥቱ የሚከተለውን ምላሽ ጽፈውለት ነበር፤ *«ያንተና የዘመዶችህ ደብዳቤ ደርሶኛል:: ቀድሞ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች ሲመጡ፤ መልካምነታቸውን ገልጸውልኝ ወዳገር ከገቡ በኋላ ለመንግሥቴ እንቅፋት ይፈጥሩብኛል፥ የሃይማኖት ችግር ይፈጥሩብኛል፥ አንተን ስለ ማውቅህ ሌሎቹ የአንተ ወገኖች እንዳንተ መልካም ይመስሉኛል፥ አገር የአምላክ ስለሆነ ለክፉዎች ካልኾነ በቀር አገሬን ለማንም አልዘጋም:: ስለዚህ እነዚህን ደጎች ኢጣልያኖች ለማየትና ለመገናኘት እወዳለሁ::»* /*ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ 1982 ዓ.ም፣ ገጽ 121፣ 321-323/::

በጋለ ርእይ የተሞላውንና ዐፄ ቴዎድሮስ የደከሙለትንና የሞቱለትን የኢትዮጵያ አሐዳዊ መንግሥት ትልም እውን ለማድረግ ዐፄ ዮሐንስ የተከተሉት የአንድነት ስልት የተገራ ክልላዊነትን የሚፈቅድና የፖለቲካ ትዕግሥትን የተላበሰ ከመኾኑም በላይ ሃይማኖታዊ ገጽታም እንደ ነበረው የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ:: ይህም በክርስቲያኑ ሕዝባቸው መካከል «የጸጋ ልጅ፣ የቅባት ተከታይ» የሚባለው ሁሉ ተደምስሶ ሁሉም ክርስቲያን በተዋሕዶ እንዲያምን በ1870 ዓ.ም በቦሩ ሜዳ ከንጉሥ ሚኒልክ ጋር በመኾን በሠሩት ጉባኤና ሕዝቡን ከእስልምና ወደ ክርስትና በመመለስ ባደረጉት እንቅስቃሴ ይገለጻል:: በዚህ የተነሣ በፈረንሳይና በኢጣልያ ጋዜጦችና መንግሥታት ዘንድ:- **«እምቢ ባይ፣ የካቶሊክና የእስላም ጠላት፣ አሳበ ግትር»** እየተባሉ ቢነቀፉም እርሳቸው ግን ***«በፈቃድ እንጂ በኃይል የተደረገ ነገር የለም»*** በማለት መልስ ሰጥተዋል:: /ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ 1848 እስከ 1966 ዓ.ም* ፥ 1989 ዓ.ም፣ ገጽ 46-48፤ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ *ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት*፥ 1982 ዓ.ም, ገጽ 61፣ 200-20::

ዐፄ ዮሐንስ የዲቁና ሥልጣነ ክህነት የነበራቸው፣ በአንድ ሚስት የቆረቡ፣ ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ በድበቅ ለመመንኮስ ሁሉ ደርሰው ነበር ይባላል:: ከዚህ የተነሣ በሕዝቡ ዘንድ *«ባሕታዊው ንጉሥ»* ይባላሉ:: ይህን ሁሉ ያነሣነው ንጉሡ ለሃይማኖት ጉዳይ ቅድሚያ ይሰጡ እንደ ነበር ለማውሳት ነው::

በመቐለው የዐፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ዙፋኑ ባለበት ክፍል ወደ ጣሪያው ወለል ከወጡ በኋላ በስተሰሜን አቅጣጫ አነስተኛ የተቆለፈ ቤት ይመለከታሉ:: ይህ ቤት ከዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት /1864-1881 ዓ.ም/ ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል የነበረበት ነው:: ቤቱ አጣኝ ካህን ተመድቦለት ይኖር ነበር:: ክብረ በዓሉ ታኅሣሥ 19 ቀን ሲኾን በአስገራሚ ሁኔታ ታቦቱ ወጥቶ ንጉሡ የሚሠየሙት፣ ካህናቱ ሥርዐት የሚያደርሱት በሰፊው የቤተ መንግሥቱ የጣሪያ ወለል ላይ ነበር::

ከ1966 ዓ.ም ሥርዐተ መንግሥት ለውጥ በኋላ ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል ከዚያ እንዲወጣ ተደርጎ ዐፄ ዮሐንስ በ1868 ዓ.ም ከቤተ መንግሥታቸው በስተ ምሥራቅ ባሠሩት የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ


/ወደ ገጽ ፴፰ ዞሯል/





© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



*ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ነው:: ማኅበራችን ይህን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት እና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዘዳንት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ነው:: አጠቃላይ የሥራ ሒደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል ይደረግበታል::*

# መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ለጠባይ ለውጥ

ባለፈው እትማችን የመንፈሳዊ ምክክር አገልግሎትን (Pastoral Counseling) አስፈላጊነትና ከሌላው የሚለይባቸውን ነጥቦች ለማንሣት ሞክረናል:: በዚህ እትማችን ደግሞ የቅድመ ምርመራና የድኅረ ምርመራ መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ ምክክር አገልግሎትን ምንነትና ዓላማ እንዲሁም ለእርሱ ተጓዳኝ የኾኑ ነጥቦች እናቀርባለን:: መልካም ንባብ::

## መንፈሳዊ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ የምክክር አገልግሎት (Pastoral HIV/AIDS Counselling)

ጸጋዬ ጥላሁን /አ.አ.ዩ/

መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት በአመካካሪውና በተመካካሪው መካከል የሚደረግ ምሥጢራዊ ግንኙነት ሲሆን ዓላማውም ተመካካሪው ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ መልኩ ለሚከሠቱ ችግሮች አመካካሪው ጋር በመ ወያየትና የመፍትሔ ሐሳብ በመፈለግ ተመካካሪውን ከገጠመው ችግር ማላቀቅ ነው:: መንፈሳዊ የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ የምክክር አገልግሎትን ደንብና ሥርዐት በመከተል ለተመካካሪዎች በጋራ መፍትሔ መፈለግ ነው:: መንፈሳዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት በትክክል ከተሰጠ እጅግ ውጤታማ ነው:: ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ምክንያት ሰዎች የሚያጋጥማቸው ቀዳሚ ችግር ተስፋ መቁረጥ ነው:: ተስፋን የሚሰጥና የሚያለመልም ደግሞ እግዚአብሔር ነው:: መንፈሳዊ የኤች.አይ ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት ደግሞ በተጠቃሚዎች የሚሰ ጠው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት በማ ድረግ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም መንፈሳዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግ ሎት ለተመካካሪዎች መንፈሳዊ ሕይወትም ትኩረት ይሰጣል፡ ያበረታታማል::

ቤተ ክርስቲያናችን ከ45 ሚልዮን በላይ ምእመናን እንዳሏት ይታወቃል:: ይህ ቁጥርም ከኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ከግማሽ በላይ የሆነውን ክፍል ይይዛል::

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ ከሚታይባቸው ሀገሮች ተርታ ተመድባ ትገኛለች:: የምእመናን ብዛት ከፍተኛ እንደ መሆኑ መጠን በሽታው እያደረሰ ካለው ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር አንጻር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ እየተጎዳች ትገኛለች:: ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለ፣ የኤድስ ሕሙማን፣ በበሽታው ምክንያት የሞቱት እንዲሁም በኤድስ ምክንያት አሳዳጊ አልባ የሆኑ ሕፃናት ቁጥር ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው የሚገኙት የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ናቸው::

ይህን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ችግር ለመቀልበስ ከማንም በላይ ለሰው ልጆች የምታስበው እናት ቤተ ክርስቲያናችን የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል በል ማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሥር የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ አቋቁማ በሀገሪቱ ውስጥ የተለያዩ ፕሮግራሞችንና ስትራቴጂዎችን ነድፋ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች:: በሥሯ ያሉ የአገልግሎት ተቋማትም /ሰንበት ት/ቤቶችንና ማኅበረ ቅዱሳንን ጨምሮ/ የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠርና በበሽታው ምክንያት የተጎዱትን ወገኖች ለመርዳት አቅማቸው በፈቀደ መጠን እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ:: አሁንም ግን ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅ ብናል:: ችግሩ የብዙ አካላትን የተቀናጀ ርብርብና ጥረት የሚጠይቅ ነው::

ስለ በሽታውና እያስከተለ ስላለው ጉዳት ብዙ ትምህርቶችና መረጃዎች ቢሰጡም ኅብረተሰቡ በተለይም በወጣቱ ዘንድ ትክክለኛ የጠባይ ለውጥ በማምጣት ረገድ ገና ብዙ ይቀራል:: ብዙዎች የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ ለማድ ረግና ከራሳቸው ጋር አዋሕደው በት ክክለኛው መስመር ለመጓዝ ሲቸገሩ ይታያሉ:: ይህ ደግሞ የሚያመለክተን የጠባይ ለውጥ እጅግ በአጭር ጊዜ ሊመጣ እንደ ማይችል ነው:: አሮጌውን /የማይፈለገውን ጠባያችንን/ በአዲስ /በሚፈለገው ጠባይ/ ለመተካት ፍላጎትንና ቆራጥነትን ይጠይቃል:: አንድ እጅግ ሲጋራ አጫሽና የጫት ሱሰኛ የሆነን ሰው ከእ ነዚህ ለሕይወት አደገኛ ከሆኑ ሱሶች ለማላቀቅ አንድ እና ሁለት ቀን ብቻ አይበቃም:: ይልቁንም ሰፊ ጊዜ፣ ማበ ረታቻና ክትትል ይፈልጋል:: በተለይም ወጣቱ በኤች. አይ.ቪ. /ኤድስ ዙሪያ ቶሎ የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ሲቸገሩ የሚታዩት የማይፈለገውን ጠባይ ለመልመድ ብዙ ጊዜ እንደ ፈጀ ሁሉ የሚፈለገውን ጠባይ ለመለማመድም በዚያው ልክ ጊዜ ስለሚጠይቅ ነው:: ከፍተኛ የሆነ የምክክር አገልግሎት፣ ክትትልና ድጋፍም ይፈልጋል:: ሆኖም ግን ሁሉም ሰው ልብ ሊለው የሚገባው ነገር በሕይወት ድርድር አለመኖሩን ነው:: በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያ የጠባይ ለውጥ ማምጣትና አለማምጣት የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄ ነው:: ምርጫው የእያንዳንዳችን ነው:: ምን አልባት ላለመወጣታችን ብዙ ምክንያቶች ልንሰጥ እንችላለን:: ምክንያት ግን እስከ አሁን ድረስ የሰው ልጆችን ከሞት አላዳነም::

በመሆኑም ሰዎች በኤች. አይ. ቪ. /ኤድስ ዙሪያ የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡ እንደዚሁም በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ምክንያት ከሚደርስባቸው የሥነ ልቡና እና ማኅበራዊ ችግር እንዲላቀቁ፡ በሰላም፣ በተስፋና በፍቅር እንዲኖሩና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ለማስቻል ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት አንዱ መን ገድ መንፈሳዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎትን መስጠት ነው::

መንፈሳዊ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት የቫይረሱን ሥርጭትና በሽታውን በመቆጣጠርና በመከላ ከል በኩል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የጎላ ነው:: በተጨማሪም በበሽታው ለተ ጎዱ ወገኖች የሥነ ልቡና ድጋፍ በማ ድረግ በኩል ከሌላው ማለትም ከኤች. አይ.ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት አንጻር የጎላ ጥቅም አለው:: ምክንያቱም አገልግሎቱ የሚሰጠው በመንፈሳውያን አባቶች ሲሆን ተመካካሪዎችን ከሥጋዊ ደኅንነት አንጻር ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሕይወታቸውንም በማበርታት ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ሕይ ወት እንዲያገኙ ማድረግ ስለሚያስችል ነው:: ይህም በመሆኑ በተመካካሪዎች ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት አለው:: እግዚአብሔር በአመካካሪውና በተመካካሪው መካከል ስለሚገኝ ለችግሩ በቀላሉ መፍትሔ ይገኛል::

መንፈሳዊ የኤች.አይ.ኤድስ የምክክር አገልግሎት ዐይነቶች ጠቅለል ባለ መልኩ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ::

### 1. የቅድመ ምርመራ መንፈሳዊ የኤች. አይ ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት

ይህ የምክክር አገልግሎት የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ መኖር አለ መኖሩን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች የሚሰጥ ነው:: እዚህ ላይ አመካካሪዎች /የቤተ ክርስቲያን አባቶች/ ሰዎች ደማቸውን ከሚሰጡበት ላብራቶሪ ሔደው አገልግሎቱን ላይሰጡ ይችላሉ:: ግን ቢያንስ ለሚያስተምሯቸው ምእመናን፣ለንስሐ ልጆቻቸውና ለመሳሰሉት በፈቃዳ ቸው እንዲመረመሩና ራሳቸውን ዐውቀው እንዲኖሩ አገልግሎቱን መስጠት ይችላሉ::

#### የአገልግሎቱ ዓላማ፦

- ሰዎች ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግና ደማቸውን በመስጠት ራሳቸውን ለማወቅ የሚያደርጉትን ጥረት ለማበረታታት፡
- ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ቢገኝ የሚያስከትለውን ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖ እንዴት መቋቋም እንደ ሚችሉ ለማገዝ፡
- ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠትና የመሳሰሉት ናቸው::

/ወደ ገጽ ፴፪ ዞሯል/



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## እልፍኝ እና ሥዕል...

/ከገጽ ፴፮ የዞረ/

ክርስቲያን ጋር ድርብ እንዲኾን ተደርጎ ነበር። ኋላ ግን በምእመናን ቁጥር መጨመርና በሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ መጥበብ ምክንያት የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ደብረ አሚን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሚባለውና በ1988 ዓ.ም መሠረቱ ተጥሎ በ1994 ዓ.ም በተጠናቀቀው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ታቦተ ቅዱስ ገብርኤል ደግሞ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ተብሎ በተሰየመው የቀድሞ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀመጥ ተደርጓል። ቤተ ክርስቲያኑና ቤተ መንግሥቱ የሚገናኙበት አንድ በር የነበረ ሲኾን ይህም ንጉሠ ነገሥቱ ሥርዐት ለመፈጸም የሚወጡበትና የሚገቡበት ነበር። ታቦተ ተክለ ሃይማኖት ከኢየሩሳሌም የመጣ ሲኾን ያስመጡትም ዐፄ ዮሐንስ ናቸው።

በቤተ መንግሥቱ የታችኛው ወለል ባሉት በሦስት ረድፍ የተከፈሉ አዳራሾች የዐፄ ዮሐንስንና የባለሟሎቻቸውን ልብሰ መንግሥት፣ የወግ ዕቃዎች፣ ከውጭ መንግሥታት የተበረከቱላቸውን ስጦታዎች፣ የጦር ምርኮዎች፣ የ<የሀ>ን ሐውልት ጨምሮ ከአክሱም፣ ዐድዋ፣ ተንቤን አካባቢ በከርሠ ምድር ምርምራ የተገኙ ቅርሶችን እንዲሁም የዝሆን ጥርስን ጨምሮ የዱር እንስሳትን ቅሪተ አካላት ተመልክተናል። የዱር እንስሳቱ ቀንድ፣ ቆዳ... ከየት እንደ መጣ ላቀረብነው ጥያቄ፦ የቤተ መንግሥቱ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ በደን የተሸፈነና የዱር እንስሳት እንደ ነበሩበት ከዚያ እንደ ተገኙ ተገልጾልናል። ከእኒህም በተጨማሪም የተለያዩ ገድላት፣ ድርሳናት፣ ቅዱሳት ሥዕላት፣ በንጉሡና በመኳንንቶቻቸው የተበረከቱ ልዩ ልዩ መስቀሎች በአግባቡ ተጠብቀው ይታያሉ። ከመካከላቸውም 200 ገጾች ያህል ቅዱሳት ሥዕላት ያሉት ገድለ ጊዮርጊስ፣ በውስጡ ብዛት ያላቸው ትንንሽ መስቀሎች በልዩ ጥበብ የተቀረጹበት የመጾር መስቀል ተመልክተናል።

በዐፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት የነበሩት ቅርሶች ለአንድ ጊዜ ያህል የመዘረፍ ዕጣ ገጥሟቸዋል፦ በ1981 ዓ.ም የሥርዐተ መንግሥት ለውጥ ጊዜ። ከተዘረፉት ውስጥ በዐይነታቸው ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ቅርስ ንዋየ ቅድሳት ይገኙበታል።

ከልዩ ልዩ የትግራይ ገዳማትና አድባራት ተዘርፈው በየአገሩ ከነበሩና ከ24 ዓመታት ቆይታ በኋላ በትግራይ ባህል ማኅበር ጥረት የተመለሱ በርካታ ቅርሶችና ቅርስ ንዋየ ቅድሳት በዐፄ ዮሐንስ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ተጠብቀው ይገኛሉ። ቤተ መንግሥቱ ራሱ ቅርስ ኾኖ ሳለ በውስጡም እኒህን ቅርሶች በመያዙ በየጊዜው ወደ ክልሉ ጎራ ባሉ ቱሪስቶች ይጎበኛል።

የመቐለ <ሃበይ ዮሃንስ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት>ን እና የከተማዋን ቆይታችንን ለጊዜው አጠናቀናል። መቐለን ተሰናብተን፣ከአዲግራት ወደ ብዘት ዘልቀን፣ አቀበቱን ወጥተን፣ በጅንዳው ተንጠላጥለን የዳሞን ተራራና ቋጥኝ ለመውጣት ከቻልን በቀጣይ እትማችን ደብረ ዳሞ ገዳም ላይ እንገናኛለን። *ርሑስ በዓለ ትንሣኤ ይግበረልና፤ መልካም የትንሣኤ በዓል ያድርግልን።*

## አስቸኳይ የርዳታ ጥሪ...

/ከገጽ ፴፮ የዞረ/

ነበረች። ከ1967 ዓ.ም ወዲህ ግን በምእመናኑ መዋጮ ትተዳደራለች።

የምእመናኑ ብዛት 255 አባወራ ሲሆን መሪጌታ አንድ፣ ካህናት ዘጠኝ፣ ዲያቆናት ስድስት አሉ። እነዚህ አገልጋይ ካህናት ከዓመት እስከ ዓመት ምንም ደመወዝ የላቸውም። ካህናቱ አገልግሎት ለሁለቱ ሰናብት፣በ12፣በ21፣ በ29 እና በዐበይት በዓላት ማሕሌትና ቅዳሴ እንዲሁም ጸሎተ ፍትሐት፣ ጥምቀተ ክርስትና ዝክርና ለሕሙማን ጸሎት በማድረግ ያገለግላሉ። ለቤተ ክርስቲያኗ ተተኪ በማፍራት የሚያገለግሉ መምህራን ግን የሏትም። ቀደም ሲል የነበሩትም ዛሬ በሕይወት የሉም። ይሁን እንጂ ያሉት ካህናት አቅማቸው በፈቀደው በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ካህናቱ የሚያገለግሉትም ሆነ የሚያስተምሩት ከእርሻ ከሚያገኙት ከእጅ ወደ አፍ በሆነች ዓመታዊ ምርት ነው። የበለጠው ችግራቸው የአልባሳት ነው። ለቤተ ክርስቲያኑ ቋሚ መተዳደርያ ወፍጮና ንብ እርባታ ቢቋቋምላቸው ችግሩን ይቀርፍላቸዋል። ስብከተ ወንጌልንም በአካባቢው በማስፋፋት ከልማድ ክርስትና ይልቅ ምእመናኑ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተሳትፎ ይበረቱ ነበር።

ይህ በእንዲህ እያለ የቤተ ክርስቲያኑ የቆርቆሮ ክዳንና ጉልላቱ በሮችና መስኮቶች በጠቅላላ ውኃ ልክ ስለሌለው፣ ግድግዳው ዝናም አጥቦት፣ ማገሮቹ ለቀው ውኃ ልኩ ፈራርሶ ለቀጣይ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስቸግር ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ቤተ ልሔሙም እንዲሁ አርጅቶ ለማደስ ከምእመናኑ አቅም በላይ ሆኖአል። ዕቃ ቤትም ስለሌለ በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ለ1564 ዓመታት ያህል የተጠበቁ እጅግ ውድ ንዋያተ ቅድሳትና ቅርሶች ለተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ተጋልጠዋል። እነዚህ ቅርሶች በየግለሰቡ ቤት በመዘዋወር ይጠበቃሉ። እግዚአብሔር ከፈቀደ ቤተ ክርስቲያኗ ከተሠራች በኋላ የግድ ዕቃ ቤትም መሠራት ያለበት ነው። ይህንም ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት በመሐንዲስ የተገመተው የእንጨትና ድንጋይ ወጪ ጉልበትን ሳያካትት 108,877 ብር ያህል ነው። የወጪውን ዝርዝር ከዝግጅት ክፍሉ ለማግኘት ይቻላል።

በመጨረሻም ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ምእመናን ሁሉ በገንዘብና በዐይነት ርዳታችሁን እንደ አቅማችሁ ትለግሱን ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፊት በማያስመልስ፣ አንገት በማያስቀልስ ልመናዋ አማልዳ ከልጅዋ ከወዳጅዋ ጸጋና በረከት ትክፈለን። አሜን።

*አድራሻ፦*

ዲ/ን ተሾመ ታዬ

የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር

011-646 34 14 ቢሮ

ፖስታ ሣ.ቁ 193000

ወንድይራድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት

*የኮሚቴዎች አድራሻ፦*

አቶ በላይ ለገሠ 011-660 27 38

መ/ር ኃይለ ማርያም ካሣ

662 30 38 /0911- 157107

## መንፈሳዊ የምክክር...

/ከገጽ ፴፱ የዞረ/

ስሜት፣ ራስን የማግለል ወይም የማጥፋት ስሜት የመሳሰሉት ናቸው።

በመሆኑም አንድ መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አመካካሪ እነዚህንና ሌሎችን ችግሮች ከተመካካሪዎች ለማላቀቅና የተለያዩ የመቋቋሚያ ዘዴዎችን እንዲያዳብሩ ቃለ እግዚአብሔርንና ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት በማድረግ ለተገልጋዮች አገልግሎቱን ይሰጣል።

### *መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አመካካሪ ምን ሊኖረው ይገባል?*

አንድ መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አመካካሪ ከብዙ ነገሮች ቢያንስ የሚከተሉት ነገሮች ሊኖሩት ይገባል። እነርሱም፦

- ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ተዛማጅ ስለሆኑ በሽታዎች በቂ ግንዛቤ ያለው፡
- ተመካካሪዎች ችግራቸውንና ስሜታቸውን እንዲገልጹ የሚያበረታታ፡
- ስለ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት በተለይም ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት ግንዛቤ ያለው፡
- ጥልቅ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያለው፡
- የሀገሪቱንና የአካባቢውን ባህልና ልማድ ጠንቅቆ የሚያውቅ፡
- ቅን፣ ትሑትና ግልጽ የሆነ፡
- ጥሩ አድማጭ የሆነ
- መረጃን በተፈለገበት ወቅት የሚሰጥ፡
- ቀላልና ግልጽ ቋንቋ የሚጠቀም፡
- ዘወትር ከሰዎች ጠንካራ ጎን የሚነሣ
- ምሥጢር ጠባቂ የሆነ... ወዘተ የሚሉት ናቸው።

ስለ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት በአጠቃላይ፥ ስለ መንፈሳዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክክር አገልግሎት ደግሞ በተለይ በአጭሩም ቢሆን ለማየት ሞክረናል። ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ላይ *«ድህነት ድህነትን እንዲወልድ»* እያደረገ ነው። ችግሩ ለሀገራችን በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ከሆነ ሁለት ዐሥርት ዓመታት አልፈዋል። ሆኖም ግን ሥርጭቱ ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይታይም። በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ችግሩ ያልጎዳው ኢትዮጵያዊ የለም። ዛሬ በሚሊዮኖች የሚቈጠሩ አሳዳጊ አልባ ሕፃናትና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች በሀገራችን ይገኛሉ። ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችንንና ሀገራችንን በእጅጉ እየጎዳ ይገኛል። ስለሆነም ከሁሉም በላይ ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት የምታስበው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሐላፊነት ተጥሎባታል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን የአገለግሎትና የአስተዳደር መዋቅሮች ይህን ችግር ለመቅረፍ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎትም ዘመኑን የሚዋጅ አገልግሎት ስለሆነ ሥልጠና በመወሰድና በዚያ ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትንና ማንዋሎችን በማንበብ ለሚጠብቋቸው ጠቦቶችና በጎች ምእመናን ውጤታማ የሆነ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት እንዲሰጡ ዘመኑ ያስገድዳቸዋል። ምእመናንን ከሥጋና ከነፍስ ጥፋት ሊታደጓቸው ግድ ይላል። አለበለዚያ ችግሩ አሁን ከሚታየው በበለጠ ለሚያ ደርሰው አስከፊ ጉዳት እነርሱም ከተወቃሽነት አይድኑም።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ታቦት ለጅቤ ባሕረ ጥምቀት የወረድኩ መሰለኝ

በሐመር መጽሔት በእጅጉ እየተደሰትኩት ነው። በ14ኛ ዓመት ቁጥር አንድ እትም የ«ክሰሞኑ በረከት» ዓምድ የበዓለ ጥምቀት ትውፊታዊና የቅርብ ዘመን የአከባበር ታሪክ አስመልክቶ በወጣው ጽሑፍ ብዙ ተምሬበታለሁ። በሀገሬ ተገኝቼ ታቦት አጅቤ ወደ ባሕረ ጥምቀት የወረድኩ እስኪመስለኝ ድረስ ተደስቼበታለሁ። ትውፊታችን፣ ሥርዐታችን እንዲህ እየተዘገበ ለትውልድ ይተላለፋል። ጸጋውን ያብዛላችሁ። በርቱ።

*አዳነች አብዲ-መድኃኔ ዓለም*
*ተስፋ ስዱዳን*
*ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት*
*አቡዳቢ*

## «መንገድህን ለታቋርጥ»

በ14ኛ ዓመት ቁጥር አንድ ሐመር መጽሔት እትም ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ «*መርሳት*» በሚል ርእስ በኃይለ ገብርኤል ዘሐና የቀረበልን ዝግጅት ሕይወትን የሚለውጥ ታላቅ ምክር ያለበት ጽሑፍ ነው። እኔም እግዚአብሔርን ከረሱ ወገኖች መኾኔን ተረድቼበታለሁ። ካለሁበት ሕይወት እንዴት ለመውጣትና ለመለወጥ እንደ ምችልም አመላክቶኛል። ጸሐፊው በመንገደኛው ዓምድ ባቀረበልን ጽሑፍም «የልብ ዐውቃ» መኾኑን አስመስክሯል። እባክህን መንገድህን አታቋርጥ፤ የታዘብኸውን ጻፍ፤ ልብ ብሎ ለሚያነብህም እያስተማርክ ነውና «ቃለ ሕይወት ያሰማልን» በሉልኝ።

*ተረፈ ገነሜ - ሆሳዕና*
*ዶ/ር ዘርፉ መልአኩ - አ.አ*

## ጃንደረባ እና በጅሮንድ

የሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትምን ጽሑፎች በጥሞና አንብቤአለሁ። ብዙ ደስ የሚሉኝ ነገሮች ቀርበዋል። መስተካከል የሚገባቸው ነገሮችም አሉ። ለምሳሌ፡- በሐዋ.ሥራ 8፥27 ላይ፡- «የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ኹሉ የሠለጠነ...» ተብሎ ከፍ ያለ መዓርግ የነበረውን ሐዋርያ ወደ በጅሮንድነት /ገንዘብ ሚኒስትርነት/ ዝቅ ማድረጋችሁ አገባብ አይደለም። ቅዱስ ሉቃስ እንደ ገለጸው ጃንደረባው የንግሥቲቱ አዛዥ ነው። «ዳን» ማለት ዳኛ፣ ንጉሥ፣ ገዥ፣ «ደረባ» ደግሞ አገልጋይ ማለት ነው። ስለዚህ ጃንደረባ /ዳንደረብ/ ማለት ንጉሥ አከል፣ የንጉሥ ተጨማሪ፣ ንጉሡ ወይም ንግሥቲቱ በሌሉበት ተክቶ የሚሠራ ማለት ነው። «በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ» ማለት በንግሥቲቱ ግዛት ላይ ሁሉ የበላይ አዛዥ መኾኑን እንጂ በጅሮድነትን አያመለክትም። በጅሮንድነት በኢትዮጵያ ታሪክ የቅርብ ጊዜ ሹመት እንጂ የቆየ አይደለም። ይህም እንኳ ቢሆን የገንዘብ ሚኒስትርነት እንኳን በዚያን ወቅት ዛሬም ቢሆን ትልቅ የሥልጣን ቦታ አይደለም። ስለዚህም «የንግሥቲቱ አዛዥ» የሚለውን ሹመት ይቃረናል፡ ገንዘብ ሚኒስትርነት የአዛዥነት ሥልጣን የለውምና።

*መ/ር የሻምበል ክንዴ*
*ባኮ ግ/ቴክ/ ሞ.የ/ማሠ/ኮሌጅ*
*ምዕ.ሸዋ*

## «ደባ»ን በገሃድ ለየኹት

በ14ኛ ዓመት ቁጥር አንድ ጥር/ የካቲት 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ኪነ ጥበብ ዓምድ ***«ደባ» ቴአትር ሲቃኝ*** በሚል ርእስ በዲ/ን ኤርሚያስ በዛብህ የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤዋለሁ። ቴአትሩን በመድረክ ላይ ባልመለከተውም ተመሳሳይ የኾነ ድርጊት በተግባር ተፈጽሞ ታዝቤአለሁ። ቦታውን አልጠቅስም፤ ግና ሰሚ ጠፍቶ፣ የእናት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ተባረው፣ የበግ ለምድ የለበሱቱ በገንዘባቸው ምናምንቴዎችን በመግዛት የቤተ መቅደሱን ህብት የሚመዘብሩበት፣ በገንዘባቸው የማይደለሉትን ደግሞ ስማቸውን በማጥፋት፣ ከምእመናን በማጋጨት፣ በማሳሰርና በመሳሰሉት በማንገላታት ያሻቸውን እያደረጉ ነው። ይኽን መሰል ብዙ ደባዎች እንዲጋለጡ በዐይነ ኅሊና ያስቃኛችሁንን «ደባ» ቴአትርን በየክፍለ ሀገሩ ለማየት እንድታበቁን እጠይቃለሁ። ይህም የሚከብድ ከኾነ በቪድዮና በቪሲዲ ተቀርጾ፣ በኦዲዮ ካሴት ተተርኮ እንድናየውና እንድንሰማው ቢደረግ መልካም ነው።

*አዜብ አብዱላሂ -ሐረር*
*ዲ/ን ዳንኤል ዐሥራት*
*ባሌ- ዶዶላ*
*ጸጋዬ ዘውዴ*
*ወልድያ*

## «ለምስት መጽሔቶችን ይላኩልኝ...»

ሁሉም ክርስቲያን ከምንም በላይ ለሃይማኖቱ ፍጹም ሊቆረቆር ይገባዋል። ***«መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ»*** በሚል ርእስ ጉዳይ በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም የቀረበልን የዝግጅት ክፍሉ አባላት ጥረት ይህን ያስተምረናል። በተለይ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ በሰጡት ቃለ ምልልስ ከመደስቴ የተነሣ አልቅሻለሁ። የሚጣል ቃል ስለሌለውም በየቀኑ አንዴ አነበዋለሁ። በአንጻሩ መምህር ጌታሁን ዐሥራት ከዱብቲ *«ሐመር ፖለቲካ ውስጥ ገብታለች»* በማለት በ14ኛ ዓመት ቁጥር አንድ እትም የሰጡትን አስተያየት ተመልክቼዋለሁ። ጽሑፉን በቅንነትና በተረጋጋ መንፈስ እንዳነበብኹት እርሳቸው የሚሉት መንፈስ የለውም። በተለይ ከክቡር ሚኒስትሩ ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ ዓላማ በሕዝቡ ዘንድ ግርታና ቅያሜ የፈጠሩ ነገሮች ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ነበር። ይህስ ቢሆን ከቶ ለምን ተደረገ የሚባል ከሆነ በእውነቱ ራስን መመርመር ሳያስፈልግ አይቀርም። ለመሆኑ መምህር ጌታሁን፡- በበኩልዎ ምን አድርገዋል? መንፈሳዊነትስ ለእርስዎ ምንድን ነው? ይልቅስ ወንድሞቻችንን በጸሎትዎ ያስቧቸው፤ ጽሑፉንም ለአራተኛ ጊዜ መለስ ብለው በጥሞና ያንብቡት። «መጽሔቱን የሚገዛኝ አጣሁ» ላሉትም ከእኔ ዘንድ ብዙ ወንድሞች ፈልገው ያጡት ስለሆነ ፈጽሞ አይከስሩም። እኔም ለትውልድ ማስተላለፍ ስለምፈልግ አምስት መጽሔቶችን ይላኩልኝ። ክፍያውንና አድራሻዬን በዝግጅት ክፍሉ በኩል ያገኛሉ።

*ዲ/ን መኩንን መልአኩ*
*አ.አ*

## ስለ ክስታኔ ጉራጌ ሕዝብ የክርስትና ታሪክ ለስተዋውቁን

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ስድስት እትም «ቤተ ክርስቲያንህን ዕውቅ» ዓምድ «ሐዋርያዊነት በኢትዮጵያ እንዴት?» በሚል ርእስ በዲ/ን ዳንኤል ክብረት የቀረበው ጽሑፍ የአባቶቻችንን ሐዋርያዊ ትጋት በሚገባ ያሳየ ነው። ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ጻድቁ አቡነ ዜና ማርቆስ ዝቋላ፣ ምድረ ከብድ /በክስታኔ ጉራጌ ክልል በስተሰሜን በኩል/ በሚገኘው አዳዲ ማርያም ተዘዋውረው ማስተማራቸውን፣ ሕዝቡን በአምልኮተ እግዚአብሔር ማጽናታቸውን የአካባቢው ታላላቅ አባቶች ይናገራሉ። ስለዚህ እባካችሁ እናንተም ይህን ታሪክ አስፋፍታችሁ ስለ ክስታኔ ጉራጌ ሕዝብ የክርስትና ታሪክ በስፋት እንድታስተዋውቁን ጥሪዬን አቀርባለሁ።

*ቃለ ወልድ ወልደ ሚካኤል*
*ሀገረ ማርያም*

/ክገጽ ፫ የዞረ/



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# አዲሱ የ«መዝሙር» ገበያ

## «ኧረ የፈጣሪ ያለህ! ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ከሰው ወገን ስለ ክብሯ የሚቆምላት የላትም ወይ?»

/ኃ/ገብርኤል ዘሐና/

እንዴት ሰነበታችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን። ባለፈው ሳምንት መንፈሴ ወደ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መራኝና ቃለ እግዚአብሔር ልማር ቁጭ አልኩ። ሰባኪው ጥቁር ቀሚሱን ለብሶ፣ መስቀሉን ደረቱ ላይ አንዠርግጎ ብቅ አለ። ዲያቆን ነው። የአንገት መስቀሉን ጫፍ ይዞ እንደ ቄሶች ያማትብበት ጀመር። አማትቦ ሲያበቃ ወደ ሰላምታ ዞረ። «እንደ ምን ከረማችሁ፤ እንደ ምን ሰነበታችሁ፤ እንደምን አደራችሁ፤ እንደ ምን ዋላችሁ? እንደ ምን ቆያችሁ? እንደ ምን መጣችሁ?»... «እግዚአብሔር ይመስገን» እያለ ይመልስ የነበረው ምእመን ለመጨረሻው ሰላምታ መልስ አጣ። መንገደኛው ብቻ «በእግሬ ነዋ!» አለላችሁዋ!! በቃ የሰሙት ሁሉ... ሣቁ... ሣቁ... ሣቁ.... ሣቁ። ቅንነትና ተገቢነት የሌለው ሰላምታ እንዲህ መልስ ያጣል። መልስ ይሰጠው ከተባለም እንዲሁ የሚያሥቅ ይሆናል።

ዘመነ መርዓዊ /የሙሽራ ዘመን/ እንዴት አለፈላችሁ? መንገደኛውማ የሰለቸኝ ቢኖር የሙሽሮቹ ቀጠሮ አለማክበር። ሰባት ሰዓት ጠርተው ዐሥር ሰዓት የሚመጡ ሙሽሮች ከመንገደኛው የማይተካ ዕድሜ ላይ ታሳቢ የሚሆን ሦስት ሰዓት መስረቃቸውን ማን በነገረልኝ። እስኪ ጎበዝ ይታያችሁ፤ እነርሱ ቻይና የሠራቻቸውን አደባባዮች በመዞር የዞረባቸው እንደ ሆነ መንገደኛው እነርሱን በመጠበቅ ይዞርበትን?

ብቻ ግድየለም ለጊዜው እነርሱን እንተዋቸውና አንድ ነገር ላውጋችሁ። መስከረም 21፣ ኅዳር 12፣ *ታኅሣሥ 19፣ ጥር 21፣ የካቲት 16፣ የት ነበር ቅዳሴ ያስቀደሳችሁት። እንጦጦ፣ ግሼን፣ የካ፣ ቁልቢ፣ ግቢ እንጦጦ፣ አራት ኪሎ ....። እኔ መንገደኛው መቼም ገና ስወለድ ዙር ተብዬ የለ፤ ሁሉን ዞርኳቸው፤ በሁሉም ቦታ ግን ተመሳሳይ ነገር ገጠመኝ፤ ገበያ... ገበያ... ገበያ... ዘመናዊ ገበያ። ጠጅ ሣር፣ አሪቲ፣ ቀበርቾ፣ ሉባንጃ፣ ከርቤ፣ ዲኝ... አይምሰላችሁ። እነዚህማ የአብያተ ክርስቲያኒቱን ማርገጃ ባልታወቀ የሊዝ ሕግ ገዝተውታል። ቅቤ፣ ዶሮ፣ ወይራ፣ ቆጤማ፣ መግዛት የፈለገ ቤተ ክርስቲያን ሊሳለም ማለዳ መገሥገሥ ብቻ ይጠበቅበታል። የቻይና ልብስማ ማራገፊያ ወደቡን ያደረገው ከቤተ ክርስቲያን ማርገጃ ነው። ሻጩም እንደ ነዚህ እንደ ለመድናቸው «ከኢየሩሳሌም የመጣ የሚያበራው መስቀል፣ ለቡዳ፣ ለቁርጥማት፣ ለውጋት...» እንደ ሚሉት የመስቀልን ክብር በተሠራበት ሀገርና በማብለጭለጭ እንደ ሚወስኑት ይጮኻል፤ ዲያቆኑና ቄሱም ከውስጥ፣ የልማት ኮሚቴውም ከወደ ቅጽሩ አንቀጽ ይጮኻሉ። የማን ይሆን የሚሰማው? አይ ባቢሎን!!*

እናንተዬ ስሙኝማ፤ አዲሱን ገበያ ደግሞ ልንገራችሁ። ግን ብነግራችሁ ምን ዋጋ አለው? ሰውዬው ነው አሉ፤ ላጤ ነው። እናቷ የሞተችባት ጥጃ አለችው። ጠዋት ከቤቱ ሊወጣ ሲል፦ «አይዞሽ ጥጃዬ+ ማታ ጥሩ ሣር ንጹሕ ውኃ አመጣልሻለሁ» ይላታል። ጥጃዪቱ ከአሁን አሁን ሣር ይመጣልኛል ብላ ምራቋን ስትውጥ መዋል። ማታ ሽጋው ሴተ ላጤ /ያላገባ ወንድ/ ከምሽቱ 6:00 እየፎከረ ሲገባ ሣሩ የለም። ነገም ከነገ ወዲያም... ከዚያም ከዚያም... ። ተስፋ ብቻ። ጥጃዪት ራብ ጠንቶባት የእናቷን መንገድ ተከተለች። ቆዳዋ ሲገፈፍ ጆሮዋ ሰብቶ /ጮማ ሆኖ/ ነበር። ሌላው ግን አጥንት ብቻ። መስማት፣ ማንበብ፣ መስማት ማንበብ... ብቻ ምን ዋጋ አለው? ፍሬ ከሌለው፤ ለማንኛውም ልንገራችሁ።

ገበያውማ «የመዝሙር ካሴት ገበያ» ነው። «መዝሙር» የሚለውን ሲሉ ስለ ሰማሁ ነው እንጂ እኔ መንገደኛው አላልኩትም። ታድያ መዝሙር ቢሸጥስ አሪቲ በሚሸጥበት ማርገጃ? ልትሉ ትችላላችሁ። ወትሮም ቢሆን ውሻ በቀደደው ጅብ መሹለኩ እሙን ነው። ይኸውላችሁ ሚኒባስ ወይም ውይይት ታክሲ ይቀርባሉ፤ በፖስተር ያሸበርቃሉ። ሞንታርቦ የተባለው የድምፅ ማጉያ ይሰቀልባቸዋል። ከካሴቱ ውስጥ «ጥሩ» የተባለው መዝሙር ሲሆን ሲሆን ከሕዝቡ ወቅታዊና ምድራዊ ችግር ጋር ተያይዞ ተመርጦ በአንድ ካሴት በሁለቱም በኩል ይቀዳል። ያ በድምፅ ማጉያው እስከ መጨረሻ ድረስ ይለቀቃል። በየመሐሉ «አጫራች» የሚመስል ሰው ያስተዋውቃል። ታድያ ምን አለበት? የዘመኑ ጥያቄ ነው። ግን ዓላማው ገንዘብ ወይስ የምእመናን ነፍስ ከምድራዊው ነገር ተለቃ ከፈጣሪዋ ጋር እንድትዋሐድበት? ደግሞስ የሞንታርቦን ያህል ድምፅ መልቀቁ ለምን? ዕንቅፋት ለመሆን? ሰው ቆሞ በተረጋጋ ኅሊና እንዳያስቀድስ፣ እንዳይጸልይ፣ እንዳይማር ኅሊናውን ለመስረቅ? «ወይ ጦርነት» አሉ ተገኝ ብረቱ።

መንገደኛው መጽሐፍ ባልማርም የተማሩቱ «... ሁሉ በአገባብና በሥርዐት ይሁን» የሚል ቃል እንዳለ ሲናገሩ በጆሮዬ ሽው ብሏል። አንድ ጊዜ ማለት የመስከረም ማርያም ዕለት እንዲህ ሆነላችሁ። አራት ኪሎ ቅድስት ማርያም በጀርባ ካለው በር ትንሽ ዝቅ ብሎ አንድ ውይይት ሞንታርቦ ተጭና ቆማለች። የተጫነችው መጮሪያ ከላይዋ ላይ ያንባርቅል። አስተዋዋቂው ያስተዋውቃል። በየመሐሉ ደግሞ «አትጋፉ፣ ረጋ በሉ፣ አይሏችሁ፣ ለሁላችሁም ይበቃል። አንተ ደግሞ ፈጠን ፈጠን ብለህ ስጣቸው።» ይላል። መንገደኛው መቼም ለመስማት የፈጠንሁ አይደል፤ ጠጋ አልኩላችሁ። «አትጋፉ» ከተባለበት ቦታ ያለአስተዋዋቂው አንድ ገዢ ስንኳ የለም። ወይ ውሸት! «አካሔዳችሁ ገንዘብን ባለመውደድ ይሁን» ነው የተባለው?

መዝሙር ቤቶቹ ምን ሆኑ? ምን ነካቸው? የመንገደኛው ጥያቄ ነው። ሥርዐቱን ጠብቆ የተሠራ ሥራ ይዞ የቀረበ ዘማሪ ካለ በቃ+ ሕዝቡ ራሱ ሔዶ ይገዛቸዋል። ደግሞ አንድ ጊዜ ውይይት ታክሲዋ ያን በትልቁ ድምፅ የሚያስተጋባውን መሣሪያ ተጭና በአዲስ አበባ አደባባይ ሁሉ ያን «መለስተኛ መዝሙር መሰል ዘፈን» እያስተዋወቀች ትሔዳለች፤ ትቆማለች። አንድ ዕድሜ የጠገቡ አረጋዊ «*ሀገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል አሉ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ታፍራ?*» አሉ። መንገደኛው ነገሩን ሊያስረዳቸው ቢያስብም፡ - «ተው ልጄ አትድከም+ ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል» ብለው ነጎዱ። ኧረ የፈጣሪ ያለህ! ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ከሰው ወገን ስለ ክብሯ የሚቆምላት የላትም ወይ? ሰንበት ት/ቤት፣ ሰበካ ጉባኤ፣ ወረዳ ቤተ ክህነት፣ ሀገረ ስብከት፣ ጠቅላይ ቤተ ክህነት.... ነገሩን አይተውት ይሆን ወይስ ዘመኑ ዘመነ አርምሞ ሆኖ ነው?

እንግዲያውስ መንገደኛውም አንድ ነገር አሰቧል። በቃ መዝሙር ሊያወጣ። ከሚዞር፣ ሥራ አጥ ቦዘኔ ከሚባል። ለዜማው ችግር የለም። ዓርብ ማታ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ የሚተላለፈውን የባህል ሙዚቃ በጥሞና መስማት ነው። ግን ማን መዝሙር መሥዋዕት ነው ይባላል። መሥዋዕት ደ'ሞ እንደ አቤል ንጹሕ መሆን አለበት፤ አይደል? ዘማሪውስ እግዚአብሔር ወደ አቤል ልቡና በተመለከተበት ዐይኖቹ ልቡናውን ቢመለከት ቢያንስ ከፍቅረ ንዋይ የጸዳ መሆን የለበትምን? የቃየን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ጸያፍ የተናቀ እንደ ሆነ ሁሉ ለገንዘብ ተብሎ ከዘፈን ዜማ ቀንጫጭቦ የሚዘምሩት «መዝሙርስ» የተናቀ አይሆን ይሆን? ደግሞ በመዝሙር መሰዳደብ፣ የፖለቲካ ስብከትን መሰበክም ተጀምሯል አሉ። እግዜር ይወቀው። ሔደ፣ ገሠገሠ... መመለሻውን እንጃ። እናንተ የያሬድ ልጆች ደባትር /ደብተሮች/ እንጃ ያሬዳዊው ዜማ ለወደፊት በሙዚየም ሳይከተት ይቀራል ብላችሁ ነው።

ሌላም አለኝ። አዲሱን «የመዝሙር» ክሊፕ አይታችሁታል? በቃ+ ሌላ ጊዜ እነግራችኋለሁ። ብቻ ዛሬ ያየናት የእባብ እንቁላል መፍትሔን በጊዜው ካልሰጠናት ነገ ባለ መርዝም እባብ ትሆናለች። ለሁሉም ልብ ይስጠን። ወርኀ ጾሙን በሰላም ያስፈጽመን። አሜን።


## ለአገልግሎት ወይስ ለ«ቢዝነስ»?

የቤተ ክርስቲያናችን ፈተና በእጅጉ የሚበረታው ከውጭ በሚመጣው ሳይሆን ከውስጥ በሚፈጠረው ድክመት መኾኑ ግልጽ ነው። በዚህ ረገድ ስለ ኦዲዮ እና ቪዲዮ መዝሙር ካሴቶቻችን ግጥምና ዜማ ሁኔታ ብዙ ተብሏል። ዜማዎቹ ያሬዳዊ ያለመሆናቸው ፣ ግጥሞቹ ኦርቶዶክሳዊ ባልሆኑና በተራ ቃላት መደረታቸው፣ ስምቅንትና ጥልቀት የጎደላቸው፣ ኪናዊ ውበት የሌላቸው መሆናቸው በተደጋጋሚ ተተችቷል። በዚሁ ሳይበቃን ከልብ የሚያሳዝነን ሌላ ችግር ደግሞ ተጨምሮብናል። ይኸውም የመዝሙር ካሴቶቻችን ሽያጭ ሁኔታ ነው። የመዝሙር ካሴቶቻችን ከነችግሮቻቸው በመዝሙር ካሴቶች ማከፋፈያዎች /መሸጫ ሱቆች/ እንደ ተወሰኑ ቢቀር መልካም ነበር ያሰኛል። ግና ወትሮም ቢሆን ፊር መልቀቃቸው ለመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ሳይሆን በሽያጫቸው ለሚገኘው ጥቅም ብቻ ነበር የሚያሰኝ ሁኔታ እየታዘብን ነው። ይኸውም ዘማርያኑ ቀደም ብለው ያወጡትንና አብዛኛው ምእመን የሚያውቃውን ካሴታቸውን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ ተያያዙት በአደንቋሪ ማስታወቂያ ለመሸጥ መሞከራቸው ነው። ቀድሞኮ ያለምንም የጎዳና ላይ ቅስቀሳ በምእመናን ዘንድ በስፋት ተዳርሰዋል። በእውነቱ ይህ አልጠግብ ባይነት ነው፤ ያሳተሙትን ካሴት ገቢ በሙሉና በከፊል ለተቸገረ ቤተ ክርስቲያን ከሰጡ ዘማርያን መማር ይገባቸዋል። በርግጥ ዘማርያኑ ከካሴት ሽያጭ መጠቀም የለባቸውም የሚል መነሻ የለንም። ይሁንና ለካሴት ሽያጭ ተብሎ ምእመኑ ሥርዐተ ቅዳሴን፣ የሠርክ እና የክብረ በዓላት መርሐ ግብሮችን በጥሞና ለመከታተል እስከለመቻል ደርሶ መታወክ የለበትም። በአንዳንድ መርሐ ግብሮችም ከመምህራኑ ዘማርያኑ የሚበዙበት አጋጣሚም አለ። በዚህ ሳቢያ የሠርክ መርሐ ግብር ላለመካፈል የወሰኑ ምእመናን ጥቂት አይደሉም። በጥቂቶች ስሕተት በተለምዶ «የግል ዘማርያን» ተብለው የሚጠሩቱን ካሴቶች ጨርሶ የማያዳምጡም አሉ። በቴክኖሎጂ ውጤቶች በአግባቡ መጠቀም የሚደገፍ ነው። ይሁንና በቅርቡ እንደ ወጣው ቪሲዲ ዘማርያኑ እንደ ዘመኑ የሙዚቃ ክሊፖች ዐይነት ቅንብር ሊያቀርቡልን አይገባም። እንዲያውም ያለ ሥልጣናቸው ካህናት ኾነው መስቀል ጨብጠው «ድውይ ሲፈውሱ» ሁሉ የሚታዩ አሉ። ይህ በእውነቱ የእኛ መንገድ አይደለም፤ መኪና ላይ ሞንታርቦ ጭኖ የመዝሙር ካሴትን ማስተዋወቅም እንዲሁ። ጥሩ ሥራ ከተሠራ ምእመኑ በራሱ ጊዜ ካሴቱን ከመግዛት ወደ ኋላ አይልም። ምናልባት ይህ ድርጊት ከዘማርያኑ ዕውቅና ውጪ በአሳታሚዎች የሚፈጸም ከሆነ ለቤተ ክርስቲያናችን ክብር ሲሉ ዘማርያኑ ድርጊቱን የማስቆም ሐላፊነት ያለባቸው ይመስለናል። በአጠቃላይ ችግሩ የሁላችንም ነውና በአፋጣኝ ሊታረም ይገባል። በቀጣይም ዘማርያኑ ከምእመናንና ከሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያናችን አካላት ጋር የሚገናኙበት የውይይት መድረክ ቢዘጋጅ መልካም ነው።

*መ/ር ብርሃኑ ደመር /ደብረ ብርሃን/ ፣ ኃይለ ገብርኤል ተሰፋዬ /አ.አ/፣ ዜና ገብርኤል ዘቂርቆስ /አ.አ/፣ ዮናስ መድኅንዬ /አ.አ.ዩ/፣ ኤርሚያስ ዓምደ ብርሃን /አየር ጤና/።*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org








## Kitaabolii qulqullun afaan Oromeeffaan Qophaa'an

**Daandii Amantii**
Kutaa - 1ffaa
Gatiin - 6.00

**Daandii Amantii**
Kutaa - 2ffaa
- Gatiin - 5.00

Kitaaboliin kun barumsa adda addaa Amantaa keenyaaf hundee ta'an of keessatti qabataniiru. Bitadhaatii kitaabolii kana dubbisaa. Lubbuu keessaniif boqonnaa argattu.

- **Qopheessaan:-** Dn. Digaafee Daanyaachaw.
- **Maxxansiisaan:-** Waldaa Qulqullootaa.

## በኦሮምኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ቅዱሳት መጻሕፍት

ፍኖተ አሚን /የእምነት መንገድ/
ቁጥር አንድ
ዋጋ - 6.00
ፍኖተ አሚን /የእምነት መንገድ/
ቁጥር ሁለት
ዋጋ - 5.00

እነዚህ መጻሕፍት ለሃይማኖታችን መሠረት የሆኑ ትምህርቶችን በውስጣቸው ይዘዋል:: ገዝተው ያንብቧቸው፤ ለጥያቄዎ መልስን ለነፍስዎም ዕረፍትን ያገኙባቸዋል::

**አዘጋጅ:-** ዲ/ን ድጋፌ ዳኛቸው
**አሳታሚ፡ና አከፋፋይ**


በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን ሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን


## የታላቋ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም መንፈሳዊ ጥሪ

በሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም 90 ኪሎ ሜትር ከተጓዙ በኋላ ወደ ቀኝ ሁለት ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ በመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የተሠራችው የደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም ትገኛለች::

ገዳሟ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና በርካታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ያፈራች እና እያፈራች ያለች ገዳም ስትሆን ብዙ መናንያን ይገኙባታል::

በዚህች ገዳም ሰኔ 21 ቀን 1998 ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቷ የሚከበር ስለሆነ ምእመናን ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በረከት እንድታገኙ ገዳሟንም እንድትጎበኙ የሕንጻ እድሳትና ልማት ኮሚቴው መንፈሳዊ ጉዞ አዘጋጅቷል::


*የታላቋ ደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም*

### የመመዝገቢያ ቦታ:-

1. ኤማሁስ መዝሙር ቤት ፥ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ፊት ለፊት፥ ስልክ ቁጥር 011-1233554/55
2. ግቢ ገብርኤል ዲ/ን አምዴ መዝሙር ቤት፥ ስልክ 0911-686864/011-5-536915/0911-791009.
3. ሸሮ ሜዳ ኪዳነ ምሕረት ስቱዲዮ፥ ስልክ ቁጥር 011-224629
4. ተዋሕዶ መዝሙር ቤት ዑራኤል መብራቱ ፊት ለፊት፥ ስልክ ቁጥር 011-5-533521
5. ኪዳነ ምሕረት መዝሙር ቤት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ፊት ለፊት፥ ስልክ ቁጥር 0911 -238910/011-5-507133
6. መቅደላ መዝሙር ቤት አውቶብስ ተራ አዲስ ከተማ ት/ቤት ፊት ለፊት፥ ስልክ ቁጥር 011-2-751316/0911-237285
7. ሐመልማል ስቴሽነሪ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ወረድ ብሎ መነን ት/ቤት ፊት ለፊት፥ ስልክ ቁጥር 0911 - 421135/011-6550812
8. አርያም መዝሙር ቤት አዲስ ከተማ መሔጃ መንገድ ኤደን ፋርማሲ ፊት ለፊት፥ ስልክ ቁጥር 011-2-752135/0911-249299 ወይም 011-2-130587 መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን::

**ገዳሟን ለመርዳት የምትፈልጉ:-** *የደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም የሕንጻ እድሳትና ልማት ኮሚቴ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 7043 በማለት መላክ የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን::*

### ለበለጠ መረጃ:-

1. አባ መርሐ ጥበብ ተሾመ፥ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም፥ ስልክ ቁጥር 0911-301726 /011-1-230072
2. ወ/ት ሔለን አሰፋ፥ ስልክ ቁጥር 0911-373712 ወይም 011-6-626667/011-1-239174



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

© ማኅበረ ቅዱሳን
ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤ እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።